

የፖለቲካ ተሳትፎ መመሪያ መጸሐፍ

በኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት የተዘጋጀ

የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት
ETHIOPIAN POLITICAL PARTIES JOINT COUNCIL

© Kristelig Folkeparti (KrF) 2025
© Ethiopian Political Parties Joint Council (EPPJC) 2025

Published by:

Kristelig Folkeparti (KrF) / The Christian Democratic Party of Norway
Oslo, Norway
www.krf.no

and

The Ethiopian Political Parties Joint Council (EPPJC)
Addis Ababa, Ethiopia

Design: Scalegate

This publication is independent of specific national or political interests. This publication was made possible with support from the Norwegian Agency for Exchange Cooperation (Norec). The contents may be freely used and copied for educational and other non-commercial purposes, provided that any such reproduction is accompanied by an acknowledgement of The Christian Democratic Party (Norway) and the Ethiopian Political Parties Joint Council as the source.

ABOUT THE CHRISTIAN DEMOCRATIC PARTY OF NORWAY (KRF)

KrF Norway has an active democracy promotion programme with partners from multiple countries. As a neutral and nonpartisan actor, the party works with political actors from across the political spectrum to support democratic development. Through facilitating an exchange of knowledge and experience, the party's goal is to contribute to strengthening democratic processes in the countries where they work.

ABOUT THE ETHIOPIAN POLITICAL PARTIES JOINT COUNCIL (EPPJC)

The EPPJC serves as a council for political parties in Ethiopia to advance multi-party democracy by fostering peaceful relations, mutual respect, and cooperation among parties across the political spectrum. Through capacity-building programs, inclusive initiatives for underrepresented groups, and mechanisms for dialogue and dispute resolution, the goal is to strengthen democratic processes within Ethiopia.

Acknowledgements

I want to extend my deepest gratitude to all those who contributed to the creation of this handbook, which I hope will be a vital resource for fostering active political participation and strengthening multi-party democracy in Ethiopia. Drawing from the experiences of the Ethiopian Political Parties Joint Council (EPPJC) and the Norwegian Christian Democratic Party (KrF), this guide equips political parties with practical strategies—from understanding core roles and responsibilities, to effective policy formulation, public engagement, media relations, inclusivity for women, youth, and persons with disabilities, and collaborative participation throughout the Joint Council. This book stands as a testament to the collaborative spirit needed to build a vibrant, respectful, and cooperative political landscape in Ethiopia.

A special thanks go to Dr. Yitagesu Zewdu whose insightful authorship brought clarity and depth to these essential topics. I am also grateful to Mr. Asebe Endeshaw and Ms. Sosina Lakew for their meticulous editing, and ensuring the content is accessible and relevant. Finally, I acknowledge the leadership of the Ethiopian Political Parties Joint Council, whose unwavering support made this publication possible. This handbook would not exist without their collective dedication. May it serve as a catalyst for meaningful political engagement across Ethiopia.

Evan Wilson
International Secretary
The Christian Democratic Party of Norway (KrF)

ማውጫ

ሰለዚህ የመምሪያ መጽሐፍ 7
የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ኃላፊነት እና ሚና 8
መቅድም 10
የመድብለ-ፓርቲ ሥርዓት የፖለቲካ ተሳትፎ እሳቤ 10

ምዕራፍ አንድ 12
የፖለቲካ ፓርቲዎች እና ምስጉን የፖለቲካ አመራር 13
1.1. የፖለቲካ ፓርቲዎችና የፖለቲከኞች ሚና እና ተግባራት 13
1.1.1. የፖለቲካ ፓርቲዎች ሚና እና ተግባራት 13
1.1.2. የፖልቲከኞች ቁልፍ ሚናዎች እና ተግባራት 17
1.1.2.1. እጩነት 19
1.1.2.2. ውክልና 20
1.2. ማኅበራዊ መሠረት በመገንባት 21
1.3. ምስጉን የፖለቲካ አመራርነት 27
1.3.1. የምስጉን ፖለቲካ አመራር ማሳያዎች 27
የምዕራፍ አንድ ማጠቃልያ 29

ምዕራፍ ሁለት 31
የፖለቲካ ፓርቲዎች የፖሊሲ ቀረፃ ሂደት 32
2.1. ፖሊሲ ምንድን ነው? 32
2.1.1. የፐብሊክ ፖሊሲ መገለጫዎች 33
2.1.2. የፐብሊክ ፖሊሲዎች ለፖለቲካ ፓርቲዎች ያላቸው ፋይዳ 33
2.1.3. የፐብሊክ ፖሊሲ ምሳሌዎች 34
2.2. ፖሊሲ ዝግጅት ሂደቶች 37
2.3. የፖሊሲ ዝግጅት የመረጃ አሰባሰብና አጠቃቀም ዘዴዎች 39
2.3.1. ማስረጃ-ተኮር የፖሊሲ ቀረጻ ለምንስ አስፈላጊ ሆነ? 40
2.3.2. መረጃ ለማሰባሰብ የሚረዱ ዘዴዎች 40
2.4. የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ 41
2.4.1.የፖሊሲምክክር 41
2.4.2. የባለድርሻ አካላትን በፖሊሲ ዝግጅት ውስጥ ማሳተፍ ለምን አስፈለገ? 42
2.4.3. ባለድርሻ አካላትን በፖሊሲ ዝግጅት ሂደት ውስጥ እንዴት ማሳተፍ ይቻላል? 43
የምዕራፍ ሁለት ማጠቃለያ 45

ምዕራፍ ሦስት 46
የፖለቲካ ኮሚኒኬሽን እና መልዕክት ቀረጻ 47
3.1. የስኬታማ የፖለቲካ ኮሚኒኬሽን/ተግባቦት 47
3.1.1. ውጤታማ የፖለቲካ ኮሚኒኬሽን ስትራቴጂ 47
3.1.2. የስኬታማ የፖለቲካ ኮሚኒኬሽን መርሆች 49
3.2. ግልጽ እና ወጥ የሆነ መልዕክት መቅረጽ 53
3.2.1. የፖለቲካ መልዕክት ምንድን ነው? 54
3.2.2. የፖለቲካ መልዕክቶች ሙከራ 54
3.3. ታዳሚን ማወቅ 55
3.3.1. የቁልፍ ሕዝባዊና ሥነ-ልቦናዊ መረጃዎችን መለየት 55
3.3.2. የታዳሚዎችን ፍላጎቶች፣ እሴቶች እና ስጋቶች መተንተን 55
3.4. ተረኮች በፖለቲካ ኮሚኒኬሽን ውስጥ 56
3.4.1. የፖለቲካ ፓርቲዎች ታሪክን መተረክ ለምን ያስፈልጋቸዋል? 56
3.4.2. ውጤታማ የፖለቲካ ኮሚኒኬሽን ተረኮች የምፍጠርያ ዘዴዎች 57
የምዕራፍ ሦስት ማጠቃለያ 58

ምዕራፍ አራት 59
ከመገናኛ ብዙኃን ጋር ግንኙነት መፍጠር 60
4.1. ከመገናኛ ብዙኃን ጋር ውጤታማ ግንኝነት መመሥረት 60
4.1.1. የመገናኛ ብዙኃን ሽፋን መጠን ወሳኝ ነው 61
4.1.2. የመገናኛ ብዙኃንን ትኩረት መሳብ 62
4.2. ውጤታማ ቃለ –ምልልስ ከመገናኛ ብዙኃን ጋር የማድረግ ዘዴ 64
4.2.1. የሚዲያ ስልጠና አስፈላጊነት 64
4.2.2. በቀጣይ በሚዲያ ሲቀርቡ እንዴት ስኬታማ መሆን ይችላሉ? 65
4.3. የፖለቲካ ፓርቲዎች ማኅበራዊ ሚዲያን የሚጠቀሙበት አግባብ 70
4.3.1. የማኅበራዊ ሚድያ፦ እድሎችና አደጋዎች 71
4.3.2. የፖለቲካ ፓርቲዎች በማኅበራዊ ሚዲያ ዘላቂ ተሳትፎ ለማድረግ የሚያስችሉ ስልቶች 72
4.3.2.1. የማኅበራዊ ሚዲያ በአግባቡ ለመጠቀም ስልት ማዘጋጀት 72
4.3.2.2. የማኅበራዊ ሚዲያ ተከታዮችን ቁጥር ማሳደግ 74

ምዕራፍ አምስት 75
የፖለቲካ ፓርቲዎች አካታችነት 76
5.1. ብዝሃነት ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መዳበር ያለው ፋይዳ 76
5.1.1. ውክልና እና ፖሊሲ 77
5.2. ሴቶችን በፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ የማካተት ስትራቴጂ 77
5.2.1. የሴቶች ፖለቲካዊ ተሳትፎን የገደቡ ጋሬጣዎች 78
5.2.1.1. ማኅበራዊ እና ባህላዊ ሳንካዎች 78
5.2.1.2. በፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ ያሉ ተቋማዊ እንቅፋቶች 79
5.2.1.3. ጾታን ከግምት ውስጥ ያላስገባ የፓርቲ ባህል 79
5.2.2. ስትራቴጂ 1፡ የፆታ እኩልነትን በፓርቲ መዋቅሮች፣ ሂደቶች እና አሠራሮች ውስጥ ተቋማዊ ማድረግ 80
5.2.2.1. የፓርቲውን የሥርዓተ-ፆታ ኦዲት (Gender Audit) ያካሂዱ 80
5.2.2.2. የፓርቲ የሥርዓተ-ፆታ የድርጊት መርሃ ግብር (Gender Action Plan) ማዘጋጀትና መተግበር 81
5.2.2.3. የሴቶችን ተዋጽኦ በፓርቲ በመዋቅሮች ውስጥ መወከላቸውን በሕጎች ማረጋገጥ 83
5.2.2.4. የፓርቲውን የሴቶች ክፍል ወይም ክንፍ ማጎልበት 84
5.2.3. ስትራቴጂ 2፡ የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ ለማሳደግ በፈቃደኝነት እርምጃዎችን መውሰድ 85
5.2.3.1. የፓርቲውን ሴት አባላት ማወቅ 85
5.2.3.2. አዳዲስ ሴት አባላትን መመልመል እና በፓርቲው ውስጥ ማቆየት 86
5.2.3.3. የእጩዎች ምልመላ ሂደቶችን ፍትሐዊና ግልጽ እንዲሆን ማድረግ 86
5.2.4. አቅምን መገንባትና ድጋፍ መስጠት 88
5.2.4. ስትራቴጂ 3፡ የሀብት ፍትሐዊ ተደራሽነትን ማረጋገጥ 88
5.2.4.1. የፋይናንስ እና የአይነት ድጋፍን በፓርቲ ውስጥ ተቋማዊ ማድረግ 88
5.2.4. ስትራቴጂ 4፡ ሥርዓተ-ፆታን በፓርቲ የኮሚኒኔሽን ተግባራት ውስጥ በስልታዊ መንገድ ማካተት 90
5.3. ወጣቶችን በፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ የማካተት ስትራቴጂ 91
5.3.1. ለምን ወጣቶችን? 91
5.3.2. የወጣቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ የሚወስኑ ሦስት ምሰሶዎች 92
5.3.3. ለተለያዩ የወጣቶች ክፍሎች የተዘጋጀ) ስልት 93
5.3.3.1. ስልት 1፡ ሁሉን አቀፍና ወጥ የሆነ የወጣቶች ስትራቴጂ ማዘጋጀት 93
5.3.3.2. ስልት 2፡ ጠንካራ እና በራሱ መወሰን የሚችል የወጣቶች ክንፍ ማደራጀት 94
5.3.3.3. ስልት 3፡ በፓርቲ መዋቅር ውስጥ እውነተኛ የወጣቶች ውክልና ማረጋገጥ 95
5.3.3.4. ስልት 4፡ የወጣቶች ማሰልጠኛ ተቋማት እና የአመራር ፕሮግራሞችን ማቋቋም 95
5.3.3.5. ስልት 5፡ የወጣቶችን አመለካከት በሁሉም የፓርቲ ፖሊሲዎች ውስጥ ማካተት 95

5.4. አካል ጉዳተኞችን በፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ የማካተት ስትራቲጂ 96
5.4.1. ዋና ዋና የሕግ ማዕቀፎች 97
5.4.2. የአካል ጉዳተኞች የፖለቲካ ተሳትፎ እንቅፋቶች 97
5.4.3. የፖለቲካ ፓርቲዎች አካል ጉዳተኞችን ለምን ያሳትፋሉ? 98
5.4.4. የአካል ጉዳተኞችን በፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ ለማሳተፍ የሚረዱ ስልቶች 99
ስልት 1፡- አካታችነትን ለማረጋገጥ ተጨባጭ እርምጃዎችን መውሰድ 99
ስልት 2፡- በግንዛቤ ማስጨበጫ እና ሥልጠና ይጀምሩ 100
ስልት 3፡- ከአካል ጉዳተኞች ማኅበራት (OPDs) ጋር ጠንካራ አጋርነት መፍጠር 100
ስልት 4፡- ለአካል ጉዳተኞች ተሳትፎ እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮችን ማሸነፍ 100
5.5. የካታችነት የፖለቲካ ባሕል ግንባታ 102

ምዕራፍ ስድስት 104
በኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ውስጥ ውጤታማ ተሳትፎ ማድረግ 105
6.1. የጋራ ምክር ቤቱ አወቃቀር እና ኃላፊነት 106
6.1.1. የጋራ ምክር ቤቱ አደረጃጀት 107
6.1.2. የጋራ ምክር ቤቱ መመሥረት ለዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ የሚፈጥረው እድል 109
6.2. በጋራ ምክር ቤቱ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ ለፓርቲዎች የሚሰጠው ፋይዳ 110
6.3. አዳዲስ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤቱ አባል የሚሆኑበት መንገድ 114
6.4. በጋራ ምክር ቤቱ ውስጥ በምን መልኩ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ 114
6.4.1. በጋራ ምክር ቤቱ የሚወከሉ አባልነት ብቃት 115
6.4.2. በጋራ ምክር ቤት መዋቅሮች ውስጥ ለውጤታማ አስተዋፅዖ እና ውክልና የሚረዱ መንገዶች 116
6.5. የጋራ ምክር ቤቱ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት 118
6.5.1. በጋራ መግባባት እና ማመቻመች ስላላቸው ልዩነቶ 118
6.5.1.1. በጋራ ምክር ቤት ውስጥ በጋራ መግባባት እና ማመቻመች ተግብራዊ ማድረግ 119
6.5.1.2. ከተለያዩ የፖለቲካ ፍላጎቶች ጋር ውጤታማ ድርድር እና ስምምነት ለማድረግ የሚያስችሉ ስልቶች 119
6.5.2. በጋራ ምክር ቤት ውስጥ ገንቢ የውይይት ባህልን ማዳበር 120

ምዕራፍ ሰባት 121
ሀገራዊውን እና በክልል/ ወይም ከተማ አስተዳደር የጋራ ምክርቤቶችን ማስተባበር 122
7.1. የጋራ ምክር ቤቶችን ለማስተባበር የመመርያ አስፈላጊነትን 122
7.1.1. የጋራ ምክር ቤቶች መካከል ውጤታማ ትብብር እንዴት መፍጠር ይቻላል? 123
7.2. በጋራ ምክርቤቶች መካከል ውጤታማ ኮሚኒኬሽን እና የትብብር መፍጠርያ ዘዴዎች 124
7.3. በጋራ ምክር ቤቶች መካከል ሀብት መጋራት እና አቅም ግንባታ 126
ለመጽሐፉ ዝግጅት በማጣቀሻነት ጥቅም ላይ የዋሉ ዋቢ ጽሑፎችና መጽሐፍት 128

ሰለዚህ የመምሪያ መጽሐፍ

ይህ የመምሪያ መጽሐፍ (Handbook) የፖለቲካ ፓርቲዎች በምን መልኩ የነቃ የፖለቲካ ተሳትፎ እና አዎንታዊ አስተዋፆ ሊኖራቸው እንደሚችል ተጨባጭ መረጃ እና ስልቶችን ለማግኘት ይስቻላል። በመምሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ መረጃዎች እና የተሳትፎ ስልቶች የጋራ ምክር ቤቱን የመተዳደሪያ ደንብ መርሆች ማዕከል አድርገው የተዘረዘሩ ናቸው። ይህን የመምሪያ መጽሐፍ በመጠቀም የፖለቲካ ፓርቲዎች በፖለቲካ ምህዳሩ ውስጥ እና በጋራ ምክር ቤቱ ውስጥ የሚኖርዎትን ፖለቲካዊ ተሳትፎ ለማጉላት የሚያበቃ አቅም ያዳብራሉ የሚል የጸና እምነት ተይዟል። ይህን መጽሐፍ ሲነያቡ የበለጠ ለመረዳት የሚያስችሉ ጉዳዮችን አስቀድመን ግልፅ ለማድረግ እንፈልጋለን።

ይህ የመምሪያ መጽሐፍ የተዘጋጀበት ዋና አላማ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ለንቁ የፖለቲካ ተሳትፎ በሚረዱ ተግባራዊ መሳሪያዎች፣ ልምዶች እና እውቀቶች ጋር የበለጠ በማስተዋወቅ ፓርቲዎች በፖለቲካ ምህዳሩ ውስጥ በሚኖራቸው ተሳትፎ የበቁ እና የተዘጋጁ እንዲሆኑ ማድረግ ነው። ይህም መሠረታዊ የሚባሉ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ሚና እና ኃላፊነት ከመረዳት አንስቶ፣ በፖሊሲ ቀረፃ፣ ጠንካራ እና አማራጭ እሳቤ በማቅረብ፣ የተሳካ የህዝብ ግንኙነት በሚገባ መተግበር፣ የአካታችነት ባህልን መገንባትን ጨምሮ ለስኬታማ የፖለቲካ ምህዳር ወሳኝ የሆኑ ሰፋፊ ተግባራትን ያጠቃልላል። የሰለጠነ እና የተካነ የፖለቲካ ፓርቲ አባልነት ለኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ጤናማነት እና እድገት ወሳኝ በመሆኑ ይህንን ታሳቢ በማድረግ የመምሪያ መጽሐፉ ተዘጋጅቷል። የኖርዌይ ክርስቲያን ዴሞክራቲክ ፓርቲ (KrF) ይህን የመምሪያ መጽሐፍ ከኢትዮጲያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ጋር በመተባበር እንዲዘጋጅ ያደረገው በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሂደቶችን ለማጠናከር የሚያደገውን ጥረትን ለመደገፍ ነው። በመምሪያ መጽሐፉ እያንዳንዱ ምዕራፍ ውስጥ ጠቃሚ የሆኑ ምሳሌዎችን፣ ጥቅሶች፣ እውነታዎችን የያዙ ከኢትዮጵያ የፖለቲካ አውድ ጋር ተስማምተው እንዲካተቱ ተደርገዋል። ቀጥለን የመምሪያ መጽሐፉን ያዋቀሩትን ክፍሎች እና ምዕራፎች በአጭሩ እንቃኛለን።

- **ስለ ኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ሚና እና ኃላፊነት የሚቃኝው ክፍል** ስለጋራ ምክርቤቱ በአጭሩ የሚያስተዋውቅ ይሆናል።
- **በማስከተል የመጽሐፉ መቅድም በመድብለ-ፓርቲ የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ ስለ ፖለቲካዊ ተሳትፎ** ጠቅለል ያለ ጽንሰ-ሀሳብ ያስተዋውቃል።
- **የመጸሐፉ የመጀመሪያ ክፍል የፖለቲካ ፓርቲዎች ሚና** የሚለውን ሀሳብ አንስቶ የፓርቲዎችን መሰረታዊ ተግባራት የሚዳስስ ሲሆን፣ በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ውስጥ ውጤታማ የፖለቲካ አመራርን የሚገልጹ አስፈላጊ ባህሪያትና ኃላፊነቶችን በጥልቀት ይዳስሳል።
- **ሁለተኛው ምዕራፍ በፖለቲካ ፓርቲዎች የፖሊሲ ቀረፃ ሂደት** ላይ የሚያተኩር ሆኖ በዚህም የፖለቲካ ፓርቲዎች በማስረጃ ላይ የተመሰረቱ ፖሊሲዎችን እንዴት ማዘጋጀት እንደሚችሉ፣ እንዲሁም የፖሊሲ ዝግጅት ሂደት ውስጥ ባለድርሻ አካላትን እንዴት ማሳተፍ እንደሚችሉ የሚያሳይ ተግባራዊ መመሪያ ነው።
- **በሦስተኛ የመጽሐፉ ክፍል የተዳሰሰው የፖለቲካ ፓርቲዎችን ስኬታማ የህዝብ ግንኙነት፣ ተግባቦት እና የመልዕክት ቀረፃ** ሂደትን ነው።
- **በምዕራፍ አራት የፖለቲካ ፓርቲዎች ከመገናኛ ብዙኃን ጋር ስለሚኖራቸው ግንኙነት** የሚመከለት ይሆናል።
- **ምዕራፍ አምስት በፖለቲካ ፓርቲዎች አሳታፊነት እና አካታችነት** ወሳኝ ጠቀሜታ ላይ የሚያተኩር ሆኖ የሴቶች፣ የወጣቶች፣ እና የአካል ጉዳተኞች ትርጉም ያለው ተሳትፎን ለማሳደግ የሚረዱ ስልቶችን በዝርዝር ያብራራል።
- **በምዕራፍ ስድስት የፖለቲካ ፓርቲዎችን በጋራ ምክርቤቱ ውስጥ ሊኖራቸው ስለሚገባ የነቃ ተሳትፎ** ያትታል።
- **የመጨረሻው ምዕራፍ ሰባት በሀገር አቀፉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋራ ምክር ቤት እና በክልል የጋራ ምክር ቤቶች መካከል ሊኖር ስለሚገባ ግንኙነት እና ትብብር** የሚያትት ነው።

ይህን የመምሪያ መጸሐፍ ለማንበብ እና ምክሮቹን ተግባራዊ ለማድረግ ፍላጎት በማሳየትዎት ከወዲሁ የከበረ ምስጋና እናቀርባለን። አባል በሆኑበት የፖለቲካ ፓርቲ ውስጥም ይሁን በተወከሉበት የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ውስጥ ሊኖርዎት በሚችለው ንቁ እና ትርጉም ያለው የተሳትፎ ሂደት ውስጥ የመምሪያ መጽሐፉ መማሪያ እና ማጣቀሻ ሆኖ ያገለግላል የሚል ጽኑ እምነት አለን። መልካም ንባብ።

አቶ ሰለሞን አየለ
የኢትዮጲያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ሰብሳቢ

እና

ኢቫን ዊልሰን
KrF International Secretary

ህዳር 2018 ዓ.ም
አዲስ አበባ

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ኃላፊነት እና ሚና

የ2010 የፖለቲካና የሕግ ማሻሻያዎችን ተከትሎ ከተቋቋሙ ተቋማት መካከል የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት አንዱ ነው። ምክር ቤቱ የተመሰረተው በመጋቢት 5 ቀን 2011 ዓ.ም በፖለቲካ ፓርቲዎች በተፈረመው የቃል-ኪዳን ሰነድ መሠረት ሲሆን፣ ይህ አሰራር በኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/11 አንቀጽ 141/2/ መሠረት ሕጋዊ መሰረት አግኝቷል።

ምክር ቤቱ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ የመድበለ-ፓርቲ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በኢትዮጵያ እውን እንዲሆን አስተዋጽኦ ሲያደርግ ቆይቷል። በተለይም በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል ሰላማዊ ግንኙነትን በማዳበር፣ በመከባበርና በመተባበር ላይ የተመሠረተ ጤናማ የፖለቲካ ፍክክር እንዲኖር አድርጓል። የ2013 አጠቃላ ምርጫ ሰላማዊ እንዲሆን የፖለቲካ ፓርቲዎችን ከማስተባበር አንስቶ፣ በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል የሚከሰቱ አለምግባባቶች በውይይት እና በመግባባት እንዲፈቱ ለማድረግ የሚያስችሉ ስራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል። ይህንን ለማሳካትም ከሀገር አቀፍ እስከ ወረዳ ድረስ የሚደርስ መዋቅር ዘርግቷል። ይህ መጽሐፍ እስከተጻፈበት ጊዜ ድረስም ከትግራይ ክልል በስተቀር በሁሉም የፌዴሬሽኑ አባል ክልሎችና በሁለቱ የከተማ አስተዳደሮች (አዲስ አበባና ድሬዳዋ) ቅርንጫፍ ምክር ቤቶች እንዲቋቋሙ ተደርጓል።

የጋራ ምክር ቤቱ ተደራሽነቱንና የፖለቲካ ተሳትፎን ለማስፋት ወሳኝ እርምጃዎችን ወስዷል። ከዚህ አንጻር፣ ከክልል እስከ ወረዳ ድረስ የሚደርሱ የጋራ ምክር ቤት መዋቅሮች እንዲቋቋሙ አድርጓል። በተጨማሪም፣ የፖለቲካ ብዝኃነትን፣ አካታችነትንና ተሳታፊነትን በተጨባጭ ለማረጋገጥ፣ የሴቶች፣ የወጣቶችና የአካል ጉዳተኞች ክንፎች በብሔራዊውና በክልል/ከተማ አስተዳደር ምክር ቤቶች ሥር እንዲዋቀሩ አድርጓል። ይህም ቀደም ሲል ውስን የፖለቲካ ውክልናና ተሳትፎ ለነበራቸው የፓርቲ አባላት ድምፃቸውን የሚያሰሙበትና ፍላጎታቸውን በጋራ የሚያራምዱበት ዕድል ፈጥሯል።

ምክር ቤቱ ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ በፖለቲካ ፓርቲዎች የአቅም ግንባታ ላይ በስፋት ሰርቷል። ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅርበት በመተባበር፣ መጠነ ሰፊና አካታች የሆኑ የአቅም ግንባታ ስራዎች አከናውኗል። ለፓርቲ አመራሮች፣ አባላት፣ ወጣቶች፣ ሴቶችና አካል ጉዳተኞች በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ተከታታይ ስልጠናዎች እንዲሰጡ በማድረግ በሺዎች የሚቆጠሩ አባላት በማዕከልና በክልል ደረጃ ስልጠና አግኝተዋል። በተጨማሪም፣ ምክር ቤቱ ወቅታዊ በሆኑና የጋራ ጉዳዮች ላይ ውይይቶችና ምክክሮች እንዲካሄዱ አድርጓል። የፓርቲ አመራሮችና የክንፍ መሪዎች ልምድና ተሞክሮ እንዲያዳብሩ የልምድ ልውውጥና የጉብኝት መርሃግብሮችን በማዘጋጀት በአገር ውስጥና ከውጭ አገር እንዲሳተፉ አድርጓል።

የጋራ ምክር ቤቱ ተቋማዊ አደረጃጀቱንና አሰራሩን ለማጠናከር ዘላቂ ጥረት ያደርጋል። ከስኬቶቹ አንዱ የመተዳደሪያ ደንቡን አዘጋጅቶ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ዕውቅና እንዲሰጠውና በአባል ፓርቲዎች እንዲጸድቅ በማድረግ ወደ ትግበራ መግባቱ ነው። ምክር ቤቱ የተመሰረተው፣ በኢትዮጵያ ጠንካራና እውነተኛ የዲሞክራሲ ሥርዓት በመገንባት፣ ለህዝቦች አብሮነት፣ መቻቻልና መከባበር አስተዋጽኦ ለማድረግ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ድምጽ የሚሰሙበት መድረክ ሆኖ ለማገልገል ነው። በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው፣ የምክር ቤቱ ራዕይ፦

“በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ የመድብለ ፓርቲ ስርዓት ተገንብቶ ማየት ነው።”

የጋራ ምክር ቤቱ ዋናውን ራዕይ ለማሳካት ዘጠኝ ያህል ዓላማዎችን በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ በዝርዝር አስቀምጧል። ከእነዚህም መካከል ዋነኞቹ፦

- የፓርቲዎችን አቅም መገንባትና የዲሞክራሲ ስርዓትን ማጠናከር፤
- የፖለቲካ አለመግባባቶችን በውይይትና በምክክር መፍታት፤
- በብሔራዊና ዓለም አቀፍ ጉዳዮች ላይ የውይይት መድረኮችን ማመቻቸት፤
- የሕግ የበላይነትንና የዜጎችን ሕገ-መንግስታዊ መብት ማስከበር፤
- ሰላማዊ፣ ነጻና ፍትሃዊ ምርጫዎች እንዲካሄዱ መደገፍ፤
- ከመንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር በጋራ መስራት፤
- የዜጎችን የፖለቲካ ግንዛቤ ማሳደግ ናቸው።

ዓላማዎቹን ለማሳካት በሚያስችል መልኩ ምክር ቤቱ ጠንካራ አደረጃጀት ዘርግቷል።

- **የአመራር አካላት**፦ የምክር ቤቱ ከፍተኛው የሥልጣን አካል ጠቅላላ ጉባኤው ሲሆን፣ ከሱ ቀጥሎ ሰባት አባላት ያሉት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተዋቅሯል።
- **ቋሚ ኮሚቴዎች**፦ በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ሥር ስድስት ቋሚ ኮሚቴዎች ተዋቅረዋል። እነዚህም፦ የምርጫና ምክክር፣ የአቅም ግንባታ፣ የሕግ ጉዳዮች፣ የአስተዳደርና ፋይናንስ፣ የጥናትና ምርምር እንዲሁም የአደረጃጀት ኮሚቴዎች ናቸው።
- **ክንፎች**፦ የምክር ቤቱን የፖለቲካ ተሳትፎና አካታችነት እውን ለማድረግ፣ ወጣቶች፣ ሴቶችና አካል ጉዳተኞች የፖለቲካ ፓርቲ አባላት መብቶቻቸውን እንዲያስከብሩ የሚያስችላቸውን የጋራ መድረክ እንዲያገኙ የሚያግዙ ሦስት ክንፎች ተቋቁመዋል።
- **የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ**፦ በምክር ቤቱ ውስጥ ኃላፊነትና ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ፣ በጠቅላላ ጉባኤ የሚመረጥና ለሱም ተጠሪ የሆነ የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ ተቋቁሟል።

የፌደራል የጋራ ምክር ቤት አደረጃጀት እንደ አርአያ በመውሰድ፣ በየክልሉ እና በሁለቱ የከተማ አስተዳደሮች (አዲስ አበባና ድሬ ዳዋ) የጋራ ምክር ቤቶች ተዋቅረዋል። እነዚህ አካላት በየደረጃው የሚገኙ (በዞን፣ በክፍለ ከተማ፣ በወረዳና በከተማ አስተዳደር) የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት አስተባባሪ ኮሚቴዎችን የማቋቋም ኃላፊነት የተሰጣቸው ሲሆን፣ ይህንን ለማስፈጸምም ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ነው።

ከምክር ቤቱ ዋነኛ ኃላፊነቶች (mandates) መካከል፣ በኢትዮጵያ ጠንካራ የመድበለ ፓርቲ ስርዓት እንዲገነባ መስራት ነው። ለዚህ ተልዕኮ መሳካትም፣ በፓርቲዎች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶችን በውይይትና በምክክር የሚፈታ የጋራ መድረክ ሆኖ ያገለግላል። በተጨማሪም፣ በኢትዮጵያ ነጻ፣ ፍትሃዊ፣ ዲሞክራሲያዊና ሰላማዊ ምርጫ እውን እንዲሆን የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማድረግ ንቁ እንቅስቃሴ እያደረገ ነው።

ምክር ቤቱ በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ በግልጽ ያስቀመጣቸውን ዓላማዎችና ተልዕኮዎች ለማሳካት፣ ከእያንዳንዱ አባል የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮችና አባላት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይጠበቃል። የፖለቲካ ፓርቲዎች እና አባሎቻቸው በምክር ቤቱ ውስጥ የሚኖራቸው ተሳትፎ፣ ሚናና ድርሻ በእውቀት፣ በመረጃ እና በወጥነት እንዲሆን፣ ይህ የመምሪያ መጽሐፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። የጋራ ምክር ቤቱን መተዳደሪያ ደንብ ወደ ተግባር ለማስገባትና ዓላማዎቹን እውን ለማድረግ የአባላቱን አቅም ማሳደግ አስፈላጊ በመሆኑ፣ ይህ መጽሐፍ ቁልፍ ሚና ይኖረዋል የሚል ጽኑ እምነት አለን።

መቅድም

የመድብለ-ፓርቲ ሥርዓት የፖለቲካ ተሳትፎ እሳቤ

አንድ ወዳጅዎ “ዲሞክራሲ ማለት ምን ማለት ነው?” ብለው ቢጠይቅዎ እንደ ፖለቲከኛ ዲሞክራሲን በደንብ የሚገልጽ ትርጉም ለመስጠት ላይቸገሩ ይችላሉ። ምናልባትም “ዲሞክራሲ ዜጎች በቀጥታ በመሳተፍ ድምጽ የሚሰጡበት እና የመንግሥት አካል እንዲሆኑ የሚመርጧቸውን ሰዎች የሚሾሙበት ሥርዓት ነው” ብለው ሊመልሱ ይችላሉ። ይህ ፍጹም ትክክለኛ መልስ ነው።

ሆኖም ይህ ወዳጅዎ አጥብቆ ጠያቂ ሆኑና “የዜጎች ተሳትፎ ወሰኑ የት ድረስ ነው? ዲሞክራሲን ዲሞክራሲ የሚያደርጉ ከምርጫ ባሻገር ያሉ ሌሎች ምን ነገሮች ናቸው?” ብለው ተጨማሪ ጥያቄዎችን ቢያቀርብልዎ ምን ይላሉ?

ዲሞክራሲ ከምርጫ ባሻገር በርካታ መገለጫዎችና መርሆዎች ያሉት ጽንሰ-ሐሳብ እና ልምምድ ነው። አንድ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እውነተኛና ጠንካራ እንዲሆን የግድ ሊኖሩት የሚገቡ መሰረታዊ ባህሪያት አሉ። ከነጻና ፍትሐዊ ምርጫዎች በተጨማሪ እውነተኛ ዲሞክራሲ የሚለካባቸው ዋና ዋና መገለጫዎችና እሴቶች የሚከተሉትን ጉዳዮች ያካትታሉ፦

የዜጎች እኩልነትና የመብቶች ጥበቃ	የዜጎች እኩልነት መረጋገጥ፣ ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች መከበር፣ እንዲሁም የመብቶች ድንጋጌ (bill of rights) በሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱ ውስጥ መካተቱ ወሳኝ ነው።
የመንግሥት ተጠያቂነትና ግልጽነት	የፖለቲከኞችና የመንግሥት አካላት ለሕዝብ ተጠያቂ መሆን፣ መንግሥት በሚያከናውናቸው ሥራዎችና በሚያወጣቸው ፖሊሲዎች ላይ ግልጽነት ማሳየቱ አስፈላጊ ነው።
የፖለቲካዊ ስርዓት ብስለት	የፖለቲካ መቻቻል፣ የመድበለ-ፓርቲ ሥርዓት መዳበር፣ በሥልጣን ላይ ቁጥጥርና ሚዛን (checks and balances) መኖር እንዲሁም የምርጫ ውጤቶችን በጸጋ መቀበል ይጠበቃል (የተሸነፈው አካልም ሥልጣንን ለአሸናፊው በሰላማዊ መንገድ ያስረክባል)።
የሕግ የበላይነትና ነፃ የፍትህ ስርዓት	ሕግ የበላይ መሆኑ መረጋገጥ አለበት። ነጻና ገለልተኛ የፍትህ ሥርዓትም መኖር አለበት።
ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ነፃነት	የዜጎች የኢኮኖሚ ነፃነትም የዲሞክራሲ ስርዓት ቁልፍ አካል ነው። በተጨማሪም ማኅበራዊ ፍትህ መረጋግጥ አለበት። በዚህም የኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊ እና ባህላዊ መብቶች መከበራቸውን ማርጋገጥ ያስፈልጋል።

እዚህ ላይ በዋናነት ልናነሳው የፈለግነው ጉዳይ የፖለቲካ ተሳትፎን ነው። ለዘላቂ እና እውነተኛ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ **የዜጎች ፖለቲካዊ ተሳትፎ** ቁልፍ መገለጫ መሆኑ በበርካታ ጥናቶችና ከሀገራት ተሞክሮም የተረጋገጠ እውነታ ነው። ቀደም ብሎ እንደተገለጸው የዲሞክራሲ ጥሬ ትርጉም ዜጎች የወደፊት ሕይወታቸውን የሚወስን መንግስት በሚመሰረትበት ሂደት ውስጥ ድምፅ እንዲኖራቸው ማስቻል ነው። ይህ ማለት ዜጎች በምን አይነት መንግስት መተዳደር እንዳለባቸው የመወሰን አቅም ይኖራቸዋል ማለት ነው። ከዚህ ረገድ ሁለት አይነት የዲሞክራሲ ሥርዓቶች ይታወቃሉ፦

ቀጥተኛ ዲሞክራሲ	በዚህ ስርዓት ውስጥ ዜጎች በሚገዙበት የሕግ ማዕቀፍ ላይ ሃሳባቸውን በቀጥታ መስጠት ይችላሉ።
የውክልና ዲሞክራሲ	በዚህ ስርዓት ደግሞ ዜጎች የሚወክሏቸውን ሰዎች (እንደራሴዎች) በመምረጥ የመረጧቸው ሰዎችም የህዝቡን ፍላጎትና አስተያየት በነጻነት የመግለጽ መብት አላቸው።

በሁለቱም ሁኔታዎች የዜጎች ተሳትፎ ዲሞክራሲን የሚያጠነክር ወሳኝ መሰረት ነው።

የሚነሳው ቁልፍ ጉዳይ “**ፖለቲካዊ ተሳትፎ በምርጫ ወቅት ብቻ ነው ወይ?**” የሚለው ነው። መልሱም “**አይደለም**” ነው።

ፖለቲካዊ ተሳትፎ የምርጫ ቀን ድምጽ ከመስጠት የዘለለ ነው። ምንም እንኳን ድምጽ መስጠት በብዙዎች ዘንድ የታወቀው የዜጎች ተሳትፎ መገለጫ ቢሆንም፣ የተለያዩ ህዝባዊ መድረኮች፣ ምክክሮች፣ ክርክሮች፣ ሰላማዊ የድጋፍ ወይም የተቃውሞ ሰልፎች እንዲሁም ስብሰባዎች እንደዚሁ የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ዋነኛ አካል የሆኑ የዜጎች የፖለቲካ ተሳትፎ ማሳያዎች ናቸው።

በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ እንደሚታየው ገዥው ፓርቲን ሳይጨምር ሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫዎች መካከል ባለው ረጅም ጊዜ ውስጥ ዜጎችንና አባላቶቻቸውን በፖለቲካዊ ጉዳዮች የማሳተፍ ውስንነት እንዳለባቸው በጥናቶችና በፓርቲዎቹ አስተያየቶች የተረጋገጠ እውነታ ነው። የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች ዜጎችንና አባሎቻቸውን በፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ በሰፊው ማሳተፍ የተቸገሩት ለምንድን ነው? ለዚህ ጥያቄ የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች በርካታ ምክንያቶች ይቀርባሉ[1]። ባለፉት ዓመታት በተሰረሩ የዳሰሳ ጥናቶች ግኝቶች እንደታየው የፖለቲካ ምህዳር መጥበብ፣ የመንግስት ወይም የገዢው ፓርቲ ጫና፣ የሀብት ውስንነትና ሌሎች ውጫዊ ተግዳሮቶች በተለይ በተቃዋሚ ፓርቲዎች ዘንድ አዘውትረው የሚነሱ ናቸው።

ይሁን እንጂ ፓርቲዎቹ ራሳቸው ውስጣዊ ውስንነቶች እንዳለባቸውም ያምናሉ። ለምሳሌ አብዛኞቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች በሚፈለገው መጠን ምሁራንንና ባለሙያዎችን መሳብ ለምን አልቻሉም? የሴቶች፣ የወጣቶችና የአካል ጉዳተኛ አባላትን በሰፊው ማፍራት የተቸገሩት ለምንስ ይሆን? ፓርቲዎች በመዋቅሮቻቸው ውስጥ ያሉ አባሎቻቸውን በምን ያህል መጠን ነው በፓርቲያዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚያሳትፉት? እነዚህና መሰል ጥያቄዎች ፓርቲዎቹ ራሳቸውን እየጠየቁ ሊመልሷቸው የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው። ውጫዊ በሆኑ ምክንያቶች አዳዲስ አባላትን ወደ ፓርቲ መሳብ አስቸጋሪ ቢሆን እንኳን፣ አባል የሆኑትን የፓርቲውን አካላት እንዴት በነቃና በተደራጀ ሁኔታ ማሳተፍ፣ ማካተትና እንዲወከሉ ማድረግ እንደሚቻል የፖለቲካ ፓርቲዎች ስልት ነድፈው ሊሰሩበት ይገባል። ይህን ለማድረግም ፓርቲዎች አባላትን ለማሳተፍና ለማነቃነቅ የሚያስችሉ ምቹ የሕግ ማዕቀፎች፣ ዘላቂ የአሰራር ስርዓት፣ የውስጥ ዲሞክራሲ፣ የአካታችነት ባህልና የአቅም ማጎልበቻ ድጋፍ የሚሰጡበት ሥርዓት እንዳላቸው መፈተሽ ይኖርባቸዋል።

ለአንድ አገር ዘላቂ ሰላምና ዕድገት የመድበለ-ፓርቲ ሥርዓት መመስረትና ማደግ እንዳለበት ለዓመታት ሲነገር የቆየ ጉዳይ ነው። ለዚህም ነው ኢትዮጵያ ከንጉሣዊ አገዛዝ፣ ከአንድ ፓርቲ ሥርዓት ወይም ከአውራ ፓርቲ የበላይነት እንድትላቀቅ የትውልዶች ትግል ሲካሄድ የቆየው።ለመድበለ-ፓርቲ ሥርዓት ሕገ መንግሥታዊ ዕውቅና የተሰጠው ሲሆን[2]፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች የተለያዩ ዓላማና አመለካከታቸውን በሰላማዊና ሕጋዊ መንገድ ለሕዝብ መግለጽ እንዲችሉ በአዋጅ[3] ሥርዓት ተበጅቶላቸዋል። ይህ ሕጋዊ ዕውቅና ማግኘቱ ብቻውን ሥርዓቱን የመድበለ-ፓርቲ ዲሞክራሲያዊ አያደርገውም። የፖለቲካ ፓርቲዎች መኖር እና በሚጠበቅባቸው ደረጃ መንቀሳቀስ መቻላቸው ወሳኝ ነው።

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለመድበለ-ፓርቲ ዲሞክራሲ ግንባታ ትርጉም ያለው አስተዋጽኦ ማድረግ የሚችሉት ጠንካራ ሆነው ሲቆሙ ብቻ ነው። ጠንካራ ፓርቲ ደግሞ ጠንካራ አባላት ያስፈልጉታል። ይህን እውን ለማድረግ ፓርቲዎች የበለጠ አሳታፊ፣ አካታች፣ ወካይ እና ዲሞክራሲያዊ መሆን አለባቸው። “የፖለቲካ ፓርቲ” ከሚለው ስም ባሻገር የፖለቲካ ፓርቲዎች ጠንክረው የፖለቲካ እንቅስቃሴ ለማድረግ የሚያስችል ማኅበራዊ መሠረታቸውን (constituencies) ማስፋትና ማጠናከር እንዳለባቸውም ይታመናል። በዚህ ረገድ እያንዳንዱ ፓርቲ አባላቱን በፓርቲው መዋቅር ውስጥ በምን ያህል ስፋትና ትጋት እያሳተፈ እንደሆነ ውስጣዊ ግምገማ (internal reflection) ማድረጉ በርካታ ጥቅሞች አሉት።

የመድበለ ፓርቲ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት የፖለቲካ ፓርቲዎች በራሳቸው ውስጥ አባሎቻቸውን ከማሳተፍ በተጨማሪ፣ በጋራ ባቋቋሙት የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ውስጥ የሚኖራቸው ንቁ ተሳትፎ ከፍተኛ ድርሻ አለው።

ፓርቲዎች በቅንነት ላይ የተመሰረተ ትብብር ሲያደርጉ፣ ልዩነቶቻቸውን በሕጋዊና ፖለቲካዊ ውይይቶች መፍታት እና በጋራ ጉዳዮች ላይ አቅማቸውን ማስተባበር ይችላሉ። ከትብብር ባሻገርም፣ ጤናማና ሰላማዊ የፖለቲካ ፉክክር ሲያደርጉ መግባባትና የመተባበር ባህል ልዩነታቸው በርዕዮተ ዓለም፣ በፖሊሲ እና ቅድሚያ በሚሰጧቸው ጉዳዮች ላይ ብቻ እንዲሆን ያግዛል። ይህም ከጥላቻ፣ ከስብዕና ማጥላላት (character assassination) ፣ ከግጭቶች፣ ከአፍራሽ ትርክቶች እና ከፕሮፓጋንዳ የራቀ የፖለቲካ ምህዳር ይፈጥራል።

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ከተመሠረተበት ጊዜ አንስቶ ከፈጠራቸው መልካም አጋጣሚዎች መካከል አንዱ ቀደም ሲል “ዓይን ለዓይን ለመተያየት በማይፈቅዱ” የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮችና አባላት መካከል ምክንያታዊና ሚዛናዊ የሆነ መቀራረብ መፍጠር መቻሉ ነው። የተራራቀ ሐሳብና ግብ ያላቸው የፓርቲ መሪዎች ወይም ተወካዮች በአንድ የምክር ቤት ጠቅላላ ጉባኤ ላይ መቀመጣቸው፣ በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ውስጥ ተወክለው በጋራ መሥራታቸው እና በምክር ቤቱ የተለያዩ መዋቅሮች ውስጥ ተመርጠው ለማገልገል ፈቃደኛ መሆናቸው በቀላሉ የሚታይ ነገር አይደለም። ይህ ለመድበለ ፓርቲ ዲሞክራሲያዊ ግንባታ ያለው አስተዋጽኦም እጅግ ከፍተኛ ነው። ይህን መልካም አጋጣሚ ጠብቆ ለማቆየት ምክር ቤቱ የበለጠ አካታችና አሳታፊ እንዲሆን ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ድርሻ ይጠበቃል። ለዚህም መሳካት የፖለቲካ ፓርቲዎች ተሳትፏቸውን በእውቀትና በመረጃ ላይ ተመስርተው ማሳደግ ይኖርባቸዋል።

በኢትዮጵያ ውስጥ የመድበለ ፓርቲ ሥርዓት ሕጋዊ ዕውቅና ካገኘ ሶስት አስርት ዓመታት ያለፉ ቢሆንም፣ ሂደቱ በርካታ ፈተናዎችና ተግዳሮቶች እንደገጠሙት ጥናቶች ያሳያሉ[4]። የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሂደት መሆኑ ሁልጊዜ የሚነገር ነው። ሆኖም፣ ይህ ሂደት ውጤታማና ተጨባጭ ለውጥ እንዲያሳይ፣ የሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች አሳታፊነትና ተካታችነት ወሳኝ መሆኑን አምኖ በጋራ መንቀሳቀስ ተገቢ ነው።

ምዕራፍ አንድ

የፖለቲካ ፓርቲዎች እና ምስጉን የፖለቲካ አመራር

የአንድ ዲሞክራሲ **ቅቡልነት** ብዙውን ጊዜ በሕዝብ የፖለቲካ መሪዎቹንና ፓርቲዎቹን በሚመለከትበት አመለካከት ይንጸባረቃል።**በአሁኑ ወቅት** የውክልናና የመድብለ-ፓርቲ ዲሞክራሲ ስርዓቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ እየተፈተኑ ነው። በብዙ የዓለም ክፍሎች **ለዓመታት የዘለቁ** የፖለቲካ ፓርቲዎች በአዳዲስና ኢ-መደበኛ እንቅስቃሴዎች እየተፈታተኑ ነው። እነዚህ እንቅስቃሴዎች ደግሞ በአብዛኛው በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ተፅዕኖ ፈጣሪ በሆኑ ግለሰቦች ይመራሉ።

ይህ ሁኔታ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ምንነት እና ሚና እንደገና እንድንመረምር ያደርገናል። የፖለቲካ ፓርቲዎች እነማን ናቸው? ምን እንዲያደርጉ ይጠበቅባቸዋል? ኃላፊነታቸውን በምን መንገድ ይወጣሉ? እነዚህን ጥያቄዎች መፈተሽ ያስፈልጋል። የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎችም በዚሁ ልክ ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ። በብዙ ቦታዎች ትክክለኛዎቹ ሰዎች በፖለቲካ ውስጥ ቢኖሩ ዴሞክራሲ ይሻሻላል የሚል ጠንካራ እምነት አለ። ይህ ስሜት በኢትዮጵያም በተለይ ተፈጻሚነት ያለው ነው። ዜጎች ብዙውን ጊዜ ብቁና ዕውቀት ያላቸው ብቻ ሳይሆኑ የኅብረተሰቡን ሰፊ ክፍል የሚወክሉ ፖለቲከኞችን ይፈልጋሉ። ምን አይነት ብቃትና አቅም ሊኖራቸው እንደሚገባ መመርመርም አስፈላጊ ነው።

በዚህ ምዕራፍ ሁለት ዋና ዋና ጉዳዮችን እንመለከታለን። በመጀመሪያ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችን የምንረዳባቸውን ቁልፍ መገለጫዎች፣ ባህሪያት፣ ሚናዎችና ኃላፊነቶች እንተነትናለን። በመቀጠል፣ ስኬታማ የፖለቲካ ፓርቲ አመራር የሚጠይቃቸውን ወሳኝ ጉዳዮች እንመለከታለን። በዚህ ምዕራፍ የምንሸፍናቸው ጉዳዮች፦

1.1. የፖለቲካ ፓርቲዎችና የፖለቲከኞች ሚና እና ተግባራት

እንደ ፖለቲካ ፓርቲ አባልነትዎ "የፓርቲዬ ሚና እና ተግባር ምንድን ነው?" ብለው በተደጋጋሚ ይጠይቃሉ? እርስዎስ እንደ ፖለቲከኛ "ለምን ፖለቲከኛ ሆንኩ? ለምን በፓርቲ ፖለቲካ ውስጥ ተቀላቀልኩ?" ብለው ራስዎን ጠይቀው ያውቃሉ?

እነዚህ ጥያቄዎች የአንድን የፖለቲካ ፓርቲ አባል ወይም አመራር የሆነ ፖለቲከኛ ሊያሳስቡት የሚገቡ ናቸው። ለጥያቄዎቹም የጠራ ምላሽ ሊኖረው ይገባል። በአጠቃላይ እንደሚታመነው አንድ የተደራጀ እና ህጋዊ የፖለቲካ ፓርቲ አባል የሆነ ፖለቲከኛ የፓርቲ ፖለቲካን ሲቀላቀል ፓርቲው ምን ተግባራትን እንደሚያከናውንና ምን ኃላፊነቶች እንደሚኖሩት አውቆና ተረድቶ ነው። በተመሳሳይ አንድ ፖለቲከኛ "የፖለቲከኞችን ጎራ የተቀላቀልኩት ምን አይነት ጥሪና ሚና ኖሮኝ ነው?" ለሚለው ጥያቄም የሰከነና ግልጽ ምላሽ ይዞ መሆን አለበት።

እስኪ መለስ ብለን የፖለቲካ ፓርቲዎችን እና የፖለቲከኞችን ሚና እና **ተግባራትን** እናስታውስ። ጠቅለል ባለ መልኩ ሲገለፅ ፓርቲዎች እና ፖለቲከኞች በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ የላቀ ሚና ያላቸው ቁልፍ ተዋንያን ናቸው። የፖለቲካ ፓርቲዎች ሚና እና ተግባራቸው በጥቅል ሲቀመጥ የምርጫ እሳቤ እንዲኖርና እንዲዋቀር፣ የዜጎችን ሃሳብና ፍላጎት በተደራጀ መልኩ በማሰባሰብ፣ መንግሥታዊ ሥርዓት በመመሥረት፣ እንዲሁም በሥልጣን ላይ ያለውን መንግሥት ተጠያቂ በማድረግ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። በተጨማሪም እነኚህ አካላት በመንግሥት እና በህዝብ መካከል ድልድይ በመሆን፣ የሕዝብን አስተያየትና ፍላጎት ወደ ፖሊሲ በመተርጎም እና የማኅበረሰብ ውክልናን በማረጋገጥ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። የበለጠ የፓርቲዎችን እና የፖለቲከኞችን **ሚና** እና ተግባራት ለመረዳት በተናጠል ዘርዘር አርጎ ማየት የበለጠ ጉዳዩን ለመረዳት ያግዛል።

1.1.1. የፖለቲካ ፓርቲዎች ሚና እና ተግባራት

በዘመናዊው ዓለም ካለፖለቲካ ፓርቲዎች ህልውና እና ተሳትፎ ዲሞክራሲ የሚባለው ዕሳቤ ተገባራዊ መሆን አይችልም። በሌላ አባባል የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሂደት ዕውን መሆን የተደራጁና ሕጋዊ የሆኑ ፖለቲካ ፓርቲዎች መኖር ቅድመ ሁኔታ ነው። በበርካታ ሀገራት ፓርቲዎች በሚያከናውኗቸው ሕጋዊና ሰላማዊ የፖለቲካ ተግባራት ምክንያት በሀገረ መንግስቱ ውስጥ መረጋጋት በማስፈን ረገድ ወሳኝ አካል ሆነዋል። በዘመናዊና ዲሞክራሲያዊ ማኅበረሰቦች ውስጥ ስልጣን የሚመነጨው ከዜጎች ይሁንታ በመሆኑ ስልጣን ለማግኘት መታገል ብዙውን ጊዜ የፖለቲካ ፓርቲዎች ዋነኛ ተግባር ነው። ለዚህም ሲባል በአብዛኛው ፖለቲካ ፓርቲዎች ህብረተሰቡ ሊደግፋቸው ወይም ሊቃወማቸው የሚችሉ አማራጭ ፕሮግራሞችን ቀርጸው ያቀርባሉ።

የፓርቲ አመራሮችና አባላት ከህብረተሰቡ የሚመጡ ሀሳቦችን ከመቀበል በተጨማሪ፣ የራሳቸውን ሀሳቦች በመለዋወጥና በመተባበር ልዩ ፖሊሲዎችንና ሕጎችን ይወስናሉ። ዋናው ዓላማም እነዚህን ሀሳቦች ለዜጎች ጥቅም ሲባል አንድ ፓርቲ ወይም የፓርቲዎች ጥምረት መነግሥት የመሆን እድሉ ሲገጥማቸው በሕግና ፖሊሲ ማዕቀፎች ውስጥ ተካተው የመንግስት የትግበራ አቅጣጫ ሆነው ይቀርባሉ። ፖለቲካ ፓርቲዎች የፖለቲካ ሥርዓቱን ለማንቀሳቀስ አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን ያከናውናሉ። እነዚህን ተግባራት በሚከተሉት ዋና ዋና ርዕሶች ስር በማደራጀት ማቅረብ ይቻላል[1]።

የማኅበረሰብን ፍላጎት ማስተጋባት

ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት በሚጥሩ አገራት ውስጥ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች (እንደ ገበሬዎች፣ ነጋዴዎች፣ ሠራተኞች፣ መብት ተሟጋቾች፣ ወጣቶች፣ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች እና ሌሎች) ፍላጎቶች፣ ስጋቶችና ምኞቶች የሚገለጹባቸው ዋና መድረኮች ናቸው።

ፓርቲዎች እነዚህን የተበታተኑ ፍላጎቶችና ሀሳቦች በመሰብሰብ፣ ወደ ግልጽ የፖሊሲ አማራጮችና ፕሮግራሞች ይለውጣሉ። በዚህ ተግባራቸውም ሰፊ የኅብረተሰብ ክፍል ፍላጎት በፖለቲካ ሥርዓቱ ትኩረት እንዲያገኝ ያግዛሉ። በዚህ መልኩ **ፓርቲዎች የሕዝብ ድምጽ ሆነው ያገለግላሉ**። የተበታተኑ ሀሳቦችና ስጋቶች በሚገባ ተደራጅተው፣ በአደባባይ የሚነገሩላቸውና የሚሞገትላቸው የጋራ ጉዳይ ሆነው እንዲቀርቡ ይሰራሉ። ይህም ማኅበራዊ ጉዳዮች በፖለቲካው ሥርዓት ውስጥ ተገቢውን ትኩረት ማግኘታቸውን ያረጋግጣል። የፖለቲካ ፓርቲዎች የኅብረተሰቡን ፍላጎትና ምኞት መወከላቸውንና መሟላታቸውን የሚያረጋግጡ ወሳኝ መሣሪያዎች ናቸው። ይህ ተግባር የማንኛውም ፓርቲ መሰረታዊና ወሳኝ ተግባራት አንዱ ነው።

እርስዎ የሚሳተፉበት የፖለቲካ ፓርቲ የሚያራምዳቸው አቋሞች፣ የሚከተላቸው ፕሮግራሞች እና የቀረጻቸው ፖሊሲዎች ምን ያህል የሕዝብን ፍላጎት የመግለጽ አቅም አላቸው ብለው ያስባሉ?

ፍላጎቶችን ማደራጀት

የፖለቲካ ፓርቲን እውነተኛ ፓርቲ ከሚያስብሉት መገለጫዎች መካከል አንዱ **የተለያዩ ፍላጎቶችን የማደራጀት** (aggregating demands) አቅሙ ነው። አንድ ፓርቲ አገር አቀፍም ሆነ አንድን ብሔር ወክሎ የተመሰረተ ክልላዊ ፓርቲ ቢሆንም የሚወክለው የብዙኃን ፍላጎቶችን ነው። ምንም እንኳን የፖለቲካ ፓርቲዎች ተቀራራቢ ፍላጎት ያላቸው ግለሰቦች ስብስብ ናቸው ተብሎ ቢታመንም አንድ ወጥ የሆነ የማህበረሰብ ፍላጎት ይኖራል ተብሎ አይታሰብም። ቢያንስ በጾታ፣ በእድሜ እና በሌሎች ስነ-ህዝባዊ ባህሪያት የተነሳ የፍላጎት ልዩነት መፈጠሩ አይቀርም። ስለዚህ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ፍላጎቶች በግልጽ ከቀረቡ በኋላ እነዚህን ብዙ ጊዜ ተቀናቃኝ የሆኑ ፍላጎቶችን ወስደው ወደ ሰፋፊና በቀላሉ ወደሚተዳደሩ የፖሊሲ መድረኮች ያደራጃሉ። የተለያዩ ፍላጎቶችን በጥንቃቄ በማጥራት፣ የጋራ መግባቢያ ነጥቦችን በመለየት፣ እንዲሁም ለብዙ ቁጥር ያላቸው መራጮች ማራኪ ወደሆነ የፖለቲካ ፕሮግራም ያዋህዷቸዋል። ይህ የማደራጀት ሂደት የተበታተኑ ፍላጎቶችን ወደ ተግባራዊ የፖሊሲ እቅዶች ለመለወጥ ወሳኝ ነው።

የፖለቲካ ፓርቲዎች ይህን ወሳኝ ሚና መወጣት ካልቻሉ የፖለቲካ ስርዓቱ ባልተቀናጁና በሚጋጩ ፍላጎቶች ሊሞላ ይችላል። ይህም የፖለቲካ አለመረጋጋትንና ውዥንብርን ሊያስከትል ይችላል።

ከዚህ አንጻር ፓርቲዎ “ማህበራዊ መሰረቴ ነው” የሚለውን ህዝብ ፍላጎቶች ለማደራጀትና ሁሉንም አካላት ወካይ የሆነ ድርጅት ለመሆን የሚያስችለውን ኃላፊነት በምን ያህል ደረጃ ተወጥቷል ብለው ያምናሉ?

ፖሊሲ መቅረጽ

የፖለቲካ ፓርቲዎች ዋና ተግባራቸው ከሆኑት መካከል አንዱ የሀገርን **የፖሊሲ አቅጣጫ የሚቀርጹበት** መንገድ ነው። ፖሊሲዎች የአንድን ሀገር ሕዝብ የጋራ ግብ ለማሳካት የሚያገለግሉ ቁልፍ መሣሪያዎች ናቸው። ይህን በሚያደርጉበት ጊዜ ፓርቲዎች የብዙሃኑን ድጋፍ ለማግኘት ይጥራሉ። ፓርቲዎች በምርጫ ወቅት የሚያቀርቡት የፖሊሲ አማራጭ አሸናፊ ሆኖ ሲወጣ መራጩ ሕዝብ በድምጹ የፖሊሲውን አዋጭነት አረጋግጦ **ስልጣን እንዲይዙ ያስችላቸዋል**። በሀገር አቀፍ፣ በክልል ወይም በከተማ አስተዳደር ምርጫዎች ሲወዳደሩ፣ ይዘው የሚቀርቡት ዋናው መሣሪያቸው ያላቸው የፖሊሲ አማራጭ ነው። የፖለቲካ ፓርቲዎች ለመራጩ ሕዝብ ቃል የገቡትን ፖሊሲዎች በማዘጋጀት፣ መንግሥት የመመሥረት ዕድል ካገኙም ያቀዱትን ይተገብራሉ።

በእርስዎ የፖለቲካ ፓርቲ ውስጥ ፖሊሲዎች እንዴት ነው የሚቀረጹት? የሚቀረጹት ፖሊሲዎች የኅብረተሰቡን ጥያቄና ፍላጎት በምን ያህል ደረጃ ያካተቱ ናቸው? ፖሊሲዎች ወቅቱን የጠበቀ ክለሳና ማሻሻያ ይደረግባቸዋል?

አባላትን መመልመልና ማሳተፍ

በዘመናዊና ዲሞክራሲያዊ ማኅበረሰቦች ውስጥ የፖለቲካ ንቃተ ህሊና ያላቸው ብዙ ሰዎች የፖለቲካ ፓርቲዎች አባላት ይሆናሉ። የፖለቲካ ፓርቲዎች ዋና ተግባር ለአባላቶቻቸው በራስ መተማመንን በመስጠት የፖለቲካው ዓለም ንቁ ተሳታፊዎች እንዲሆኑ ማብቃት ነው።

ፓርቲዎች ለሀገራቸው ብቁ መሪዎችን የማፍራት ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው። ከታችኛው የአስተዳደር ደረጃ እስከ ከፍተኛው የመንግሥት ሥልጣን ድረስ ያሉ አመራሮች በፖለቲካዊ ዕውቀት፣ በአመራር ክህሎት፣ በሥነ ምግባርና በሕዝብ አገልጋይነት መንፈስ ታንጸው ብቁ እንዲሆኑ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ይህንን ኃላፊነት ለመወጣት፣ ፓርቲዎች የሚከተሉትን ማከናወን አለባቸው፦

- **የአባላት አቅም ግንባታ**፦ አባላትን በመመልመል በፓርቲ አሠራሮችና በአመራር ሂደቶች ላይ አካታች በሆነ መንገድ በማሳተፍ ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ።
- **የመሪዎች ዝግጅት**፦ ነገ የሀገሪቱ የአካባቢ አስተዳዳሪዎች፣ የክልል አመራሮች፣ ሚኒስትሮች፣ ጠቅላይ ሚኒስትሮች፣ ፕሬዝዳንቶች ዲፕሎማቶች እና የሕግ አውጪ ምክር ቤት አባላት ከፓርቲያቸው እንደሚወጡ ማሰብና ለዚያ የሚያበቃ ዝግጅት ማድረግ።
- **የስልጠናና የልምድ ልውውጥ**፦ አባላትን በፖሊሲ ቀረጻ፣ በሕግ ማርቀቅና በአመራር ጥበብ ላይ በስልጠናና በልምድ ልውውጥ መድረኮች ማብቃት።

እርስዎ የሚሳተፉበት ፓርቲ ምን ያህል ለአባላቱ አሳታፊና አካታች ነው? ፓርቲው ያለዎትን የፖለቲካና የአመራርነት ዕውቀት፣ ክህሎትና በራስ መተማመን ለማሳደግ ምን ያህል ድጋፍ ያደርጋል? በፖሊሲ ቀረጻ፣ ሕጎችና መመሪያዎች ማርቀቅ ሂደት ውስጥ ምን ያህል ንቁ ተሳታፊ ነዎት?

የመራጮች ትምህርት መስጠት

የቅርብ ጊዜ የምርጫ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ፓርቲዎች የሚያቀርቧቸው ጉዳዮች እና አማራጮች እንዲሁም የእጩዎች መብዛት መራጮችን ሊያደናግር ይችላል። በዚህ ምክንያት፣ ዜጎች በምርጫ ወቅት ትክክለኛ ውሳኔ ለማድረግ ችግር ይገጥማቸዋል። ስለሆነም የፖለቲካ ፓርቲዎች አንዱ ልዩ ተግባር **ፖለቲካን ለዜጎች ይበልጥ ተደራሽ ማድረግ ነው**። በዚህ ረገድ ፓርቲዎች መራጮችን ስለፖለቲካዊ ጉዳዮች፣ ስለ እጩዎቻቸው እና ስለራሳቸው የፖሊሲ አቋሞች በማሳወቅና በማስተማር ትልቅ ሚና ይጫወታሉ። በምርጫ ዘመቻዎች፣ በክርክሮች እና በሕዝባዊ ንግግሮች አማካኝነት ውስብስብ የሆኑ የፖሊሲ ጉዳዮችን በማቃለልና በፓርቲዎች መካከል ያሉ ቁልፍ ልዩነቶችን በማጉላት መራጮች የፖለቲካ ውሳኔዎችን አንድምታ እንዲረዱ ይረዳሉ። ይህ ተግባር ትርጉም ያለው የምርጫ ውሳኔዎችን ማድረግ የሚችል መረጃ ያለው ዜጋ ለመፍጠር ወሳኝ ነው።

በተጨማሪም የፖለቲካ ፓርቲዎች መራጮች ለድምጽ ሰጪነት እንዲመዘገቡ፣ ፓርቲያቸው በሚያዘጋጃቸው ሕዝባዊ መድረኮች ላይ እንዲታደሙ፣ የፓርቲያቸው ደጋፊ ሆነው በጎ ፈቃደኝነት እንዲያገለግሉ እና በድምጽ መስጫ ቀን ወደ ጣቢያዎች ሄደው ድምጽ እንዲሰጡ የማበረታታት ሥራ ይሰራሉ።

እርስዎ አባል የሆኑበት ፓርቲ ለመራጮች ምን ያህል ተደራሽ ነው? መራጩ ሕዝብ የፓርቲያችሁን ፖሊሲና አማራጭ ሃሳቦች እንዲረዳ ምን ያህል ጥረት ይደረጋል?

በምርጫ መፎካከር	በዲሞክራሲያዊ ማህበረሰቦች ውስጥ ምርጫ በፖለቲካ ፓርቲዎች ላይ የተመሰረተ ነው። በመሆኑም፣ በምርጫ መወዳደር የፖለቲካ ፓርቲዎች ዋና ተግባር ነው። በኢትዮጵያ ሕግ ደግሞ በምርጫ መሳተፍ ለፖለቲካ ፓርቲዎች ግዴታ ነው። በአዋጅ ቁጥር 1162/11 አንቀጽ 98 ንዑስ አንቀጽ 1(መ) ድንጋጌ መሠረት፣ አንድ ፓርቲ ለሁለት ተከታታይ ሀገራዊ ወይም አካባቢያዊ ምርጫዎች ሳይሳተፍ ከቀረ፣ በምርጫ ቦርድ ውሳኔ ከምዝገባ ሊሰረዝ ይችላል። በመሆኑም፣ በምርጫ መሳተፍ የፖለቲካ ፓርቲዎች ዋና ተግባር ነው። ለዚህም ሂደት ፓርቲዎች የሚከተሉትን ያከናውናሉ፦ • **እጩዎችን መመልመልና መስየም**፦ ለምርጫ የሚወዳደሩ እጩዎችን መልምለው ይሰይማሉ። በእጩነት እንዲመዘገቡ ያደርጋርሉ። • **የምርጫ ቅስቀሳ ማካሄድ**፦ የምርጫ ቅስቀሳ ስልቶችን በማዘጋጀት ገንዘብና ቁሳቁሶችን በማሰባሰብ የምረጡኝ ዘመቻ ያደርጋሉ። • **ከሌሎች ፓርቲዎች ጋር መወዳደር**፦ ድምጽ ለማግኘት በቀጥታ ከተቀናቃኝ ፓርቲዎች ጋር ይወዳደራሉ። በምርጫ ወቅት በፓርቲዎች መካከል የሚደረገው ፉክክር ለመራጮች አማራጮችን ከማቅረቡም በላይ ሥልጣን በሰላማዊ መንገድ እንዲተላለፍ ያስችላል። ፓርቲዎች በምርጫ የሚያሳዩት ተቀዳሚ ፍላጎት ማሸነፍ እንደሆነ ይታወቃል። ለዚህም ሲሉ ማኅበራዊ መሰረታቸውን ወይም የድምጽ ባንካቸውን (vote bank) ያደራጃሉ። የሚያቀርቧቸው እጩዎች ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወይም ለክልል ምክር ቤቶች መመረጣቸውን ለማረጋገጥ ሰፊ እንቅስቃሴ ያደርጋሉ። ሁሉም ፓርቲዎች እጩዎቻቸው ከተፎካካሪዎቻቸው የበለጠ እምነት የሚጣልባቸው መሆናቸውን ለመራጮች ለማሳመን ይጥራሉ። መራጩ እንዲደግፋቸው አማራጭ ፖሊሲዎችን በማዘጋጀት ቅስቀሳ ያደርጋሉ። የመራጩ ህዝብ የፓርቲዎችን የፖሊሲ ስኬቶች ወይም ውድቀቶች ተጠያቂ የማድረግ ችሎታ ስላለው ለምርጫ የሚደረገው ቅስቀሳ በጥናት ላይ የተመሰረተ መሆን ይኖርበታል። ፓርቲዎ በምርጫ ለመፎካከር እንዴት ያሉ ዝግጅቶችን ያደርጋል? የመራጩን መሰረት ለማስፋትስ ምን አይነት ጥረቶችን ያከናውናል? የእርስዎ ምላሽ ምን ይሆን?
መንግሥት ምሥረታ	በዲሞክራሲያዊ ሥርዓቶች ውስጥ የፖለቲካ ፓርቲዎች የመንግሥት ምስረታና ውጤታማ አሠራር ወሳኝ አካል ናቸው። ሥልጣን ከመሳሪያ ሳይሆን ከሕዝብ ድምጽ በነጻና ፍትሃዊ ምርጫ የሚመነጭ ከሆነ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች በመንግሥት ምስረታ ሂደት ውስጥ ዋነኛ ተዋናዮች ናቸው። ይህ ሂደት የምርጫ ስኬትን ወደ ትክክለኛ የመንግሥት አሠራር መለወጥን የሚያካትት ሲሆን፣ ያለ ፓርቲዎች ይህ ሂደት ውስብስብና እጅግ ፈታኝ ይሆናል። ኢትዮጵያ በምትከተለው የፓርላማ ሥርዓት፣ በሕግ አውጪው አካል ወይም በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አብላጫ መቀመጫ ያገኘው ፓርቲ ወይም የፓርቲዎች ጥምረት **በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 56 መሠረት መንግሥት ይመሰርታል**። ይህ አሠራር በክልልና በከተማ አስተዳደር ምክር ቤቶችም ይሠራል። የእርስዎ ፓርቲ የመንግሥት ሥልጣን የያዘ ከሆነ፣ የተቃዋሚ ፓርቲዎችን ትችትና ተቃውሞ በሚዛናዊነት ወስዶ ምን ያህል ጥቅም ላይ ያውላል? የእርስዎ ፓርቲ ተቃዋሚ ከሆነ ደግሞ፣ ገንቢ፣ ሚዛናዊና በመረጃ ላይ የተመሠረተ ትችትና ተቃውሞ ለመንግሥት ያቀርባል?

ከላይ የተዘረዘሩት ሰባት ዋና ዋና ተግባራትና ሚናዎች በመድበለ ፓርቲ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ ከሕጋዊ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚጠበቁ ናቸው። ይህ መምሪያ መጽሐፍ በተዘጋጀበት ወቅት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከ60 በላይ ሀገር አቀፍና ክልላዊ ፓርቲዎች ተመዝግበው ሕጋዊ እውቅና እንዳገኙ የምርጫ ቦርድ መረጃ ያሳያል። አብዛኞቹ ፓርቲዎች በመመሥረቻ ሰነዶቻቸው በተለይም በመተዳደሪያ ደንቦቻቸው ላይ ከሞላ ጎደል ከላይ የተዘረዘሩትን ተግባራት ለመፈጸም እንደተደራጁ በግልጽ አስቀምጠዋል። ከተዘረዘሩት ተግባራት መካከል የትኞቹን ፓርቲዎች በወጥነት ለመፈጸም እና ተግባራዊ ለማድረግ ጥረት እንዳደረጉ መለየት ቁልፍ ጥያቄ ነው። ለዚህም የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚከተሉትን ዋና ዋና ነጥቦች በመጠቀም የውስጥ ኦዲት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

- የምንወክለዋለን የሚሉትን የማህበረሰብ ክፍል ፍላጎት ምን ያህል አሰተጋብተናል? የልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ፍላጎት በማደራጀት ምን ያህል ሰርተናል?
- በማህበረሰብ አንገብጋቢ ችግሮች ላይ በመረጃ ላይ የተመሰረተ ፖሊሲ ቀርጸናል ወይ?
- አባላትን ለመመልመል፣ በውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ውስጥ ለማሳተፍ እና ለማካተት ምን ያህል ሰርተናል?
- የማህበረሰብን የፖለቲካ ንቃት ለማሳደግ የሚያስችሉ የመራጮች ትምህርት በማዘጋጀትና በመስጠት ረገድ ምን ያህል ፈጽመናል?
- በምርጫዎች ላይ የነቃና የተደራጀ ተሳትፎ አድርገናል ወይ?

እነዚህን ጥያቄዎች በሐቀኝነት በመመለስ፣ ፓርቲው የትኞቹ ጉዳዮች ላይ ጥንካሬ እንዳለው እና የትኞቹ ላይ ደግሞ ድክመት እንዳለበት መለየት ይችላል። ጥንካሬን ይዞ ለማስቀጠል እና ድክመቶችን ለመሙላት ጥረት ለማድረግም እንደ መነሳሳት ያገለግላል። በመሆኑም፣ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች ከላይ በተዘረዘሩት ጉዳዮች ላይ ራሳቸውን እንዲፈትሹ ይመከራሉ።

1.1.2. የፖልቲከኞች ቁልፍ ሚናዎች እና ተግባራት

የፖለቲከኞችን ቁልፍ ተግባራትና ሚናዎች ከመዘርዘራችን በፊት፣ **“ፖለቲከኛ መሆን ምን ማለት ነው?”** የሚለውን ጥያቄ በአጭሩ መመለስ አስፈላጊ ነው። ይህን የመምሪያ መጽሐፍ እያነበቡ ያሉት እርስዎ ፖለቲከኛ ከሆኑ፣ “**ፖለቲከኛ ነኝ ሲሉ ምን ማለተዎ ነው?**” የሚለውን ጥያቄ ለአፍታ ያስቡበት።

ፖለቲከኛ መሆን ማለት ምን ማለት ነው? ለምንስ ፖለቲከኛ ለመሆን መረጡ?

የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ጉዳዬ ነው ብለው ያስባሉ? ለግለሰቦችና ለማህበረሰቦች መብት መከበር ለመቆም ቁርጠኛ ነዎት? ማኅበራዊ ለውጥ ለማምጣት ከፍተኛ ፍላጎት አለዎት? የፖለቲካ ለውጥ ለማምጣት በተደራጀና ሕጋዊ በሆነ መንገድ በሚንቀሳቀስ የፖለቲካ ፓርቲ ውስጥ በአባልነት ተመዝግበው የተወሰነ ርዕዮተ ዓለም ወይም አቋም ያራምዳሉ? እነዚህን ጥያቄዎች በአዎንታ ከመለሱ፣ **እርስዎ ፖለቲከኛ ነዎት**።

ብዙውን ጊዜ **ፖለቲከኛ** የሚባለው በምርጫ አሸንፎ ወይም በሹመት የመንግሥት ሥልጣን የያዘ እንዲሁም በሥራ አስፈፃሚው ወይም በሕግ አውጪው አካል ውስጥ የተካተተ ግለሰብ ነው። ሆኖም፣ በዚህ መጽሐፍ አውድ “**ፖለቲከኛ**” የሚለው ቃል የመንግሥት ሥልጣን ይዘው ሕዝብን የሚያስተዳድሩ ግለሰቦችን ብቻ ሳይሆን በሕጋዊ መንገድ በተደራጁና ዕውቅና ባገኙ የፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ በመታቀፍ የሚንቀሳቀሱ ሰዎችንም ሁሉ ያጠቃልላል። በቀላሉ ለመረዳት በንግሥት ሥልጣን ላይ ያሉ ፖለቲከኞችን “**ተመራጭ ፖለቲከኞች**” (elected officials) ተበለው የሚሰየሙ ሲሆን የመንግሥት ስልጣን የሌላቸው ፖለቲከኞች “**የፓርቲ ፖለቲከኞች**” (party officials) በመባል ይታወቃሉ።

ፖለቲከኞች የፖለቲካ ፓርቲ አባላት ሊሆኑ ወይም ገለልተኛ ሊሆኑ ቢችሉም፣ ዋነኛ ሚናቸው የሚያገለግሉትን ሕዝብ መወከል እና ለመላው ማኅበረሰብ የሚጠቅሙ ውሳኔዎችን ማድረግ ነው። የፖለቲከኞች ኃላፊነት አንድን ማኅበረሰብ የሚያስተዳድሩ ሕጎችንና ፖሊሲዎችን ማውጣት እንዲሁም የኅብረተሰቡ ፍላጎቶች መሟላታቸውን ማረጋገጥ ነው። የመንግሥት ሥልጣን ላይ የሚቆዩ ፖለቲከኞች የፓርቲያቸው ሕጎች እና ፖሊሲዎች ወደ ተግባር እንዲገቡ ያስፈጽማሉ። በሌላ በኩል፣ የመንግሥት ሥልጣን ለመያዝ ያልቻሉ ፖለቲከኞች ግን የሚወክሉትን ማኅበረሰብ መብትና ጥቅም ለመጠበቅ ይከራከራሉ፣ ይደራደራሉ፣ የውሳኔ ሐሳቦችን ያቀርባሉ፣ ይተባበራሉ እንዲሁም በሕጋዊ መንገዶች ሁሉ ይታገላሉ። በመሆኑም ፖለቲከኞች በሚወክሏቸው ሰዎች ፍላጎት መሠረት ውጤታማ ውሳኔዎችን መስጠት መቻል አለባቸው። ውሳኔ መስጠት ያልቻሉ ፖለቲከኞችም ቢሆኑ የተሰጡት ውሳኔዎች ለሚቆሙለት ማኅበረሰብ የሚበጁ መሆናቸውን በመለየት እንደ ሁኔታው ለተግባራዊነቱ ይተባበራሉ፣ አለያም ውሳኔውን ለማስቀየር በሚችሉት መንገድ ሁሉ ጥረት ያደርጋሉ።

ፖለቲከኞች በሁሉም የመንግሥት አስተዳደር መዋቅር ውስጥ ይገኛሉ። ከታች፣ ከቀበሌ ጀምሮ እስከ ከፍተኛ የመንግሥት የሥልጣን አካል እስከሆነው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ድረስ ፖለቲከኞች አሉ። ከየአካባቢው ባለሥልጣናት አንስቶ እስከ የሀገር መሪዎች (ፕሬዝደንቶች ወይም ጠቅላይ ሚኒስትሮች) ድረስ ያሉ ፖለቲከኞች የማኅበረሰቡን አሠራር በመምራት ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ።

ከመንግሥት አካል ውጪ በፓርቲ መዋቅር ውስጥ ያሉ ፖለቲከኞችን ስንመለከት ከታችኛው የቅርንጫፍ መዋቅር እስከ ከፍተኛው የፓርቲ ጽሕፈት ቤት ያሉ አባላትና አመራሮች **ሕዝባቸውን በመወከልና ድምጽ በመሆን** ቁልፍ ሚና የመወጣት ኃላፊነት አለባቸው። ለዚህም ሲባል፣ እነዚህ ፖለቲከኞች በሚወክሉትና በሚያገለግሉት ማኅበረሰብ ላይ አዎንታዊ ለውጥ የሚያመጡ መፍትሄዎችን ለማግኘት **ከተለያዩ ወገኖች ጋር አብረው መሥራት ይጠበቅባቸዋል**። ሕዝባቸውን ሕይወት የሚያሻሽሉ ሕጎችንና ፖሊሲዎችን ለመቅረጽ እንዲሁም ለመተግበር፣ የተለያየ የፖለቲካ አመለካከትና አቋም ካላቸው ሰዎች ወይም ፓርቲዎች ጋር ጭምር ውጤታማ በሆነ መንገድ መሥራት መቻል አለባቸው። ከጉዳዩ እውቀት በተጨማሪ የፖለቲካ አባላትና አመራሮች ሕዝብንና መገናኛ ብዙኃንን የመረዳትና የመግባባት ችሎታ ሊኖራቸው ይገባል። እንዲሁም የሕዝባቸውን ፍላጎትና አመለካከት ማዳመጥና ለጥቅማቸው መሥራት መቻል አለባቸው።

ሳጥን 1.1፡ የሥኬታማ ፖለቲከኛ መግለጫ ባሕሪያት

ስኬታማ ፖለቲከኛ ለመሆን፣ ፖለቲከኞች ልዩ የሆነ የክህሎትና የባህሪ ጥምረት ሊኖራቸው ይገባል።

- በቃልም ሆነ በጽሑፍ ከሕዝብ እና ባለድርሻ አካላት ጋር ውጤታማ ግንኙነት የመፍጠር፣ የመደራደር፣ ገንቢ ትችቶችን የመቀበል እና በቡድን የመሥራት ችሎታን ማዳበር፣
- ለሥነ ምግባር ተገዢ፣ ለሕዝብ ፍላጎትና ለፓርቲ ዓላማ ታማኝ መሆን ያስፈልጋል። እንዲሁም የመመረጥ ዕድል ወይም የሃሳብ ተቀባይነት ባይኖርም እንኳን በራስ መተማመንና በጽናት መቆም ይጠበቃል።
- ውስብስብ መረጃዎችን በጥልቀት የመተንተን፣ በግፊት ውስጥ የመስራት እና ሚዛናዊ የመፍትሔ ሃሳቦችን የመፍጠር ችሎታ ወሳኝ ነው። ጥሩ የጊዜ አጠቃቀም ክህሎትም ሌላው አስፈላጊ ነገር ነው።

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት እና የናሽናል ዲሞክራቲክ ኢንስቲትዩት (NDI) በ2016 የጋራ ምክር ቤቱንና የፖለቲካ ፓርቲዎችን ሚናና ድርሻ በተመለከተ አንድ ጥናት አካሂደዋል። በጥናቱ ላይ ከተሳተፉ የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች አንዱ፣ "የፖለቲከኛ በጣም አስፈላጊ ባሕርያት ምንድናቸው?" ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ሲሰጡ፣ የሚከተለውን ሀሳብ አቅርበዋል፦

> "ለፖለቲከኛ ከሌሎች ሰዎች ወይም ፖለቲከኞች ጋር አብሮ ለመስራት ጥሩ የመግባባት ችሎታ ወሳኝ ነው። ፖለቲከኛ ስንሆን የሀሳብ ግጭቶች፣ አለመግባባቶችና ትችቶች ይገጥሙናል። ስለዚህ ግጭቶችን ለመጋፈጥ አለመፍራትና ግጭት አፈታት ላይ የዳበረ ችሎታ ሊኖረን ይገባል። ለፖለቲከኛ ሰው፣ ትንተናዊ አስተሳሰብ (analytical mind) ጠቃሚ ከመሆኑም በላይ፣ ጥሩ የህዝብ ግንኙነት ችሎታ ሊኖረው ይገባል። የጽሁፍ እና የንግግር ችሎታው የላቀ መሆን አለበት። እንዲሁም ከግለሰቦችና ከቡድኖች ጋር በግልፅ የመነጋገር ብቃት ያስፈልጋል። በሁሉም ደረጃ ካሉ የፖለቲካ ሰዎች፣ በተለይም ከራስ ፓርቲ አባላትና አመራሮች፣ ከፓርላማ አባላት፣ ከመንግስት ባለስልጣናት አንስቶ እስከ 'ተራው ዜጋ' ድረስ ሰዎችን የማሳመን እና ተፅዕኖ የማሳደር ችሎታ ወሳኝ ነው።
>
> ወቅታዊ መረጃን የመከታተል፣ የመተንተንና ትርጉም የመስጠት አቅም ያስፈልጋል። ፖለቲከኛ ሲሆኑ የሀገር ውስጥ ጉዳይን ብቻ ሳይሆን ዓለም አቀፋዊና ጂኦ-ፖለቲካዊ ጉዳዮችን መከታተል፣ መረዳትና ከራስ የፖለቲካ አቋም አንፃር ትርጉም መስጠት ጠቃሚ ነው። በአጠቃላይ፣ ፖለቲከኛ ስለ ችግሮች መናገር ብቻ ሳይሆን፣ ችግሮችን ስልታዊ በሆነ መንገድ የመፍታት ብቃትም ሊኖረው ይገባል። ስልታዊና ስትራቴጂካዊ ጉዳዮችን ጠንቅቆ ማወቅም ይጠበቅበታል።" በማለት ምላሽ ሰተዋል።

በኢትዮጵያ ውስጥ በተለይም የመንግስት ሥልጣን ያልያዙ የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች አባላትና አመራሮች **ፖለቲከኝነትን እንደ የትርፍ ጊዜ ሥራ** ይቆጥሩታል። የፓርቲ አመራሮችን ወይም አባላትን ቀጥሮ የማሰራት አቅም ያላቸው ፓርቲዎች እጅግ በጣም ጥቂት ናቸው። ይህ ሆኖ ግን ፖለቲከኝነት ከሌሎች የሥራ ወይም የሙያ አይነቶች በእጅጉ የተለየ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። የፖለቲከኞች የመጨረሻ ግብ መንግሥት መሆን ነው። እንደሚባለው፣ "ለጽድቅ" ተብሎ ፖለቲከኛ አይኮንም። የፖለቲካ ፓርቲዎች ወደ ቤተ መንግሥት የሚያደርሱ ባቡሮች ናቸው እንጂ ወደ ሰማይ ቤት የሚያመሩ መኮራኩሮችም አይደሉም። በዲሞክራሲያዊ ስርዓት ውስጥ አንድ ፖለቲከኛ የመንግሥት አካል መሆኑ የሚወሰነው በምርጫ ውጤት ነው። በመሆኑም፣ ፖለቲከኛ ለመሆን በምርጫ ሥርዓት ውስጥ አልፎ የሕዝብን ውክልና አግኝቶ የመንግስት አካል ለመሆን ጥረት ይደረጋል። ስኬታማ ለመሆንም ብቃት ይጠይቃል።

ሳጥን 1.2፡ የስኬታማ ፖለቲከኛ ኃላፊነቶች

የማኅበረሰቤን በአግባቡ መወከል የምችል፣ የሕዝቤን መሠረታዊ እና ዘመን ያስቆጠሩ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል መሪ ለመሆን እፈልጋለው ብለው ሁሌ ያስባሉ? እንግዳውስ በተሰለፉበት የፖለቲካ መስክ ውስጥ ባለዕራይ፣ ችግሮችን ለመፍታት ተለዋዋጭ አቋም ለማራመድ የሚያስችል ስልት የሚከተል፣ ተነሳሽነት ያለው፣ የተጠና እና በዙ "አደጋ የማያስከትል ኃላፊነት ወሳጅ" ("calculated risk taker") ፖለቲከኛ ሆነው መገኘት ይጠበቅበዋል። ፖለቲከኛ ሲሆኑ የሚከተሉትን ኃላፊነቶች መወጣት ይጠበቅብዎታል፦

- የፖለቲካ ሂደቶችን በሚገባ መረዳትና ለሚወክሉት ሕዝብ መብትና ጥቅም መከበር መሟገት፤
- አውንታዊ ተጽኖ ለመፍጠር ቁጠኝነት ማሳየትና ሳያወላውሉ ለቆሙለት ዓላማ ቅቡልነት ማግኘት እና ስኬት መሞገት፤
- የምሃብረሰብን የወደፊት ዕጣ ፈንታ በመቅረጽ ረገድ ወሳኝ ሚና ልመጫወት ዝግጁ ሆኖ መገኘት፤
- እወክለዋለው ብለው የሚያስቡትን ማኅብረሰብ ውክልና በአግባቡ ለመሸከም ዝግጁ መሆን እና ፍላጎታቸውን ማስክበር፤
- ችግር ፈች የሆኑ የፖሊሲዎችንና ፕሮግራሞችን ለመቅረትጽ የሚያስችል ብቃት አዳብሮ መገኘት፤
- ለሚወክሉት ወይም ቆሜለታለው ለሚሉት ማኅብረሰብ የበለጠ ቅርብ፣ ተደራሽ መሆን እና ያለበትን ሥጋት፣ የሚያነሳቸውን ጥያቄዎች፣ ቅድሚያ የሚሰጠውን ፍላጎት ለመለየት ከሕዝብ ጋር ንቁ ግንኙነት ማድረግ፤
- የሚወክሉትን ማኅብረሰብ ፍላጎት ለማሟላት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅርበት መሥራት፤
- ሕዝቤ የሚሉትን አካል ዋና ዋና አጀንዳዎችን ለሚመለከታቸው አካላት ማስረዳት፣ ለፍላጎቶቹ ጥብቅና መቆም፣ መሟገት፣ መጎትጎት፣ ድምጽ ማሰማት፣ አጋር አካላትን ማስፋት፤
- የጋራ ግቦችን ለማሳካት ከሌሎች አካላት ጋር ግንኙነት መፍጠር፣ የትብብር መንፈስን ማነሳሳትና በቅርበት መስራት። በተለይም ከፓርቲዎ አባላትና አመራር ጋር፣ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወይም የክልል ምክርቤቶች ተመራጮች ጋር፣ ከሌልች የፖለቲካ ፓርቲዎች ተወካዮች ጋር፣ ከአከባቢ፣ የክልልና የፌደራል መንግሥት ኃላፊዎች ጋር፣ ከፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት የሥራ ኃላፊዎች ጋር በቅርበት መወያየት፣ የጋራ አቋም ለመያዝ መሞክር፤
- ወቅታዊ መረጃዎችን፣ ዜናዎችን እና ዴታዎችን መከታተል፣ መተንተን፣ ከፓርቲዎ፣ ከሚወክሉት ሕዝብ እና ከሚከተሉት አቋም አንፃር መተንተን፣ ጥቅምና ጉዳቱን መለየት፣ እንደ አፈላግላጊነቱ ግብረ መልስ መስጠት ወይም ምክረ ሃሳቦችን ማዘጋጀት።

1.1.2.1. እጩነት

ፖለቲከኛ ተመራጭ ለመሆን ማለፍ ያለበት ሂደት አለ። የፖለቲካ ፓርቲ አባል የሆኑ ፖለቲከኞች ለምርጫ ሲዘጋጁ የፓርቲያቸውን ድጋፍ ለማግኘትና በእጩነት ለመቅረብ በእጩ ምልመላ ሂደት ውስጥ ያልፋሉ። በኢትዮጲያ ሕግ መሠረት ማንኛውም ፖለቲከኛ እጩ ሆኖ ለመቅረብ አስፈላጊ የሆኑ መመዘኛዎችን የማሟላት ግዴታ አለበት። በኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/11 አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ እንደተቀመጠው፣ ለምርጫ የሚወዳደሩ ፖለቲከኞች ለእጩነት የሚያበቁትን መመዘኛዎች ማሟላት ይጠበቅባቸዋል።

በአጠቃላይ፣ አንድ ፖለቲከኛ ሊገነዘበው ከሚገቡት ቁልፍ ጉዳዮች አንዱ ንቁ ተሳትፎ ለማድረግ የፖለቲካ ልምምድ ውስጥ ማለፍ አስፈላጊ መሆኑ ነው። የፖለቲካ ፍላጎትዎን በተለያዩ ተዛማጅ ሙያዎችና ተቋማት ውስጥ መጠቀም ይቻላል።

የመንግስት ስልጣን ለመያዝ እድል እስኪገኝ ድረስ፣ በሲቪል ሰርቪስ ባለሙያነት መስራት፣ ለአካባቢ አስተዳደር አካላት ገንቢ አስተያየቶችን መስጠት፣ የሰራተኛ ማኅበር አመራር መሆን፣ በበጎ አድራጎት ወይም በጋዜጠኝነት መስክ መሳተፍ (ለምሳሌ የፓርቲዎ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ዘጋቢ በመሆን) ይቻላል።

ሳጥን 1.3፡ ለእጩነት የሚያበቁ መመዘኛዎች

ማንኛውም ሰው፦

ሀ) ኢትዮጵያዊ ዜጋ የሆነ እና ለመመረጥ የተመዘገበ፤
ለ) በምዝገባ ዕለት እድሜው 21ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሆነው፤
ሐ) ከምርጫው ዕለት አስቀድሞ በምርጫ ክልሉ ውስጥ በመደበኛነት አንድ ዓመት ከኖረ ወይም የትውልድ ቦታው በእጩነት ሊቀርብበት በፈለገበት የምርጫ ክልል ውስጥ ከሆነ፤
መ) መወዳደር የሚፈልግበት ከተማ ወይም ወረዳ ከአንድ በላይ የምርጫ ክልሎችን የሚያቅፍ ከሆነ እና በከተማው ወይም በወረዳው ውስጥ ለሁለት ዓመት በመደበኛነት የሠራ ከሆነ በዚያው ከተማ ወይም ወረዳው በፈለገው የምርጫ ክልል፣
ሠ) በህግ ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብቱ ያልተገፈፈ፤
ረ) በአዕምሮ ህመም ምክንያት ለመወሰን ብቃት የሌለው መሆኑ ስልጣን ባለው አካል ወይም በበቂ ማስረጃ የተረጋገጠበት ካልሆነ፤
ሰ) በግል የቀረበ እጩ ከሆነ ራሱ፣ ለውድድር ያቀረበው የፖለቲካ ድርጅት ከሆነ ድርጅቱ ቦርዱ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚያወጣውን የምርጫ ሥነ ምግባር ደንብ ተቀብሎ ከፈረመ፤ በእጩነት ሊቀርብ ይችላል።

በየደረጃው በሚገኙ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ፣ በፓርቲዎ ውስጥ ባሉ ክንፎች (ለምሳሌ የሴቶች እና የወጣቶች ክንፎች) ወይም ሌሎች መድረኮች ላይ በንቃት መሳተፍ፣ እንዲሁም የሕግና ፍትህ ጉዳዮችን በቅርበት በመከታተልና በመተንተን የፖለቲካ ልምድ መገንባት ይቻላል።

በፖለቲካዊ መስክ መሳተፍ ለፖለቲከኞች ከፍተኛ ትምህርት እና ልምድ ያስገኛል። ከሁሉም በላይ፣ ፖለቲካ ውስን በሆኑ ሀብቶች ውስጥ የድርጊት አቅጣጫን የመወሰን ጥበብ መሆኑን ለመረዳት ይረዳል። የሁሉንም ሰው ፍላጎት የሚያሟላ በቂ ሀብት ፈጽሞ ስለማይኖር፣ ፖለቲከኞች በሚያደርጓቸው ውሳኔዎች ሁልጊዜም ሁሉንም ሰው ማስደሰት አይቻልም። አንዳንድ ሰዎችን ቅር ሊያሰኙ ይችላሉ። ዋናው ነገር **የአብላጫውን ማህበረሰብ ጥቅም እና ፍላጎት ማስጠበቅ** መቻሉ ነው። ይህም በማህበረሰቡ ውስጥ እውነተኛ ለውጥ የማምጣት እድል ይሰጣል። ለዚህ ግንዛቤ የሚያበቃ የፖለቲካ አስተዳደርና አመራር ልምምድ ወሳኝ መሆኑን መገንዘብ ተገቢ ነው።

እርስዎ የተቃዋሚ ፓርቲ አባል ነዎት? በቀጣይ ምርጫዎች ተወዳድረው የመንግሥት ሥርዓት አካል የመሆን እድል ቢመቻችልዎ፣ በሕዝብ አስተዳደር ተግባር ውስጥ ብቁ ሆነው ለመገኘት ከወዲሁ የሚያደርጉት ዝግጅት አለ? ይህን የመምሪያ መጽሐፍ ካነበቡ በኋላ ምን ለማድረግ አሰቡ?

1.1.2.2. ውክልና

ወደ የፖለቲከኞች ሚና እና ተግባራት መለስ ስንል ፖለቲከኞች፣ ምንም እንኳን በመንግሥት እርከን ውስጥ ያላቸው የሥልጣን ደረጃ ወይም በተቀዋሚ ፓርቲ ውስጥ ያላቸው የኃላፊነት ድረጃ ምንም ይሁን ምን፣ ለዲሞክራሲያዊ ማኅበረሰቦች ሥራ ወሳኝ የሆነ ብዙ ገጽታ ያለው ሚና እና ተግብራት ያከናውናሉ። እነዚህ ሚናዎች እርስ በርሳቸው የተሳሰሩ ከመሆናቸውም በላይ፣ ብዙውን ጊዜ የሚጋጩ ፍላጎቶችንና ኃላፊነቶችን በስሱ የማመጣጠን ችሎታን ይጠይቃሉ። የፖለቲከኞች ዋና ዋና ሚናዎች እና ተግባራትን[2] እንደሚከተለው በአጭሩ ዘርዝረን እንመልከት፦

የሕዝብ ተወካይ መሆን

የሕዝብ ተወካይ መሆን ሁለት ገጽታ አለው። አንደኛውና መደበኛ የሆነው፣ በምርጫ አሸንፎ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወይም የክልል ምክር ቤት አባል በመሆን የሕዝብ ወኪል መሆን ነው። ሁለተኛውና መደበኛ ያልሆነው ግን በቀጥታ በሕዝብ ሳይመረጡ፣ ለተወሰነ የማኅበረሰብ ክፍል ድምፅ በመሆን፣ ፍላጎቱን በማስተጋባት፣ በመሟገት፣ በማደራጀት ወይም በቡድን መሪነት የሚደረግ ውክልና ነው።

- **መደበኛ ውክልና**፦ የመደበኛ ውክልና ዋነኛ መሠረት ፖለቲከኞች የመረጣቸውን ሕዝብ ፍላጎትና አስተያየት በትክክል መወከል ነው። ይህ ማለት የየምርጫ ክልላቸውን ወይም በአጠቃላይ የሚያገለግሉትን ሕዝብ ፍላጎቶች፣ ስጋቶችና ምኞቶች መረዳትን ይጠይቃል። ውጤታማ ተወካዮች የሕዝባቸውን ፍላጎት ለማንፀባረቅ በትኩረት ማዳመጥ፣ የሕዝብ መድረኮችን ማካሄድ፣ የሕዝብ አስተያየት መጠየቂያ (surveys) ማከናወን እንዲሁም ክፍት የመገናኛ መስመሮችን መዘርጋት አለባቸው። ይህ ሚና የመራጮችን ድምፅ ወደ ሕግ ማውጫ ክርክሮች እና የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ማምጣትንም ያካትታል።
- **መደበኛ ያልሆነ ውክልና**፦ መደበኛ ያልሆነ ውክልና ደግሞ የተመራጭነት ቦታ ሳይዙ የተወሰኑ ጉዳዮችን ወይም ማህበረሰቦችን የሚደግፉበት መንገድ ነው። በዚህም የሚወክሉትን ማኅበረሰብ በማነሳሳት፣ በማደራጀትና በማብቃት ጥያቄዎቻቸው ወደፊት እንዲመጡ ያደርጋሉ። የሚወክሏቸው የማህበረሰብ ፍላጎቶች እንዲፈጸሙና ስጋቶቻቸው እንዲፈቱ በመርዳት የሕዝባቸው ድምፅና ተወካይ ሆነው በብቃት መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል።

እርስዎ የሕዝብ ተወካይ ሆነው የተመረጡ ፖለቲከኛ ከሆኑ፣ የመረጠዎትን ማኅበረሰብ በምን ያህል መጠን ወክያለሁ ብለው ያምናሉ? በተወሰኑ የሕግ ወይም የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ከሚወክሉት ማኅበረሰብ ጋር ውይይት ያደርጋሉ? የሕዝብን ጥያቄ፣ ፍላጎትና ስጋት በየጊዜው ለማዳመጥ የሕዝብ ከተውጣጡ ተወካዮች ጋር የጋራ ስብሰባዎችን (town hall meetings) ያካሂዳሉ?

የተቃዋሚ ፓርቲ አባል ሆነው በምርጫ አሸንፈው የሕዝብ ተወካይ ባይሆኑም፣ እወክለዋለሁ ወይም ቆሜለታለሁ ብለው ከሚያስቡት ማኅበራዊ መሠረት የሆነውን ሕዝብ በምን መልኩ ነው ወክዬዋለሁ ብለው የሚያስቡት? የሚወክሉትን ማኅበረሰብ ለማነጋገር እና ጥያቄውን፣ ፍላጎቱንና ስጋቱን በየጊዜው ለማዳመጥ የሚጠቀሙት ዘዴዎችስ ምንድናቸው?

የሕዝብ ጉዳዮች ተሟጋች መሆን	ፖለቲከኞች የተወሰኑ ጉዳዮችን፣ ፖሊሲዎችን ወይም ቡድኖችን ወክለው ይሟገታሉ። ለምሳሌ የአካባቢ ጥበቃ፣ የኢኮኖሚ ልማት፣ የማኅበራዊ ፍትህ፣ ወይም የተጋላጭ የማኅበረሰብ ቡድኖች (ሴቶች፣ ሕፃናት፣ ወጣቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ ተፈናቃዮች) መብቶች እንዲጠበቁና እንዲከበሩ አስፈላጊ ናቸው ብለው የሚያምኑባቸውን ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ባህላዊና ሌሎች አገራዊ ጉዳዮች ላይ ግንባር ቀደም ሆነው ድምፅ ያሰማሉ፣ ይደግፋሉ እንዲሁም ይሟገታሉ። ይህ ተሟጋችነት በብዙ መልኩ ሊገለጽ ይችላል። ከእነዚህም መካከል በሕዝብ ፊት መናገር፣ ሕግ ማውጣት፣ ባልደረቦችን ማግባባት (ሎቢ ማድረግ) እና ከሌሎች የፖለቲካ አካላት ጋር መደራደር ይገኙበታል። ውጤታማ የመሟገት ችሎታቸው በአሳማኝ ክህሎቶቻቸው፣ በፖሊሲ ግንዛቤያቸውና ጥምረት የመፍጠር አቅማቸው ላይ የተመሠረተ ነው። እርስዎ እንደ ፖለቲከኛ የሚወክሉት ማኅበረሰብ በምን ጉዳይ ላይ ተሟግተውለታል? ያነሱት ጥያቄ ተቀባይነት እንዲያገኝስ ምን ዓይነት ዘዴ ተጠቀሙ?
የፖሊሲ አውጪነት ሚና	የፖለቲካ ፓርቲዎችና ፖለቲከኞች ማዕከላዊ ተግባራት ከሚባሉት ጉዳዮች መካከል በፖሊሲ ዝግጅት ሂደት ውስጥ መሳተፍ ነው። ይህ ሂደት የህዝብ ችግሮችን መለየት፣ ሊሆኑ የሚችሉ መፍትሄዎችን መመርመር፣ ረቂቅ ህጎችን ማዘጋጀት፣ በእነዚህ ረቂቅ ህጎች ላይ መከራከር፣ የፖሊሲ ሀሳቦችን ማርቀቅ እና በመጨረሻም በሕጎችና ደንቦች ላይ ድምጽ መስጠትን ያጠቃልላል። የፖሊሲ ዝግጅት መረጃ የመሰብሰብ፣ የትንተና ክህሎት፣ የመደራደር ችሎታ፣ እና የተለያዩ ፖሊሲዎች በህብረተሰቡ ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ ጥልቅ ግንዛቤን የሚጠይቅ ውስብስብ ሂደት ነው። የመንግስት ስልጣን የያዙ ፖለቲከኞች በሲቪል ሰርቫንቶችና ባለሙያዎች እየተረዱ፣ የህዝብን ህይወት የሚቀርጹ ፖሊሲዎችን የማውጣት፣ የመተግበርና ውሳኔዎችን የመስጠት የመጨረሻ ኃላፊነት አለባቸው። በተቃዋሚ ፓርቲዎች ውስጥ የሚሳተፉ ፖለቲከኞች ደግሞ ከሕዝብ ጋር በቀጥታ እየተገናኙ የፖሊሲ ሀሳቦችን የማዳበር፣ አማራጭ ፖሊሲዎችን በፓርቲያቸው ውስጥ የማርቀቅና የማስጸደቅ፣ እንዲሁም ገዥው ፓርቲ የሚያወጣቸውን ፖሊሲዎች በመከታተል ጉድለታቸውን በማሳየት ማሻሻያ እንዲደረግባቸው ምክረ ሃሳብ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል። እርስዎ እንደ ፖለቲከኛ፣ በፖሊሲ ማርቀቅና ማጸደቅ ሂደት ውስጥ ያለዎትን ሚና እና ተግባር እንዴት ይገመግሙታል?
የማኅብረሰብ መሪነት	ፖለቲከኞች ከመደበኛ የመንግሥት ወይም የፓርቲ መሪነታቸው ባሻገር፣ በማኅበረሰቡ ውስጥ እንደ ተፅዕኖ ፈጣሪና ታዋቂ ሰዎች ይቆጠራሉ። በእነዚህ ሚናቸው የጋራ ተግባራትን ሊያነሳሱ፣ አለመግባባቶችን ሊፈቱ፣ የማኅበረሰብ ትስስርን ሊያበረታቱ እንዲሁም ለአካባቢያዊ ችግሮች ምላሽ ሊሰጡ ይችላሉ። ይህ የማኅበረሰብ ሚና ብዙውን ጊዜ በማኅበራዊ ዝግጅቶች ላይ መገኘትን፣ የአካባቢ እንቅስቃሴዎችን መደገፍን፣ እና ለእርዳታ ወይም ለመመሪያ ለሚፈልጉ ዜጎች እንደ መገኛ ነጥብ ሆኖ ማገልገልን ያጠቃልላል። ውጤታማ የማኅበረሰብ አመራር ለመሆን ርኅራኄን፣ ተቆርቋሪነትን፣ ተደራሽነትን፣ አክብሮትን እና ከሰዎች ጋር በግል ደረጃ የመገናኘት ችሎታን ይጠይቃል። የፖለቲከኛነት ሚና ከጀመሩ በኋላ ከሚወክሉት ማኅበረሰብ ጋር ምን ያህል ተቀራርበው እየሰሩ ነው? የማኅበረሰብ ችግሮችን ለመፍታት እንደ ፖለቲከኛ የእርስዎ ሚና ምን መሆን አለበት ብለው ያምናሉ?

1.2. ማኅበራዊ መሠረት በመገንባት

የፖለቲካ ፓርቲዎች ዋና ዓላማቸው ምርጫ ማሸነፍ ሲሆን ይህንንም ለማሳካት **“ማኅበራዊ መሠረት”** መገንባትና ማስቀጠል አለባቸው። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ “ማኅበራዊ መሠረት” የሚለው ቃል የፖለቲካ ሳይንስ ላይ የሚታወቀውን **“የምርጫ ክልል” (constituency)** የሚለውን ጽንሰ ሃሳብ ተክቶ ጥቅም ላይ ውሏል።

“ማኅበራዊ መሠረት” ማለት አንድን ፓርቲ የሚያውቁ፣ በየጊዜው የሚደግፉ እና ከፓርቲው ጋር የሚተባበሩ ደጋፊዎችን፣ መራጮችን እና አክቲቪስቶችን የያዘ ስብስብን ያመለክታል። እነዚህን ማኅበራዊ መሠረቶች መገንባት ቀጣይነት ያለው እና ሁለገብ ሂደት ነው። ፓርቲዎች ሰፊ ድጋፍ ለመጠየቅ ከሚያደርጉት እንቅስቃሴ ጀምሮ፣ ከፍተኛ በሆነ መንገድ የታለሙ ግለሰቦችንና ቡድኖችን ኢላማ ያደረገ ቅስቀሳ (targeted outreach) የመሳሰሉ የተለያዩ ስልቶችን መጠቀም ይጠበቅባቸዋል። በዓለም ዙሪያ ባሉ ዲሞክራሲያዊ ሀገሮች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ማኅበራዊ መሠረት ወይም የምርጫ ክልል በአብዛኛው የፖለቲካ ተወካይ ለመምረጥ የዜጎች ድምፅ የሚቆጠርበት በግዛት የተወሰነ አካባቢ ተደርጎ ይወሰዳል። ይሁንና፣ የማኅበራዊ መሠረት ፍቺ በጂኦግራፊያዊ ገደብ ብቻ የተወሰነ አይደለም።

ለፖለቲካ ፓርቲዎች ማኅበራዊ መሰረታቸውን እንዴት ማሳደግና መገንባት እንደሚችሉ መረዳት ቁልፍ ጥያቄ ነው። ፓርቲዎች ማኅበራዊ መሰረታቸውን ለመገንባት የተለያዩ ስልቶችን መጠቀም ይችላሉ።

- **በመጀመሪያ** ፓርቲዎ የሚወክለው የኅብረተሰብ ክፍል የትኛው ነው?
- **በሁለተኛ ደረጃ** ፓርቲዎ ማኅበራዊ መሰረቱን ለማስፋት የሚከተላቸው ስልቶችስ እንዴት ያሉ ናቸው?

በበርካታ የመድብለ ፓርቲ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት በሚያራምዱ ሀገራት ውስጥ የፖለቲካ ፓርቲዎች ማኅበራዊ መሠረታቸን ለመገንባት የሚከተሏቸው ስልቶችን[3] አስከትለን በአጭሩ እናያለን።

የርዕዮተ ዓለም አንድነት	ፓርቲዎች ብዙውን ጊዜ የሚጀምሩት ከተወሰኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የሚስማሙ ግልጽ እሴቶችን፣ መርሆችን እና የፖሊሲ አቋሞችን በማብራራት ነው። ይህ ርዕዮተ ዓለማዊ "ምልክት" (brand) ሊሆኑ የሚችሉ ደጋፊዎች ራሳቸውን ከፓርቲው ጋር እንዲያገናኙ እና እንዲለዩ ያስችላቸዋል። አብዛኛው ፖለቲካ ፓርቲዎች የሚከተሉት ወይም የሚያራምዱት ርዕዮተ ዓለም እንዳላቸው ይታመናል። የሚከተሉት ፕሮግራምና የሚያራምዱት የፖሊሲ ማዕቀፍ ከዚህ ርዕዮት አለም የሚቀዳ መሆን እንዳለበትም ይታመናል። በስፋት እንደሚታወቀው የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም የማኅበራዊ እንቅስቃሴ፣ የድርጅት ወይም የፓርቲ ሥነ ምግባራዊ አስተሳሰቦች፣ መርሆዎች፣ አስተምህሮዎች፣ ትርክቶች ወይም ምልክቶች ስብስብ ነው። እነዚህ የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለሞች ኅብረተሰብ እንዴት መስራት እንዳለበት ያብራራሉ። እንዲሁም ለተወሰነ ማኅበራዊ ሥርዓት ግንባታ ምን መሆንነት ማብራሪያ (blueprint) ያቀርባሉ። በመሆኑም በየትኛውም መልኩ የተደራጁ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚያምኑበት እና አቅጣጫቸውን የሚያሰምሩበት ርዕዮተ ዓለም እንዲኖራቸው ይመከራል። ለመሆኑ እርስዎ አባል የሆኑበት የፖለቲካ ፓርቲ የሚከተለው ርዕዮተ ዓለም እንዴት ያለ ይሆን? ቁምነገሩ ርዕዮት ዓለም ማኅበራዊ መሠረትን ለመገንባት ወሳኝ መንገድ መሆኑን መረዳት ነው። ፓርቲዎች በቁልፍ ጉዳዮች (ለምሳሌ የኢኮኖሚ ፖሊሲ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ጉዳዮች፣ የውጭ ግንኙነትና ደህንነት ወዘተ) ላይ አቋም በመውሰድ ተመሳሳይ እምነት ያላቸውን ግለሰቦች ወይም የፓርቲው ፖሊሲዎች ጥቅሞቻቸውን በተሻለ ሁኔታ ያስጠብቅልናል ብለው የሚያምኑ ሰዎችን እና ብድኖችን ይስባሉ። የጠራና ወጥነት ያለው ርዕዮት ዓለም ይዞመገኘት እና ከርዕዮት ዓለሙ ጋር በደንብ ተስማምቶ የተቀረጸ የፖሊሲ አማራጭ አንድን ፓርቲ ከሌላው የሚመረጥ ሊያደረገው ይችላል። ፓርቲዎ የማኅበራዊ መሠረቱን ለማስፋት፣ የሚከተለውን ርዕዮተ ዓለምና የሚያራምደውን የፖሊሲ ማዕቀፍ ምን ያህል በስፋት ለማስተዋወቅ ጥረት አድርጓል? ፓርቲዎ የሚከተለው ርዕዮተ ዓለም፣ “ማኅበራዊ መሠረቴ ነው” ከሚለው ማኅበረሰብ ጋር ምን ያህል ይጣጣማል? ይህንን በተመለከተ ምን ያህል እርግጠኛ ነዎት?

የፓርቲ አደረጃጀት መዋቅርና እና ቅስቀሳ

የፓርቲን ማኅበራዊ መሠረት ለመገንባትና ለማስፋት ወሳኝ ከሆኑ ጉዳዮች መካከል የፓርቲዎች መዋቅራዊ አደረጃጀት፣ እስከታች ድረስ የሚዘረጋ የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት መኖር እና ማኅበራዊ ንቅናቄ ወይም ቅስቀሳ ማካሄድ በጉልህ የሚጠቀሱ ናቸው። ለዚህ ሁነት እውን መሆን ጠንካራ የፓርቲ አደረጃጀት መገንባት በጣም ወሳኝ ነው። ይህም እንደ ፓርቲው አይነት በ**ፌደራል**፣ በክልል፣ በዞን፣ ወረዳና በአካባቢ ደረጃዎች ጽሕፈት ቤት ቢኖረው ተደራሽነቱን ያሳድገዋል፣ የማስተባበር አቅምንም ይጨምርለታል። ለምሳሌ አገር አቀፍ ፓርቲዎች **ፌደራል** ዋና መስሪያ ቤት፣ የክልልና የዞን ቅርንጫፍ መስሪያ ቤት፣ የወረዳ ማዕከል ወይም ኮሚቴዎች፣ የአካባቢ ቀበሌ አስተባባሪዎች ቢኖሩት በየደረጃው ማኅበራዊ መሠረቱን ለመገንባት እድል ይሰጠዋል።

ፓርቲዎች በአብዛኛው የሚተማመኑት ከታች ወደ ላይ በሚደረገው የህዝብ ቅስቀሳ ላይ ሲሆን ይህም በአካባቢ ደረጃ ሰዎችን ለማሰባሰብ ነው። ይህ ደግሞ የሚከተሉትን ያጠቃልላል፦

- ከቤት ወደ ቤት የማግባባት ሥራ (Door-to-door canvassing) ለምሳሌ የፓርቲው አባል ወይም ደጋፊ ለመሆን የሚፈልጉትን ግለሰቦችን እና መራጮችን ቤታቸው ድረስ በመሄድ በቀጥታ ማነጋገር፤
- የስልክ ቅስቀሳ (Phone banking) በተለይም እምቅ የፓርቲው ዓላማ እና እሴቶች ደጋፊዎች ይሆናሉ ተብለው ለሚታሰቡ ወገኖች በመደወል ስለፓርቲው አጠቃላይ መረጃ መስጠት አባል ወይም ደጋፊ እንዲሆኑ እንዲሁ በምርጫ ወቅት ለፓርቲው ድምጽ በመስጠት እንዲሳተፉ ማበረታታት፤
- የህብረተሰብ ስብሰባዎችና ሰልፎች (Community meetings and rallies) በማካሄድ በርካታ ሰዎችን ለመሳተፍ የሚያስችሉ መድረኮችን ማቅረብና ከማኅበረሰቡ ጋር የአብሮነት ስሜትን ማዳበር፤
- የበጎ ፈቃደኞች መረቦች (Volunteer networks) በመዘርጋት የተለያዩ የፓርቲ ደጋፊዎችን ማብዛት። የምርጫ ዘመቻዎችንና የፓርቲ እንቅስቃሴዎችን ለማካሄድ በጎ ፈቃደኞችን በየጊዜው መመልመል፣ ስለፓርቲው የግንዛቤ ስልጠና መስጠትና ማስተባበር፤
- ማኅበራዊ ሚድያን በመጠቀም ስለፓርቲው ማንነትና ምንነት ሰፊ የማስተዋወቅ ሥራዎችን በመስራት ተጨማሪ አባላትና ደጋፊዎችን ለማሰባሰብ መሞከር። በተለይ የማኅበራዊ ሚድያ ተጠቃሚ የሆኑ ወጣቶችና ጎልማሶችን በሚስብ መልኩ መረጃዎችን በማቅረብ የነቃ ተሳትፎ ማካሄድና ከዘመኑ ጋር መራመድ የፓርቲውችን ንቅናቄ ይደግፋል።

ፓርቲዎ ማኅበራዊ መሠረቱን ለማስፋት፣ አባላትና ደጋፊዎችን ለማሰባሰብ ምን አይነንት ዘዴ ይጠቀማል?

የእጩዎች ምልመላ እና ስያሜ

የፖለቲካ ፓርቲዎች የማኅበራዊ መሠረታቸውን ለማስፋትና ድጋፋቸውን ለማጠናከር ከሚጠቀሙባቸው ስልቶች አንዱ፣ ለምርጫ የሚያቀርቧቸው እጩዎች **ስብዕና፣ ተወዳጅነት፣ ተፅዕኖ ፈጣሪነት እና በማኅበረሰብ ዘንድ ያላቸው ተቀባይነት** ነው። ለዚህም ዓላማ ፓርቲዎች ከራሳቸው ርዕዮተ ዓለም ጋር የሚጣጣሙ እና ምርጫ የማሸነፍ ብቃት ያላቸውን ግለሰቦች በመመልመል ማኅበራዊ መሠረታቸውን ይገነባሉ። ታዋቂና ተፅዕኖ ፈጣሪ እጩዎች የፓርቲዎችን ደጋፊዎች የማስፋትና ማኅበራዊ መሠረት ግንባታ ዋና ማዕከል ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ የሆነበት ምክንያት፣ መራጮች ከምናባዊ የፓርቲ ፕሮግራሞች ይልቅ ከግለሰቦች ጋር በቀጥታ የመገናኘት ዝንባሌ ስላላቸው ነው። የእጩዎች ምልመላና ስያሜ ሂደት (ለምሳሌ የቅድመ-ምርጫ ወይም የካውከስ ስብሰባዎች) የፓርቲ አባላትን በማሳተፍ በተመረጡ ተወካዮች ላይ የባለቤትነት ስሜት እንዲፈጠር ያደርጋል።

የእርስዎ ፓርቲ የእጩዎች ምልመላና ስያሜ ሂደት ላይ ማኅበራዊ መሠረቱን ለማስፋት ምን ያህል ጥረት እያደረገ ነው?

የየአጀንዳ ባለቤትነት እና ክብደት

የፖለቲካ ፓርቲዎች ብዙውን ጊዜ በሕዝብ አእምሮ ውስጥ የአንዳንድ አጀንዳዎች "ባለቤት" ይሆናሉ። ለምሳሌ፣ አንድ ፓርቲ በኢኮኖሚ ጉዳዮች ላይ ጠንካራ ተደርጎ ሊታይ ሲችል፣ ሌላው በማኅበራዊ ደህንነት ላይ የተሻለ እንደሆነ ሊታሰብ ይችላል። ፓርቲዎች የተወሰኑ አጀንዳዎችን በተከታታይ በማጉላት እና እነሱን ለመፍታት የተሻለ ብቃት እንዳላቸው በማቅረብ፣ ለእነዚያ አጀንዳዎች ቅድሚያ የሚሰጡ አባላትን፣ ደጋፊዎችን እና መራጮችን ሊያሰባስቡ ይችላሉ። ፓርቲዎች የነጠረና በጉልህ የተለየ አጀንዳ ወይም እርሰ ጉዳይ ሲኖራቸው በሚያራምዱት አቋም ምክንያት ማኅብራዊ መሠረታቸውን የማስፋት እድል ሊገጠማቸው የሚችልበት አጋጣሚ በርካታ ነው።

የእርስዎ ፓርቲ የሚያራምዳቸው አጀንዳዎች ቅቡልነትን ለማግኘት፣ ድጋፍ ለማሰባሰብ፣ አባላት ለማብዛትና ማኅበራዊ መሠረትን ለመገንባት ምን ያህል ብቁ ነው ብለው ያስባሉ? ወደ ኃላስ መለስ ብሎ የአጀንዳዎችን ክብደት በየጊዜው ለመፈተሽና ለመለወጥ፣ ለማሻሻል ወይም አዲስ አጀንዳ ለመጨመር ጥረት ያደርግ ይሆን?

በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል፣ ጥምረት፣ ቅንጅት ወይም ትብብር መፍጠር	የፖለቲካ ፓርቲዎችን ማኅበራዊ መሠረት ከሚያሰፉና ከሚገነቡ ዘዴዎች አንዱ በፓርቲዎቹ መካከል የሚድረግ ውህደት፣ ጥምረት፣ ቅንጅት ወይም ትብብር ነው። ፓርቲዎች ከመሠረታዊ ደጋፊዎቻቸው ባሻገር ተደራሽነታቸውን ለማስፋት ብዙውን ጊዜ ጥምረት፣ ቅንጅት ወይም ትብብር በመፍጠር ይሳተፋሉ። ይህ ምንም እንኳን በሌሎች ጉዳዮች ላይ ቢለያዩም፣ የተወሰኑ የጋራ ዓላማዎችን የሚያጋሩ ሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የጥቅም ቡድኖች ወይም የማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ጋር ጥምረት መፍጠርን ያካትታል። እነዚህ ጥምረቶች፣ ቅንጅቶች ወይም ትብብሮች ጊዜያዊ (ለተወሰነ ምርጫ) ወይም ይበልጥ ዘላቂ (የአስተዳደር ጥምረት መፍጠር) ሊሆኑ ይችላሉ። ከተለያዩ ቡድኖች ጋር በመስራት፣ ፓርቲዎች ሰፋ ያለ ፍላጎቶችን መሰብሰብ እና በርካታ መራጮችን መሳብ ይችላሉ። ለአጭር ጊዜ ምርጫን ተከትሎ የሚመጣ መጣመር ወይም መቀናጀትም ይሁን በዘለቄታ በትብብር ለመሥራት የፖለቲካ ፓርቲዎች ግንባር ሲፈጥሩ ከሚፎካሯቸው የፖለቲካ ኃይሎች ባሻገር አለስፈላጊ ከሆኑ የድጋፍና ድምጽ ቅርምትና ሽሚያ ሊታደጋቸው ይቻላል። ይህም ጠንካራ ማኅበራዊ መሠረት ለመገንባት አይነተኛ ዘዴ ይሆናል። ፓርቲዎ አባል የሆነበት የፖለቲካ ፓርቲዎች ጥምረት፣ ቅንጅት ወይም ትብብር አለ? ማኅበራዊ መሠረቱን ለማስፋት ምን ያህል ተጠቅሞበታል?
የተግባቦትና የሚዲያ ስትራቴጂ መኖር	አንድን የፖለቲካ ፓርቲ ማኅበራዊ መሠረቱን እንዲያሰፋና እንዲገነባ ከሚያስችሉት መገዶች መካከል የሚከተለው የሕዝብ ግንኙነት ስልቱ ነው። ማኅበራዊ መሠረትን ለመገንባት ውጤታማ የሕዝብ ግንኙነት ወሳኝ ነው። ፓርቲዎች መልዕክቶቻቸውን ለማስተላለፍ፣ እጩዎቻቸውን ለማስተዋወቅ እና ተቃዋሚዎቻቸውን ለመተቸት ባህላዊ ሚዲያዎችን (ቴሌቪዥን፣ ራዲዮ፣ የህትመት ውጤቶች)፣ ቀጥተኛ የመልዕክት ልውውጥ (direct mail) እና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣውን ማኅበራዊ ሚዲያ ይጠቀማሉ። በተለይም ማኅበራዊ ሚዲያ ለሚከተሉት የፓርቲያቸውን ማንነትና ዓላማዎች በሰፍፊው ለማስተዋወቅና ድጋፍ ለማሰባሰብ ሁነኛ መሳሪያ ሆኗል። ለፖለቲካ ፓርቲዎች የማኅበራዊ መዲያን ውጤታማ በሆነ መንገድ መጠቀም መቻላቸው በርካታ ቱርፋቶች አሉት። ከነዚህም መካከል፡ • ቀጥተኛ ተሳትፎ (Direct engagement) የማኅበራዊ ሚዲያው አንዱ በረከት ነው። ከፓርቲው አባላት፣ ከደጋፊዎች እና እምቅ መራጮች ጋር በቀጥታ ለመገናኘት እድል ይፈጥራል። እነኝህ ወገኖች የሚያጸባርቁትን ፍላጎቶች፣ ስጋቶች እና ቅድሚያ የሚሰጧቸውን ጉዳዮች በቀጥታ ለመስማት ያስችላል። ግብረመልሶችን ለመስጠት፣ የሚተቻቸው ጉዳዮችም ካሉ ምክንያታቸውን ለመረዳት ያስችላል። • ፈጣን እና ተጨባጭ መረጃ ማሰራጨት (Information dissemination) ለፓርቲዎች ካለው ፋይዳ አንፃር የማኅበራዊ ሚዲያን በአግባቡ መጠቀም ጠቀሜታው በርካታ ነው። የፓርቲውን ዜናዎች፣ የፖሊሲ ማሻሻያዎች፣ አዳዲስ አጀንዳዎች፣ የምርጫ ዘመቻ መልዕክቶች እና ማስታወቂያዎች በፍጥነት እና መጠነኛ በሆነ ወጪ በስፋት ለማሰራጨት በማስቻሉ የፓርቲውን አባላት እና ደጋፊዎች መድረስ ብቻ ሳይሆን ማኅበራዊ መሠረትን ለመገንባትና ለማስፋት በርካታ ጠቀሜታ ይኖሩታል። • ማኅበራዊ ሚዲያን በሰፊው መጠቀም ሌላኛው ጥቅሙ አባላትን፣ ደጋፊዎችን እና እምቅ ድምጽ ሰጪዎችን ማሰባሰብ (Mobilization) ማስቻሉ ነው። ዝግጅቶችን ለማደራጀት፣ የድርጊት ጥሪዎችን ለማድረግ እና መራጮችን ወደ ድምጽ መስጫ ለማምጣት ማኅበራዊ ሚዲያን መጠቀም አዋጭ ዘዴ የሚሆንበት አጋጣሚ ብዙ ነው። • ፓርቲዎች በታለመ መልኩ መልዕክት ማስተላለፍ (Targeted messaging) ሊጠቀሙበት ይችላሉ። የመረጃ ትንተናን (data analytics) በመጠቀም መልዕክቶችን ለተወሰኑ የህዝብ ክፍሎች (demographic groups) ለማበጀት እና ለማሰራጨት ማኅበራዊ ሚዲያው የተሻለ እድል ይፈጥራል። በተለይ ወጣቶችን ለማነሳሳት እና የፓርቲው ደጋፊዎች እንዲሆኑ ከማስቻል አንፃር ያለውን ጠቀሜታ ተረድቶ ይህን የሚዲያ መድረክ መጠቀም በርካታ ጥሞች ሊያስገኝ ይችላል። የፓርቲዎ የተግባቦት ስልት የፓርቲዎን ድጋፍ ለማጠናከርና የማኅበራዊ መሠረቱን ለማስፋት ምን ያህል ውጤታማ ነው? ፓርቲዎ የማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀሙ ምን ያህል የተጠና እና ውጤታማ ነው?

የሚከተለው ሠንጠረዥ ማኅበራዊ መሠረትን ለመገንባትና ለማጎልበት የሚያገለግሉ በርካታ ስልቶችን ይዘረዝራል። ከእያንዳንዱ ስልት ጋር በተያያዘ የፖለቲካ ፓርቲዎች ያላቸውን የሀብት ውስንነት ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ **ኦንላይን መተግበር** የሚችሉበትን መንገድ እንጠቁማለን።

በተጨማሪም፣ ስልቱ በሶስት ደረጃዎች ማለትም ቅድመ-ምርጫ (1)፣ በምርጫ ወቅት (2) እና ድህረ-ምርጫ (3) መተግበር እንዳለበት እንጠቁማለን። ይሁን እንጂ፣ የማኅበራዊ መሠረት የመገንባት ሂደት ቀጥተኛ መስመር ብቻ እንደማይከተል መገንዘብ ያስፈልጋል። ይልቁንም፣ ሂደቱ ውስብስብና ተደጋጋሚ (cyclical) ነው።

ሰንጠረዥ 1.1፡ የማኅበራዊ መሠረት መገንባት ስልት/ስትራቴጂ

ስልት/ስትራቴጂ	በኦንላይ መካሄድ ይቻላልን?	በየትኛው የምርጫ ወቅት? (ቅድመ ምርጫ (1)፣ በምርጫ ወቅት (2)፣ ድህረ ምርጫ (3))
ፓርቲው በሚንቀሳባቸው የክልል አካባቢዎች በተለያዩ ቦታዎች አቅም በፈቀደ መጠን ቢሮዎችን ይክፈቱ። ቢሮዎች መክፈት ሳይቻል ቋሚ ተወካዮችን መመደብ። እነዚህን ቢሮዎች ወይም ቋሚ ተወካዮች መረጃ ለማሰራጨት፣ እንቅስቃሴዎችን ለማስተባበር እና በየጊዜው አዳዲስ አባላትን/ደጋፊዎችን ለመመልመል ይጠቀሙባቸው።	አይ	1፣ 2፣ 3
ደጋፊ ሊሆኑ የሚችሉ ሰዎች አሉ ተብሎ የሚገመቱ ቦታዎች ላይ ትኩረት በማድረግ ለምሳሌ ባኅላዊ፣ ሀይማኖታዊና የትምህርት ተቋማት፣ የንግድ ማኅበረሰብ፣ ወጣቶች፣ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች ማኅበራት፣ አርሶ አደሮች/አርብቶ አደሮች የሚንቀሳቀሱባቸው አከባቢዎች በመገኘት ከተመረጡ ሰዎች ጋር ለመቀራረብና ለመወያየት የሚያስችሉ የግንኙነት መረብ ለመዘርጋት ጥረት ያድርጉ።	አዎ	1፣ 2፣ 3
ሁሉም ተሳታፊዎች የመናገር፣ ሃሳብ ማካፈል እና ጥያቄ ማንሳት የሚችሉበት እና እድል የሚያገኙበት ሁሉን አቀፍና አካታች ስብሰባዎችን ያካሂዱ። እነዚህ ስብሰባዎች በሚከተሉት ምክንያቶች በመደበኛነት ሊካሄዱ ይችላሉ፦ • የፓርቲውን ማንነት፣ ርዕዮተ ዓለም፣ ዓላማዎች፣ አጀንዳዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ግቦች የመሳሰሉ ጉዳዮች ለማስረዳት፤ • ማኅበረሰቡ ውስጥ ያሉ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና መሰል ጥያቄዎች፣ ፍላጎቶች፣ ስጋቶች እና ተያያዥ ጉዳዮችን ለማድመጥ፤ • ከፓርቲው አጀንዳ ጋር የተያያዙ የጋራ አቋሞችን ለመመልከትና ለመስማማት፤ • ስለፓርቲው ለአባላት፣ ደጋፊዎች እና እምቅ ድምጽ ሰጪዎች መረጃ ለምስጠት፤ • የፓርቲው ማኅበራዊ መሠረት ናቸው የተባሉ ዋና ዋና አካላት ስለፓርቲያቸው፣ አከባቢያቸው፣ ክልላቸው ወይም ሀገራቸው ያላቸውን አመለካከት እንዲያካፍሉ እና ለሰፊው ማኅበረሰባቸው ተቀባይነት ባላቸው አቋሞች ላይ መመሪያ እንዲሰጡ ማስቻል ናቸው። በእንደዚህ ዓይነት ስብሰባዎች የፓርቲው ማኅበራዊ መሠረት ከሆኑ አካላት የሚነሱ አስተያየቶችን፣ ምክረ ሀሳቦችን እና ጥያቄዎችን በትኩረት ማዳመጥ ወሳኝ ነው።	አዎ	1፣ 2፣ 3
እምቅ ደጋፊዎችን (ግለሰቦችን እና ቡድኖችን) በግል ማግኘት (ለምሳሌ በደብዳቤ ወይም በኢሜል፣ ስልክ በመደወል፣ የቴሌ ግራም ወይም የዋትስ አፕ መተግብርያዎችን ተጠቅሞ መልዕክት መላክ) ፤ ምናልባትም ቀድሞ ቃል በተገባ የጋራ ጥቅም ላይ በመመስረት ማግባባት። • ማኅበራዊ መሠረታችን ነው በተባለ ምርጫ ክልል ውስጥ ያሉ የተለያዩ አካላትን ለማሳተፍ መሞከር ጠቃሚ ሊሆን ይችላል (ለምሳሌ የሃይማኖት፣ የብሔር፣ የጾታ፣ የእድሜ እና ሌሎች የቡድኖች ልዩነቶችን ከግምት ውስጥ በማስገባት) ፤ • ልምድ ያካበቱ የማህበረሰብ አደራጆችን ማሳተፍም ጠቃሚ ሆኖ ሊገኝ ይችላል። በሌላ አነጋገር፣ ለአካባቢያዊ ችግሮች መፍትሄ በማግኘት ልምድ ያላቸውን፣ የማኅበረሰቡን ችግር በአጋቡ የሚረዱ፣ በባህልና በተጽኖ ፈጣሪነታቸው የተሻለ ቅቡልነት ያላቸውን ሰዎች ማካተት።	አዎ	1፣ 2፣ 3

ሰልፎችን ማደራጀት ወይም አሁን ባሉ ተቃውሞዎች ወይም የድጋፍ እንቅስቅሴ ውስጥ መሳተፍ እና/ወይም መምራት።	ይህን በአካል ብቻ ሳይሆን በመጎበራዊ ሚድያ ዘመቻዎች አማካይነት መከውን ይቻላል	1፣ 2፣ 3
ያሉትን ወይም ሊኖሩ የሚችሉትን የዜጎችን ልምድ፣ፍላጎት፣ ስጋትና ጥያቄዎች በተሻለ ለመረዳት የሚያስችል (አሳታፊነት ያለው) ጥናት ማካሄድ።	አዎ	1፣ 2፣ 3
ለፓርቲው ማኅበራዊ መሠረት ለሆነው ማኅበረሰብ የተሟጋችነት (Advocacy) ስራዎችን ለማከናወን ከዜጎች የተሰበሰበ ወይም ስለ ዜጎች ሁኔታ የተሰበሰቡ መረጃዎችንና ጥናቶችን መጠቀም በጣም ጠቃሚ ነው። ይህ ማለት፦ • ከዜጎች በተሰበሰቡ መረጃዎች ለምሳሌ በሕዝብ አስተያየት ጥናቶች፣ በውይይት መድረኮች፣ ወይም በቀጥታ ከዜጎች በተሰበሰቡ መረጃዎች ላይ መመስረት፤ • ስለ ዜጎች በተደረጉ ጥናቶች ለምሳሌ በማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወይም ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ የተሰሩ ጥናቶችን በመጠቀም የዜጎችን ፍላጎትና ችግር ለመረዳት ይቻላል። እነዚህን መረጃዎች በመጠቀም የሚቀርቡት የድጋፍና የተሟጋችነት ክርክሮች ጠንካራና በማስረጃ የተደገፉ እንዲሆኑ ይረዳል። ይህም የውሳኔ ሰጪዎችን ቀልብ ለመሳብ እና የተፈለገውን ለውጥ ለማምጣት ወሳኝ ነው።	አዎ	1፣ 2፣ 3
ከህብረተሰቡ (ወይም ከሚጠበቁ አባላት) ጋር በመተባበር የፖሊሲ ወይም የአቋም መግለጫዎችን ማዘጋጀት።	አዎ	1፣ 2
ከሌሎች ንቅናቄዎች እና/ወይም የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ጥምረት መፍጠር።	አዎ	1፣ 2፣3
ፓርቲው ስለሚሳተፍባቸው ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ለምሳሌ ምርጫ፣ ሀገራዊ ምክክር፣ የሰላም ድርድር፣ የሕግ ማሻሻያ ሂደት፣ ከፓርቲዎች ጋር ስለፈጠረው ጥምረት ወዘተ ሂደትና ውጤት ለህዝብዎ በቀላል ቋንቋና በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች በየጊዜው ያሳውቁ።	አዎ	1፣ 2፣3
የምርጫ ውጤቶችን አስመልክቶ በሚደረጉ የድህረ ምርጫ **ውይይት** (post election reflection) በንቃት መሳተፍና ሃሳብ፣ መከራከርያ ነጥቦች ማንሳት፣ ትምህርት የሚሏቸውን ነገሮች ልይቶ ማንሳት ያስፈልጋል። • ድህረ-ምርጫ ትንተና የምርጫ ውጤቶችን መመርመርን፣ የመራጮችን ባህሪ መረዳትን፣ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲውንና የመሪዎችን አፈጻጸም መገምገምን ያካትታል፤ • ይህ ሂደት የመራጮች ምርጫ ላይ ተጽዕኖ ያደረጉ ነገሮችን መመርመር፣ የዘመቻ ስልቶችን መገምገም፣ እና ለወደፊት ምርጫዎች ትምህርት የሚሆኑ ነጥቦችን መለየትን ያጠቃልላል። ይህም ፓርቲውን ከማኅበራዊ መሠረቱ ከሆኑት ድጋፊዎቹ ጋር የበለጠ እንዲቀራረብና ትምህርቶችና ልምዶችን ለመቀመር ያስችለዋል።	አዎ	3
ለፖለቲካ አዲስ አቀራረብ ያለውን ጥቅም በተግባር ማሳየትና ምሳሌ መሆን።	አዎ	1፣ 2፣3

1.3. ምስጉን የፖለቲካ አመራርነት

በዚህ ምዕራፍ ቀጥለን የምንመለከተው የፖለቲካ አመራሮችን ስኬታማነትና ውጤታማነት ስለሚወስኑ ጉዳዮች ነው። የፖለቲካ ፓርቲ ስኬታማ ሊሆን የሚችለው በፓርቲው መዋቅር፣ ተቋማዊ አቅም ወይም በአባላት ብዛት ብቻ እንዳልሆነ ከኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች አጠቃላይ ሁኔታ መረዳት ይቻላል። የፖለቲካ ፓርቲን ውጤታማና ዘመን ተሻጋሪ ከሚያደርጉት ወሳኝ ግብዓቶች መካከል **የፖለቲካ አመራር** ዋናው ነው። ስለዚህ፣ በመቀጠልም የምርጥ ወይም ምስጉን የፖለቲካ አመራርነት መገለጫዎችን እናያለን።

1.3.1. የምስጉን ፖለቲካ አመራር ማሳያዎች

ዓለም ከፍተኛ ራዕይ ባላቸው የፖለቲካ መሪዎች የተሞላች ብትሆንም መልካም ወይም ምስጉን አመራር ብቃት የሚታይባቸው ግን ጥቂቶች ናቸው። ብዙ የፖለቲካ መሪዎች እንደ አቋም (integrity) እና ተጠያቂነት (accountability) ያሉ ለመልካም መሪነት ወሳኝ የሆኑ ባህሪያት በእጅጉ የሚጎድላቸው እንደሆነ በስፋት ይነገራል። "ፖለቲከኛ" ለሚለው ቃል በርካታ አሉታዊ ትርጉሞች መሰጠቱ የአጋጣሚ ነገር አይደለም። ስለ ፖለቲከኞች ያሉ አሉታዊ አመለካከቶችን ስንመለከት፣ ብዙውን ጊዜ ከሐቀኝነት የጎደላቸው፣ በሙስና የተጨማለቁ እና ከተራው ዜጋ ፍላጎትና የአኗኗር እውነታ የራቁ ናቸው በሚሉ አስተሳሰቦች ላይ ያተኩራሉ። በፖለቲከኞች ላይ በተደጋጋሚ ከሚሰነዘሩ ትችቶች መካከል ለሕዝብ አገልግሎት ቅድሚያ ከመስጠት ይልቅ ለግል ጥቅማቸው ማሰብ፣ ሥነ ምግባር የጎደለው ወይም ሕገ-ወጥ ድርጊት መፈጸም፣ እንዲሁም ሐሰተኛ ወይም አሳሳች መግለጫዎችን መስጠት ይገኙበታል። ይህ አመለካከት በሰፊው ሕዝብ ዘንድ የቱንም ያህል ሥር የሰደደ ቢሆንም፣ ሁሉንም ፖለቲከኞች ይወክላል ማለት ግን አይደለም።

ፖለቲከኛ መሆን በራሱ በቀላሉ የሚታይ ፈተና አይደለም። በተለይ ታዳጊ የዲሞክርሲ ሂደት ውስጥ እያለፉ ባሉ ሀገራት አውድ ፖለቲከኛ መሆን በበርካታ መሰናክሎች የተሞላ ነው። በተለይ ደግሞ የተቃዋሚ ፓርቲ አባል ወይም መሪ መሆን የሚያሳጣው ጉዳይ ብዙ በመሆኑ፣ አንዳንድ ፖለቲከኞች "ፖለቲከኛ" መሆንን "ሰማዕት" ለመሆን ከመዘጋጀት ጋር ያመሳስሉታል። ለዚህም ምክንያት አድርገው የሚያቀርቡት ፖለቲከኛነት የሕዝብን ዕሮሮና ጥያቄ ማስተጋባት ስለሚጠይቅ እስር፣ እንግልት፣ ሥራ ማጣት፣ ስደት፣ የቤተሰብ ሕይወት መቃወስ፣ እንዲሁም ሲከፋም መሰወርና ግድያን ሊያስከትል ይችላል የሚሉትን ጉዳዮች ነው።

የፖለቲካ መሪዎች በህዝብ ሕይወት ላይ ወሳኝ ተጽዕኖ ማሳደር የሚችሉ ቁልፍ አካላት ናቸው። በሕግ ማዕቀፎችና በመንግሥታዊ ፖሊሲዎች አማካኝነት የሥልጣንና የሃብት ክፍፍልን ይወስናሉ። በዜጎች ገቢ፣ ግብር፣ አኗኗርና ግብዓት አቅርቦት ላይ የመወሰን ሥልጣን አላቸው። ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በሀገር ደህንነትና በዜጎች ሕልውና ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ውሳኔዎችንም ያሳልፋሉ።

ከመንግሥት ውጪ ያሉ ፖለቲከኞችም የሚፈጥሯቸው ትርክቶችና የሚሰጧቸው አስተያየቶች በዜጎችና በመንግሥት መካከል ያለውን ግንኙነት በመቅረጽ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ የብዝሃ ማንነትና አመለካከት በሰፈነበት ማህበረሰብ ውስጥ፣ የፖለቲከኞች አመለካከት በዜጎች መካከል ያለውን ግንኙነት በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ መልኩ የመወሰን አቅም አለው። ከዚህ የምንረዳው የፖለቲካ መሪ መሆን ከፍተኛ ተጽኖ መፍጠሪያ መሳሪያ መታጠቅ ማለት ነው ።

- የፖለቲካ አመራር ከሆነ ሰው ከአጭር ጊዜ የግል ጥቅሞች ባሻገር ማየት የሚችልና የሀገርን የረጅም ጊዜ እድገትና መሻሻል (betterment) ላይ እንዲያተኩር ይጠይቃል። ጠንካራ የፖለቲካ አመራር **ማራኪ ስብዕናና ታማኝነትን** ከማጣመር ባሻገር፣ ሁኔታዎችን የመገምገም እና ለብዙሃኑ የሚበጀውን በመምረጥ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ የማድረግ ችሎታን እንዲኖረው ይጠበቃል።

- ከሁሉም በላይ በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ ያለ የፖለቲካ ፓርቲ አመራር "ፖለቲከኛ" ከመሆን ያለፈ **ብቃት ይጠይቃል**። ይህም የመንግሥት የሥራ ኃላፊነትን ከመልቀቅ፣ ምርጫ ከመሸነፍ ወይም የፓርቲ ሥልጣንን ከማጣት ጋር የሚያያዝ ቢሆንም እንኳ **ለፍትሕ መቆም የሚችል ሐቀኝነትና ችሎታ ሊኖረው ይገባል**። ይህ ማለት ደግሞ ፖለቲካን እንደ ሴራ፣ መዋሸት፣ መዝረፍ ወይም በግል የመበልጸጊያ መንገድ አድርጎ ከሚመለከተው የተሳሳተ አመለካከት ራስን ማላቀቅን ይጠይቃል።

ለእርስዎ የምስጉን የፖለቲካ መሪነት መገለጫዎች እንዴት ያሉ ጉዳዮች ናቸው? የፖለቲካ ሕይወትዎ ሲያበቃ በምን ሊታወሱ ይፈልጋሉ?

ምስጉን የፖለቲካ አመራር ክህሎት ያለው ሰው ውጤታማነትንና ውድቀትን በቀላሉ መለየት የሚችል ስኬታማ መሪ መሆኑን ያረጋግጣል። ስኬታማ መሪዎች የራሳቸው የሆነ አርቆ አሳቢ ራዕይ ያላቸው ሲሆኑ፣ ራዕያቸን በዘመናዊው ዓለም ወደ ስኬት እንዴት መቀየር እንደሚችል ይረዳሉ። ቀጥለን የምንዘረዝራቸው ጉዳዮች በፖለቲካ አመራር ስኬታማ ለመሆን የሚያስፈልጉ ወሳኝ መርሆችና ክህሎቶችን የሚያሳዩ ናቸው። እርስዎ ስኬታማ የፖለቲካ መሪ ለመሆን ከፈለጉ የሚከተሉትን ችሎታዎች እንዲኖረዎት ያድርጉ፦

ጥሩ የመግባባት ችሎታ	**ራዕይዎን ለቡድንዎ በግልፅ ካላስተላለፉ** እና የያዙትን ግቦች ለማሳካት የሚያስችለውን ስልት ካልነገሯቸው፣ የሚፈልጉትን ውጤት ማግኘት እጅግ ከባድ ይሆንብዎታል። በቀላል አነጋገር መልዕክትዎን ለቡድንዎ በብቃት ማስተላለፍ ካልቻሉ፣ ጥሩ መሪ መሆን አይችሉም። ቃላት ሰዎችን ሊያነሳሱ፣ ሊያነቃቁ፣ ሊያበረታቱ እና ሊታሰብ የማይችለውን ነገር እንዲሰሩ ሊያደርጉ ይችላሉ። በተቃራኒው ጥሩ የመግባባት፣ የመናገርና የመጻፍ ችሎታ የሚያንሰዎ ከሆነ እንደመሪ ያሰቡትን ለመፈጸም ችግር ሊገጥሞዎ ይችላል።
ፖለቲካዊ ቅቡልነት ማግኘት	ውጤታማ የፖለቲካ አመራር የፓርቲውን **አባላት ቅብሉነት፣ ከፍ ሲልም የዜጎች ህጋዊ እውቅና (legitimation)** ሊኖረው ይገባል። አንድ የፖለቲካ መሪ በሚመራው የፓርቲ አባላት ወይም የመንግሥት ስልጣን ያለው ከሆነ በምዕላተ ሕዝቡ ዘንድ ህጋዊ ተቀባይነት ሊኖረው ይገባል። ይህም ከአባላት ወይም ከዜጎች ጋር ግልጽና ሐቀኛ ግንኙነት መፍጠርን፣ ፍላጎቶቻቸውንና ስጋቶቻቸውን ማዳመጥን፣ እንዲሁም በዚሁ መሠረት ለውጥ ለማምጣት መተግበርን ያካትታል።
ታማኝነትና ቅንነት	**ታማኝነትና ቅንነት ጠንካራ መሪን የሚፈጥሩ ሁለት ዋና ዋና ባሕርያት** ናቸው። እነዚህን ባሕርያት ችላ ከተባሉ ከሚመሩት የፓርቲ አባላት እና ከደጋፊዎች ታማኝነትን መጠየቅ አይቻልም። መሪዎች ስኬታማ የሚሆኑት ለመሠረታዊ መርሆቻቸውና እምነቶቻቸው በመጽናት ነው። ይህ ደግሞ ያለ ሥነ ምግባር ሊሆን አይችልም። ለያዙት ዓላማ እና ለቆሙለት አቋም፣ ለሕዝብና ለሀገር ታማኝ መሆን የመሪ ትልቁ ስብዕና ማሳያ ነው።
ውሳኔ ሰጪ መሆን	አንድ መሪ **በትክክለኛው ጊዜ ትክክለኛውን ውሳኔ መስጠት መቻል** አለበት። መሪዎች በሕዝባቸው፣ በፓርቲያቸው ወይም በአባላቸው ላይ ትልቅ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ እርምጃዎችን ይወስዳሉ። ስለዚህ አንድ መሪ ውሳኔ ከመወሰኑ በፊት በጥንቃቄና በጥልቀት ማሰብ ይኖርበታል። ለውሳኔ የሚያበቁ መረጃዎችንና ማስረጃዎችን ማሰባሰብ፣ መተንተን ይጠበቅበታል።
ተግባራትን ውጤታማ በሆነ መንገድ ማከፋፈል (ውክልና መስጠት)	የፖለቲካ መሪ በሁሉም ነገር አዋቂ ሆኖ ወይም መስሎ መታየት ወይም መገኘት አይጠበቅበትም። ይልቁንም ስኬታማ መሪ በተለያዩ የሙያ ዘርፎች የተካኑና በራሳቸው የሚተማመኑ ባለሙያዎችን መለየት መቻል አለበት። ለውጤታማ አመራር በዋና ዋና ኃላፊነቶች ላይ ማተኮር ወሳኝ ሲሆን **ቀሪዎቹን ተግባራት ለሌሎች ባልደረቦች መስጠት ያስፈልጋል**። በዚህም ተከታዮቹን/ባልደረቦችን/ ሰራተኞቹን/ ማብቃትና ተግባራትን ማከፋፈል (ውክልና መስጠት) አስፈላጊ ይሆናል። ባልደረቦችን/ሰራተኞችዎን በጥቃቅን ነገሮች ሁሉ ለመቆጣጠር (micromanage) ሲሞክሩ የመተማመን እጦት ሊያድግ ይችላል። ከሁሉም በላይ ደግሞ ወሳኝ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በሚገባ ተግባብቶ መስራት ያስቸግራል። በተጨማሪም ስራዎችን ወይም ኃላፊነቶችን ሲሰጡ ስልጣን ከተጠየቂነትና ኃላፊነትን ከመውሰድ ጋር እንደሚመጣ የበታች ባልደረቦች እንዲያውቁ ማድረግ ይገባል።
ራዕይና ዓላማ ያለው መሪ ሆኖ መገኘት	ተጽዕኖ ፈጣሪ መሪዎች ዓላማና ራዕይ አላቸው። ይህም ያለውን ወቅታዊ ሁኔታ በጥልቀት መረዳትን እና በሚወሰዱ እርምጃዎች ሊመጡ የሚችሉ ውጤቶችን መገመትን ያካትታል። የወደፊቱን መሳል ብቻ ሳይሆን ሕልሞቻቸውንም ለደጋፊዎቻቸው ይገልጻሉ። ደጋፊዎቻቸው ሰፋ ያለውን ምስል ማየት ከቻሉ፣ ወዴት እያመሩ እንደሆነ መረዳት ይችላሉ። ጠንካራ መሪዎች ለምን ወደዚያ አቅጣጫ እንደሚያመሩ በግልጽ ይናገራሉ።

በአጠቃላይ የአንድ የፖለቲካ መሪ የመጀመሪያ ግቡ የራሱን ጥቅም ማሳደድ ሳይሆን ቆሜለታለሁ የሚለውን ማኅበረሰብ ወይም መንግሥቱን መወከል መሆን አለበት። ፖለቲካ ውስብስብና ብዙ ጊዜም አስቸጋሪ ሊሆን እንደሚችል ከግምት ውስጥ በማስገባት ጠንካራ መሪ ተግባራቶቹን ለሀገር በሚበጀው መንገድና **“ሀገር ከራስ በፊት”**/ “the nation before self” በሚለው መርህ መመራት አለበት። በመሆኑም **የፖለቲካ መሪ** ለሀገር ጥቅም ሲል አስፈላጊ ከሆነ ከባድ እርምጃዎችን ለመውሰድ የሚያስችል ብቃት ሊኖረው ይገባል።

ስኬታማ የፖለቲካ መሪ ደጋፊዎቹን መምራት፣ ማክበርና ማዳመጥ እንዲሁም የጋራ ተጠያቂነትንና የቡድን ሥራን ማበረታታት አለበት። ከተለያዩ በላድርሻ አካላት ለምሳሌ ከመንግሥት፣ ከምርጫ ቦርድ፣ ከፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ከፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት፣ ከሲቪል ማኅበራት፣ ከልዩ ልዩ የማኅበረሰብ አካላት እና ከፓርቲው አባላት ጋር ተቀራርቦ መሥራት ይጠበቅበታል። በመጨረሻም፣ የፖለቲካ መሪ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ የሚደረጉ አስፈላጊ ስብሰባዎች ላይ ለመገኘት በስፋት መጓጓዝ ሊኖርበት ይቻላል። ይህ የመሪነት ወሳኝ ድርሻ ነው። ምክንያቱም መሪው ከሌሎች የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች እና ከዓለም አቀፍ ታዋቂ መሪዎች ጋር ጠቃሚ ግንኙነቶችን (ኔትወርኮችን)፣ ዲፕሎማሲያዊ ትስስርን መፍጠር እና ዕውቀትን ለመገንባት ያስችለዋል። ባጭሩ የፖለቲካ መሪ ሀገራዊ እና ዓለም አቀፋዊ እይታ ሊኖረው ይገባል።

የምዕራፍ አንድ ማጠቃልያ

በዚህ ምዕራፍ፣ ስኬታማ የፖለቲካ መሪዎች ሊያሳዩዋቸው የሚገቡ ባሕሪያትና ብቃቶች ላይ ትኩረት አድርገናል። ምዕራፉን ከመዘጋታችን በፊት፣ የስኬታማ መሪነት መለኪያዎች ላይ የተመሠረቱ የፍተሻ ጥያቄዎችን እናቀርባለን። ይህ የፍተሻ ዘዴ ሁለት አካላትን ይመለከታል። በመጀመሪያ፣ እርስዎ የፖለቲካ መሪ ከሆኑ፣ የራስዎን ብቃት የሚፈትሹባቸው ጥያቄዎች ቀርበዋል። በሌላ በኩል፣ መሪ ባይሆኑም እንኳ፣ ሌሎች መሪዎችን እንዴት መገምገም እንደሚችሉ ግንዛቤ እንዲያገኙ የሚያስችሉ ጥያቄዎችም ተካተዋል። እነዚህን ጥያቄዎች በሐቀኝነት በመመለስ፣ ጉድለት ያለባቸውን ጉዳዮች ለይተው ማወቅ እና እነዚያን ክፍተቶች ለመሙላት ምን ማድረግ እንደሚችሉ ማሰብ ይችላሉ።

ሰንጠረዥ 1.2፡ የስኬታማ ፖለቲካ መሪ ብቃት ማሳያ የፍተሻ ጥያቄዎች

የብቃት ማሳያ	ራሶዎን ይፈትሹ (Self-Assessment)	የፖለቲካ መሪዎችዎን ይፈተሹ (Checking Leaders)
ታማኝነት (Integrity)	እንደ ፖለቲካ መሪ በሐቀኝነት እና በሥነ ምግባር የታነጸ ባህሪን ሁልጊዜ አሳያለሁ ብለው ያምናሉ? ወይስ ሌሎችን እያሳሳትኩ ወይም የሞራል ስሜት ሳይኖረኝ እሰራለሁ ነው የሚል የህሊና ጥያቄ ይነሳበዎታል?	የፖለቲካ መሪዎቻችንን በቃላቸው ልንተማመን እንችላለን? ሁልጊዜ ታማኝነትን፣ የሥነ ምግባር ባህሪን እና የማይለወጡ እሴቶችን ያሳያሉ? ወይስ የሐሰት ወሬዎችን፣ ማሳሳትን ወይም የሞራል ጉድለት ታይቶባቸዋል?
ብልህነት (Intelligence)	ለፖለቲካ የመሪነት ሚና የሚያስፈልገውን የብስለት እና የአስተውሎት አቅም አዳብሬያለሁ ብለውም ያስባሉ? ትክክለኛና ውጤታውጤታማ ውሳኔዎችን ሁል ጊዜ ለመውሰን የሚያስችል የአእምሮ ዝግጁነት አለኝ፣ የወሰንኩትን ውሳኔ ለማስፈጸም የሚያበቃ ብቃት አለኝ ብለው ያስባሉ? ወይስ በእነዚህ ዘርፎች ወጥነት ያለው ልምድ የለኝም ብለው ያምናሉ?	የፖለቲካ መሪዎቻችን ለእኛ ለተከታዮቻቸው አርያ የሚሆን አሰፋላጊ የሆኑ የአእምሮ ብስለት ማሳያ አቅሞችን በየጊዜው ያሳሉ? ውጤታማ ውሳኔ አሰጣጥ እና አፈጻጸም ላይ ወጥነት ያለው ታሪክ አላቸው ወይስ ይህ የጎደለባቸው ጊዜያት አሉ?
ጉልበት (Energy)	የፖለቲካ መሪነት የሚጠይቀውን ትጋት እና ከባድ ኃላፊነቶች ለመቋቋ የሚያስፈልገኝን ጉልበት እና ጥንካሬ አሉኝ ብለው ያሳብሉ?	የፖለቲካ መሪዎቻችን የተከቶችን ፈታኝ መስፈርቶች ለመቋቋም የሚያስፈልገውን ጉልበት እና ብርታት ይዘዋል? ወይስ ውጤታማነታቸውን በሚያደናቅፍ መልኩ የተፈጥሮ ተጽእኖ ውስጥ ያሉ ይመስላሉ?
አርቆ አስተዋይነት (Visionary)	ግልጽ የሆነ ራዕይ አለኝ እና እሱን ለማሳካት የሚያስችል ዕቅድ ማቅረብ እችላለሁ? ወይስ የዕቅዴ ጽንሰ-ሀሳብ ግልጽ ያልሆነ እና የመፈጸሚያ መንገድ የለውም?	የፖለቲካ መሪዎቻችን መሪ ግልጽ የሆነ ራዕይ አላቸው? እሱን ለማሳካት በሚገባ የተብራራ ዕቅድ ማቅረብ ይችላሉ? ወይስ የዕቅዳቸው ጽንሰ-ሀሳብ ግልጽ ያልሆነ እና እሱን ለማሳካት ግልጽ መንገድ ለማሳየት አይችሉም?
ተግባቦት (Communication)	ምርጥ ሀሳቦችን ለማምጣትና ሃሳቤን በግልጽ ማስረዳት፣ በንቃት የሌሎችን ንግግር ማዳመጥ እና ገንቢ ውይይት ማድረግ እችላለሁ? ወይስ በአብዛኛው ስለራሴ ብቻ የማወራ፣ ሌሎችን የማላዳምጥ ሆኜ የተግባቦት ችሎታ እንዳለኝ ለመግለጽበራስ መተማመንን ብቻ አሳያለሁ?	የፖለቲካ መሪዎቻችን ሌሎችን በንቃት ያዳምጣሉ፣ ግልጽና ምርጥ ሀሳቦችን አመጭተው ሌሎች ብትክክል ይገልፃሉ፣ ገንቢ ውይይት ያደርጋሉ? ወይስ በአብዛኛው ስለራሳቸው ብቻ የሚያወሩ ሲሆን ሁልጊዜ የተግባቦት ብቃትን መናገር መቻላቸውን ብቻ ችሎታ አድረገው ያቀርባሉ?
ቆራጥነት (Decisive)	በሁሉም ነገሮች ላይ በቂ መረጃ ባይኖረኝም እንኳ ጥንቃቄ የተሞላበት ትንተና ካረኩ በኋላ ከባድ ውሳኔዎችን ማድረግ እችላለሁ? ወይስ የመውሰን ስልጣን ስላለኝ በቂ ችሎታ ባላዳበርኩባቸው ጉዳዮች ላይ የባለሙያዎችን ምክር ሳልመለከት በድንገት ወስናለሁ?	የኛ ፖለቲካ መሪዎች የተሟላ መረጃ ሳይኖራቸው ሲቀር ከጥንቃቄ የተሞላበት ትንተና ካካሄዱ በኋላ ከባድ ውሳኔዎችን በቆራጥነት የመወሰን ችሎታ አላቸው? የተሟላ ዕውቀትና እና ልምድ ባላዳበሩባቸው ጉዳዮች ላይ የባለሙያዎችን ምክር እና አስተያየት ሳይመለከቱ በድንገት በራሳቸው ብቻ የሚወስኑ ናቸው?

የስሜት ብልህነት (Emotionally Intelligent)	ከሌሎች ጋር ገንቢ በሆነ መንገድ ለመገናኘት እና ለመግባባት እችላለሁ? አዎንታዊ ግንኙነቶችን ለመጠበቅ ቅንነትን፣ ርህራሄን አሳያለሁ፣ በሌሎች ጫማ ውስጥ ሆኜ ለማሰብ እሞክራለሁ? ወይስ ግንኙነቶችን እንደ ግብይት እቆጥራለሁ? የራሴን ፍላጎቶች ብቻ አስቀድማለሁ? የሌሎች ጉዳይ ጉዳዬ የሚሆነው እኔን እስከጠቀመ ብቻ ነው?	የፖለቲካ መሪዎቻችን ሌሎች ሰብአዊ ርህራሄን ያሳያሉ? አዎንታዊ ግንኙነቶችንና መግባባቶችን ለመጠበቅ ከሌሎች ጋር ገንቢ በሆነ መንገድ ለመገናኘት ይጥራሉ? ወይስ ግንኙነቶችን እንደ ግብይት ብቻ የሚመለከቱ እና የራሳቸውን ፍላጎት ብቻ የሚያስቀድሙ ናቸው?
ተጠያቂነት (Accountable)	ስህተቶቼን አምኜ ሙሉ ኃላፊነት እወስዳለሁ? ወይስ ለስኬቶች ብቻ ምስጋናውን ወስጄ ነገሮች ሲበላሹ በሌሎች ላይ ጣት እቀስራለሁ?	የፖለቲካ መሪዎቻችን ነገሮች ሲበላሹ ስህተታቸውን አምነው ሙሉ ኃላፊነት ይወስዳሉ? ወይስ ለጥሩ ነገሮች ብቻ ምስጋና እና እውቅና እንዲሰጣቸው የሚፈልጉ እና ነገሮች ሲበላሹ የሌሎች ኃላፊነት እንደሆነ አርገው ጣት ይቀስራሉ?
ውክልና (Delegation)	ያለብኝን ተደራራቢ ኃላፊነት ለመወጣት ሰዎችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ማሳተፍ እችላለሁ? ለሌሎች በውክልና የሰጠሁትን ተግባራት ለማከናወን ሙሉ በሙሉ ብቃት እንዳላቸው እና ሥልጣን እንዳላቸው ማረጋገጥ እችላለሁ? ወይስ የሰጋቸው ስራዎች እንዲሰሩ የትዕዛዝ እና ቁጥጥር ዘይቤ እጠቀማለሁ?	የኛ የፖለቲካ መሪዎች በፖለቲካ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት ሰዎችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ያሳተፉሉ? ኃላፊነት የሰጧቸው ሰዎች የተሰጡ ተግባራትን ለማከናወን ሙሉ በሙሉ ብቃት እንዳላቸው እና ሥልጣን እንዳላቸው ያረጋግጣሉ? ወይስ የትዕዛዝ እና ቁጥጥር ዘይቤ ይጠቀማሉ?
አበረታችነት (Inspirational)	ሌሎች በንቃት እንዲሳተፉ በሚያነሳሳ መንገድ አበረታታለሁ? ወይስ ፍርሃትን በመትከል ሌሎችን ተስፋ አስቆርጣለሁ ወይም በራሳቸው እንዳይተማመኑ ዝቅ አርጌ እመለከታቸዋለሁ?	የፖለቲካ መሪዎቻችን ሌሎችን ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ በሚያበረታታ መንገድ ያነሳሳሉ? ወይስ ሌሎችን በማዋረድ እና በመስደብ ፍርሃትን ይተክላሉ? በራስ መተማመን እንዳይኖር ያደርጋሉ?
ራስን ማወቅ (Self-Awareness)	የባህሪዬን ገጽታዎች፣ ጭንቀቶችን እና ስሜቶችን በእውነት ተረድቻለሁ? ሌሎች እንዴት እንደሚያዩኝ እና በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ራሴን እንዴት እንደማቀርብ አውቃለሁ?	የኛ ፖለቲካ መሪዎች የራሳቸውን ጥንካሬ እና ድክመቶች ላይ ግንዛቤ አላቸው? የእነሱ ድርጊት እና ባህሪ በሌሎች እንዴት እንደሚታይ የሚያውቁ ይመስላሉ?
አክብሮት (Respect)	የልዩነት ሀሳብ ብኖረኝም የሌሎችን አመለካከቶች አከብራለሁ? የጋራ ስምምነትን ለመገንባት እና የተለያዩ አመለካከቶችን ለማክበር ጥረት አደርጋለሁ?	የፖለቲካ መሪዎቻችን የሌሎችን አመለካከት ያከብራሉ? ሰዎች የየራሳቸው ዋጋ፣ ሀሳብ እና ፍላጎት እንዳላቸው አምነው በፓርቲው እንቅስቃሴ ውስጥ ያካትታሉ?
ርህራሄ (Compassion)	ሌሎች ስጋቶቻቸውን ሲያጋሩ ወይም ሲናገሩ፣ ርህራሄ በማሳየት በማሳየት በዚያ መረጃ ላይ ትርጉም ያለው እርምጃ እወስዳለሁ?	አባላት ስጋቶች በሚነሱበት ጊዜ የኛ የፖለቲካ መሪዎች በተቀበሉት መረጃ ላይ ትርጉም ያለው እርምጃ ይወስዳሉ? ጉዳዮችን ለመፍታት ካዩትና ከሰሙት ነገር በመነሳት ርህራሄን ያሳያሉ?
ምስጋና (Gratitude)	አብሬያቸው ለምሰራቸው ሰዎች ላበረከቱት አስተዋጽዖ እና ጥረት ያለማቋረጥ ከልብ አመሰግናለሁ? ለስኬታቸው እውቅና ሰጣለሁ?	የኛ የፖለቲካ መሪዎች ለፓርቲ አባላት እና ባልደረቦች ላደረጉት አስተዋጽዖ በተደጋጋሚ ከልብ አመስጋኞች ናቸው? አድናቆት በግልጽ የሚታይበት አካባቢ ይፈጥራሉ?

ምዕራፍ ሁለት

የፖለቲካ ፓርቲዎች የፖሊሲ ቀረፃ ሂደት

ይህ ምዕራፍ የሚያተኩረው በፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ነው። እያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ የሚመሰረተው በምርጫ ተወዳድሮ የመንግሥትን ሥልጣን በመያዝ የፓርቲውን ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ግቦች እና ዓላማዎች ለማስፈጸም ነው። አንድ ፓርቲ የሚያራምደውን ርዕዮተ ዓለምና ተልዕኮን ወደ ተግባር ለመለወጥ ቁልፍ መሣሪያ ያስፈልገዋል። ይህ መሣሪያ ደግሞ ፖሊሲ ነው። በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫ ለመወዳደርና ለማሸነፍ ለመራጩ ሕዝብ ሊያቀርቡት የሚገባ የመወዳደሪያ ሐሳብ ሊኖራቸው ይገባል። ይህ ሐሳባቸው የሚገለጸው በሚያቀርቧቸው አማራጭ ፖሊሲዎች ነው። በመሆኑም፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዴት የተሳካ ፖሊሲ ቀርጸው ተወዳዳሪ መሆን እንደሚችሉ ጠንቅቀው ማወቅ አስፈላጊ ነው።

2.1. ፖሊሲ ምንድን ነው?

የፖለቲካ ፓርቲዎች በሕዝብ ጉዳዮች ላይ ግልጽ የሆነ አቋም በመያዝ ለህብረተሰቡ ማሳወቅ አለባቸው። በዚህ መንገድ መራጮች ፓርቲዎቹ በምን ጉዳዮች ላይ ምን ዓይነት አቋም እንዳላቸውና ምን ዓላማ እንዳላቸው በመረዳት ምርጫቸውን ማስተካከል ይችላሉ።

በብዙ ታዳጊ ዲሞክራሲያዊ ሃገራት ውስጥ ያሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ግን ይህንን አያደርጉም። በፖሊሲ ላይ የተመሠረተ የረጅም ጊዜ ማንነት ከመፍጠር ይልቅ በፓርቲ መሪዎች ስብእና ወይም በብሔራዊ/በብሔረሰባዊ ማንነት ላይ ያተኩራሉ። በርካታ ፓርቲዎች የፖሊሲ አቋሞችን ለመወያየትና መራጮችን በሃሳብ ዙሪያ ለማሰባሰብ የሚያስችል ክህሎትና ልምድ ይጎድላቸዋል። በምርጫ ክርክሮች ወቅትም በግልጽ እንደሚታየው ፓርቲዎች በተለያዩ ሕዝባዊ ጉዳዮች ላይ ያላቸውን አማራጭና ጠንካራ የፖሊሲ ሐሳብ ከማቅረብ ይልቅ የሌሎች ፓርቲዎችን ስህተቶችና ጉድለቶች በማጋለጥ ላይ ሰፊ ጊዜ ያጠፋሉ። ይህ ደግሞ ፓርቲዎችን አማራጭ የሌላቸው ከሳሾች ብቻ እንዲመስሉ ያደርጋቸዋል።

ፖሊሲ ማለት በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ ያሉ አንገብጋቢ ችግሮችን ለመፍታት የሚረዱ ተነሳሽነቶች፣ ውሳኔዎች እና ተግባራት ናቸው። ፖሊሲዎች የሕዝብን ጥቅም ማስጠበቅ፣ የማኅበራዊ ችግሮችን መፍታት፣ ሀብት ማከፋፈል፣ እና የሰዎችን ባሕሪ መቆጣጠር የመሳሰሉ ሰፋፊ ዓላማዎችን ይሸፍናሉ። የሁሉም ፖሊሲዎች የጋራ ግባቸው መሆን የሚገባው የሰውን ልጅ ደህንነት ማስጠበቅ እና እድገትን ማረጋገጥ ነው።

በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ በምርጫ ተወዳድሮ ማሸነፍ እና የመንግሥት ሥርዓት ለማቋቋም የሚፈልግ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ፖሊሲ እንዲኖረው ይጠበቃል። የፖለቲካ ፓርቲዎች ፖሊሲ የሚቀርጹትና መንግሥት ለመሆን የሚያበቃ ስልጣን ሲኖራቸው ወደ ትግበራ የሚሸጋገሩት የሕዝባቸውን ማኅበራዊ፣ አኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች በመፍታት የተሻለ እድገት እና መሻሻል ለማስመዝገብ በመሆኑ ስለፖለቲካ ፓርቲዎች ፖሊሲ ሲነሳ የሚያተኩረው ፐብሊክ ፖሊሲን በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ነው።

ገዥ ፓርቲ ለመሆን ለሚፈልግ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የፐብሊክ ፖሊሲ ጽንሰ-ሐሳብ ብቻ ሳይሆን እንዲኖረው የሚጠበቀው መንግሥት ሲመሰርት የማኅበረሰብን ማኅባራዊ፣ አኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች ለምፍታት የሚተገብራቸውን ጉዳዮች በተጨባጭ የሚያረጋግጡ ትክክለኛ ዕቅድ ማሳያ (blueprint) ሊኖረው ይገባል። ይህ የዕቅድ ማሳያ መሳርያ ፐብሊክ ፖሊሲ ይምንለው ነው።

ሳጥን 2.1: ከፖሊሲ ጋር ተያያዙ ቁልፍ ቃላት

- **ፐብሊክ ፖሊሲ (Public Policy)** :- የማኅበረሰብን ማህበራዊ፣ አኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ችግሮችን ለመፍታት የሚወሰዱ እርምጃዎችና ውሳኔዎችን ያካትታል፤
- **ማህበራዊ ፖሊሲ (Social Policy)** :- የማህበራዊ ደህንነትን ለማሻሻል የሚያተኩሩ የፖሊሲ አይነቶች፤
- **ሀገር ውስጥ ፖሊሲ (Domestic Policy)** :- በአንድ የተወሰነ ሀገር ወሰን ውስጥ ያሉ ብሄራዊ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች፤
- **መደበኛ ፖሊሲ (Formal Policy)** :- በይፋ የጸደቁ እና በሕግ አስገዳጅነት ያላቸው ፖሊሲዎች፤
- **መደበኛ ያልሆነ ፖሊሲ (Informal Policy)** :- የሰዎችን ድርጊቶች የሚነኩ ያልተፃፉ ደንቦች እና ልምዶች፤
- ***ፖሊሲ አውጪዎች* (Policy Makers)** :- በመንግስት፣ በፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም በተቋማት ውስጥ ፖሊሲዎችን የሚቀርጹ እና የሚያወጡ ግለሰቦች ወይም ባለስልጣናት።

ፐብሊክ ፖሊሲ ማህበራዊ፣ አኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችሉ **ስትራቴጂዎችን እና እቅዶችን በመቅረጽ** ዙሪያ ያጠነጥናል። በመሆኑም ፐብሊክ ፖሊሲ ማለት የፖለቲካ ፓርቲዎች የመንግሥት ሥርዓት ለመመሥረት ሲችሉ እንደ መንግሥት የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ግቦችን ለማሳካት የሚያወጧቸው **ሕጎች፣ መመሪያዎች፣ ደንቦችና እርምጃዎች ማዕቀፍ** ነው። በሌላ አነጋገር አንድ ፓርቲ መንግስት ሲሆን የተለየን አንድ ጉዳይ ወይም ችግርን ለመፍታት ያለውን ዓላማና ቁርጠኝነት የሚያሳይ ተጨባጭ የዕቅድ መግለጫ ነው።

አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ፐብሊክ ፖሊሲውን ሲያዘጋጅ፣ በመሠረቱ የመንግሥት ባለሥልጣናት እና ኤጀንሲዎች ውሳኔዎችን እንዴት እንደሚቀርጽ እና በማኅበራዊ፣ በኢኮኖሚ እና በፖለቲካዊ ገጽታዎች ላይ ጥልቅ ተጽዕኖዎች እንዴት እንደሚያሳድር በሰፊው ይዘረዝራል። በዚህም የተነሳ የፖሊሲ ዝግጅት ከመንግስት ኤጀንሲዎች፣ ፖሊሲ አውጪዎች እና ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ትብብርን የሚጠይቅ፣ መረጃ ማሰባሰብን፣ መተንተንን ማካትት ያለበት ሂደት ነው።

እነዚህ ፖሊሲዎች ከኢኮኖሚያዊ ስትራቴጂዎች እና ማህበራዊ ደህንነት ፕሮግራሞች አንስቶ ትምህርት፣ ጤና አጠባበቅ፣ የአካባቢ ጥበቃ እቅዶች፣ የመሠረተ ልማት ግንባታ፣ የኢንዱስትሪ ማስፋፋት፣ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር፣ የውጪ ጉዳይ ግንኙነት፣ የደህንነትና ጸጥታ፣ የፆታ እኩልነት፣ የሴቶችና የወጣቶች አካታችነት ሥርዓትን ጨምሮ በበርካታ ሕዝባዊ የሆኑ ሰፊ ወሳኝ ዘርፎችን ሊሸፍኑ ይችላሉ። አንድ ፓርቲ የሚደግፋቸው ፖሊሲዎች በጥልቅ የሚወሰኑት **በፖለቲካዊ ርዕዮተ ዓለሞቹ፣ በነባሩ የህብረተሰብ እሴቶች እና አሁን ባለው የኢኮኖሚ፣ የየማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና የአለም አቀፋዊ ሁኔታዎች** ነው።

- በፓርቲያችሁ የሚዘጋጁ ፖሊሲዎች ሲቀረጹ ምን ምን ጉዳዮችን ታሳቢ ያደርጋሉ?

2.1.1. የፐብሊክ ፖሊሲ መገለጫዎች

ፐብሊክ ፖሊሲ ምንነት እና ባህሪያት መረዳት የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚያዘጋጇቸው ፖሊሲዎች በኅብረተሰብ ላይ ያላቸውን ጠቀሜታ እና ተጽዕኖ ለመገንዘብ ያስችላሉ[1]።

ዓላማ ያለው ነው	ፐብሊክ ፖሊሲ በፖለቲካ ፓርቲዎች ሲቀረጽ የተለዩ ችግሮችን ለመፍታት ወይም የተወሰኑ ማኅበራዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት ታስቦ የተዘጋጀ (purposeful) ነው። ፓርቲዎች ፖሊሲዎችን ሲቀርጹ ፖሊሲ አላቸው ለማስባል ብቻ ታስቦ የዘፈቀደ ወይም የተመሰቃቀለ የሀሳብ ድርድራ ሳይሆን፣ የተለዩ ጉዳዮችን ለመፍታት ስልቶች እንዲታዩ የሚደረግበት ጥረት ነው። ፖሊሲዎች ኢኮኖሚ ሁኔታን ለማሻሻል፣ የሕዝብ ጤና አጠባበቅን ለማሳደግ፣ ወንጀልን ለመቀነስ፣ የሕዝብን ደህንነት ለማስጠበቅ፣ ከጎረቤት እና ከዓለም ሀጋራት ጋር በሰላም ለመኖር ወይም የአየር ንብረት ለውጥን ተፅዕኖ ለመቀነስ ላይ ሊያተኩሩ ይችላሉ። ዋናው ጉዳይ የተለየና የተቆጠረ ዓላማ ያለው የፖሊሲ ማዕቀፍ መሆኑ ነው።
ሥርዓታዊ ነው	ፐብሊክ ፖሊሲ አንድን ችግር ለመፍታት የሚደረግ የአንድ ጊዜ ውሳኔ ሳይሆን፣ በተለየ ጉዳይ ላይ የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት በጋራ የሚሰሩ የተቀናጁ ተግባራት (systematic) ስብስብ ነው። ፖሊሲዎች በተለምዶ በተለያዩ ባለድርሻ አካላት እና ውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች አማካኝነት በስልታዊ መንገድ ተዘጋጅተው የሚተገበሩ ናቸው። በመሆኑም የፖሊሲዎች ቅንጅትና መናበብ ወሳኝ ሂደት ነው። አንደኛው ፖሊሲ ከሌኛው የፖሊሲ ማዕቀፍ ጋር በሚገባ መናበብ መቻል አለበት።
ስልታዊ ነው	ፐብሊክ ፖሊሲ የአጭር ጊዜ ፍላጎቶችን ብቻ ሳይሆን የረጅም ጊዜ ግቦችን ለማሳካት ያለመ (strategic) ነው። የፖሊሲ አውጪዎች የውሳኔዎቻቸው ሊሆኑ የሚችሉ ውጤቶችን በጥልቀት በመመልከት ዘላቂ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ፖሊሲዎችን ለመፍጠር ይሞክራሉ። ይህ ማለት ፖሊሲዎች ለመተግበር ጊዜ ሊወስዱ የሚችሉ መሆናቸውን መረዳት እና ከፍተኛ የሀብት ኢንቨስትመንት ሊጠይቁ የሚችሉ እንደሆነ መረዳትን ይጠይቃል።

2.1.2. የፐብሊክ ፖሊሲዎች ለፖለቲካ ፓርቲዎች ያላቸው ፋይዳ

በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ ፓርቲዎች ለሕዝብ የሚያቀርቡት ተጨባጭ የፖሊሲ አማራጭ ሊኖራቸው ይገባል። **የፖሊሲ ዝግጅት የአካዳሚያዊ ልምምድ አይደለም**። ፖሊሲዎች የማይጨበጡና ተደራሽ ባልሆኑ ዕሳቤዎች የተሞሉ መሆን የለባቸውም። ይልቁንም በተጨባጭ ወደ መሬት ወረደው የሚተገበሩና የማኅበረሰብን ችግሮች ፈተው ወደተሻለ የእደገት ደረጃ የሚያሸጋግሩ መሆን አለባቸው። በመሆኑም ፓርቲዎች የሚያዘጋጇቸው ፐብሊክ ፖሊሲዎች ፓርቲው ውስብስብ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን እንዴት እንደሚፈታ የሚያሳይ እና በምርጫ ተወዳድሮ ከተመረጠና የመንግሥት ሥርዓትን ማቋቋም ከቻለ እነዚህን ፖሊሲዎች ወደትግበራ አስገብቶ ትልቅ ለውጥ እንዲያመጣ የሚያስችለው ወሳኝ መሳሪያዎች ናቸው።

የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚከተሏቸው ዋና ዋና የፖሊሲ ጉዳዮች የፓርቲውን ማንነት የሚያሳዩ እና በምን ጉዳዮች ላይ እንደሚያተኩር የሚያመላክቱ **ምሰሶዎች (building blocks)** ናቸው። የፓርቲው የፖሊሲ ትንተና፣ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን የሚይዝበት፣ የአስተዳደር ዘቤው፣ የምርምር ዘዴዎች፣ ማህበራዊ ፍትህ እና የህዝብ አስተዳደር ያሉ ዘርፎች ከንድፈ ሐሳብና አካዳሚያዊ ክርክር ባሻገር ፓርቲው ራዕዩን ለመቅረጽ የሚጠቀምባቸው ተግባራዊ መሳሪያዎች ናቸው። በእነዚህ ጉዳዮች ላይ የተሟላ እውቀት መኖር አንድን ፓርቲ ወቅታዊ የፖሊሲ ጉዳዮችን በአጠቃላይ እንዲገነዘብ ያስችለዋል።

ፐብሊክ ፖሊሲዎች ማህበረሰብን ለመቅረጽ እና በግለሰቦች ሕይወት ላይ ጥልቅ ተጽዕኖ ለማሳደር የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚጠቀሙበት ዋናው ዘዴ ነው። የአንድ ፓርቲ ፖሊሲዎች ከጤና አጠባበቅና ትምህርት እስከ አካባቢና ማህበራዊ ደህንነት ድረስ ያለውን እያንዳንዱን የአስተዳደር ገጽታ ይነካሉ። ውጤታማ የፐብሊክ ፖሊሲን በመደገፍ፣ አንድ ፓርቲ የሃብት ፍትሃዊ ክፍፍልን ለማረጋገጥ፣ ማህበራዊ ፍትህን ለማስፋፋት እና ማህበራዊ ችግሮችን ለመፍታት ያለውን ቁርጠኝነት ያሳያል።

አንድ ፓርቲ የፐብሊክ ፖሊሲውን በጥንቃቄ ሲያዘጋጅ በሰዎች ሕይወት ላይ በጎ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ተነሳሽነቶችን፣ ፕሮግራሞችን፣ ፕሮጀክቶችን በማዘጋጀትና በመተግበር የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማድረግ ያስችለዋል። ፓርቲው የፖሊሲ ችግሮችን የመለየት እና የመተንተን ችሎታ ሲኖረው፣ ውጤታማና ፈጠራን ማዕከል ያደረጉ መፍትሄዎችን ማቅረብ ያስችለዋል። ለለውጥ መሟገት እና ዘላቂ ልማትን ማረጋገጥ ይችላል።

- እርስዎ አባል የሆኑበት የፖለቲካ ፓርቲ አማራጭ ፖሊሲዎችን ለመቅረጽ ወይም ያሉትን ፖሊሲዎች ለማሻሻል ምን ያህል ጥረት ያደርጋል?
- እንደ ፓርቲ አባል፣ የፓርቲውን ፖሊሲዎች ምን ያህል በቅርበት ያውቃሉ?
- የእርስዎን ፓርቲ የፖሊሲ ማዕቀፎች የማኅበረሰቡን ተጨባጭ ችግሮችና ስጋቶች ከመፍታት እንዲሁም ፍላጎቶችን ከማሟላት አንፃር በምን ያህል ደረጃ ይተማመኑባቸዋል?

2.1.3. የፐብሊክ ፖሊሲ ምሳሌዎች

በዚህ መጽሐፍ የምናቀርባቸው የፖሊሲ ምሳሌዎች በዋና ዋና የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ቢሆንም የማንኛውንም ፓርቲ ፖሊሲ የሚወክሉ አይደሉም[2]።

ምሳሌ 1፡ መሰረታዊ ፖሊሲዎች

መሰረታዊ ፖሊሲዎች የማህበራዊ ችግሮችን የተወሰኑ ጉዳዮችን ለመፍታት የተነደፉ የፐብሊክ ፖሊሲ ናቸው። እነዚህ ፖሊሲዎች አንገብጋቢ ችግሮችን ለመፍታት ቀጥተኛ ትኩረት በማድረጋቸው ይታወቃሉ። ከዚህ በታች የመሰረታዊ ፖሊሲዎች አንዳንድ ምሳሌዎች እና የተለያዩ ማህበራዊ ችግሮችን በመፍታት ረገድ ያላቸው ሚና ቀርበዋል።

ሰንጠረዥ 2.1. የመሰረታዊ ፖሊሲዎች ምሳሌ

የፖሊሲ አይነት	የፖሊሲ ትንተና	የፖሊሲ አቅጣጫዎች
የሥርዓተ ትምህርት ማሻሻያ ፖልሲ	የትምህርት ፖሊሲ ማሻሻያ በኢትዮጲያ ያለውን የትምህርት ሥርዓት ከፍተኛ ጥራት ያለው እና ለሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ተደራሽ መሆኑን ያረጋግጣል። የትምህርት ፖሊሲ የመምህራንንና የተማሪዎችን የትምህር አፈፃፀም ለማሻሻል፣ የትምህርት ጥራትን ለማሳደግ፣ እና በኢትዮጲያ ያለውን የእውቀት ክፍተት ለማጥበብ ያለመ ነው። በአካዳሚያዊ መስክ የሚወሰዱ ማሻሻያዎች ምሳሌዎች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ:	**ሥርዓተ ትምህርት ማሻሻያ (Curriculum Enhancement)**: ከጊዜ ወደ ጊዜ ከሚለዋወጡ የትምህርት ፍላጎቶች እና የሥራ ገበያ ፍላጎቶች ጋር የሚጣጣም የመማሪያ ሥርዓተ ትምህርትን ማሻሻል እና ማዘመን።
		የመምህራን ስልጠና ፕሮግራሞች (Teacher Training Programs): መምህራን ክህሎቶቻቸውን እና ብቃቶቻቸውን እንዲያሻሽሉ የሚያግዙ ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት።
		ጥራት ያለው ትምህርት የማግኘት ዕድል ማስፋት (Access to Quality Education): ሁሉም ተማሪዎች ከፍተኛ ጥራት ያለው ትምህርት፣ በመንግስታዊ፣ በግል ወይም በማኅበረሰብ የትምህርት ተቋማት ውስጥ የማግኘት ዕድል እንዳላቸው ለማረጋገጥ እርምጃዎችን መውሰድ።

የወንጀል መከላከል እና የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፖሊሲ	የወንጀል የመከላከልና የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ የፐብሊክ ፖሊሲ የሚያተኩረው የወንጀል መከሰት እድልን መቆጣጠር፣ ፍትህ ስርዓትን ፍትሃዊነት፣ ውጤታማነት እና እኩልነት በማሻሻል ላይ ነው። እነዚህ ፖሊሲዎች ወንጀልን ለመቀነስ፣ የህዝብን ደህንነት ለማሳደግ እና ለሁሉም ዜጎች ፍትህን ለማረጋገጥ የታለሙ ናቸው። ዋና ዋናዎቹ ነጥቦች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፦	**የወንጀል ቅጣት ማሻሻያ (Criminal Sentencing Reform):** አስገዳጅ ዝቅተኛ ቅጣት እና ከፈተኛውን እስራት ቅጣት የቅጣት ጣሪያ ለመወሰን የወንጀለኛ መቅጫ ሕጎችን፣ መመሪያዎችን እና የአፈጻጸም ደንቦችን እንደገና መገምገም እና ማሻሻል።
		ወንጀልን ምጣኔን መቀነስ (Crime Reduction): የወንጀል መጠኖችን ለመቀነስ በከተማ ደረጃ ወንጀልን አስቀድሞ በመከላከል ላይ ያተኮሩ ውጤታማ እርምጃዎችን ለመውሰድ የሚያስችሉ የማሻሻያ ስራዎችን መሥራት፣ ማኅበረሰብን በስፋት ያሳተፉ የወንጀል መከላከል አድረጃጀቶችን እስና ሥርዓቶችን ዘግቶ ወደ ሥራ ማስገባት።
		የታራሚዎች ተሀድሶ (Prisoner Rehabilitation): ታራሚዎች የቅጣት ጊዚያቸውን ሲጨርሱ ወደ ማህበረሰቡ ተቀላቅለው ሰላማዊና አምራች ዜጎች እንዲሆኑ በሚያስችሉ የተሀድሶ ፕሮግራሞችን በማረሚያ ቤቶች በጥራት ተግባራዊ ማድረግ።
የቴክኖሎጂ እና ፈጠራ ፖሊሲዎች ፖሊሲ	የቴክኖሎጂ እና ፈጠራ ፖሊሲዎች የቴክኖሎጂ እድገትን፣ ፈጠራን እና ተወዳዳሪነት መስፋትን ያበረታታሉ። እነዚህ ፖሊሲዎች ምርምርን እና ልማትን ለማስተዋወቅ፣ ለማስፋፋት፣ የቴክኖሎጂ ኢንዱስትሪን ለማጠናከር እና የኢኮኖሚ እድገትን ለማፋጠን ያለመ ነው። የፖሊሲ አቅጣጫዎችቹ የሚከተሉትን ጉዳዮች ሊያካትቱ ይችላሉ፦	**የምርምር ሥራዎችን ለማገዝ የገንዘብ ድጋፍ መጠንን ማሳደግ (Research Funding):** እንደ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ባሉ ዘርፎች ፈጠራን ለማስፋፋት የምርምር ሂደቶችን ለመደገር ለተመራማሪዎች የገንዘብ እርዳታዎችን እና ማበረታቻዎችን መስጠት።
		ጅማሬ የሥራ ፈጠራ እንቅስቃሴዎችን መደገፍ (Startup Support): የኢኮኖሚ ልማትን ለማነቃቃት ለጅማሬ የሥራ ፈጠራ እና የቢዝነስ እንቅስቃሴዎች የታክስ እፎይታን ጨምሮ የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ፣ የባንክ ብድር እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ማበረታታት እና የሕግ ከለላ እንዲያገኙ ድጋፍ ማድረግ።

ምሳሌ 2፡ የቁጥጥር ፖሊሲዎች

የቁጥጥር ፖሊሲዎች የሚባሉት የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ እና የተወሰኑ ኢንዱስትሪዎች በሥነ ምግባርና በደኅንነት እንዲመሩ እና እንዲሠሩ ለማረጋገጥ የሚረዱ ናቸው። እነዚህ ፖሊሲዎች ብዙ የሥራ ዘርፎችን የሚሸፍኑ ናቸው። የቁጥጥር ፖሊሲዎች ከምንላቸው መካከል ለምሳሌ ያህል ከዚህ በታች ቀርበዋል፦

ሰንጠረዥ 2.2. የቁጥጥር ፖሊሲዎች ምሳሌ

የፖሊሲ አይነት	የፖሊሲ ትንተና	የፖሊሲ አቅጣጫዎች
የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲ	የአካባቢ ጥበቃ ደንቦች የቁጥጥር ፖሊሲዎች አካባቢን ከጥፋት ለመጠበቅ፣ ብክለትን ለመቀነስ፣ የተራቆቱ አከባቢዎች መልሰው እንዲያገግሙ እና ዓለም አቀፍ የተፈጥሮ ችግሮችን ለመፍታት ያለሙ ናቸው። የአካባቢ ጥበቃ ደንቦች ዋና ዋና ክፍሎች የሚከተሉትን ጉዳዮች ሊያካትቱ ይችላሉ፦	**የበካይ ጋዝ የልቀት ደረጃዎች (Emission Standards):** ከኢንዱስትሪ ተቋማት፣ ከተሽከርካሪዎች እና ከኃይል ማመንጫዎች የሚወጡ የብክለት ልቀቶችን መገደብ።
		ሥነ-ምህዳር ጥበቃ (Ecosystem Protection): እንደ ረግረጋማ ቦታዎችና ደኖች ያሉ ወሳኝ ሥነ-ምህዳሮችን ለመጠበቅና የተራቆቱ አከባቢዎች አገግመው ወደ ነበሩበት ለመመለስ የሚያስችሉ እርምጃዎችን መውሰድ።
		ዘላቂ ልምዶችን ማዳበር (Sustainable Practices): የረጅም ጊዜ የአካባቢ ሚዛንንና ጤናን ለማረጋገጥ ዘላቂነት ያለው ግብርናን፣ ደን ልማትንና አሳ ሀብት አጠቃቀም ሥርዓት ማስተዋወቅ።

የምግብ ደኅንነት ማረጋገጫ ፖሊሲ	የምግብ ደኅንነት ፖሊሲዎች የምግብ ምርቶችን ጥራት እና ደኅንነት በመቆጣጠር የሕብረተሰብ ጤናን ለመጠበቅ ወሳኝ ናቸው። እነዚህ ፖሊሲዎች በምግብ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎችን ለመከላከል እና የምግብ አቅርቦት ሰንሰለትን ደኅንነት ለማረጋገጥ ትኩረት ያደርጋሉ። ዋና ዋና ጉዳዮች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፦	**ምርመራዎችና ኦዲቶች (Inspections and Audits):** የምግብ ተቋማትን አሰራርና የምርት ሂደት መፈተሽ እና የንጽሕናና ደኅንነት መስፈርቶችን አውጥቶ ማስፈጸም።
		የምልክት ማድረጊያ መስፈርቶች (Labeling Requirements): በምግብ ምርቶች ላይ የግብዓት፣ የመጠቀሚያ ጊዚ ማብቂያቸውን፣ የአለርጂና የተመጣጠነ ምግብ መረጃዎችን በትክክል በማሸጋዎች ላይ ማስቀመጥን ግዴታ ማድረግ።
		የብክለት ገደቦች (Contaminant Limits): እንደ ፀረ-ተባይ መድኃኒቶችና ተጨማሪ ንጥረ ነገሮች ያሉ ብክለቶችን በምግብ ምርቶች ውስጥ መገደብ።
የአሠሪና ሠራተኛ ፖሊሲ	የአሠሪና የሠራተኛ ሕጎች፣ መመሪያዎችና ደንቦች የቅጥር መስፈርቶችን በማውጣት፣ ፍትሐዊ የሥራ ልምዶችን በማረጋገጥ እና የጉልበት ብዝበዛን በመከላከል የሠራተኞችን መብትና ደኅንነት ለመጠበቅ ታስበው የሚዘጋጁ ናቸው። እነዚህ ፖሊሲዎች የሚከተሉትን ጉዳዮች ያካትታሉ፦	**ዝቅተኛ የደመወዝ ሕጎች (Minimum Wage Laws)፦** ሠራተኞች ፍትሐዊ ካሣ እንዲያገኙ ዝቅተኛ ደመወዝ መወሰን ማስቀመጥ ያስፈልጋል።
		የሥራ ቦታ ደኅንነት መስፈርቶች (Workplace Safety Standards)፦ በሥራ ቦታ የሚደርሱ አደጋዎችን እና ጉዳቶችን ለመከላከል የደኅንነት ደንቦችን መተግበር።
		የጸረ የመድልዎ ሕጎች (Anti-Discrimination Laws)፦ በዘር፣ በብሔር፣ በቋንቋ፣ በፆታ ወይም በአካል ጉዳት ላይ የተመሠረተ መድልዎንና መገለልልን የሚከለክሉ ሕጎችን ማስፈጸም።

ምሳሌ 3፡ የሀብት ክፍፍል ፖሊሲዎች

የሀብት ክፍፍል ፖሊሲዎች ሀብቶችና ጥቅሞች በማኅበረሰቡ ውስጥ ላሉ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች በፍትሐዊነት እንዲከፋፈሉ ለማረጋገጥ የሚቀረጹና የሚተገበሩ ፖሊሲዎች ናቸው። እነዚህ ፖሊሲዎች በማኅበረሰብ መካከል ያለውን የሀበት ልዩነቶች ለመቀነስ እና ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ መረጋጋትን በመፍጠር የማኅበረሰብን ደህንነትን ለማሳደግ ያለሙ ናቸው። ቀጥለን የምናያቸው የሀብት ክፍፍል ፖሊሲዎች ምሳሌዎች ናቸው፦

ሰንጠረዥ 2.3. የሀብት ክፍፍል ፖሊሲዎች ምሳሌ

የፖሊሲ አይነት	የፖሊሲ ትንተና	የፖሊሲ አቅጣጫዎች
የመኖሪያ ቤት ፖሊሲ	የመኖሪያ ቤት ልማት ፖሊሲ ለኅብረተሰቡ አባላት ተመጣጣኝና በቂ የመኖሪያ ቤት ለማቅረብ ያለመ የማኅበራዊ ፖሊሲ አካል ሲሆን ዜጎችን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ አስፈላጊ የሆነ የልማት አካል ነው። እነዚህ ፖሊሲዎች የተለያዩ ተግባራትን የሚያጠቃልሉ ሲሆን ከእነዚህም መካከል፦	**ተመጣጣኝ የመኖሪያ ቤት ፕሮግራሞች (Affordable Housing Programs)፦** ዝቅተኛና መካከለኛ ገቢ ላላቸው ግለሰቦች እና ቤተሰቦች የመኖሪያ ቤት አቅርቦት ወጪን በመደጎም አስተማማኝና ዘላቂ ቤት የማግኘት ዕድላቸውን ማሻሻል።
		አከባቢዎችን መልሶ ማልማት (Zoning Reform): የተጎዱ የመኖርያ አከባቢዎችን መልሶ በመገንባት የመኖሪያ ቤቶችን ዓይነቶች የበለጠ ማሻሻል እና መሠረተ ልማቶች በተልይም የኤሌትሪክ ሃይል፣ ንጹህ ውሃ፣ ስልክ፣ መንገድ፣ የንጽህና አገልግሎት መስጫውችን ማዘመንና ተደራሽ ማድረግ።

የማኅበራዊ ዋስትና መርሐ ግብሮች ፖሊሲ	ይህ ማኅበራዊ ፖሊሲ ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ለገጠማቸው ግለሰቦች እና ቤተሰቦች የገንዘብ ድጋፍ ለመስጠት ያለመና ማኅበራዊ ዋስትናን ለማረጋገጥ ያለመ ፖሊሲ ነው። ዋና ዋና የፖሊሲ ክፍሎቹ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፦	**የሥራ አጥነት ጥቅማጥቅሞች (Unemployment Benefits)፦** ሥራቸውን ለጊዜው ላጡ ሠራተኞች ጊዚያዊ የገንዘብ ድጋፍ በመስጠት ወደሚቀጥለው የሥራ እድል የሚያደርጉት ሽግግ ር በፈተና የተሞላ እናይሆን ዋስትና መስጠት።
		አካል ጉዳት ጥቅማጥቅሞች (Disability Benefits)፦ የአካል ጉዳት ያለባቸው ግለሰቦች መሠረታዊ ፍላጎቶቻቸውን እንዲያሟሉ የሚያስችሉ ፓኬጆች በማዘጋጀት ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ድጋፍ እንዲያገኙ ማስቻል።
		የጡረታ አበል (Retirement Pensions)፦ በጡረታ መርሐ ግብሮች አማካኝነት ለታቀፉ ዜጎች የወቅቱን ኢኮኖሚያዊና ማኅባራዊ ተግዳሮቶች ያገናዘበ የገንዘብ ዋስትና ማረጋገጥ።
የግብርና ልማት ፖሊሲ	የግብርና ልማት ፖሊሲዎች የተረጋጋና ዘላቂ የምግብ አቅርቦት ለማረጋገጥ ለገበሬዎች (ለአርሶ እና አርብቶ አደሮች) የሚሰጡ ድጎማዎችንና ድጋፍ ፕሮግራሞችን ያካትታሉ። የእነዚህ ፖሊሲዎች ክፍሎች የሚከተሉትን ሊያጠቃልሉ ይችላሉ፦	**የግብርና ግብዓት አቅርቦት (Agricultural input supply)፦** የግብርና ልማትን ለማሳደግ የሚያስፈልጉ ዋና ዋና ግብዓቶችን በተለይም ምርጥ ዘርን፣ ማዳበርያን፣ የአረም ማጥፊያን ኬሚካሎችን፣ የእንስሳት ህክምናና መኖ አቅርቦቶችን እና የመሳሰሉ ወሳኝ የግብርና የግብዓት አቅርቦቶችን መደጎም።
		የሰብል መድን (Crop Insurance)፦ ገበሬዎችን ከሰብል ከተፈጥሮ አደጋዎች በተለይም በድርቅ፣ ጎርፍ፣ በአንበጣ መንጋ በእንስሳት በሽታ እና መሰል አደጋዎች በሚደርስ የምርትና የገንዘብ ኪሳራን ለመከላከል የመድን ዋስትና መስጠት። **የዋጋ ድጋፍ ፕሮግራሞች (Price Support Programs)፦** የእርሻ ምርቶች የወለል ዋጋ ወይም ዝቅተኛ የመሸጫ ዋጋ (price floors) በማውጣት የገበሬዎችን ገቢ ማረጋጋት ማረጋገጥና ኢኮኖሚያዊ ዋስትና መስጠት።

ምሳሌ4፡የድጋሚሀብትክፍፍልፖሊሲዎች

የድጋሚ ሀብት ክፍፍል ፖሊሲዎች የፌዴራል፣ የክልልና የአካባቢ የግብር ውሳኔዎችን እንዲሁም በገቢ ልዩነትና በሀብት ክፍፍል ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ሌሎች የፋይናንስ ጉዳዮችን በማስተባበር ረገድ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። የድጋሚ ሀብት ክፍፍል ፖሊሲዎች በርካታ ምሳሌዎች ያሉት ሲሆን የሚከተሉትን ፖሊሲዎችን ማየት ይቻላል፦

2.2. ፖሊሲ ዝግጅት ሂደቶች

በመደበኛነት የፖሊሲ ዝግጅት ሂደት በርካታ ደረጃዎችን ያካትታል። በዋንኛነት የሚጠቀሱት ሂደቶች ችግርን መለየት፣ አጅነዳ ቀረፃ፣ ፖሊሲን መንደፍ፣ የፖሊሲ ትግበራ እና ግምገማ ናቸው። ፖሊሲዎች ተቀርጸው ሲተገበሩ የሚያልፏባቸው በርካታ ፖለቲካዊ ክርክርንና ትችቶች፣ በባለድርሻ አካላት ተቃውሞ እና ቅሬታዎችን ሊያስተናግዱ እንደሚችሉ ከግምት ውስጥ ማስገባት ያፈልጋል። በመሆኑም በፖለቲካ ፓርቲዎች የሚቀረጹ ፖሊሲዎች እያንዳንዱን ሂደት ሲያልፉ በብርቱ ጥንቃቄ መሆን አለበት።

የፖለቲካ መሪዎችና ተቋማት አጀንዳዎችን በማውጣት፣ ፖሊሲዎችን በመቅረጽና በመተግበር ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። ይህም የፖሊሲዎቹን አቅጣጫና ውጤታማነት በእጅጉ ይወስናል። በመሆኑም፣ የተሻለ ፖሊሲ ለማዘጋጀት እንዲቻል የፖሊሲ ዝግጅት ሂደቶች ምንድናቸው የሚለውን ጉዳይ መረዳት ትልቅ ጠቀሜታ አለው።

- የእርስዎ የፖለቲካ ፓርቲ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ፖሊሲዎችን ሲያወጣ የሚከተላቸው ሂደቶች እንዴት ያሉ ናቸው?
- የፖሊሲ ዝግጅትስ ምንድነው ብለው ያስባሉ?

የፖሊሲ ዝግጅት ሂደት የፖለቲካ ፓርቲዎችን የፖለቲካ ግቦች ወደ ተግባራዊ የህዝብ ፖሊሲዎች የሚቀይር፣ የተወሰኑ ውጤቶችን ለማምጣት የሚነደፍ፣ የተቀናጀ የደረጃዎች ቅደም ተከተል ነው። ፖሊሲ አውጪዎች ሁልጊዜ ሁለት ዋና ዋና ፈተናዎች ያጋጥሟቸዋል።

- አንደኛው **አስቸኳይና አንገብጋቢ** ለሆኑ ወቅታዊ ችግሮች ምላሽ ሰጪ ስልቶችን ማዘጋጀትና ማስተዳደር ነው።
- ሁለተኛው **የረጅም ጊዜ** ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ችግሮችን በመፍታት ለጉዳዮች ዘላቂ መፍትሄ መፈለግ ነው።

የፖሊሲ አውጪዎች እነዚህን ሁለቱን ጉዳዮች ሚዛናዊ በሆነ መልኩ ማስተናገድ የሚጠበቅባቸው በመሆኑ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለፖሊሲ ዝግጅት ሂደት ትኩረት ሰጥተው መዘጋጀት ይኖርባቸዋል።

በዋናነት ፖሊሲዎችን ማዘጋጀት ሁልጊዜ የሚለዋወጡ የማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ፍላጎቶችን ማስተዳደርን ያካትታል። የፖለቲካ ውሳኔ ሰጪዎች የፖሊሲ ማበልጸግን ወደ ተፈለገው ግብ በብቃት ለመምራት የፖለቲካዊ ተለዋዋጭነትና የሚጋጩ ፍላጎቶችን እና ጥቆሞችን ለማስተዳደር የግጭት አፈታት ላይ ጠንካራ ግንዛቤ ሊኖራቸው ይገባል። ፖሊሲ አውጪዎች አስቸኳይ ችግሮችን የሚፈቱ ፖሊሲዎችን በመቅረጽ የመንግሥት ሥርዓቶችን በማሳደግ እና ማኅበረሰቡን ወደተሻለ የወደፊት ሕይወት በመምራት ረገድ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። ሆኖም ግን የሚወጡ ፖሊሲዎች የዛሬን ችግር ከመፍታት አለፈው በዘላቂነት አስተማማኝ እድገትና ደህንነት ለማረጋገጥ የሚአስችሉ የፖሊሲ ማዕቀፎችንም ማካትት ይኖርባቸዋል።

የፖሊሲ ዝግጅት እርከኖች እንደሚከተል እናስተውላለን፦

ችግሮች መለየት	የፖለቲካ ፓርቲዎች መንግሥት ለመመሥረት እድል ሲኖራቸው የመንግሥታዊ ጣልቃ ገብነት የሚያስፈልጋቸውን ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ችግሮች ወይም ጉዳዮች ለይተው ማወቅ ያስፈልጋቸዋል። የችግሩን ስፋትና ክብደት፣ ከየት መጣነትና ተጽኖ ለመረዳት ምርምር ማድረግ፤ መረጃ ሰብስብ እና መተንተን ይኖርባቸዋል። የተለዩ ችግሮችን ምክንያትና ውጤት፣ በማኅበረሰቡ ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ በግለጽ ማስቀመጥና መረዳት ያስፈልጋል። ይህ ፖለቲካ ፓርቲዎች የፖሊሲ ቀረፃ ለማድረግ ከመጀመራቸው በፊት የሚፈጽሙት ተቀዳሚ ተግባር መሆን ይኖርበታል።
ርዕሰ ጉዳይ/አጀንዳ መምረጥ	በፖሊሲ ማውጣት ሂደት ውስጥ የርዕሰ-ጉዳይ አመራረጥ በፖሊሲ ዝግጅት ሂደት ውስጥ ሁለተኛውና ወሳኝ እርምጃ ሲሆን፣ ያሉትን ችግሮች ከመለየት ባለፈ፣ በፖሊሲ አጀንዳው ላይ ያላቸውን ጠቀሜታና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ደረጃ መወሰንን ያጠቃልላል። ይህ ሂደት ችግሩ ያለበትን ሰፊ ኢኮኖሚያዊ፣ የፖለቲካዊና ማኅበራዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ ማስገባትን ይጠይቃል። ፖሊሲ እንዲቀረጽላቸው የሚፈለጉ ችግሮች ወይም ጉዳዮች የሚቀርቡበት መንገድ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም የሕዝብን ትኩረት የሚስቡ አንግብጋቢ ጉዳዮች ምንድናቸው የሚለው የፓርቲዎችን የፖሊሲ ቀረፃ ትኩረት ኃይል ያለው ከመሆኑም በላይ፣ የፖሊሲ ዝግጅት የመጨረሻ ደረጃዎችን በእጅጉ ይቀርጻል።
የፖሊሲ ቀረጻ	የፖሊሲ ቀረጻ ደረጃ ፖሊሲው ሊያሳካቸው ያሰባቸው ዓላማዎች በጥልቀት የሚመረመሩበት፣ ሊሆኑ የሚችሉ ችግር ፈቺ መፍትሄዎች የሚዘጋጁበት እና የተሻለ ውጤታማ በሆኑ ስልቶች ላይ ውሳኔዎች የሚወሰኑበት የፖሊሲ ዝግጅት ክፍል ነው። በዚህ ደረጃ ተግባራዊ የሚደረጉ ዋና ዋና ድርጊቶች መካከል • የማኅበረሰብን ችግሮችሮችን ለመፍታት አማራጭ መፍትሄዎችን መፍጠር፣ • የእያንዳንዱን መፍትሄ አቅጣጫ አዋጭነት እና ውጤታማነት መገምገም፤ • የእያንዳንዱን መፍትሄ የአጭር ጊዜ እና የረጅም ጊዜ ተፅዕኖዎችን ግምት ውስጥ ማስገባት፤ እና • ምርጡን መፍትሄ መምረጥ እና ለአፈጻጸሙ እቅድ ማውጣት ናቸው። በዙህ ሂደት በፖሊሲ ቀረጻ ደረጃ የፖሊሲ ሃሳቦች ተለይተው የቀረቡትን ችግሮች ለመፍታት በሚያስችሉ ረቂቅ ህጎች፣ ደንቦች ወይም ዕቅዶች መልክ ይዘጋጃሉ።

የፖሊሲ አቅጣጫ ውሳኔ	ፖሊሲዎች ጸድቀው ወደ ትግበራ ከመግባታቸው አስቀድሞ የቀረበውን የፖሊሲ መፍትሄ ለሚመለከታቸው ውሳኔ ሰጪዎች ማቅረብ አለበት። ከባለድርሻ አካላትና ፍላጎት ካላቸው ወገኖች ግብዓትና አስተያየት መጠየቅ እንዲሁም የፕሮፖዛሉን ጥቅሞች መከራከርና መወያየት እና አስፈላጊ የሆኑ ግብረመልሶችን ማካተት ይገባል። በፖሊሲው እና በአተገባበሩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ መስጠት ያስገልጋል። በፖለቲካ ፓርቲ ደረጃ የፓርቲው ረቂቅ የፖሊሲ ሃሳቦች በፓርቲ ባልድርሻ አካላት አማካይነት እንዲጸድቁ ከተደረገ በኋላ የፓርቲው ይፋዊ የፖሊሲ አቅጣጫ ሆነው እንዲታወቁ ይደረጋል። በመንግሥት ሥልጣን ላይ ያለ ፓርቲ ፖሊሲዎቹ ሀገራዊ ሆነው ወደ ትግበራ እንዲሸጋገሩ የሕግ አውጪ አካላት ወይም አስፈፃሚ አካላት የፖሊሲ ሃሳቦችን ማጽደቅ አለባቸው።
የፖሊሲ ትግበራ	የፖለቲካ ፓርቲዎች በርጫ ተውዳደረው መንግሥት የመመሥረት እድል ሲኖራቸው የቀረጹትን ፖሊሲ ወደ መተግበርና ወደማስፈጸም ይሸጋገራሉ። ይህ ምዕራፍ ፖሊሲዎች በአስተዳደራዊ ውሳኔዎች ወደ ተግባር የሚለወጡበት ሲሆን፣ ዓላማዎች በስትራቴጂያዊ ተግባራት እና በትክክለኛ የሀብት ክፍፍል መሳካታቸውን ያረጋግጣል። በትግበራው ወቅት ግልጽ ግንኙነትና መመሪያዎች ወሳኝ ናቸው። ይህ የሚሆንበት ምክንያት የመንግሥት አስተዳዳሪዎች ፖሊሲዎችን እንዲተረጉሙ እና በቂ መረጃ ላይ የተመሠረቱ ውሳኔዎች እንዲሰጡ ስለሚያስችላቸው ነው።
የፖሊሲ ግምገማ	በፖሊሲ ግምገማው ምዕራፍ፣ የገዢው ፓርቶ የፖሊሲ አውጪዎች ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የፖሊሲውን ውጤቶች ይገመግማሉ። ግምገማ ማለት የፖሊሲን አፈጻጸም ከተቀመጡለት ዓላማዎች አንጻር የሚለካ ሥርዓታዊ ሂደት ነው። ይህ ሂደት የፖሊሲውን ተፅዕኖ፣ ቅልጥፍና እና ወጪ ቆጣቢነት በተመለከተ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ጥራት ነክ (qualitative) እና ቁጥር ነክ (quantitative) ዘዴዎችን ሊያካትት ይችላል። የፖሊሲዎቹን ውጤታማነት ለማሻሻል አስፈላጊ የሆኑ ማስተካከያዎችን ይወስናሉ። መንግሥት ለመመሥረት እድል ያላገኙ ተቀዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች በትግበራ ላይ ያሉትን የመንግሥት ፖሊሲዎች ከአፈጻጸም ጥራትና ቅልጥፍና፣ አዋጭነትና ስኬታማነት አንጻር በመገምገም መንግሥትን ተጠያቂ ለማድረግ ይችላሉ። በተጨማሪም የራሳቸውን ፖሊሲ ወቅታዊነትና የተማላ መሆንን ከወቅታዊ የሕዝብ ጥያቄዎች እና በሥራ ላይ ካሉ የመንግሥት ፖሊሲዎች አዋጭነት አንጻር በመገምገም የፖሊሲ ክለሳ ወይም ማሻሻያ በማድረግ ፖሊሲያቸውን ይበልጥ ተወዳዳሪ ማድረግ ይቻላሉ።

2.3. የፖሊሲ ዝግጅት የመረጃ አሰባሰብና አጠቃቀም ዘዴዎች

ማስረጃን መሰረት ያደረገ ፖሊሲ አወጣጥ ማለት የፖሊሲ አቅጣጫዎችን ለመወሰን ከፖለቲካዊ አስተያየት ወይም ንድፈ ሀሳብ ይልቅ እውነታዎችን እና ታማኝ፣ ተዛማጅነት ያላቸውን ማስረጃዎች ሰብስቦ መተንተን ነው። ለምሳሌ፣ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ የጤና አጠባበቅ ፖሊሲ ለማውጣት ሲዘጋጅ በርዕዮተ ዓለም እምነቶች ከመመራት ይልቅ ሳይንሳዊ ማስረጃዎችን ቢጠቀም፣ የሚወጣው ፖሊሲ የማኅበረሰቡን የጤና ችግር በትክክል ሊፈታ ይችላል።

በፖሊሲ ዝግጅት ሂደት ውስጥ፣ ችግሮችን ለመለየት፣ ምንጫቸውን እና ያደረሱትን ተጽዕኖ ለመረዳት፣ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮችን ለመለየት እንዲሁም ችግሮቹ እንዴት ሊፈቱ እንደሚችሉና ምን ዓይነት ተጨባጭ መፍትሄዎች እንዳሉ ለማወቅ ሳይንሳዊ ዘዴዎችን መጠቀም ያስፈልጋል። መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በመተንተንና ምክረ ሀሳቦችን በማካተት የሚዘጋጅ ፖሊሲ የበለጠ ስኬታማና ችግር ፈቺ ሊሆን ይችላል።

ማስረጃን መሰረት ያደረገ ፖሊሲና አሠራር መርህ የፖሊሲ ውሳኔዎች ከፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች የግል ፍላጎት ወይም ከየትኛውም ወገንተኝነት የጸዱ እና በማኅበረሰብ ወይም በሀገር ፍላጎት የሚመሩ መሆን አለባቸው የሚል ነው።

2.3.1. ማስረጃ-ተኮር የፖሊሲ ቀረጻ ለምንስ አስፈላጊ ሆነ?

ማስረጃ-ተኮር የፖሊሲ ቀረጻ ሁለት ግቦች አሉት[3]:

- የመጀመሪያው አንድ አማራጭ ፖሊሲ ተቀርጾ ከመውጣቱ በፊት **በትግበራ ላይ ያለው ፖሊሲ ወይም ፕሮግራም ግምገማዎች የሚሰጡንን መረጃዎች እና እውቀት** ለፖሊሲ ውሳኔዎች መጠቀም ለመቻል ነው። ለምሳሌ በትግበራ ላይ ያለ የጤና አጠባበቅ ፖሊሲ ጥንካሬው፣ ድክመቱ፣ መፍትሄ ሰጭነቱ፣ ውጤታማነቱ፣ ተደራሽነቱ፣ ያስመዘገበው እድገት የመሳሰሉት ጉዳዮች ከተመረመሩ በኋላ በሚገኘው መረጃ ላይ ተመስርቶ አንድ ፓርቲ የተሻለ ወይም አማራጭ ነው የሚለውን የፖሊሲ አቅጣጫ ቢያቀርብ የበለጠ ተጨባጭነት ያለው እና የመራጩን ቀልብ ሊገዛ የሚችል ፖሊሲ ልቀርጽ ይችላል።
- ሁለተኛ ደግሞ ለወደፊት ውሳኔዎች የተሻለ መረጃ ለመስጠት ተጨማሪ እውቀትን መገንባት ሰለሚያስችል ነው። ይህ አቀራረብ ከፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች ግለሰባዊ ፍላጎቶች ወይም ተሞክሮዎች፣ ከርዕዮተ ዓለም አቋም፣ ከግምታዊ መላምቶች ይልቅ ከነባራዊ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም ጥብቅ **የጥናት ግኝቶችን፣ መረጃዎችን፣ ትንታኔዎችን**፣ አዳዲስ ፈጠራዎችን እና ግምገማዎች ቅድሚያ ይሰጣል።

2.3.2. መረጃ ለማሰባሰብ የሚረዱ ዘዴዎች

የፐብሊክ ፖሊሲ ምርምር ዋነኛ ዓላማው ለማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊ እና ሌሎች ለኅብረተሰብ ትርጉም ያላቸው ጉዳዮች ላይ ምላሽ መስጠት ነው። በተጨማሪም የፖሊሲ ምርምር አስፈላጊነት የሚታየው የፖሊሲ ባለድርሻ አካላትን ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን መለየትና የፖሊሲ ምላሾችን መረዳት ነው። እንዲህ ያሉ ጉዳዮችን ለመረዳት ሲሞክር ምርምሩ ለእነዚህ የፖሊሲ ተዋናዮች ተግባራትና ምላሽ ሰጪነት አስተማማኝ መሠረት ሆኖ ያገለግላል። ስለዚህ በጥሩ ማስረጃ ላይ የተመሠረተ የፖሊሲ ዝግጅት ሂደት ለማከናዎን የፖለቲካ ፓርቲዎች ሊከተሏቸው የሚችሏቸው ዘዴዎች አሉ። ከነዚህ መካከል የሚከተሉት ጠቃሚ እና ቀላል ዘዲዎች ናቸው።

ታሪካዊ ሰነዶች እና መዛግብት ምርምር	የፖለቲካ ፓርቲዎች ለፖሊሲ ዝግጅት መረጃ ለማሰባሰብ ከሚጠቀሟቸው ዘዴዎች አንዱ ሰነዶችን መመርመር አንዱ ነው። ታሪካዊ ሰነዶች እና መዛግብት ምርምር ማለት የፖሊሲ ጉዳዮችን ለመረዳት ያለፉ መረጃዎችን መመርመር ሲሆን፣ እነዚህም ብዙ ጊዜ ቤተ-መጻሕፍትና መዛግብት ውስጥ ይገኛሉ። ይህ ምርምር የመጀመሪያ ደረጃ ምንጮች (ያልተተነተኑ ኦሪጅናል ሰነዶች እንደ ማስታወሻ ደብተሮች፣ የ ስብሰባ ቃለ ጉባኤዎች፣ ያልተነተኑ ዴታዎች ወይም የግል ትዝታዎች/ማስታወሻዎች) እና ሁለተኛ ደረጃ ምንጮች (እንደ ጋዜጦች፣ የምርምር ጥናት ሪፖርቶች፣ ጆርናሎች፣ የኢንተርኔት መረጃዎች፣ የመንግስት እና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ሪፖርቶች ወይም እንደ መጻሕፍት ያሉ የተተነተኑ መረጃዎች) ያካትታል።
የዳሰሳ ጥናት	የፖለቲካ ፓርቲዎች አሁናዊ ሁነታዎችን ለምረዳት እና የፖሊሲ መረጃ ግብዓት ለማሰባሰብ በቀላሉ ሊጠቀሙባቸው ከሚችሏቸው ቀላል የጥናት ዘዴዎች አንዱ የዳሰሳ ጥናት (Surveys) ዋንኛው ነው። የዳሰሳ ጣንት (Surveys) በቁጥራዊ ጥናት ውስጥ ዋነኛ ዘዴ ሲሆን አይነታዊ/የጥራት መረጃዎችን ለመሰብሰብም ጥቅም ላይ ይውላል። የዳሰሳ ጥናት ደረጃቸውን የጠበቁ መጠይቆች ተዘጋጀተው መረጃ የሚሰባሰብበት ዘዴን ያካትታል። ብዙውን ጊዜ የዳሰሳ ጥናቶች የተዋቀሩ ወይም “ዝግ-መጨረሻ” (closed-ended questions) ጥያቄዎች ይጠቀማል። ይህም ቁጥራዊ ዴታ የሚሰበሰብበት ነው። ለተጨማሪ ዝርዝር መረጃ ሲባል ያልተዋቀሩ ወይም መጨረሻቸው ክፍት የሆኑ ጥያቄዎችንም ያካትታል። እነኝህ ሁለቱን ያጣመሩ "መጠይቅ-ቃለ-መጠይቆች" (questerviews) (ዝግ እና ክፍት-መጨረሻ ጥያቄዎችን የሚያጣምሩ) ሆነው ጥቅም ላይ ይውላሉ። የዳሰሳ ጥናቶች በዙውን ጊዜ ዝግ ጥያቄዎች በምርጫ ዘዴ አካተው ስለሚቀርቡ ለፖለቲካ ፓርቲዎች በዚህ ዘዴ መረጃ ለመሰብሰብ ቀላል ይሆንላቸዋል። ለምሳሌ መረጃ ለማሰባሰብ መጠይቆችን አዘጋጅቶ መላሾችን በስልክ፣ በኢሜል፣ ኦንላይን፣ መጠይቆችን በጽሑፍ በመበተን ወይም በአካል ተገኝቶ በማነጋገር ጥያቄዎቹ እንዲሞሉ ማድረግ ይቻላል። መረጃ አሰባሰቡ የሚወሰነው ምላሽ እንዲሰጡ በተለይ መላሽ ቡድን (target population) የመገኘት ሁኔታ እና የመረጃ አሰባሰብ ዝግጅቶች (logistics) ላይ ነው። በዳሰሳ ጥናት ውስጥ ቁልፍ ከሆኑ ጉዳዮች አንዱ ናሙና መምረጥ (sampling) ነው። የዕጣ ናሙና (Probability sampling) በአጠቃላይ ተመራጭ ዘዴ ነው። ምክንያቱም በተለዩ ቡድን ውስጥ ላሉ ለእያንዳንዱ ግለሰብ በናሙናው ውስጥ የመካተት ዕድል ይሰጣል። የተለመዱ የዕድል ናሙና ቴክኒኮች ቀላል የዘፈቀደ (simple random) ፣ ንብርብር የዘፈቀደ (stratified random) ፣ ክላስተር (cluster)፣ ኮታ (quota) እና ባለብዙ-ደረጃ ናሙና (multistage sampling) ይካትታሉ። ለተወሰነ እና ላልተወሰነ ሕዝብ (finite and infinite populations) ተገቢውን የናሙና መጠን ለመወሰን የሚያገለግሉ ቀመሮች ስላሉ እነሱን መጠቀም ይቻላል።

የጉዳይ ጥናቶች (Case Studies)	የፖለቲካ ፓርቲዎች ለሚያዘጋጁት ችግር ፈቺ እና አዋጭ ፖሊሲ ሊጠቀሙባቸው ከሚችላቸው የጥናት አይነቶች አንዱ የጉዳይ ጥናቶች (Case Studies) ናቸው። የጉዳይ ጥናት ማለት መለስተኛ ክስተቶችን (ለምሳሌ ሁኔታዎችን፣ ባለድርሻ አካላትን፣ አንዳንድ ክንውኖችን፣ ድርጊቶችንና ሂደቶች፣ ተቋማትን፣ ማኅበረሰቦችን እና ሌሎችም ጉዳዮች) በእያንዳንዱ አውድ ውስጥ በጥልቀት መተንተን ነው። ምንም እንኳን በጉዳይ ጥናት ውስጥ የአይነታዊ/የጥራት ወይም የቁጥር/ስታቲስቲክስ መረጃዎችን መቀላቀል ቢቻልም፣ የጉዳይ ጥናት ሁልጊዜም በአውዳዊ ሁኔታዎችና በሚታይ ክስተት መካከል ያለውን ግንኙነት በዝርዝር የሚተነተን ነው። ስለሆነም፣ ለፖሊሲ ዝግጅት በምርመራ ላይ ባሉት ጉዳዮች ላይ ዝርዝር መረጃ በሚያስፈልግበት ጊዜ የጉዳይ ጥናቶች ዘዴ አዋጭ አማራጭ እንደሆኑ ይታሰባሉ።

2.4. የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ

በፖሊሲ ዝግጅት ሂደት ውስጥ የፖለቲካ ፓርቲዎች በርካታ ባለድርሻ አካላትን ማሳተፍ ይጠበቅባቸዋል።

- የፖለቲካ ፓርቲዎች ባለድርሻ አካላትን በፖሊሲ ዝግጅት ወይም ትግበራ ውስጥ ማሳተፍ ያለባቸው ለምንድን ነው?
- ለመሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች በፖሊሲ ዝግጅት ወይም ትግበራ ውስጥ ባለድርሻ አካላትን ማሳተፍ የሚችሉትስ እንዴት ነው?

ችግር ፈቺ እና ውጤታማ ፖሊሲ በመቅረጽም ሆነ በመተግበር ሂደት ውስጥ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት ማማከር እና ማሳተፍ በፖሊሲ ዝግጅት ሂደት ውስጥ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። ፓርቲዎች ባለድርሻ አካላትን በፖሊሲ ዝግጅት ወይም አተገባበር ሂደት ውስጥ ሲያሳትፉ ሕጋዊ ግዴታዎችን ከመወጣት ባለፈም እውነተኛ ጥቅሞች እንዳሉት መገንዘብ ይኖርባቸዋል።

ስለዚህ ባለድርሻ አካላት በፖሊሲ ውስጥ ለምን አስፈላጊ እንደሆኑ እና ባለድርሻ አካላትን በፖሊሲ ዝግጅት ውስጥ ለማሳተፍ የሚረዱ እርምጃዎችን በተመለከተ ግንዛቤዎችን ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጡ ጉዳዮችን በዚህ ክፍል እንመለከታለን[7]።

2.4.1.የፖሊሲምክክር

በፖሊሲ ዝግጅት ሂደት ውስጥ ባለድርሻ አካላትን ማሳተፍ የሚለው ሀሳብ ሲነሳ የፖሊሲ ምክክር (policy consultation) የሚለው ሃሳብ ቁልፍ ጉዳይ ሆኖ እናገኘዋለን። ለመሆኑ የፖሊሲ ምክክር ስንል ምን ማለታቸን ነው?

የፖሊሲ ምክክር የባለድርሻ አካላትን የማሳተፍ ሂደት አንዱ ዓይነት ነው። ይህ የሚያመለክተው የፖሊሲዎችን ጉዳዮች ለመለየት፣ ለማዘጋጀት፣ ለመቅረጽ፣ ለማጽደቅ እና ተግባራዊ ለማድረግ ወይም ለመገምገም የሚያገለግል አሳታፊሂደት ነው። በተለምዶ፣ ይህ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ወይም ድርጅቶች በሕዝብ ፖሊሲዎች ጉዳይ ላይ ከማኅበረሰብ አባላትና ከተጎጂ ቡድኖች ጋር መመካከርን ያካትታል። በተመሳሳይ የፖለቲካ ፓርቲዎችም በፖሊሲ ዝግጅት ሂደት ውስጥ ባለድርሻ አካላት የሚሏቸውን ከአባላትና ደጋፊዎች አንስቶ ማኅብራዊ መሰረታችን ከሚሉት የሕዝብ ተወካዮች ጋር፣ ምሑራን፣ ባለሞያዎችና መሰል አካላት ጋር አካታች በሆነ መንገድ ፖሊሲዎቻቸው መመካከር ይችላሉ። ይህም ይጠበቅባቸዋል።

በፖሊሲ ማበልጸግ ውስጥ የባለድርሻ አካላትን ማሳተፍ የተለያዩ ዘዴዎችን ሊያካትት ይችላል፤ ከትኩረት ቡድኖች (focus groups) ፣ ቃለ-መጠይቆችና ቅኝቶች (surveys) ጀምሮ እስከ በጎ ፈቃደኝነት፣ የምክክር ፓናሎች እና የሥራ ቡድኖች ድረስ ያሉትን ዘዴዎች ያጠቃልላል።

2.4.2. የባለድርሻ አካላትን በፖሊሲ ዝግጅት ውስጥ ማሳተፍ ለምን አስፈለገ?

በቀላል አነጋገር፣ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ እና ምክክር ሳይኖር የፖለቲካ ፓርቲዎች ጥሩና ውጤታማ ፖሊሲዎችን መንደፍም ሆነ መተግበር እጅግ ከባድ ነው። ይህ ደግሞ የፖሊሲው የትግበራ ሂደት ውጤታማ እንዳይሆን ምክንያት ይሆናል። ባለድርሻ አካላትን ማሳተፍ አስፈላጊ የሚሆንባቸው አንዳንድ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው።

ግንኙነቶችን ለማጠናከር	ለፖለቲካ ፓርቲዎች ባለድርሻ አካላትን ማማከር በማኅበረሰቡ ውስጥ የተሻለ ግንኙነቶችን ለመገንባት ይረዳል። እነዚህም ግንኝነቶች ፖሊሲዎችን ለመንደፍና ለመተግበር ጥሩ መሠረት ሊሆኑ ይችላሉ። ጠንካራ የባለድርሻ አካላት ግንኙነቶች መተማመንን ለማሳደግ፣ ተአማኒነትን ለመግባባት፣ እርስ በርስ ለመግባባት፣ ትብብርንና መረዳዳትን ለማመቻቸት ይረዳሉ። በተጨማሪም የፖለቲካ ፓርቲዎች ከባለድርሻ አካላት ጋር በመገናኘት፣ ፖሊሲዎቻቸውን ለማዘጋጀት ወይም ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዱ እውቀቶችን፣ ልምዶችን እና ክህሎቶችን ማግኘት ይችላሉ።
ማኅበራዊ ካፒታልን ለመገንባት	በፖሊሲ ምክክር ውስጥ ባለድርሻ አካላትን የመሳተፍ ዕድሎች በማኅበረሰቡ ውስጥ ማኅበራዊ ካፒታልን ለመገንባት እንዲችሉ ለፖለቲካ ፓርቲዎች አስተዋጾ ያድርጋል። ይህም ፓርቲውችን ራሳቸውን ለማሳደግ እና ፈተናዎችን የመቋቋም አቅማቸውን ሊገነባ ይችላል። ፓርቲዎች ፖሊሲዎቻቸውን ለማዘጋጀት ለባለድርሻ አካላት ለምክክር ሲጋብዙ ሰዎች ካሳተፋቸው ፓርቲ ጋር የበለጠ ጠንካራ የሆነ የባለቤትነት ስሜት ሊያዳብሩ፣ አዳዲስ ግንኙነቶችን ሊፈጥሩ እና በጋራ ፍላጎቶች ላይ ተመስርተው ትስስር ሊፈጥሩ ይችላሉ። ይህም የምክክር ሂደቱ ካበቃ በኋላም ቢሆን ፓርቲዎች ከባለድርሻ አካላት ጋር ያላቸውን ግንኙነት እና ተጠቃሚነታቸውን እንዲቀጥሉ ያስችላቸዋል።
መተማመንን መገንባት	በፖሊሲ ሂደት ውስጥ ከባለድርሻ አካላት ጋር መማከር የፖለቲካ ፓርቲው ምን ያህል ግልጽ እና ተጠያቂ መሆኑን ለማሳየት ይረዳል። ይህ እርስዎ ፓርቲ በሚያከናውኑት ሥራ ላይ እምነት ለመገንባት እና በፓርቲው ላይ ያለውን መተማመን ለማጠናከር ይረዳል።
የተሻለ ግንዛቤ ለመያዝ	የፖለቲካ ፓርቲዎች ከባለድርሻ አካላት ጋር ከተማከሩ በኋላ ስለፓርቲው ለፖሊሲዎች መሠረት የሚሆነውን የተሟላ ምስል እንደሚያገኙ አይጠራጠሩም። በአንድ አካባቢው የሚኖሩ ሰዎች ብዙውን ጊዜ ስለአከባቢያቸው ጠቃሚ እውቀት፣ መረጃ፣ የፈጠራ ሐሳቦች እና ስለ አካባቢያቸውና ማኅበረሰባቸው ጥልቅ ግንዛቤ ይኖራቸዋል። ከባለድርሻ አካላት ጋር መመካከርም ፓርቲው ለሚያዘጋጀው ፖሊሲ ግብዓት የሚሆን ሰፋ ያሉ እና የተለያዩ አመለካከቶችን ለመስማት ዕድል ይሰጣል። ያለበለዚያ ግን ጠቃሚ መረጃዎች ፓርቲዎችን ሊያመልጡት ይችላል። ማኅበረሰቡ የሚፈልገው ምንድን ነው የሚለውን ጉዳይ ከመለየት አንስቶ ችግሮቹ በምን ዘዴ ሊፈቱ እንደሚችሉ ለመገንዘብ ምክክሮቹ በጣም አስፈላጊ ናቸው። ይህን ሲደርግ ነው የፓርቲዎች ፕሮጀክት፣ ፕሮግራም ወይም ፖሊሲ የተጎዱ ባለድርሻ አካላት የሚፈልጉትን የሚያንፀባርቅ መሆኑን ማረጋገጥ የሚቻለው። ይህም ሲሆን በማኅበረሰቡ ዘንድ የእርሶዎ ፓርቲ የመደገፍ ዕድሉ ከፍ ያለ ይሆናል።
ስጋትን መቀነስ	ለፖለቲካ ፓርቲዎች ስለፖሊሲዎቻቸው ከባለድርሻ አካላት ጋር የመመካከር ሌላው ጥቅም በምክክሩ የሚያገኟቸው ግንዛቤዎች ሊከሰቱ የሚችሉ አሉታዊ ውጤቶችን ለመለየት መርዳታቸው ነው። ይህ ደግሞ ያልታሰቡ መዘዞችን ስጋት ለመቀነስ የሚያስችሉ የመከላከያ እርምጃዎችን እንዲወስዱ ይረዷቸዋል።
ግጭትን መቀነስ/ መቆጣጠር	ከባለድርሻ አካላት ጋር መማከር ሊፈጠሩ የሚችሉ ተቃውሞዎችን እና ግጭቶችን ገና በጅምር ለማወቅ ይረዳል። ይህም የፖለቲካ ፓርቲዎች ፖሊሲ ቀርጸው ካሰተዋወቁ ብሎም ለመተግበር እድል ኖራቸው ፖሊሲውን ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ ለመቆጣጠር አስቸጋሪ በሚሆንበት ጊዜ ከሚፈጠሩ ችግሮች ያድናል። በተጨማሪም፣ በሰዎች ላይ ተጽዕኖ በሚያሳድሩ ለውጦች ላይ የቁጥጥር ስሜት እንዲኖራቸው፣ አስተያየታቸውን እንዲሰጡ እና ለአዲሱ ወይም ለተሻሻሉ ፖሊሲዎች እውቅና እንዲሰጡ ያበረታታል።
ሕጋዊ እና ሰብአዊ መብቶች እና ግዴታዎችን ማሟላት	አንዳንድ ፖሊሲዎች በሕግ የተቀመጡ መስፈርቶችን ለማሟላት የባለድርሻ አካላትን ማማከርንና ማሳተፍን ይጠይቃሉ። ይህ ማለት ፖሊሲው (ወይም ለውጡ) አስፈላጊ መሆኑን እና ከባለድርሻ አካላት ጋር በመነጋገር ተገቢውን ትጋት ማድረጋችሁን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ ይጠበቅባችኋል ማለት ነው። በተጨማሪም፣ የማኅበረሰብ ምክክር የሰብአዊ መብት እና ግዴታዎች መሟላታቸውን ለማረጋገጥ ወሳኝ አካል ነው። በእርግጥም፣ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ከሰብአዊ መብት ጉዳዮች ጋር ለተያያዙ የድርጅት ሪፖርቶች የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የመመሪያ መርሆዎች ሪፖርት ማቅረቢያ ማዕቀፍ (UN Guiding Principles Reporting Framework) አካል ነው። በመሆኑም ፓርቲዎች በፖሊሲ ዝግጅትና አፍጻጸም ወቅት ባለድርሻ አካላትን ማሳተፍ ከሰብዓዊ መብቶች ጋር ግንኝነት እንዳለው ተረድተው አሳታፊ መድረኮችን መፍጠር ይጠበቅባቸዋል።

2.4.3. ባለድርሻ አካላትን በፖሊሲ ዝግጅት ሂደት ውስጥ እንዴት ማሳተፍ ይቻላል?

ቀጥለን የምንመለከተው የፖለቲካ ፓርቲዎች በፖሊሲ ዝግጅት ወቅት የሚመለክታቸውን ባለድርሻ አካላት በምን መልኩ ማሳተፍ ይችላሉ የሚለውን ጉዳይ ነው። ለፖሊሲ ዝግጅት የሚደረገው የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ከሌሎች ተሳትፎዎች ጋር ተመሳሳይ ሂደት ይከተላል። ባለድርሻ አካላትን ማሳተፍ አምስት ቁልፍ ደረጃዎችን ያካትታል። ቀጥለን እንመልከታቸው፦

ደረጃ 1: ስትራቴጂካዊ ይሁኑ	የፓርቲዎች ፖሊሲዎች ከባለድርሻ አካላት ጋር መማከርን በቶሎ በጀመሩ የተሻለ ይሆናል። ምርጫ ከመቃረቡ አስቀድሞ ምክክር መጀመር የጠራ የፖሊሲ አቅጣጫ ይዞ ለመውጣት ያግዛል። ነገር ግን ባለድርሻ አካላትን ከማነጋገርዎ በፊት በምክክሩ ሊያሳኩ የሚችሉትን ግብችን እና ዓላማችን ለይቶ መጀመር አስፈላጊ ነው። የሚከተሉትን ያስቡ፦ • ከባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ምን ለማሳካት ዓላማ አድርገው ነው የተነሱት? • ባለድርሻ አካላት በፖሊሲ ምክክር ላይ እንዲሳተፉ የሚፈልጉት ለምንድን ነው? • በየትኛው የፖሊሲ ዝግጅትና ትግበራ ወቅት ነው ባለድርሻ አካላት እንዲሳተፉ የሚፈልጉት? • የፖሊሲ ምክክር ሂደቱ ተሳክቷል የሚሉት ምን ሲሟላ ነው?
ደረጃ 2: በፖሊሲ ምክክሩ ላይ የትኞቹ ባለድርሻ አካላት መጋበዝ እንዳለባቸው ይለዩ	ባለድርሻ አካላትን ሲለዩ እና ዝርዝርዎን ሲያዘጋጁ (የመገናኛ መረጃን ለምሳሌ ስልክ ቁጥር፣ ኢሜል ጨምሮ) በፓርቲዎ ፖሊሲዎች በምን መልኩ ሊነኩ የሚችሉ፣ በፖሊሲ አፈጻጸሙ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ወይም ፍላጎት ያላቸውን አካላት ግምት ውስጥ ያስገቡ። ሁሉም ባለድርሻ አካላት መሳተፍ ላይችሉ ይችላሉ (በእርግጥ ሁሉንም በአንድ መንገድ እና በአንድ መድረክ ማሳተፍ አይቻልም) ፣ ነገር ግን ይህንን ችግር በሚቀጥለው ደረጃ መፍትሄ ያገኙለታል።
ደረጃ 3: ፓርቲዎ ባለድርሻ አካላትን ይወቁ	እዚህኛ ደረጃ ላይ ሲደርሱ የፓሪቲዎን ባልድርሻ አካላት ልየታ (stakeholder mapping) እና የባለድርሻ አካላት ትንተና (stakeholder analysis) ለማድረግ ጊዜው ነው። በአጭሩ ይህ ሂደት የሚከተሉትን ያካትታል፦ • እያንዳንዱ ባለድርሻ አካል ያለውን ተጽዕኖ/ኃይል/ፍላጎት ደረጃ መመዝገብ • አስፈላጊ የሆኑ ስነ-ሕዝብ (demographic) መረጃዎችን መመዝገብ • ባለድርሻ አካላት ይሆናሉ የሚሏቸውን አካላት ጉዳዮችን/ችግሮችን፣ ፍላጎቶችን እና ምርጫዎችን መመዝገብ • ከባለድርሻ አካላትን የሚጠበቁ ነገሮች (በተለይ በምክክሩ ውስጥ ያላቸው የተሳትፎ ደረጃ) መመዝገብ • ከላይ በተጠቀሰው ትንተና መሠረት ባለድርሻ አካላትን በቡድን መከፋፈል

ደረጃ 4: የፖሊሲ ምክክር ዘዴዎችን ያቅዱ	**ሀ. የፓርቲዎን የፖሊሲ ምክክር ሲያቅዱ ሁሉንም ዝርዝሮች እና ደረጃዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርብዎታል። ለምሳሌ፦** • ለምን ከባለድርሻ አካላት ጋር መገናኘት አስፈለገ? • የፖሊሲ ምክክር ተሳታፊ የሆኑ ባላድርሻ አካላት እንዴት እና በየትኛው የምክክር ደረጃዎች ግብረመልሶቻቸውን ይሰጣሉ? • ምን አይነት ግብዓቶች እና ሀብቶች ያስፈልጎታል? **ለ. ባለድርሻ አካላትን የሚያሳትፉባቸውን መስመሮች የመገናኛ ዘዴዎች (channels) እና ባለድርሻ አካላት በምክክሩ እንዴት መሳተፍ እና ምላሾቻቸውን ሊሰጡ እንደሚችሉ ይወስኑ። ለምሳሌ፦** • መጠይቆችን (Questionnaires) በመሙላት • በዳሰሳ ጥናቶች (Surveys) • ቃለ-መጠይቆች (Interviews) • የትኩረት ቡድኖች ውይይት (Focus Groups Discussion) • ስልክ ጥሪዎች (Phone calls) • በኢሜይል መልእክት በመለዋወጥ • በአካል የሚደረጉ ውይይቶች (In-person conversations) • ስብሰባዎች • የማኅበራዊ ሚዲያ ልጥፎች (Social media posts) • ልዩ ልዩ መረሐግብሮች (Events) • የማኅበረሰብ የውይይት መድረኮች • ገበያ ቦታዎች **ሐ. ባለድርሻ አካላት በፖሊሲ በምክክርዎ ሂደት ውስጥ ምን ሚና ሊጫወቱ እንደሚችሉ ይወስኑ። ለምሳሌ፦** • በጎ ፈቃደኞች (Volunteers) • የማኅበረሰብ አማካሪ ፓናል (Community advisory panel) • የፕሮጀክቱን የተወሰኑ ክፍሎች የሚቆጣጠሩ የሥራ ቡድኖች (Working groups to oversee specific parts of the project)
ደረጃ 5: ማስተካከል፣ መለካት፣ ሪፖርት ማድረግ	በፖሊሲ ምክክር ሂደት ውስጥ ውስጥ የመጨረሻው እርምጃ የፓርቲዎን በሂደቱ ያሰየውን እድገት መለካት፣ በእሱ ላይ ሪፖርት ማድረግ እና ግኝቶችን መሠረት በማድረግ አቀራረብዎን ማስተካከል ነው። ይህ የሚከተሉትን ያካትታል፦ • ከምክክሩ የተገኙ ግብረመልሶችን ለፖሊሲ ዝግጅቱ ግብዓት አርጎ በመውሰድ ተግባራዊ ማድረግ • የሰበሰቧቸውን አስተያየቶች እና ግንዛቤዎች ለሚመለከታቸው አካላት ማጋራት • የፖሊሲ ምክክር ሂደቱ ምን ያህል በጥሩ ሁኔታ እንደሄደ መገምገም • ስለፖሊሲ ዝግጅት ሂደቱና ውጤቱ ለባለድርሻ አካላትን ማሳወቅ • ሪፖርቶችን ማዘጋጀት እና ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ማሰራጨት

ከላይ የተዘረዘሩት ስልቶች የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚያዘጋጇቸው ፖሊሲዎች የበለጠ አሳታፊ፣ አካታች እና ውጤታማ እንዲሆኑ ያስቻላቸዋል።

የምዕራፍ ሁለት ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ዋና ተግባራትና ኃላፊነቶች መካከል አንዱ የሆነውን የ**ፖሊሲ ዝግጅት ሂደት** ተመልክተናል። በምዕራፉ መጀመሪያ የፖሊሲን ምንነት እና የህዝብ ፖሊሲ (public policy) ጽንሰ-ሀሳብን በጥልቀት አብራርተናል። በፖሊሲ ዝግጅት ሂደት ውስጥ መታሰብ ስላለባቸው ጉዳዮች፣ ለምሳሌ የመረጃ አሰባሰብ፣ ትንተና፣ ዝግጅት፣ ማፅደቅ፣ መተግበርና መገምገም ምንነት ላይ በዝርዝር ተወያይተናል። በተጨማሪም፣ ለፖሊሲ ዝግጅት የሚያገለግሉ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎችንና ባለድርሻ አካላትን የማሳተፍ ስልቶችን መርምረናል።

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች ለራስዎ በማቅረብ፣ የፓርቲዎን የፖሊሲ ዝግጅት ሂደት በተመለከተ ተጨማሪ ውይይት እንዲያደርጉ እንመክራለን።

- የእርስዎ ፓርቲ የፖሊሲ ዝግጅት ሂደት ምን ይመስላል?
- በፖሊሲ ዝግጅት ወቅት ፓርቲዎ መረጃ ለማሰባሰብ ጥናት ያካሂዳል?
- ፓርቲዎ ፖሊሲ ለማዘጋጀት የትኞቹን የጥናት ዘዴዎች ቢጠቀም የተሻለ እንደሆነ ለሥራ ኃላፊዎች ምክረ ሐሳብ ያቀርባሉ? ለምን?
- የእርስዎ ፓርቲ በፖሊሲ ዝግጅት ወቅት ምን ያህል ባለድርሻ አካላትን ያሳትፋል?
- ባለድርሻ አካላትን ማሳተፍ ያለው ፋይዳ ምንድነው ብለው ያስባሉ?
- በፖሊሲ ዝግጅት ወቅት የትኞቹን ባለድርሻ አካላት እንዲያሳትፍ ይመክራሉ? ለምን

ምዕራፍ ሦስት

የፖለቲካ ኮሚኒኬሽን እና መልዕክት ቀረጻ

በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ ፖለቲካ እና **ተግባቦት/ኮሚኒኬሽን)** ሊነጣጠሉ የማይችሉ ጉዳዮች ናቸው። የፖለቲካ ፓርቲዎች ሃሳቦቻቸውን፣ ፕሮግራሞቻቸውን፣ ርዕዮተ ዓለማቸውን እና ፖሊሲዎቻቸውን ለሕዝብ ማስተዋወቅና ማሳመን የሚችሉት በፖለቲካዊ ኮሚኒኬሽን/ተግባቦት ነው። ፓርቲዎች ስልጣን ለመያዝ በሚያደርጉት ሕጋዊ ሂደትም ሆነ ስልጣን ላይ ከወጡ በኋላ ዓላማቸውን ለሕዝብ ለማስተላለፍ እና በቂ ድጋፍ ለማደራጀት የሚችሉት ለሕዝብ ተደራሽ በመሆን ነው።

ስለዚህ የማንኛውም የፖለቲካ ኮሚኒኬሽን/ተግባቦት ዓላማ ለተወሰኑ ታዳሚዎች ወይም መልዕክት ተቀባዮች መረጃ ማስተላለፍ ነው። እነዚህ መልዕክት ተቀባዮች ፓርቲዎቹ ኢላማ የሚያደርጓቸው የውሳኔ ሰጪዎች ወይም የማህበረሰብ ክፍሎች ሲሆኑ፣ የመልዕክት አሰራጮች ደግሞ መገናኛ ብዙኃን ሊሆኑ ይችላሉ። በአሁኑ ጊዜ የመገናኛ ብዙኃን ቴክኖሎጂ በዘመነበት ሁኔታ የፖለቲካ ፓርቲዎች ማኅበራዊ ሚዲያን በመጠቀም በቀጥታ ለሕዝብ ተደራሽ የመሆን ዕድል አግኝተዋል። (በዚህ መጽሐፍ ተግባቦትን ኮሚኒኬሽን ብለን እንጠቀማለን።)

በምዕራፍ ሦስት የምናተኩረው የፖለቲካ ፓርቲዎች **ስኬታማ የመግባባት ሥራዎችን በመስራት** እንዴት ለሕዝብ፣ በተለይም ለማኅበራዊ መሰረታቸው፣ የበለጠ ተደራሽ ሊሆኑ እንደሚችሉ ነው።

3.1. የስኬታማ የፖለቲካ ኮሚኒኬሽን/ተግባቦት

በፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ውስጥ **ኮሚኒኬሽን** የፖለቲካ ፓርቲዎች ሀሳቦቻቸውን፣ ፖሊሲዎቻቸውን እና ራዕያቸውን የሚገልጹበት መሰረታዊ መሳሪያ ነው። ይህንን የሚያደርጉትም የህዝብን አስተያየት ለመቀየር፣ ድጋፍ ለማሰባሰብ እና የምርጫ ድልን ለማግኘት ነው። ስለዚህ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ዓላማዎች ስኬታማ የሚሆኑት የኮሚኒኬሽን ዘዴዎችን በብቃት በመጠቀማቸው ላይ በቀጥታ የተመሰረተ ነው።

ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ለህዝባቸው ተደራሽ የሚሆኑበትን የኮሙኒኬሽን ስራ በተለያዩ ደረጃዎች ያከናውናሉ። በወቅታዊና ስትራቴጂካዊ ጉዳዮች ላይ ያላቸውን አቋም፣ ፍላጎትና ስጋት ለህዝብ እና ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ያሳውቃሉ። ሕዝባችን ለሚሉት የማህበረሰብ ክፍልም ጥሪ ያስተላልፋሉ። ይህ ሁሉ የኮሚኒኬሽን ስራቸው አካል ነው። ይሁን እንጂ፣ በአሁኑ ጊዜ ዜናዎች ለውጥን ሳይሆን የለውጡን ፍጥነት የሚያመለክቱበት ዘመን ላይ ደርሰናል። ዜናዎች በዜናዎች፣ መልዕክቶች በመልዕክቶች ይደራረባሉ። አንዱ ተነቦ ሳያልቅ ሌላ ጽሁፍ ይወጣል፤ አንዱ ዜና ተደምጦ ሳይገባደድ ሌሎች ዜናዎች አየሩን በፍጥነት ይሞሉታል።

3.1.1. ውጤታማ የፖለቲካ ኮሚኒኬሽን ስትራቴጂ

የቱንም ያህል የፖለቲካ ፓርቲዎች ስኬታማነት የሚለካው ባላቸው የፖለቲካ ፕሮጀክት፣ ፖሊሲ፣ ተወዳሪነት፣ በማኅበረሰብ ውስጥ በገነቡት የቅቡልነት ስኬት፣ በፖለቲካ ፓርቲ መሪዎቹ ስብዕና እና በመሳሰሉት ብዙ ሌሎች ሁኔታዎች ላይ እንደሚመሰረት መሆኑ የማይዘንጋ ቢሆንም ስኬታማ ኮሚኒኬሽን ቁልፍ ሚናን ይጫወታል። ለዚህም ሴክታማ የፖለቲካ ኪሚኒኬሽን ስትራቴጂዎች ያስፈልጋሉ። ቀጥለን የምናያቸው ስልቶች ለውጤታማ የፖለቲካ ኮሚኒኬሽን/ተግባቦት ወሳኝ መሳርያዎች የተባሉ ናቸው[1]።

ትርክት	በፖለቲካው መስክ ስኬታማ የኮሙኒኬሽን ስትራቴጂን ለመተግበር የመጀመሪያው እርምጃ አንድን የፖለቲካ ፓርቲን ኅብረተሰቡ እንዲተማመንበት የሚያቀርበው ትርክት (narrative) ነው። ፓርቲዎች ያላቸውን ሀሳብ የሚገልጹበት መንገድ ከፖሊሲው እኩል አስፈላጊ ነው። ይህም በሚፈጥሩት ትርክት የሚገለጽ ነው። መራጮችም ይሆኑ ምዕላተ ሕዝቡ ከፓርቲዎች አስቀድመው ማወቅ የሚፈልጉት ለሀገራቸው ወይም ለክልላቸው ያላቸውን አጠቃላይ ራዕይ ነው። የሚወሰዱ ፖለቲካዊ እርምጃዎች ቆይቶ የሚመጣ በመሆኑ አስቀድመው ፓርቲዎችን የሚመዝኑት በቃላቸው ነው። ይህም በኢንግሊዘኛው ሶስቱን "C"ዎች የሚያጣምር ትክቶችን መፍጠርን ያካትታል፦ **ወጥነት (consistency)**፣ **አስተማማኝነት (credibility)** እና **ተከታታይነት (coherence)**።

የቃላት አጠቃቀም

በፖለቲካ ኮሚኒኬሽን ውስጥ የቃላት አጠቃቀም በጣም ወሳኝ ጉዳይ ነው። የፖለቲካ ፓርቲዎች በቃላት አጠቃቀማቸው ላይ ብርቱ ጥንቃቄ ማደረግ ይጠበቅባቸዋል። “ቃል ይገላል፣ ቃል ያድናል” እንደሚባለው በፖለቲካ ኮሚኒኬሽን ውስጥ ውጤታማ የቃላት አጠቃቀም ላይ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።

ማኅብረሰቡ የሚደግፈውን ወይም መራጮች ድምፃቸውን ለመስጠት ፓርቲ የተወሰኑ ፍላጎቶቻቸውን እንደሚወክል ለማወቅ ይፈልጋሉ። ይህን ለማወቅ መረጃ ለማግኘት የተለያዩ ሚዲያዎችን ይዳስሳሉ። የፖለቲካ ፓርቲዎችን የምርጫ ፕሮግራሞች፣ የፓርቲውን መሪዎች ቃለ ምልልሶች፣ የፓርቲውን ድረ-ገጾችን እና የማኅበራዊ ሚዲያዎችን ይመለከታሉ። ለሁሉም የማኅበረሰብ አካል የሚመጥን እና ትርጉም የሚሰጥ መልእክት ለመቅረጽ ትክክለኛዎቹን ቃላት እንዴት እናገኛለን?

ቁልፉ ዘዴ **የምንፈልጋቸውን ታዳሚዎች ማዳመጥ ነው**። ምን ማስተላለፍ እንዳለብን ብቻ ሳይሆን እንዴት ማስተላለፍ እንዳለብንም ለማወቅ ከሚረዱ ዋና መንገዶች አንዱ ኢላማ ያደረግነውን ማኅበረሰብ ቀርብ ብሎ ማድመጥ ነው። መልዕክቱ የሚተላለፈው ለነማን ነው ብሎ አስቀድሞ ታዳሚውን መለየት ያስፈልጋል።

ለምሳሌ፣ ለአንድ ወገን "አስፈላጊ ማሻሻያ" (“necessary reform”) ተብሎ የሚታሰበውን አውንታዊ አቀባበል ሌሎች ወገኖች ሲሰሙት “ማኅበራዊ መፍረስ" (“social dismantling”) ብለው ወደሚገልጹት አፍራሽ መረዳት ሊቀይር ይችላል። የመልዕክት ማስተላለፊያ ድምጸቱ ሳይቀር እንደታዳሚዎቹ አይነት መወሰን አለበት። ለወጣቶች የሚተላለፈው መልዕክት፣ ጥቅም ላይ የሚውሉ ቃልት ለአዋቂዎች ወይም ታማኝ ደጋፊዎች ከሚተላለፍ መልዕክት በተልየ ቃና መሆን ይኖርበታል።

የፖለቲካ ፓርቲዎች እና መሪዎች የፖሊሲዎቻቸውን መሠረታዊ መልዕክቶች ላይ ማተኮር ይኖርባቸዋል። የኮሚኒኬሽን ግባቸው አላስፈላጊ ውዝግብ መፍጠር ሳይሆን ስለፓርቲያቸው እና ፖሊሲዎቻቸው መረዳትን መፍጠር ነው። ስለሆነም መልክቶቻቸውን ሊገባ በሚችል መንገድ ማስተላለፍ አለባቸው። በዚህ ረገድ መልዕክትን በአጭር ቃላት ማስተላለፍ አስፈላጊ ነው። "አጭርነት የጥበብ ነፍሱ ነች" ይባላል።

ተለዋዋጭ የኮሚኒኬሽን ስልት መጠቀም

እንደ ፖለቲከኛ ካለፉት ልምዶቻችን የወሰድናቸው ተሞክሮዎች አሉን። በባለፈው ምርጫ ወቅት ውጤት ያላመንበትን የኮሚኒኬሽን ዘዴ፣ የቅስቀሳ ዘመቻ አሁን ደግመን መተግበር ውድቀትን ከመድገም የተለየ ውጤት አያመጣም። ከባለፈው ጊዜ አሁን ላይ አንዳንድ ነገሮች ሊለውጡ ይችላሉ። በተለዋዋጭ እና በማይገመት የፖለቲካ አውድ ውስጥ እንዳለ ፖለቲከኛ ወደፊት ምን ሊያጋጥም እንደሚችል ስለማይታወቅ ተለዋዋጭ ስልት እና ለክስተቶች ምላሽ መስጠት የሚችል የኮሚኒኬሽን ስልት መጠቀም ያፈልጋል።

ይህንን አንድ አውሮፕላን አብራሪ በበረራ ወቅት የመድረሻውን ከማወቁ በተጨማሪ በመንገዱ ላይ ሊያጋጥሙት የሚችሉ ሁኔታዎች ምን ሊሆኑ እንድሚችሉ አስቦ የሚያደርገውን ቅድመ ጥንቃቄ ጋር ማዛመድ ያስፈልጋል። ለምሳሌ አንድ አብራሪ ከጎን የሚነፍስና አውሮፕላኑን የሚንቀንቅ ንፋስ ቢያጋጠም፣ ያልተጠበቀ የአየር ሁኔታ (እንደ ጭጋግ፣ አቧራ) ቢያጋጥም፣ በመንገዱ ላይ ያለውን የትራፊክ ፍሰት ከወትሮው የተለይ ቢሆን ምን ማድረግ እንዳለበት ማወቅ እና የሚወስደውን እርምጃ የአውሮፕላኑን አቅም እና ብቃት ግምት ውስጥ ማስገባት ዝግጅት ማድረግ ይኖርበታል።

በፖለቲካዊ ኮሚኒኬሽን ውስጥ ያልተጠበቁ ክስተቶች ያጋጥማሉ። እነዚህ ተለዋዋጭ የፖለቲካ ገጽታዎች ለምሳሌ በፓርቲው ላይ የሚነገሩ መጥፎ ዜናዎች፣ የባለድርሻ አካላት ተስፋዎች እና አመለካከቶች መለዋወጥ፣ ድንገተኛ የፖለቲካ ክስተቶች፣ ወይም ያልታሰቡ የፖለቲካ ተዋናዮች ድንገት ብቅ ብለው የሁሉንም ማኅበረሰብ ትኩረትን የመሳብ ተጽዕኖን ያካትታሉ። በዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ በተለመደውን የኮሚኒኬሽን ስልት እንከተል ብንል አድማጭ ላይኖረን ይችላል። ጥሩ የኮሚኒኬሽን ስልቶችን የሚከተሉ ፓርቲዎች ተለዋዋጭ ዘዴን መከተል ወሳኝ በሆኑ ለጊዜው እና ለሁኔታው በሚመጥን መልኩ መልዕክቶችን በመፍጠር በፍጥነት ምላሽ ይሰጣሉ።

ለእያንዳንዱ የመገናኛ ብዙኃን የተለየ ስልት መጠቀም	የማኅበራዊ ሚዲያዎች እና አጠቃላይ ዲጂታል የመገናኛ ብዙኃን መምጣት በፖለቲካ ኮሚኒኬሽን ውስጥም ቢሆን አዳዲስ የመገናኛ መንገዶችን ፈጥሯል። አሁን ያለው የመገናኛ ብዙኃን ምርጫ በጣም ሰፊ ሆኗል። የትኛውን ሚዲያ መጠቀም እንዳለባቸው ፓርቲዎች መስፈርቶችን ሲያወጡ ግራ መጋባትን ሊፈጥር ይችላል። **ጥንቃቄ ያድርጉ**፦ ዋናው ነገር በእያንዳንዱ የመገናኛ ብዙኃን ላይ ተመሳሳይ ይዘትን ማስተላለፍ ሳይሆን፣ የታለመላቸው ታዳሚዎችዎ በሚገኙባቸው የመገናኛ ብዙኃን ላይ ተስማሚ ይዘት ማቅረብ ነው። ከዚህም በላይ፣ አንዳንድ የፖለቲካ ኮሚኒኬሽን ቅርጸቶች ከአንዳንድ የመገናኛ ብዙኃን ጋር በተሻለ ሁኔታ ሲሠሩ ከሌሎች ጋር ደግሞ ውጤታማ ላይሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ፣ አጫጭር ቪዲዮዎች ለፌስቡክ፣ ለቲክቶክ፣ ቴሌግራም ለመሳሰሉ የማኅበራዊ ሚዲያ ገጾች በጣም ጥሩ ናቸው። ለሌሎች መድረኮች ለምሳሌ ቴሌቪዥን እና ሬድዮ ግን ጥሩ የአቀራረብ ስልት ላይሆኑ ይችላሉ። በሌላ በኩል ማኅበራዊ ሚዲያ ገጾች የሁለትዮሽ ግንኙነት መደረኮች መሆናቸውን ማስታውስ ያስፈልጋል።
የእውነተኛነት እና የርኅራኄ እሴት	ፖለቲከኞችን ፖለቲከኛ የሚያስብላቸው የሕዝብ ተወካዮች መሆናቸው ነው። ለዚህም ነው ፖለቲከኞች ከዜጎች ጋር መቀራረብ የሚያስፈልጋቸው እና የኛ የሚሉትን ማኅበረሰብ ፍላጎታቸውን፣ ስጋቶቻቸውን እና ሀሳቦቻቸውን በቀጥታ ማወቅ አስፈላጊ የሆነው። ዜጎች ወይም መራጮች በግል የሚያውቋቸውን እና አሳማኝ የሆኑ ፖለቲከኞችን ይፈልጋሉ። ፖለቲከኞች ለህዝባቸው ቅርብ መሆን የሚችሉት በኮሚኒኬሽን ስልቶች ነው። በዲጂታል ዘመን ውስጥ ያለን ቢሆንም በአካል ተገናኝቶ በአፍ የሚነገሩ ቃላት እና ፕሮፓጋንዳ ጠቀሜታቸውን አሁንም ፈጽሞ አላጡም። ፖለቲከኞች ሕዝባችን የሚሉትን አካል በኦንላይንም ይሁን በሕዝባዊ ምድረኮች እና ስብሰባዎች ወቅት፣ በዝግጅቶች ላይ፣ ወይም በግል ሲያገኟቸው **እውነተኛነትን እና ርኅራኄን ማሳየት ይጠበቅባቸዋል**። ይህ አይነት የፖለቲካ ኮሚኒኬሽን ስትራቴጂ የአንድን የፖለቲካ መሪ ጠንካራ ገጽታ ለመገንባት (ተክለ ስብእና/ብራንድ ለመፍጠር) ዕድል ይፈጥራል።

3.1.2. የስኬታማ የፖለቲካ ኮሚኒኬሽን መርሆች

እያንዳንዱ ፓርቲ መልዕክቱን ለሕዝብ ለማድረስ የተለያዩ ዘዴዎችን እንደሚጠቀም ይታመናል። ለመሆኑ ስኬታማ የፖለቲካ ኮሚኒኬሽን የሚመራባቸው መርሆዎች ምንድን ናቸው?

ውጤታማ የፖለቲካ ኮሚኒኬሽን ፓርቲዎች ከአባሎቻቸው፣ ደጋፊዎቻቸው እና ከመራጮች ጋር ለመገናኘት፣ መልዕክታቸውን ለማስተላለፍ፣ መተማመንን ለመገንባት እና ድጋፍ ለማሰባሰብ ወሳኝ መሳሪያ ነው። የፖለቲካ መግባባት ባለሙያዎች እንደሚመክሩት፣ ፓርቲዎች በኮሚኒኬሽናቸው ስኬታማ ለመሆን የሚከተሉትን ዋና ዋና መርሆዎች መተግበር አለባቸው[2]።

ግልጽና ቀላል የፖለቲካ ኮሚኒኬሽን

ውጤታማ የፖለቲካ ኮሚኒኬሽን ዋና መሠረቱ **ግልጽነትና ቀላልነት** ነው። የፖለቲካ ፓርቲዎች በግልጽ እና በቀላሉ መግባባት ሲችሉ፣ ትክክለኛ የሕዝብ ግንዛቤ ይፈጠራል፣ የመራጮች ተሳትፎ ይጨምራል እንዲሁም ግንኙነታቸው ቀልጣፋ ይሆናል።

የፖለቲካ ኮሚኒኬሽን መልዕክት ግልጽና ቀላል ካልሆነ ግን ሕዝብ ግራ ይጋባል፣ ጊዜ ይባክናል እንዲሁም የተሳሳተ ጥረት በመደረጉ የፓርቲው ግቦች ሊደናቀፉ ይችላሉ። ስለዚህ፣ በቴሌቪዥን የሚተላለፉ የፖሊሲ ክርክሮች፣ በማኅበራዊ ሚዲያ የሚለቀቁ መልዕክቶች ወይም በሕዝባዊ ስብሰባዎች ላይ የሚነገሩ ሐሳቦች ዓላማቸውን እንዲመቱ ከተፈለገ፣ ሁልጊዜም ውስብስብና የተንዛዛ ሳይሆኑ በቀላል አገላለጽ መቅረብ አለባቸው። ይህም የፓርቲው መልዕክት በሰፊው ታዳሚ ዘንድ በቀላሉና በትክክለኛ ትርጉሙ እንዲደርስ ያደርጋል።

የመልዕክት ግልጽነትና ቀላልነትን እንዴት ማረጋገጥ ይቻላል?

በፖለቲካ ኮሚኒኬሽን ሂደት ውስጥ ግልጽና ቀላል መልዕክት ለማስተላለፍ፣ የሚከተሉትን ነጥቦች መከተል ይገባል።

- **የአዕምሮ ግልጽነት ይኑርዎት**፦ ማንኛውንም መልዕክት ከማዘጋጀትዎ በፊት ስለሚናገሩት ወይም ስለሚጽፉት ጉዳይ ለራስዎ ግልጽ መሆን አለብዎት። በዚህም መልዕክቱ ምን እንደሆነ (ዋናው ፖሊሲ ወይም ሃሳብ) ፣ ለምን እንደተላለፈ (ዓላማው)፣ ለማን እንደታሰበ (ታዳሚው) እና የሚጠበቀው ውጤት ምን እንደሆነ (ድምጽ ማግኘት፣ አመለካከትን መቀየር) በእርግጠኝነት መለየት ያስፈልጋል። እነዚህ ነጥቦች በአዕምሮዎ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ግልጽ ካልሆኑ፣ የሚያስተላልፉት መልዕክት ለሌሎችም ግልጽ ሊሆን አይችልም።
- **ቀለል ያለና ግልጽ ቃላትን ይጠቀሙ**፦ የፖለቲካ ፓርቲዎች አላስፈላጊ የሙያ ቃላትን (jargon)፣ ውስብስብ አገላለጾችን እና ለተሳሳተ ትርጓሜ ሊዳርጉ የሚችሉ ፈሊጣዊ አባባሎችን ማስወገድ አለባቸው። ቀላል፣ ቀጥተኛ እና ግልጽ ቃላትን መጠቀም የተሳሳተ ትርጓሜ የመስጠት ዕድሉን በእጅጉ የሚቀንስ ሲሆን፣ መልዕክቱ በሰፊው ሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ ያደርጋል።

የዕርስዎ ፓርቲ ከሌሎች ፓርቲዎች በምን እንደሚለይ ማሳየት

በፖለቲካ ኮሚኒኬሽን ውስጥ የዕርስዎን ፓርቲ ከሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚለይበትን ጉዳዮች በጉልህ ማሳየት ያስፈልጋል። የፓርቲዎን ልዩ ማንነት ከሌሎች ለመለየት የሚከተሉትን ርዮተ ዓለም፣ የተለየ አስተሳሰብዎን፣ የፖሊሲ ቅድሚያ የሚሰጧቸውን ጉዳዮች እና ዋና እሴቶቻችሁን ማጉላት ይገባል። የፓርቲዎ ኮሚኒኬሽን ስልት የሚያተኩረው በሚደግፉት ነገር ላይ ብቻ ሳይሆን፣ ከሌሎች ተቃዋሚዎች በተለየ መልኩ ራስዎን እንዴት እንደሚያቀርቡም ጭምር ነው።

ይህንን ለማሳካት ቁልፍ ጉዳዮችን ከራሳችሁ ፓርቲ እይታ አንጻር ማቅረብ፣ መፍትሄዎቻችሁን ከተቀናቃኝ ፓርቲዎች ጋር ማነፃፀር እንዲሁም ለታለመላቸው የመራጮች ወይም ማኅበራዊ መሰረት የሚስማማ ልዩ ቋንቋ መጠቀም ይቻላል። የዕርስዎ ፓርቲ ለሀገር ያላውን የረጅም ጊዜ ራዕይ፣ የተለየ የኢኮኖሚ ፍልስፍና ወይም በማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ ያለውን አቋም ማጉላት ያስፈልጋል። ይህን የማድረግ ዋናው ግብ መራጮች ፓርቲያችሁ የሚቆምለትን ነገር በቀላሉ እንዲረዱት እና ከሌሎች ፓርቲዎች ለምን የተሻለ ተመራጭ እንደሆነ እንዲገነዘቡት የሚያስችል ግልጽ እና የማይረሳ ማንነት መፍጠር ነው።

ተዓማኒነት

ለፖለቲካ ፓርቲዎች ተዓማኒነት መገንባት መቻል ውጤታማ በፖለቲካ ኮሚንኬሽን ለመፍጠርያ ወሳኝ መንገድ ነው። ከሕዝብ ጋር እምነት ለመገንባትና መልእክቶቻቸውን በእውነተኛ የራስ መተማመን ለማስተላለፍ ያስችላቸዋል። ይህ ተዓማኒነት በሁለት ወሳኝ ልኬቶች ላይ የተመሠረተ ነው፦ እውቀትና ችሎታ (expertise) እና ታማኝነት (trustworthiness)። እውቀትና ችሎታ አንድ ፓርቲ በፖሊሲ ጉዳዮችና በአስተዳደር ረገድ ያለውን እውቀትና ብቃት የሚያንፀባርቅ ሲሆን፣ ታማኝነት ደግሞ ሐቀኝነቱን፣ ቅንነቱን እና መርሆችን ማክበሩን ያመለክታል።

ለአንድ የፖለቲካ ፓርቲ ዘላቂ ህልውና እና ስኬታማነት ተዓማኒነትን መገንባት እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው። የፖለቲካ ፓርቲዎች በፖለቲካ ኮሚኒከሽናቸው ውስጥ ታማንኝነትን ለማግኘት እውነተኛ ማስረጃና መረጃን መጠቀም፣ ተዓማኒ የሆኑ ምንጮችን መጥቀስ፣ ቁጥራዊ መረጃዎችን ማቅረብ፣ እንዲሁም ትክክለኛነትንና ተጨባጭነትን ለማሳየት እንደ ቁጥራዊ ማሳያ ሰንጠረዦችን እና ምስላዊ መርጃዎችን መጠቀም የሚኖራቸው ፋይዳ ከፍተኛ ነው። ከዚህም በላይ፣ የሕዝብ ችግሮችን ለመፍታት ያላቸውን እውቀትና ሥልጣን ለማሳየት፣ የአባሎቻቸውን ተገቢ ብቃቶችና ልምዶች ማጉላት፣ ስኬቶችንና የተሳኩ ተነሳሽነቶችን ማሳየት ይገባቸዋል።

ተዓማኒነትን ማስጠበቅ የማያቋርጥ ግልጽነትና ተጠያቂነትን ይጠይቃል። የፖለቲካ ፓርቲዎች ስለ ዓላማዎቻቸው፣ ስለ ፖሊሲዎቸውና ስለ ቀጣይ ግልጽ መሆን አለባቸው። እነዚህን ልምዶች በመቀበል፣ ፓርቲዎች መራጮችን ለማሳመን፣ ድጋፍ ለማሰባሰብ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመምራት የሚያስፈልጋቸውን ወሳኝ እምነት መገንባትና ማስቀጠል ይችላሉ። ለአንድ የፖለቲካ ፓርቲ እምነትን ለመገንባት ዘመናትን ሊፈጅበት ይችላል። ሆኖም ግን የገነባውን እምነት ለመናድ አንዲት ክስተት ከበቂ በላይ ልትሆን ስለምትችል በፖለቲካ ኮሚኒኬሽን ውስጥ ተዓማንነትን ማስቀጠል እጅግ በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ነው።

ተዛማጅነት

ውጤታማ የፖለቲካ ኮሚኒኬሽን ተልዕኮ መልዕክቶችን መበተን ሳይሆን፣ ከሕዝብ ጋር መገናኘት ነው። ለፖለቲካ ፓርቲዎች ይህ ማለት ከሕዝቡ እሴቶች፣ ስጋቶች እና ምኞቶች ጋር በጥልቅ የሚጣጣሙ መልዕክቶችን መቅረጽ መቻል ነው። መልዕክቶች በእውነተኛ መንገድ ተዛማጅነት ያላቸው እና የሰዎችን የዕለት ተዕለት ተሞክሮ የሚናገሩ መሆን አለባቸው። ይህን ለማድረግ ጥልቅ የታዳሚዎች ግንዛቤን ይጠይቃል።

ለሕዝብ ቆሚያለሁ የሚሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ማኅበራዊ መሰረቴ ነው የሚሉትን ወይም ኢላማ ያደረጉትን የሕዝብ ክፍል ተስፋዎች፣ ስጋቶች፣ ፍላጎቶች፣ ፍራቻዎች፣ ተግዳሮቶች እና ዕለታዊ እውነታዎች በትክክል መረዳት አለባቸው። እውነታዎችና የፖሊሲ ዝርዝሮች የቱንም ያህል ወሳኝ ቢሆኑም፣ የፖለቲካ መልዕክቶች ውሳኔዎችን የሚገፋፉ ስሜታዊ ግንኙነቶችን ችላ ካሉ ብዙውን ጊዜ ስኬታማ አይሆኑም። ፓርቲዎች የመልዕክቶቻቸውን አወቃቀር ስሜትን፣ ተስፋን ወይም የጋራ ዓላማን እንዲያነሳሱ ማዘጋጀት አለባቸው። ይህ አቀራረብ የታሰበው የፓርቲው መልዕክት ጆሮ አግኝቶ እንዲሰማ ብቻ ሳይሆን፣ ከሕዝብ ፍላጎትና ስሜት ጋር እንዲስማማ ያደርጋል። ልክ አንድ ቀልደኛ ቀልዶቹ ከታዳሚው እውነታ ጋር "የተዛመዱ" ካልሆኑ እንደማያስቅ ሁሉ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ሊወክሏቸው የሚፈልጓቸውን ዜጎች ዕለታዊ ትግሎችና ፍላጎቶች ማወቅ ካልቻሉ የፖለቲካ ኮሚኒኬሽኖቻቸው "ይወድቃሉ" ማለት ነው።

የፖለቲካ ኮሚኒኬሽን ተዛማጅነትን ማግኘት፦እውነተኛ የፖለቲካ ኮሚኒኬሽን ተዛማጅነትን ለማግኘት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች የታለመላቸውን ታዳሚዎች የጋራ ባህሪያት፣ ዋና እምነቶችና እሴቶች፣ የጋራ ፍራቻዎችና መሠረታዊ ፍላጎቶችን በስልታዊ መንገድ ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው። በተጨማሪም፣ ማንኛውንም የግንኙነት ክፍተቶች ለማጥበብ ተመራጭ የሆኑ የንግግር ዘይቤዎችን፣ የአካባቢ ቃላትን ወይም ተገቢ የሆነ ወቅታዊ ማጣቀሻዎችን መጠቀም ላይ ትኩረት ማድረግ አለባቸው። ለምሳሌ፣ ስለ ኢኮኖሚ ፖሊሲ የሚነገሩ መልዕክቶች ረቂቅ የኢኮኖሚ ሞዴሎችን ከማቅረብ ይልቅ፣ የጋራ ስጋት የሆኑትን እንደ የዋጋ ግሽበት፣ የፋይናንስ ደህንነት ፍላጎት ወይም ለተሻለ የአኗኗር ሁኔታ መጣርን ቢነኩ የበለጠ ውጤታማ ይሆናሉ።

ሁሉም ሰው የራሱን ሕይወት፣ ፈተናዎች፣ ስጋቶች፣ ትግሎችና ሕልሞች የሚያንጸባርቁ ጉዳዮችን በአንድ ፓርቲ የፖለቲካ ኮሚኒኬሽን ውስጥ ሲያይ፣ ከፓርቲው ጋር ጠንካራ ግንኙነት ይፈጥራል።

ተዛማጅነት ለስኬታማ ኮሚኒኬሽን ምሰሶ የሆነበት ምክንያት፦ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሊገነዘቡት የሚገባ ወሳኝ ጉዳይ ተዛማጅነት ለውጤታማ የፖለቲካ ኮሚኒኬሽን ምሰሶ መሆኑን ነው። ምክንያቱም ተዛማጅነት በኮሚኒኬሽን ውስጥ መግባባትን ያሳድጋል፣ መተማመንን ይገነባል እንዲሁም ስሜታዊነትን ያዳብራል። አንድ የፖለቲካ ፓርቲ የሕዝቡን ተግዳሮቶችና ምኞቶች በእውነት መረዳት ሲችል፣ ግንኙነትንና ግንዛቤን የሚያሻሽል ወሳኝ ድልድይ ይገነባል። ይህ የጋራ መሠረት መልዕክቶችን ይበልጥ ውጤታማና የማይረሱ ከማድረግ ባለፈ ደጋፊን ያሰፋል፣ ያበረታታል። ይህ ደግሞ የመተማመን መጨመርን እና በፓርቲው እና በሕዝቡ መካከል ጠንካራ ግንኙነትን ያመጣል። ይህ ባህሪ ከሌለ፣ በጣም ጥሩ ዓላማ ያላቸው መልዕክቶች እንኳን ተገቢነት የሌላቸው ወይም "ከእውነታው የራቁ" ተብለው ሊታለፉ የሚችሉ ሲሆን፣ የሚፈለገውን የፖለቲካ ተሳትፎና ድጋፍ ማመንጨት ይሳናቸዋል።

ታዳሚዎችን ኢላማ ማድረግ እና መለየት

ውጤታማ የፖለቲካ ኮሚኒኬሽን ሕዝብ ወይም ማኅበራዊ መሰረቶች አንድና ወጥ አካል አለመሆናቸውን ይገነዘባል። ይልቁንም እያንዳንዱ ቡድን ልዩ ፍላጎቶች፣ ስጋቶች እና ጥቅሞች አሉት። ከዚህም በተጨማሪ፣ ሁሉም ሰው መረጃን በአንድ ዓይነት መንገድ አይቀበልም። ስለዚህ የፖለቲካ ፓርቲዎች መልዕክታቸውን ለተወሰኑ ቡድኖች ማበጀት እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው። ይህ ደግሞ እንደ ዕድሜ፣ ጾታ፣ ገቢ እና የጂኦግራፊያዊ አካባቢ ያሉ የስነ-ሕዝብ መረጃዎችን በጥልቀት መረዳትን ይጠይቃል። በተጨማሪም፣ ከመሠረታዊ እሴቶች፣ አመለካከቶች፣ የአኗኗር ዘይቤዎች እና ፍላጎቶች ጋር የተያያዙ የስነ-ልቦና መገለጫዎችን ማውጣትም ያካትታል። ፓርቲዎች፣ መረጃን ከየት እንደሚያገኙ (ለምሳሌ ማኅበራዊ ሚዲያ፣ ቴሌቪዥን፣ ሬዲዮ ወይም የኅብረተሰብ ስብሰባዎች) በመለየትና በመተንተን፣ በጣም ውጤታማ የሆኑ የመገናኛ መንገዶችን መምረጥ አለባቸው።

የመልዕክት ማበጀት ኃይል፦ የመልዕክት ማበጀት ኃይል፣ የፓርቲዎችን መሠረታዊ መርሆችና ፖሊሲዎች ለተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች የማላመድ ችሎታ ላይ የተመሰረተ ነው። የፓርቲው መሠረታዊ መርሃግብር ሳይለወጥ ቢቆይም፣ አቀራረቡ ከተወሰኑ ጉዳዮች ጋር በቀጥታ እንዲጣጣም ሊለያይ ይችላል። ለምሳሌ፣ አንድ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ለወጣቶች ሲቀርብ የሥራ ፈጠራ እና የብድር አቅርቦት ላይ ሊያተኩር ይችላል። በዕድሜ ለገፉ መራጮች ደግሞ ትኩረቱ የዋጋ ግሽበትን መቆጣጠርና የጡረታ ዋስትና ላይ ሊሆን ይችላል። ይህ አቀራረብ፣ መልዕክቱ ለግለሰቡ በቀጥታ የሚመለከተው እንዲመስል በማድረግ፣ ተሳትፎን በእጅጉ ያሳድጋል። ይህም እያንዳንዱ ደጋፊ ወይም መራጭ "ይህ ፓርቲ ለእኔ ምን ይጠቅመኛል?" ለሚለው ጥያቄ ምላሽ እንዲያገኝ ያግዛል።

ታዳሚን የመለየት ጥቅሞች፦ በፖለቲካ ኮሚኒኬሽን ውስጥ ታዳሚን ወይም ማኅበራዊ መስረትን መለየት/መከፋፈል፣ የመረጃ ብዛትን ለማስወገድ እና እያንዳንዱ መልዕክት ወቅታዊ፣ ተዛማጅነት ያለውና ተፅዕኖ ፈጣሪ መሆኑን ለማረጋገጥ ወሳኝ ነው። የፖለቲካ ፓርቲዎችም በሰፊው ሕዝብ ውስጥ ያሉትን የተለያዩ “ታዳሚዎቻቸውን” መገንዘብ እና ማስተናገድ አለባቸው። ይህ ትክክለኛነት ፓርቲዎች ስለተወሰኑ ፖሊሲዎች ለመነጋገር፣ ልዩ ተግዳሮቶችን ለመፍታት ወይም ለተለያዩ ቡድኖች ጠቃሚ ዕድሎችን ለማጉላት ያስችላቸዋል። ይህም ወሳኝ መረጃ በማይዛመዱ ነገሮች ብዛት ውስጥ እንዳይጠፋ ያደርጋል፣ እንዲሁም የባህል ልዩነቶችን እና የቋንቋ ብዝሃነትን ግምት ውስጥ በማስገባት የኮሚኒኬሽን ጥረቶችን ውጤታማና አሳማኝ ያደርጋል።

ልብ የሚነካ አቀራረብ

በፖለቲካ ኮሚኒኬሽን ውስጥ የሰዎችን ልብ ለመንካት የሚያስችል ንግግር ማድረግ ወይም የኮሚኒኬሽን ሥራዎችን መስራት እጅግ አስፈላጊ ነው። ይህም ከደረቅ የፖሊሲ ክርክሮች አልፎ ከዜጎች እና ከመራጮች ጋር ጥልቅ ስሜታዊ ግንኙነት ይፈጥራል። ይህን የሚያደርጉት የፓርቲዎን እሴቶች የሚያጎሉ ማራኪ ታሪኮችን በመናገር፣ ግልጽ ቋንቋን በመናገር እና በቀላሉ ሊተረጎሙ የሚችሉ ምሳሌዎችን በመጠቀም ነው። ለምሳሌ የኢኮኖሚ እቅድዎን ዝም ብለው ከመዘርዘር ይልቅ፣ የፓርቲው የኢኮኖሚ እቅድ ተጠቃሚ ስለሚሆኑ የኅብረተሰብ አካላት ታሪክ በመንገር ፖሊሲው ትክክለኛ የሰዎች ህይወት ላይ ያለውን ተጽዕኖ ማሳየት ይቻላል።

ተስፋን እና እምነትን ለማነሳሳት በራስ መተማመን እና ስሜታዊ በሆነ መንገድ መናገር ያስፈልጋል። ክርክሮችንም እንደ አመክንዮአዊ መፍትሄዎች ብቻ ሳይሆን፣ እንደ የጋራ ማንነትና ህብረተሰባዊ ምኞቶች መገለጫዎች አድርጎ ማቅረብ ያስፈልጋል። የሰዎችን ተስፋዎች፣ ፍርሃቶች እና ህልሞች በመንካት፣ ከማንኛውም እውነታ ላይ ከተመሰረተ ክርክር የበለጠ አሳማኝ የሆነ ኃይለኛ ስሜታዊ ትስስር ለመገንባት ያስችላል።

የዕርስዎ ፓርቲ የፖለቲካ ኮሚኒኬሽን መርሆች ከላይ የተዘረዘሩትን መለኪያዎች ያሟላል ብለው ያስባሉ?

ሰንጠረዥ 3.1፡ የስኬታማ ኮሚኒከሽን መርሆች ቅጽ/checklist

የስኬታማ ኮሚኒኬሽን ማሳያ መርሆች	አዎ/አይ
ግልጽና ቀላል የፖለቲካ ኮሚኒኬሽን	
የዕርስዎ ፓርቲ ከሌሎች ፓርቲዎች በምን እንደሚለይ ማሳየት	
ተዓማኒነት	
ተዛማጅነት	
ታዳሚዎችን ኢላማ ማድረግ እና መከፋፈል	
ልብ የሚነካ አቀራረብ	

3.2. ግልጽ እና ወጥ የሆነ መልዕክት መቅረጽ

ትርጉም ያለው፣ የማይረሳ እና አሳማኝ የፖለቲካ መልዕክት ማስተላለፍ አንዱ እና ዋንኛው የፖለቲካ ኮሚኒኬሽን ግብ ነው። ለአንድ ፖለቲከኛ፣ በምርጫ ለሚወዳደር እጩ ወይም የፖለቲካ ፓርቲ አመራር እና አባል ከሚገጥማቸው ፈተናዎች አንዱ፣ ለታለመላቸው የፓርቲው ደጋፊዎች፣ ምዕላት ሕዝቡ ወይም መራጮች **ትርጉም ባለው፣ በማይረሳ እና አሳማኝ** በሆነ መንገድ መልዕክት ማስተላለፍ ነው[3]።

ሁሉም የሚባል በሚቻል መልኩ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች የገንዘብና የሀብት ውስንነት አለባቸው። የፓርቲ አመራሮችና አባላትም የዚህ የማይመረጥ እጣ ተጋሪዎች ናቸው። ለምሳሌ እርስዎ ውስን ጊዜ፣ ገንዘብ እና የበጎ ፈቃደኞች ድጋፍ ስላለዎት ብንል፣ ሕዝብን እንደልብ የማግኘትና መልዕክት የማስተላለፍ ዕድል ላይኖርዎት ይችላል። ከፓርቲ ደጋፊዎች ወይም ከመራጭ ጋር የመገናኘት ዕድል ሲያገኙ (ለምሳሌ በአካል፣ በዜና ማሰራጫዎች ወይም ኦንላይን ላይ) ይህን ዕድል በአግባቡ ለመጠቀም ቢፈልጉ ምን ያደርጋሉ?

የፖለቲካ ኮሚኒኬሽን ዋነኛ ዓላማ ስለ ፓርቲዎ አስፈላጊ ነገሮችን በመንገር ድጋፍ ማሰባሰብ ነው። ለፓርቲዎ ድጋፍ ለማግኘት ወይም መራጮች እርስዎና ፓርቲዎ ማን እንደሆናችሁ እንዲያስታውሱ፣ እንዲሁም ቢመርጧችሁ የሚያመጡትን ለውጥ እንዲረዱ ለማድረግ፣ ባለዎት ውስን ሀብት ተጠቅመው ምን ያደርጋሉ?

ሳጥን 3.1: ቁልፍ ነጥቦች

- በኮሚኒኬሽን ውስጥ **መልዕክት** ማለት በመልዕክት ላኪና በተቀባይ መካከል የሚጋራ መረጃ ነው።
- መልዕክቶች መረጃን ለማካፈል **ቃላትንና ድርጊቶችን** ለምሳሌ የሰውነት ቋንቋንና የድምፅ ቃናን ይጠቀማሉ።
- መልዕክቱ ግልጽ ሲሆንና አድማጩን የተለየ ነገር እንዲያስብ ወይም እንዲሠራ ሲያደርግ **ውጤታማ ግንኙነት** ይፈጠራል።

እያንዳንዱን የመገናኛ ዕድል ለእርስዎ እንዲሰራ ለማድረግ፣ ግልጽ፣ አጭር እና ኃይለኛ መልዕክት ማስተላለፍ ይጠበቅብዎታል። የሚያስተላልፉት መልዕክት፣ ሕዝቡ ለምን ፓርቲዎን መደገፍ እንዳለበት ወይም መራጮች ለምን እርስዎን ድምጽ መስጠት እንዳለባቸው የሚገልጽ እንዲሁም በእርስዎና በተቀናቃኝዎ ፓርቲ መካከል ያለውን ልዩነት የሚያሳይ አጭርና እውነተኛ መግለጫ መሆን አለበት። ተዓማኒነት ያለው መልዕክት መንደፍ እና በተከታታይ ማሰራጨት ለፓርቲዎ የሕዝብ ድጋፍ ለማሰባሰብና ኢላማ የተደረጉ መራጮችን ለማሳመን ወሳኝ ነው።

በፖለቲካ ኮሚኒኬሽን ውስጥ መልዕክት መቅረጽ ወሳኝ ምዕራፍ በመሆኑ በዚህ ንኡስ ክፍል ውስጥ **የፖለቲካ መልዕክት ምንድን ነው?፣ የፖለቲካ መልዕክት መኖሩ ለምን አስፈላጊ ነው? እና ለፓርቲዎ ድጋፍ ለማሰባሰብና ለምርጫ ዘመቻ ትክክለኛና አሳማኝ መልዕክት እንዴት መቅረጽ ይቻላል?** የሚሉትን ጉዳዮች እንመረምራለን።

3.2.1. የፖለቲካ መልዕክት ምንድን ነው?

በንግግር ጥበብ (rhetorical) እና በፖለቲካ ኮሚኒኬሽን ውስጥ መልዕክት ማለት በቃላት (በንግግር ወይም በጽሑፍ) እና/ወይም በሌሎች ምልክቶችና ምስሎች የሚተላለፍ መረጃ ነው ተብሎ ይገለጻል። አንድ መልዕክት (የቃልም ሆነ ቃል ያልሆነ፣ ወይም ሁለቱም) የኮሚዩኒኬሽን ሂደት ይዘት ነው። በኮሚዩኒኬሽን ሂደት ውስጥ የመልዕክቱ አስተላላፊ መልዕክቱን ወደ ተቀባዩ ያስተላልፋል[4]።

በፖለቲካ ኮሚኒኬሽን ውስጥ ዋናው ተልዕኮ የፖለቲካ መልዕክት ማስተላለፍ ነው። ተወዳዳሪ በሆነው የፖለቲካ ምህዳር ውስጥ፣ የፖለቲካ መልዕክት ማለት የማንኛውንም የፖለቲካ ፓርቲ ስትራቴጂን፣ ዘመቻን ወይም አመራርን በስልት የሚያጎላ የቃል ወይም የቃል ያልሆነ ግንኙነት ነው። ይህ በዋነኛነት ከምርጫ ክልል ወይም ከተወሰኑ ታዳሚዎች ጋር በብቃት መገናኘትን ይመለከታል። ለምሳሌ በምርጫ ቅስቀሳ የፖለቲካ መልዕክት ሊሆን የሚችለው አንድ ሰው ፓርቲዎን ለምን መደገፍ እንዳለበት ወይም በምርጫ ቀን ለእርስዎ ፓርቲ ወይም ዕጩ ተወዳዳሪ ለምን ድምጽ መስጠት እንዳለበት የሚገልጽ መግለጫ ነው። የታለመላቸውን ታዳሚዎችዎን ከወሰኑ በኋላ፣ ፓርቲዎን እንዲደግፉ ለእርስዎ ድምጽ እንዲሰጡ ለማሳመን ምን እንደሚሉ መወሰን ያስፈልግዎታል። ይህም ለፓርቲዎ ድጋፍ የሚያሰባስቡበት ወይም የምርጫ ቅስቀሳ መልዕክትዎ ነው።

የፖለቲካ መልዕክቶች ከተለያዩ ምንጮች የሚቀዱ ናቸው። ለምሳሌ የማኅበረሰብ አንገብጋቢ እና መሰረታዊ ጥያቄዎችን በመለየት፣ የመራጮችን ስሜት በጥልቀት በመረዳት፣ እና በተወሰኑ የሕዝብ ክፍሎች ውስጥ ባሉ ወቅታዊ ጉዳዮች በማጤን በጥንቃቄ የሚቀረጹ ናቸው። በፖለቲካ መሪዎች ዘንድ መልዕክት ማስተላለፍ እጅግ በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ሰፊ እምነት አለ። አንድ ፓርቲ የሚመርጣቸው መልዕክቶች የሕዝብን ምላሽ አቅጣጫ የሚያሲዙ እና የምርጫ ውጤቶችን በእጅጉ የሚወስኑ ናችው።

3.2.2. የፖለቲካ መልዕክቶች ሙከራ

አብዛኛውን ጊዜ የፖለቲካ ፓርቲዎች መልዕክቶቻቸውን የሚቀርጹትና የሚያቀርቡት መቼ ነው? ያዘጋጁትን ጽሑፍ ወይም ንግግር ለመገምገምና ለማሻሻል በቂ ጊዜ አለዎት? ወይስ መልዕክቱ ከተላለፈና አሉታዊ ምላሽ ከሰጠ በኋላ በሚያዩት ስህተት ይበሽቃሉ ወይም ይጸጸታሉ?

አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ዋና መልዕክቱን አስቀድሞ በቀረጸና ባጠናቀቀ ቁጥር፣ ረቂቁን ለማጥራትና ለማሻሻል ብዙ ጊዜ ያገኛል። ለምሳሌ፣ በቅድመ ዝግጅት ደረጃ የምርጫ ዘመቻ መልዕክት ማዘጋጀት፣ የተለያዩ የሕዝብ ክፍሎች የፓርቲዎን ሀሳቦች እንዴት እንደሚተረጉሙና ምላሽ እንደሚሰጡ ለመፈተሽ ብዙ ዕድሎችን ይሰጣል።

የመልዕክት ሙከራ ብዙ ቅርጾችን ሊይዝ ይችላል። ፓርቲዎ ለሚቀጥለው ምርጫ የሚያስተላልፋቸውን ዋና ዋና መልዕክቶች መፈተሽ ከፈለገ፣ የሚከተሉትን ዘዴዎች ሊከተል ይችላል፦

ውስጣዊ ግምገማ	መልዕክቱን ለሕዝብ ይፋ ከማድረግ በፊት በፓርቲው የውስጥ መድረክ ላይ በማቅረብ እንዲተችና አስተያየት እንዲሰጥበት ማድረግ።
የሕዝብ ምላሽ ምዘና	መልዕክቱን በሕዝባዊ ስብሰባዎች ወይም በፖለቲካዊ ሰልፎች ላይ በማስተዋወቅና የሕዝቡን ፈጣን ምላሽ መገምገም።
ማኅበራዊ ሚዲያ ትንተና	መልዕክቱን በፖለቲካዊ የማኅበራዊ ሚዲያ መድረኮች ላይ በማሰራጨትና የታዳሚዎችን ተሳትፎና ምላሽ መተንተን።
የቤት ለቤት ዘመቻ	ከቤት ወደ ቤት በመሄድ የመልዕክት ዘመቻዎችን ማቅረብ ቀጥተኛና ጠቃሚ አስተያየቶችን ለማግኘት ያግዛል።
የዳሰሳ ጥናት	እንደ የሕዝብ አስተያየት ዳሰሳ (polling) ያሉ የቁጥር ጥናቶችን ማካሄድ የተወሰነ አስተያየት ያላቸውን ሰዎች ትክክለኛ ቁጥር ይሰጣል። በሌላ በኩል፣ የአይነታዊ (qualitative) ጥናት ደግሞ ሰዎች ለምን እንደሚያስቡና ተነሳሽነታቸው ምን እንደሆነ ጠቃሚ ግንዛቤዎችን ይሰጣል።

- የፓርቲዎን መልዕክት ለመፈተሽ የቱን ዘዴ መጠቀም ያስባሉ?

ዛሬ ዛሬ የሚሞከሩ መልዕክቶችን መፍጠር እና በተለያዩ የሕዝብ ክፍሎችና ጂኦግራፊያዊ አካባቢዎች ላይ ያላቸውን አፈጻጸም በተራቀቀ የሕዝብ አስተያየት ዳሰሳና በተመረጡ የኦንላይን ማስታወቂያዎች አማካኝነት መገምገም የተለመደ ሆኗል። የሚናገሩት ነገር በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ መልኩ እየተቀበለ መሆኑን መለየት የምርጫ ስኬት ለሚፈልግ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ መሰረታዊ ክህሎት ነው።

3.3. ታዳሚን ማወቅ

በዛሬው ውስብስብ እና ብዙ ጊዜ በተከፋፈለ የፖለቲካ ምህዳር ውስጥ፣ ስኬታማ የፖለቲካ ኮሚኒኬሽን ለመስራት፣ የሕዝብ አስተያየትን ለመቅረጽና ፖሊሲን ለመወሰን ለሚፈልግ ወይም ውጤታማ የምርጫ ዘመቻ ለማካሄድ የሚፈልግ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲታ ታዳሚውን መረዳት (understanding the audience) የመጀመሪያው እና ወሳኝ እርምጃ ነው። አንድ ፓርቲ አሳማኝ መልእክት ከማዘጋጀቱ በፊት፣ የፖለቲካ መልዕክቱን ለማን እንደሚያደርስ ወይም ድምጽ ሰጪዎች እነማን እንደሆኑ እና እነሱን ግድ የሚላቸው ጉዳይ ምን ምን እንደሆነ እና ምን አይነት ነገሮች ለእነሱ አስፈላጊ እንደሆነ በጥልቀት መገንዘብ አለበት። ይህ ደግሞ ቁልፍ የሆኑ የስነሕዝብ እና የስነልቦና (demographics and psychographics) መረጃዎችን በጥንቃቄ መመርመር፣ የድምጽ ሰጪዎችን እሴቶች እና ስጋቶች በጥልቀት መተንተን፣ እንዲሁም በትክክል የታለመ መልእክት ማዘጋጀትን ያጠቃልላል[5]።

3.3.1. የቁልፍ ሕዝባዊና ሥነ-ልቦናዊ መረጃዎችን መለየት

አንድ የፖለቲካ ፓርቲ በብቃት የፖለቲካ ኮሚኒኬሽን ለመስራትና ከህዝብ ጋር ለመግባባት ከፈለገ በጥቅሉ ሕዝብን ከላይ ላይ አውቀዋለው ከሚል ያለፈ በጥልቀት ማኅበረሰቡን ለመረዳት መሞከር አለበት። ይህም ለምሳሌ የመራጮችን ስነ-ሕዝባዊ ባህሪያት (demographic characteristics)፣ እንደ ዕድሜ፣ ፆታ፣ የገቢ መጠንና የትምህርት ደረጃ፣ ዝርዝር ትንተና ይጠይቃል። በተመሳሳይ አስፈላጊ የሆነው ደግሞ የመራጮችን ሥነ-ልቦናዊ ባህሪያት (psychographic characteristics)፣ ማለትም ዋና እሴቶቻቸውን፣ የፖለቲካ አመለካከታቸውን፣ የአኗኗር ዘይቤያቸውን እና በእውነት የሚያነሳሳቸውን ነገር መረዳት ነው።

ሰንጠረዥ 3.1፡ ስነ-ሕዝባዊ እና ሥነ-ልቦናዊ ባህሪያት

ስነ-ሕዝባዊ ባህሪያት	ሥነ-ልቦናዊ ባህሪያት
ዕድሜ	እሴቶች (ለምሳሌ፡ እኩልነት፣ ነጻነት)
ፆታ	አመለካከቶች (ለምሳሌ፡ በመንግስት እና በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ያሉ አመለካከቶች)
የገቢ መጠን	የአኗኗር ዘይቤ (ለምሳሌ፡ የከተማና የገጠር ነዋሪነት፣ የሥራ ዘርፍ፡- ነጋዴ፣ አርሶ አደር፣ አርብቶ አደር፣ በደሞዝ ተቀጣሪ)
የትምህርት ደረጃ	የባህርይ መገለጫዎች (ለምሳሌ፡ ወግ አጥባቂ፣ ለዘብተኛ፣ ሊበራል (ከነጻ አስተሳሰብ ጋር የሚራመድ))

እንደ ፖለቲካ ፓርቲ ስኬታማ የፖለቲካ ኮሚኒኬሽን ለማድረግ የታዳሚዎችን ማንነት በሥነ-ሕዝብ ባህሪያትና ሥነ-ልቦናዊ መረጃዎች መሠረት አስቀድሞ መረዳት ወሳኝ ነው። ለምሳሌ የመራጮችን ሰፊ ልዩነት አስቡት፡- አዛውንትና ወጣት መራጮች፣ የከተማና የገጠር ነዋሪዎች እንዲሁም የተማሩና ከሁሉም የሙያ ዘርፎች የተውጣጡ ባለሙያዎች አሉ። እነዚህን ሁሉ የተለያዩ ቡድኖች የሚናገር አንድ ዓይነት መልዕክት በኅብረተሰብ ሚዲያ ላይ ለመፍጠር መሞከር ከንቱ ልፋት ነው። እንዲያውም፣ **“ለሁሉም-ይሆናል” (one-size-fits-all)** የሚለው አካሄድ ከማንም ጋር ውጤታማ ግንኙነት ለመፍጠር አያስችልም።

ስኬታማ ለመሆን የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ቅስቀሳ ጥረታቸውን በሕዝቡ የተወሰኑ ንዑስ ክፍሎች ላይ በስልት ማተኮር አለባቸው። በሌሎችም የፖለቲካ ኮሚኒኬሽን እንቅስቃሴዎቻቸው በተለየ ሁኔታ የሚለዩዋቸውን ታዳሚዎች ታሳቢ ማድረግ ይኖርባቸዋል። ይህን በማድረግ፣ ፓርቲው የእነዚያን ቡድኖች ልዩ ፍላጎቶችና እሴቶች በማንጸባረቅ፣ እነሱን ለመደገፍ በጣም ቅርብ ከሆኑ መራጮች ጋር ጠንካራ ግንኙነት መፍጠር ይችላል።

3.3.2. የታዳሚዎችን ፍላጎቶች፣ እሴቶች እና ስጋቶች መተንተን

አንድ ፓርቲ የታለመላቸውን ታዳሚዎች በትክክል ከለየና ከተረዳ በኋላ ቀጣዩ ወሳኝ እርምጃ የእነሱን **ፍላጎቶች፣ እሴቶችና ስጋቶች** መተንተን ነው። እንዲሆኑላቸው የሚፈልጓቸው ነገሮች ምንድን ናቸው? በጣም የሚጨነቁላቸው ጉዳዮች ምንድን ናቸው? የዕለት ተዕለት ችግሮቻቸው ወይም የሚያስጨንቋቸው ነገሮች ምንድን ናቸው? የእርስዎን ፓርቲ እንዲደግፉ የሚደርጓቸው ጉዳዮች ምንድን ናቸው? ድምጽ እንዲሰጡ፣ በጎ ፈቃደኝነት እንዲሠሩ ወይም ለዓላማ እንዲሟገቱ የሚያነሳሳቸው ምክንያቶች ምንድን ናቸው?

ይህን ጥልቅ ግንዛቤ ለማግኘት የፖለቲካ ፓርቲዎች የተለያዩ የምርምር ዘዴዎችን መጠቀም ይችላሉ:

- **የዳሰሳ ጥናት (Surveys) እና የትኩረት ቡድኖች ውይይት (focus groups discussion):-** እነዚህ የታለመላቸው ታዳሚዎችን ወካይ ከሆኑ ሰዎች ቀጥተኛና ጥልቀት ያለው አስተያየት ይሰጣሉ። ይህን ለማከናወን ቁልፍ የሚባሉ ጥያቄዎችን አዘጋጅቶ ሰዎች ምላሽ እንዲሰጡባቸው መጋበዝና በተለያዩ ዘዴዎች መረጃዎችን መሰብሰብ ይቻላል። የፓርቲዎችን ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶችን እነዚህን መሰል መረጃዎችን ከሕዝዝብ መሐል ለመሰብሰብ መጠቀም ይቻላል።

- **ማኅበራዊ ሚዲያን ማዳመጥ እና መተንተን:-** የኦንላይን ላይ በተለያዩ ገፆች (ለምሳሌ ፌስ ቡክ፣ ኤክስ፣ ቲክ ቶክ፣ ዩቱዩብ) ላይ የሚደረጉ ውይይቶችን መከታተል፣ ሰዎች በትኩረት ስለ ምን ጉዳይ እያወሩ እንደሆነ መረዳት፣ የሚያነሷቸውን ስጋቶች፣ የሚጠቁማቸውን የመፍትሔ ሐሳቦች ማዳመጥ ፍላጎቶቻቸው ምን እንደሆነ ያሳያል፤ ይህም ስለ ሕዝብ ስሜት ግልጽ ግንዛቤን ይሰጣል።

- **የሕዝብ አስተያየት ዳሰሳ (public opinion polls) እና የምርምር ጥናቶች:-** እነዚህ በብዙ ጉዳዮች ላይ የቁጥር መረጃዎችን ይሰጣሉ። ይህም ስለ መራጮች ቅድሚያ የሚሰጧቸው ነገሮች ያሉ ግምቶችን ለማረጋገጥ ይረዳል። ከምርጫ በፊት የሚሰሩ እነዚህን መሰል ጥናቶች አግኝቶ ማየትና መተንተን ያስፈልጋል።

የፖለቲካ ፓርቲዎች ይህን መሰል መረጃዎች አግኝተው መተንተን ሲችሉ ነው፣ ማንኛውም መልዕክት ከመዘጋጀቱ በፊት መመለስ ያለባቸውን ሁለት መሠረታዊ ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት የተሻለ ዕድል የሚኖራቸው። እነዚህም:-

1. የታለመላቸው ደጋፊዎች እና ድምጽ ሰጪዎች እነማን ናቸው?
2. የፓርቲያችን ደጋፊዎች ወይም ድምጽ ሊሰጡን የሚችሉ አካላት በጣም የሚጨነቁባቸው ጉዳዮች እና ችግሮች ምንድን ናቸው?

3.4. ተረኮች በፖለቲካ ኮሚኒኬሽን ውስጥ

በፖለቲካዊ ኮሚኒኬሽን ዓለም ውስጥ ታሪክ መንገር ስሜታዊ መልዕክት የሚያስተላልፉ እና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴን የሚያነሳሱ ትረካዎችን የመቅረጽ ጥልቅ ጥበብ ነው። በዋናነት ሁለት መሠረታዊ ነገሮችን ይጠቀማል። ስሜትና ተግባር።) ተመራማሪዎች እንደሚነግሩን መልዕክት በማስተላለፍ ውስጥ ታሪክ መንገር እጅግ በጣም ጠንካራ የኮሚኒኬሽን ዘዴ እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል። ይህም አድማጩ ማኅበረሰብ እንዲያስብ፣ እንዲያስታውስ እና ምላሽ እንዲሰጥ ወይም እንዲነቃነቅ በማድረግ በፓርቲው መልዕክት እና በአድማጩ መካከል ጥልቅና ዘላቂ ትስስር ይፈጥራል።

3.4.1. የፖለቲካ ፓርቲዎች ታሪክን መተረክ ለምን ያስፈልጋቸዋል?

ሰው ልጆች ገና ከልጅነታቸው ጀምሮ ለትረካና ለታሪክ ቅርበት አላቸው። ለዚህም ነው አብዛኞቻችን ቤተሰቦቻችን ተረት እየነገሩ ያሳደጉን። ታሪኮች ምንም እንኳን ውስብስብና ጥልቅ የሆኑ የፖሊሲ ሀሳቦችን ባይገልጹም፣ ትኩረትን በቀላሉ የመሳብ እና ከሁሉም በላይ የማስታወስ ችሎታን የመጨመር ኃይል አላቸው።

ለመራጮችም ደረቅ የፖሊሲ ነጥቦችን ብቻ ከመዘርዘር ይልቅ ራዕያቸውን በታሪክ የሚያቀርቡ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ይበልጥ ይቀበላሉ። ይህም ወሳኝ የሆነ ስሜታዊ ትስስር ይፈጥራል፣ በደጋፊዎች ዘንድ የፓርቲውን ታማኝነትና ቁርጠኝነት ያጠናክራል እንዲሁም ገና ያልወሰኑ መራጮችን ለመሳብ ይረዳል።

የሚከተሉትን ዋና ዋና የታሪክ አተራረክ ዘዴዎችን በመጠቀም የፖለቲካ ፓርቲዎች በፖለቲካ ኮሚኒኬሽናቸው ውስጥ ይበለጥ ውጤታማ ሊሆኑ ይቻልሉ።

የፖሊሲዎች ተጽዕኖ ማሳየት	የፖለቲካ ፓርቲዎች የአዳዲስ ፖሊሲዎችን ዝርዝር ከመዘርዘር ይልቅ፣ ተጨባጭ ሁኔታዎችን በመጠቀም ለዜጎች የሚሰጠውን ቀጥተኛ ጥቅም ሊያሳዩ ይችላሉ። ለምሳሌ፣ የአንድ የኢኮኖሚ ማሻሻያ እቅድ አንቀጾችን ከማቅረብ ይልቅ፣ ፓርቲው በዚያ ፖሊሲ አማካኝነት ሊያድግ፣ ተጨማሪ ሰራተኛ መቅጠርና ቤተሰቡን ማስተዳደር የቻለ አንድ ትንሽ የንግድ ሥራ ባለቤት ታሪክ ሊያቀርብ ይችላል። ይህ ረቂቅ የሆኑ ፖሊሲዎችን ተጨባጭና ትርጉም ያላቸው ያደርጋቸዋል።

ማኅበራዊ ችግሮችን መፍታትና መፍትሔዎችን ማቅረብ	የፖለቲካ ፓርቲዎች ታሪክን በመጠቀም አስቸኳይ ማኅበራዊ ችግሮችን መለየትና ያቀረቡትን የመፍትሔ ሐሳብ አሳማኝ በሆነ መንገድ ማቅረብ ይችላሉ። በቂ የጤና አገልግሎት እጦት ያለበትን አንድ ማኅበረሰብ የሚመለከት ታሪክ አስቡ። ፓርቲው የበጀት ምደባን ዝርዝር ከማቅረብ ይልቅ፣ በሕክምና ችግር ውስጥ ያለ አንድ ቤተሰብን ታሪክ በመናገር፣ የፓርቲው የጤና አገልግሎት ማሻሻያዎች እንዴት ቀጥተኛ በሆነ መንገድ ስቃያቸውን እንደሚያቀልና ለሁሉም የጤና አገልግሎት ተደራሽነት እንደሚያሻሽል ማሳየት ይችላል። ይህ ፓርቲው ወይም አገሪቱ ከዚህ በፊት ያሳለፏቸውን ችግሮች ለማጉላትም ሊያገለግል ይችላል።
የመራጮችን ግንዛቤ ማሳደግ እና ማስተማርና	ታሪኮች ከፖለቲካዊ ውሳኔዎች፣ ዘመቻዎች ወይም ርዕዮተ-ዓለማዊ አቋሞች በስተጀርባ ያለውን "ምክንያት" ለማሳየት ኃይለኛ መሣሪያ ናቸው። ለምሳሌ፣ ዜጎች አዳዲስ ማኅበረሰባዊ ግዴታዎችን እንዲያከናውኑ ለማበረታታት ወይም የታቀደውን ሕገ-መንግሥታዊ ማሻሻያ አስፈላጊነት ለማስረዳት፣ ፓርቲው እነዚህ ለውጦች እንዴት ዜጎችን እንደሚያበረቱ፣ ዲሞክራሲያዊ ተቋማትን እንደሚያጠናክሩ ወይም ለቀጣዩ ትውልድ የተሻለ የወደፊት ዕጣ እንደሚያስጠብቁ የሚገልጽ ትረካ መፍጠር ይችላል። ይህ አካሄድ የሕዝብን ግንዛቤ አንድ ለማድረግና የጋራ ዓላማ ስሜት ለመፍጠር ይረዳል።

3.4.2. ውጤታማ የፖለቲካ ኮሚኒኬሽን ተረኮች የምፍጠርያ ዘዴዎች

የፖለቲካ ፓርቲዎች በፖለቲካ ኮሚኒኬሽናቸው ውስጥ ወይም በሚቀርጹት መልዕክት ውስጥ ታሪኮችን ለማካተት ቢፈልጉ መከተል ያለባቸው ዘዴዎች በሚከተለው መልኩ አምስቱን ደረጃዎች መከተል ይቻልሉ።

ደረጃ 1፡ የችግር መለየት	ፓርቲያችሁ ሊፈታው ያሰበውን አንገብጋቢ የማህበራዊ ችግር ወይም ፈተና በግልጽ ለይታችሁ አስቀምጡ። ይህን ችግር ከማኅበረሰቡ ጋር በሚገናኝ እና የማይረሳ አውድ በመስጠት አበልጽጉት። ለምሳሌ: ለአብዛኛው ሕዝብ እየጨመረ የመጣው የኑሮ ውድነት።
ደረጃ 2፡ የመፍትሄ መዘርጋት	ችግሩን ለመቅረፍ ፓርቲያችሁ የሚያቀርባቸውን መፍትሄዎች ሃሳቦች ወይም አማራጭ የፖሊሲ ዕቅዶችን አስቀምጡ። ለምሳሌ: ተመጣጣኝ የቤት ዋጋ እና የደመወዝ ጭማሪን የሚያካትት የተሟላ ዕቅድ።
ደረጃ 3፡ ሊጠበቁ የሚችሉ ጥቅሞችን አስቀድሞ ማሳየት	የፓርቲያችሁን መፍትሄዎች በመተግበር የሚገኙትን አዎንታዊ ውጤቶች እና ተጨባጭ ተጽእኖዎች አስቀድማችሁ አሳዩ። ፖሊሲዎቻችሁ ሲተገበሩ የኑሮ ሁኔታ ምን ሊመስል ይችላል? ለምሳሌ: ቤተሰቦች ቤት መግዛት፣ ለልጆቻቸው በቂ ምግብ ማኝየት፣ የልጆች የትምህርት ወጪ መሸፈን መቻል እና የተሻለ የኑሮ ጥራት ማግኘት ይችላሉ።
ደረጃ 4፡ ታሪኩን በክፍል መዘርጋት	እነዚህን ሶስት ደረጃዎች ወደ ማራኪ የትረካ ቅደም ተከተል በመቀየር አመክንዮአዊ እና ስሜትን የሚነካ ፍሰት መኖሩን አረጋግጡ። ይህ ደግሞ ችግር ያለበትን አንድ ዜጋን ወይም ቡድን በማስተዋወቅ፣ የፓርቲውን መፍትሄ እንደ ለውጥ መጀመሪያ በማቅረብ፣ እና አዎንታዊ ውጤቱን በማሳየት ይከናወናል።
ደረጃ 5፡ ትረካውን ማቅረብ	ታሪኩን ጻፉት ወይም ይተርኩት። እዚህ ላይ የቃላት አጠቃቀም ወሳኝ ይሆናል። ቋንቋው ተፈጥሯዊ፣ ከአድማጭና ከተመልካቹ እውነታ ጋር የሚዛመድ እና እውነተኛ ስሜትን የሚቀሰቅስ መሆን አለበት። ግልጽ ገለጻዎችን እና ሰዎች በቀላሉ ሊገናኙዋቸው የሚችሉ ልምዶችን ተጠቀሙ።

የምዕራፍ ሦስት ማጠቃለያ

ይህን ምዕራፍ ስናጠቃልል የምንመለከተው በዝርዝር ያየናቸውን የስኬታማ የፖለቲካ ኮሚኒኬሽን ስትራቴጂዎች፣ መርሆችን እና መመሪያዎችን እንዴት አዋህደን መጠቀም እንቻላለን የሚለውን በክለሳ መልክ በአጭሩ በማስቀመጥ ነው።

በፖለቲካዊ ኮሚኒኬሽን ውስጥ ስኬታማ ለመሆን፣ ውጤታማ የኮሚኒኬሽን ስታራቴጂና መርህ መያዝ፣ ታዳሚዎችዎን በጥልቀት መረዳት፣ ግልጽ እና አሳማኝ መልዕክት ማስተላለፍ እንዲሁም ተአማኒነትን እና መተማመንን ለመገንባት መዘጋጀት ይጠይቃል። በዚህ ምዕራፍ ላይ የተዘረዘሩትን ስልቶች በመከተል፣ የታለሙትን ታዳሚዎችዎን የሚማርክ እና ግቦችዎን ለማሳካት የሚረዳ አሸናፊ የኮሚኒኬሽን ስልት ማዘጋጀት ይችላሉ።

የስኬታማ የፖለቲካዊ ኮሚኒኬሽን ቁልፍ ነገሮችን ለማሳየት፣ አንድ እውነተኛ ምሳሌ እንመልከት። እንበልና፣ ብዙ ወጣት መራጮች ባሉበት ወረዳ ለሥልጣን የሚወዳደሩ ፖለቲከኛ ነዎት። በዚህ ጊዜ የሚከተሉትን ያካተተ የመገናኛ ስልት ማዘጋጀት ይችላሉ፦

- ለወጣት መራጮች አስፈላጊ የሆኑ ቁልፍ ጉዳዮችን ለይቶ ማወቅ፣ ለምሳሌ የሥራ እድል ፈጠራ፣ የተሻለ የሞያ ክህሎት ስልጠና፣ ለሥራ ጀማሪዎች የተሻለ የብድር አቅርቦት።
- እነዚህን ጉዳዮች የሚመለከት፣ ወጣቶችን የሚያማክል ቋንቋና ምስል በመጠቀም ግልጽና አሳማኝ መልዕክት መፍጠር።
- በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ያለዎትን ዕውቀትና ልምድ በማሳየት፣ እንዲሁም በማኅበራዊ ሚዲያና በማኅበረሰብ ዝግጅቶች ላይ ከወጣት መራጮች ጋር በመገናኘት ተአማኒነትንና መተማመንን መገንባት።

ይህ የማኅበራዊ ግንኙነት ስልት ቁልፍ ክፍሎች በሚከተለው የአዕምሮ ካርታ (mind map) ላይ ተብራርቷል።

ይህን ስልት በመከተል ከወጣት መራጮች ጋር የሚስማማ እና ግቦችዎን ለማሳካት የሚረዳ ውጤታማ የግንኙነት ስልት ማዘጋጀት ይችላሉ።

ምዕራፍ አራት

ከመገናኛ ብዙኃን ጋር ግንኙነት መፍጠር

ለፖለቲካ ፓርቲዎች ከመገናኛ ብዙኃን ጋር ጠንካራና አዎንታዊ ግንኙነት መፍጠር የፖለቲካ ግባቸውን ለማሳካት ወሳኝ ነው። አንድ የፖለቲካ ፓርቲ በማኅበረሰቡ ዘንድ ሊታወቅና ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችለው በልዩ ልዩ የመገናኛ ዘዴዎች ለሕዝብ ተደራሽ ሲሆን ብቻ ነው። ፓርቲው የሚከተለውን ርዕዮተ ዓለም፣ የቀረጸውን ፕሮግራም፣ ፖሊሲ ወይም ፕሮጀክት በሰፊው ለሕዝብ ማስተዋወቅ የሚችለው መገናኛ ብዙኃንን በአግባቡ ሲጠቀም ነው። ይህን ማድረግ ካልተቻለ ግን ስለ ፓርቲው ማንነት ዕውቀት የሚኖረው በጥቂት የፓርቲው መሪዎችና አባላት መካከል ብቻ ሆኖ ይቀራል። ለዚህም ነው ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች በተቻለ መጠን ለሕዝብ ተደራሽ የሚያደርጋቸውን ባህላዊም ይሁን ዘመናዊ የማኅበራዊ ሚዲያዎችን ተጠቅመው ስለ ፓርቲያቸው ምንነት፣ ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ግብ፣ ዓላማ፣ አቋም፣ ስትራቴጂ፣ ተስፋና ፍላጎት ለሕዝብ ማስተዋወቅ ያለባቸው።

በኢትዮጵያ ሚዲያዎች እና የፖለቲካ ፓርቲዎች ግንኙነት ውስብስብ እና ከጊዜ ወደ ጊዜ በሚለዋወጥ ሁኔታ ውስጥ ነው። የመንግሥት ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን የማኅበራዊ ሚዲያው ለገዥውም ሆነ ለተቃዋሚ ፓርቲዎች እንዲሁም ለፖለቲካ አቀንቃኞች ወሳኝ መድረክ ሆኖ ብቅ ብሏል። ይህ ሁኔታ ባህላዊና ዲጂታል መድረኮች በፖለቲካዊ ውይይቶች ውስጥ የተለያዩ፣ ግን እርስ በርስ የተያያዙ ሚናዎችን የሚጫወቱበትን ተለዋዋጭ ሁኔታ ፈጥሯል።

4.1. ከመገናኛ ብዙኃን ጋር ውጤታማ ግንኙነት መመሥረት

- የእርስዎ ፓርቲ የመገናኛ ብዙኃንን ትኩረት በምን ያህል ደረጃ ይስባል?
- ከምርጫ ውጪ ባለው ጊዜ ውስጥ፣ ፓርቲዎ ምን ያህል ጊዜ የጋዜጣ፣ የቴሌቪዥን ወይም የሬዲዮ ርዕሰ ዜና ሆኖ ያውቃል?
- የፓርቲዎ ምስል ወይም ብራንድ በማኅበረሰቡ ውስጥ ዘልቆ ገብቷል?

የመገናኛ ብዙኃንን ትኩረት ለመሳብ አለመቻል የበርካታ የፖለቲካ ፓርቲዎች ችግር ነው። በተለይ በርከት ያሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ባሉበት የፖለቲካ ምህዳር ውስጥ የመገናኛ ብዙኃንን ትኩረት መሳብ እና በፓርቲው መሪዎች የሚተላለፍ ቁልፍ መልዕክት የዜና ማሰራጫዎች ርዕሰ ዜና መሆን አስቸጋሪ ነው።

ከ60 በላይ ከሆኑት የፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል በፌዴራል ወይም በክልል ደረጃ ባሉ ዋና ዋና የመገናኛ ብዙኃን ስማቸው ተነስቶ የማያውቅ የፖለቲካ ፓርቲ ጥቂት አይደለም። በተለይ የአዳዲስ የፖለቲካ ፓርቲዎች ፈተና በሕዝብ ዘንድ አለመታወቅ ነው። ይህ የሚሆነውም በቂ የሚዲያ ሽፋን ለማግኘት ባለመቻላቸው ነው።

ምንም እንኳን በኢትዮጵያ አውድ እስካሁን የተሰራ ጥናት ባይኖርም በሌሎች አገራት በመገናኛ ብዙኃን ሽፋንና በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል ያለውን ግንኙነት የሚመረምሩ ጥናቶች ተሰርተዋል። ውጤቶቹ እንደሚያሳዩት፣ በርካታ የፖለቲካ ፓርቲዎች ባሉባቸው አገራት ውስጥ አብዛኞቹ ፓርቲዎች በመገናኛ ብዙኃን ላይ የሚሸፈኑት በጥቂቱ ነው። ለምሳሌ ሳጥን 4.9 ውስጥ ያለውን የአምስተርዳም ዩኒቨርሲቲ ጥናት ሪፖርት እንመለከት[10]።

ይህ መረጃ አዲስ ለተመሠረቱ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚያበረታታ ላይሆን ይችላል። በኢትዮጵያም ከጥቂት ፓርቲዎች በስተቀር፣ አብዛኞቹ በየጊዜው በዜና አውታሮች ሲጠቀሱ አይታይም።

- ለመሆኑ የእርስዎ ፓርቲ በአንድ ዓመት ውስጥ በዜና ማሰራጫዎች ምን ያህል ጊዜ ተጠቅሶ ያውቃል?
    - አንድ ጊዜ?
    - ሁለት ጊዜ?
    - ወይስ ከሦስት ጊዜ በላይ? ቆጥረው ይድረሱበት።

ሳጥን 4.9፡ በመገናኛ ብዙኃን ሽፋን እና በአዳዲስ የፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል ባለው ግንኙነት፦

"በኔዘርላንድስ ውስጥ የመገናኛ ብዙኃን ሽፋን የማያገኙ ብዙ አዳዲስ ፓርቲዎች አሉ። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ ባለው ጊዜ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ በምርጫ የተሳተፉ 183 ፓርቲዎች ነበሩ። ከንዚህ ውስጥ 80 ያህሉ በብሔራዊ መገናኛ ብዙኃን ውስጥ አንድ ጊዜም እንኳ ያልተጠቀሱ ሲሆን፣ 33ቱ ፓርቲዎች ብቻ ከሶስት ጊዜ በላይ ዜና ላይ ወጥተዋል"

4.1.1. የመገናኛ ብዙኃን ሽፋን መጠን ወሳኝ ነው

ለነባርም ይሁን ለአዳዲስ የፖለቲካ ፓርቲዎች **የሚዲያ ሽፋን ማግኘት** እጅግ ወሳኝ ነው። ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ሲመሰረት ለሕዝብ የሚበጅ አማራጭ ሃሳብ አለኝ ብሎ ስለሚያምን፣ አዳዲስ ሃሳቦችንና ድምጾችን በማምጣት የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ጤናማነትን ያሳድጋል። በዚህ ሂደት የመገናኛ ብዙኃን ለስኬቱ ትልቅ ሚና አላቸው።

መራጮች ስለ ፓርቲዎ ካላወቁ ድምጽ ሊሰጡ አይችሉም። ስለዚህ፣ ፓርቲዎ ለመገናኛ ብዙኃን ቅርብ መሆንና ሰፊ ሽፋን ማግኘት ለፓርቲዎ ስምና መልካም ገጽታ (brand) ብቻ ሳይሆን፣ ፋይዳ ያለው ተቋም መሆኑን ለማሳየት ይረዳል። ታዲያ **የመገናኛ ብዙኃንን ትኩረት እንዴት መሳብ ይቻላል?**

አንድ የፖለቲካ ፓርቲ የሚያገኘው የሚዲያ ትኩረት የሚወሰነው ፓርቲው በሚያነሳቸው ጉዳዮች የዜና ዋጋ እንዳለው ሲታሰብ ነው። ይህ ደግሞ የሚዲያ ተጠቃሚዎች ሊፈልጉት ከሚችሉት ነገር ጋር የተያያዘ ነው።

- ፓርቲው ምን ያህል ለማኅበረሰብ ጉዳዮች ቅርበት አለው?
- የቱን ያህል የሕዝብ ድምጽ ሆኗል?
- ምን አይነት አዳዲስ እና ጠቃሚ ሃሳቦች ይዞ መቷል?
- ምን አይነት አማራጭ ፖሊሲ አለው?
- የቱን ያህል በስልጣን ላይ ያለውን የፖለቲካ ፓርቲ ገንቢ በሆነ መልኩ ተጠያቂ ያደርጋል? በምን ያህል ደረጃ ፓርቲው ለሰላማዊ የፖለቲካ ሥርዓት ለውጥ ይታትራል?

እነዚህና መሰል ጉዳዮች የፖለቲካ ፓርቲዎችን የሚሰጣቸው መፍትሄዎች ለብዙኃን መገናኛ ዘዴዎች ቅርብ ሊያደርጓቸው እና የሕዝብንም ትኩረት እንዲስቡ ሊያደርጓቸው ይችላሉ[11]።

። በጎ ባልሆኑ ጉዳዮች የፖለቲካ ፓርቲዎች እና መሪዎች የሚያገኙት የዜና ሽፋን ለጊዜው ትኩረት ሊያሰጥ ቢችልም ፓርቲውን በረዥም ጊዜ ተመራጭ ሊያደርገው አይችልም። ስለሆነም **የፖለቲካ ፓርቲዎች በምን ጉዳይ ላይ የሚዲያ ሽፋን ማግኘት እንዳለባቸው በጥንቃቄ መወሰን** አለባቸው።

የአንድ የፖለቲካ ፓርቲ ስኬት ከሕዝባዊ ገጽታው ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው። በሌላ አገላለጽ ፓርቲው በሕዝብ ዘንድ እንዴት ይታወቃል? የሚለው ወሳኝ ጉዳይ ነው። የድምፅ ሰጪዎች ከፖለቲከኞች ጋር ፊት ለፊት የሚገናኙበት ዕድል ውስን ስለሆነ ስለእነሱ ያላቸው ግንዛቤ በአብዛኛው የሚቀረጸው በመገናኛ ብዙኃን በሚያዩትና በሚሰሙት ነው።

ለዚህም ነው **የሚዲያ ሽፋን** እና **የፓርቲዎች ተደራሽነት** የሕዝብን አስተያየት በመቅረጽ ወሳኝ የሚሆኑት። እንዴት?

ተደራሽነት ተወዳጅነትን ያመጣል	ጥናቶች እንደሚያሳዩት በሚዲያ የመታየት ዕድል (visibility) እና የአንድ ፖለቲከኛ ተወዳጅነት መካከል ጠንካራ ትስስር አለ። አንድ የፖለቲካ ፓርቲ እና መሪዎቹ በዜና ውስጥ በብዛት በታዩ ቁጥር በሕዝብ ይበልጥ የታወቁ ይሆናሉ። ይህ ተደራሽነት መልካም ስም ለመገንባት፣ ዜጎችን ስለ ፓርቲው ውሳኔዎችና አቋሞች ለማስረዳት እንዲሁም ግቦቹንና ዕቅዶቹን ለማስተዋወቅ ይረዳል።
የድመፀት ኃይል	የሚዲያ ሽፋን የሚሰጥበት ድምጸት (tone) የሕዝብን አስተያየት በመቅረጽ በእጅጉ ይወስናል። ምርምሮች ስለ አዎንታዊ ዜና ተጽዕኖ የተለያዩ ግኝቶችን ቢያቀርቡም ስለ አሉታዊነት ተጽዕኖ ግን ግልጽ የሆነ ስምምነት አለ። አሉታዊ የዜና ዘገባ የአንድን ፖለቲከኛ ተወዳጅነት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል። ብዙ ጊዜም ከአዎንታዊ ዘገባ የበለጠ አሉታዊ ዜና ክብደት አለው። ስለዚህ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚዲያ ትኩረት ከመፈለግ በተጨማሪ ዘገባው ገንቢ መሆኑን ለማረጋገጥ ቀዳሚ ሆነው መሥራት አለባቸው።
ዘላቂ የምርጫ ዘመቻ	በምርጫ ጊዜና በምርጫዎች መካከል ባለው ጊዜ መካከል ያለው ልዩነት በአብዛኛው እየደበዘዘ መጥቷል። በአሁኑ ወቅት እንደቀድሞው ጊዜ “የመስቀል ወፍ” እንደሚባለው በምርጫ ሰሞን ብቻ ብቅ ብሎ ምረጡኝ ማለት አዋጭ አልሆነም። ስለዚህ የፖለቲካ ፓርቲዎችና መሪዎቻቸው ውሳኔዎችን ሲወስኑና ከሕዝብ ጋር ግንኙነት ሲፈጥሩ፣ በድምጽ ሰጪዎች ዘንድ ባላቸው ተቀባይነትና ተወዳጅነት ላይ የሚያስከትለውን ተጽዕኖ ዘወትር ማሰብ ያለባቸው በ"ዘላቂ የምርጫ ዘመቻ" ("permanent campaign”) መርህ መሠረት ነው። ከምርጫ እስከ ምርጫ ለሕዝብ ተደራሽ መሆን አስፈላጊ ነው። ይህ አይነት ተከታታይ ተሳትፎ የሕዝብ አስተያየት የሚቀረፀው ከምርጫው በፊት ባሉት ወራት ብቻ ሳይሆን በየጊዜው ያለማቋረጥ ለሚደያ ቅርብ ሆኖ ፓርቲዎን እና ዓላማውን ደጋግሞ በመናገር መሆኑን ያረጋግጣል።

ሌላው የፖለቲካ ፓርቲዎች ለኢትዮጵያ ለሕዝብ ራሳቸውን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማስተዋወቅ የተለያዩ የመገናኛ ብዙኃን ዘዴዎችን መጠቀም አለባቸው። የትኞቹን የሚድያ አውታሮች ነው መጠቀም ያለብን? ብለው ከጠየቁ መልሱ ሁሉንም የሚል ነው። ለምን?

ቴሌቪዥንና ሬዲዮ	የመንግሥትና የግል ብሮድካስተሮች በተለይም የኢንተርኔት ተደራሽነት ዝቅተኛ በሆነባቸው አካባቢዎች ሰፊና የተለያዩ ታዳሚዎችን ለመድረስ አሁንም ሁነኛ መድረኮች ናቸው።
የኅትመት ሚዲያዎች	ጋዜጦችና ሌሎች የኅትመት ውጤቶች የተማረ የከተማ ነዋሪን ለመድረስና የፖሊሲ አቋሞችን በጥልቀት ለመተንተን ወሳኝ ናቸው።
ዲጂታልና ማኅበራዊ ሚዲያዎች	እንደ ፌስቡክ፣ ቲክ ቶክ፣ ቴሌግራም፣ ዩቱዩብ፣ ረንብል፣ እና ኤክስ (የቀድሞው ትዊተር) ያሉት መድረኮች ከወጣት መራጮች ጋር ለመገናኘት፣ ሕዝብ ለማንቃት፣ ለማነቃነቅ፣ ድጋፍን ለማደራጀት እና ፈጣን ምላሽ ሰጪ መልዕክቶችን ለማሰራጨት ወሳኝ ናቸው። ፓርቲዎች በእነዚህ መድረኮች ላይ ጠንካራና ወጥ የሆነ ተሳትፎ ሊኖራቸው ይገባል።

የተለያዩ መድረኮች የተለያዩ ዓላማዎች አሏቸው። አንድ ፓርቲ በሬዲዮ ሰፋ ያለ ሽፋን ለማግኘት፣ በማኅበራዊ ሚዲያ ከወጣቶች ጋር ለመገናኘት፣ እንዲሁም በቴሌቪዥን በሚተላለፉ የሕዝብ ውይይት መድረኮች ላይ ጥልቅ የፖሊሲ ክርክሮችን ለማድረግ ሊጠቀም ይችላል። ቁልፉ በሁሉም መድረኮች ላይ ወጥ የሆነ መልዕክት ያለው የተቀናጀ ስትራቴጂ መተግበሩ ነውቀጥሎ የሚነሳው ጥያቄ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዴት የመገናኛ ብዙኃንን ትኩረት መሳብ ይችላሉ? የሚለው ነው።

4.1.2. የመገናኛ ብዙኃንን ትኩረት መሳብ

በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁኔታ ውስጥ፣ የመገናኛ ብዙኃን ዘርፍ ተለዋዋጭ ነው። ብዙ ጊዜ ሚዲያዎች በመንግሥት የተያዙ ወይም ፓርቲያዊ ዝንባሌ ያላቸው እና ገና በማደግ ላይ ያለ በመሆኑ የመገናኛ ብዙኃንን ትኩረት ማግኘት የአንድ የፖለቲካ ፓርቲ ስኬት ወሳኝ አካል ነው። ይህ ትኩረት የማግኘት ብቻ ሳይሆን፣ ተአማኒነት ያለው የሕዝብ ገጽታን የመገንባት፣ የተለያዩ መራጮችን የማግኘት እና የፓርቲውን መርሆዎች በብቃት የማስተላለፍ ጉዳይ ነው። ስለዚህ የፖለቲካ ፓርቲዎች የመገናኛ ብዙኃንን ትኩረት ለማግኘት እና እራሳቸውን ለሕዝብ ለማስተዋወቅ ሊጠቀሙባቸው የሚችሉባቸውን ዘዴዎች ምንድናቸው የሚሉትን ቀጥለን እናያለን።

የምርጫ ዘመቻዎን መወሰን እና ታዳሚዎችዎን መለየት	ከማንኛውም የመገናኛ ብዙኃን ጋር ግንኙነት ከመፈጠሩ በፊት የፖለቲካ ፓርቲው የራሱን ማንነት እና ዓላማዎች በግልጽ መረዳት አለበት። • ግብዎትን **በግልጽ ይወስኑ**፦ የፓርቲዎ ዋና መልዕክት ምንድነው? ለተለየ የፖሊሲ ለውጥ ዘመቻ እያካሄዱ ነው? ለአንድ መጪ ክስተት ግንዛቤ ለመፍጠር ነው? ወይስ የክልሎዎን ሕዝብ ጥቅም በተለየ መልኩ ማስጠበቅ? **መራጮችዎን ይወቁ፦** እንደ ኢትዮጵያ ባለ የተለያየ ብሔር፣ ቋንቋ እና ክልላዊ ስነ-ሕዝብ ባለበት አገር ለሁሉም የሚሆን አንድ አይነት መልዕክት ማስተላለፍ ውጤታማ አይደለም። ፓርቲዎች የታለመላቸውን ታዳሚዎች (ከተማ ውስጥ ያሉ ወጣቶች፣ የገጠር ገበሬዎች ወይም የተለየ የሙያ ዘርፍ) መለየት እና ልዩ ስጋቶቻቸውን፣ ፍላጎቶቻቸውን እና የመገናኛ ብዙኃን አጠቃቀማቸውን ልማዶች መረዳት አለባቸው። ይህም የተዘጋጀ መልዕክትን ለመጠቀም እና በጣም ተስማሚ የሆኑ የመገናኛ ብዙኃን መድረኮችን ለመምረጥ ያስችላል። ለምሳሌ፣ አንድ ፓርቲ የገጠር ነዋሪዎችን ለመድረስ የማኅበረሰብ ሬዲዮን፣ እና ለከተማ ወጣቶች ደግሞ እንደ ፌስቡክ፣ ቲክ ቶክ እና ኤክስ (ትውተር) ያሉ ማኅበራዊ ሚዲያ መድረኮችን ሊጠቀም ይችላል።

አሳማኝ የፖለቲካ ትርክት መፍጠር	እያንዳንዱ የተሳካ የፖለቲካ ዘመቻ የሚገነባው በፖሊሲ ነጥቦች ዝርዝር ላይ ብቻ ሳይሆን ጠንካራ ትርክት ላይ ነው። አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ለሕዝብና ለመገናኛ ብዙኃን በተፈጥሮው የሚስብና ጠቃሚ የሆነ ትርክት ይዞ ማግኘት አለበት። • **የዜና ማዕዘንዎን ያግኙ**:- አንድ ፓርቲ አዲስ ፖሊሲን ከማስታወቅ ይልቅ፣ መልዕክቱን ፈጠራን በሚያጎላ፣ ትክክለኛ የሕዝብን ችግርን በሚፈታ መልኩ፣ ወይም ሰፊ የሆነ የሕዝብ ውይይትን በሚጋብዝ መልኩ ትኩረት በሚስብ ትርክት ዙሪያ ማቅረብ አለበት። ለምሳሌ፣ ስለ አዲስ የእርሻ ፖሊሲ የሚገልጽ ታሪክ የኢትዮጵያን የምግብ ዋስትና ስለማጠናከርና የአካባቢ ማኅበረሰቦችን ስለ መደገፍ ወደሚያወራ ትረካ ሊቀየር ይችላል። • **ትረካዎን በመረጃ ይደግፉ**: - አሳማኝ ትርክት በተአማኒ መረጃዎች የተደገፈ መሆን አለበት። ስለ አንድ ችግር ስታቲስቲክስ መስጠት ወይም የአንድ ፖሊሲ ሊያስገኘው የሚችለውን አወንታዊ ተጽእኖ ማሳየት ለትረካው ክብደት ይሰጠዋል እንዲሁም ፓርቲው በማስረጃ ላይ የተመሠረቱ መፍትሄዎችን ለመስጠት ያለውን ቁርጠኝነት ያሳያል።
ስልታዊ የፕሬስ ግብዓቶች እና አስቀድሞ የሚንቀሳቀስ የኮሚኒኬሽን ስልት	የፖለቲካ ፓርቲዎች የራሳቸውን ይዘት በመፍጠር እና በማሰራጨት ትረካውን ለመቅረጽና ለሕዝብ መረጃ ለመስጠት ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ንቁ የኮሚኬሽን ሥራዎችን መስራት አለባቸው። • **ውጤታማ የፕሬስ መግለጫዎችን መጻፍ**:- የፕሬስ መግለጫ ከመገናኛ ብዙኃን ጋር መደበኛ ግንኙነት ለመፍጠር ወሳኝ መሣሪያ ነው። አጭር፣ ግልጽ እና ዜና-አዘል መሆን አለበት። እንዲሁም የአንድ ክስተት፣ የፖሊሲ ማስታወቂያ ወይም የፓርቲ ስኬትን ማንነት፣ ምንነት፣ መቼነት፣ የትነት እና ለምንነት በግልጽ ማስቀመጥ አለበት። በጥሩ ሁኔታ የተጻፈ የፕሬስ መግለጫ፣ በጥራት የላቀ ፎቶግራፎች ወይም ቪዲዮዎች የታገዘ ከሆነ፣ መልዕክትዎ የመተላለፍ ዕድሉን በእጅጉ ከፍ ያደርገዋል። • **የባለሙያ አስተያየት መስጠት**:- ፓርቲዎች መሪዎቻቸውንና ቁልፍ አባሎቻቸውን በየዘርፋቸው እንደ ባለሙያ አድርገው ማቅረብ አለባቸው። አግባብነት ባላቸው ዜናዎችና ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የባለሙያ አስተያየት በቅድሚያ በመስጠት፣ ፓርቲዎች እንደ እውቀትና እምነት የሚጣልበት ምንጭ ስማቸውን መገንባት ይችላሉ። ጋዜጠኞች ትንታኔና ተጨማሪ ማብራሪያ ለመስጠት ታማኝ ድምፆችን ይፈልጋሉ፤ በተከታታይ ጠቃሚ መረጃ የሚሰጥ ፓርቲ ደግሞ የበለጠ ዕድል ያገኛል። • **ወቅታዊ ጉዳዮችን መጠቀም**:- አንድ ፓርቲ አሁን ባለው የዜና ፍሰት ላይ ግንዛቤ ሊኖረው ይገባል። ከዚያም መልዕክቶቹን ከትልቅ ብሔራዊ ወይም ዓለም አቀፍ ትረካ ጋር የሚያገናኝባቸውን መንገዶች መፈለግ አለበት። ይህ ፓርቲዎች ትርክታቸውን ከወቅታዊ ጉዳይ ጋር በማገናኘት፣ መልዕክታቸውን ከፍተኛ ትኩረት ወዳለበት ውይይት ውስጥ ማስገባትና ተደራሽነቱንና ተዛማጅነቱን ማሳደግ ይችላሉ።
የመገናኛ ብዙኃን ሥልጠና እና የዝና አያያዝ	የመገናኛ ብዙኃንን ትኩረት ማግኘት የጉዳዩ መጀመሪያ ነው። አንድ ፓርቲ የመገናኛ ብዙኃንን ጥያቄዎች እንዴት እንደሚመልስ እና በጫና ውስጥ ሆኖ እንዴት እንደሚግባባ ልክ እንደ መጀመሪያው ሁሉ አስፈላጊ ነው። • **ለቃለ መጠይቅ መዘጋጀት**:- የፓርቲ ኃላፊዎችና ቃል አቀባዮች ከመገናኛ ብዙኃን ጋር የሚደረጉ ቃለ መጠይቆችን በብቃት እንዲያስተናግዱ ሥልጠና ማግኘት አለባቸው። ይህ ሥልጠና በግልጽ እና በአጭሩ ዋናውን መልእክት ወይም "soundbite" እንዴት ማስተላለፍ እንደሚቻል፣ እንዲሁም ከአስቸጋሪ ጥያቄዎች ወደ ፓርቲው ዋና ዋና ነጥቦች "እንዴት መመለስ" እንደሚቻል ላይ ማተኮር አለበት። ይህ መልእክቶች እንዳይዛቡ ይከላከላል። እንዲሁም የፓርቲው ገጽታ ወጥነት ያለውና አዎንታዊ ሆኖ እንዲቀጥል ያደርጋል። • **የመገናኛ ብዙኃን ሽፋን መጠቀም**:- አንድ ፓርቲ የመገናኛ ብዙኃን ሽፋን ካገኘ በኋላ ይህ ሽፋን የበለጠ እንዲጠናከር መደረግ አለበት። ፓርቲው የተገኘውን ጽሑፍ፣ ቃለ መጠይቅ ወይም የዜና ዘገባ በሁሉም የማኅበራዊ ሚዲያ ገጾቹ እና በዜና መጽሔቶቹ ላይ ማጋራት አለበት። ይህ ሽፋን በፓርቲው ድረ-ገጽ ላይ በሚገኝ “ፕሬስ” ወይም “ሚዲያ” በሚል ክፍል ውስጥ ሊቀመጥ ይችላል። ይህም እንደ የሥራ ውጤቶች ማሳያ ሆኖ የሚያገለግል ሲሆን፣ ከደጋፊዎችና ከወደፊት አጋሮች ጋር ያለውን ተአማኒነት ይገነባል። • **የተለመዱ ስህተቶችን ማስወገድ**:- ፓርቲዎች እንደ አጠቃላይ እና ያልተመረጡ መልእክቶችን መላክ፣ የመገናኛ ብዙኃን ሽፋን እና ብዙ ነገር እንደሚሠራ ቃል መግባት ወይም ሀሳብን "በግዳጅ ለመሸጥ" ("hard sell") መሞከርን የመሳሰሉ የተለመዱ ስህተቶችን ማስወገድ አለባቸው። እነዚህ ስልቶች ከጋዜጠኞችና ከመገናኛ ብዙኃን ጋር ያለውን ግንኙነት ሊጎዱ ይችላሉ። ይህም ለወደፊት ግንኙነቶች አስቸጋሪ ያደርጋቸዋል። እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ከፍተኛ ፉክክርና ጥርጣሬ ባለበት የመገናኛ ብዙኃን ዓለም ውስጥ፣ ሙያዊ አሠራርና በግልጽ የተቀመጠ ስልት ወሳኝ ናቸው።

4.2. ውጤታማ ቃለ –ምልልስ ከመገናኛ ብዙኃን ጋር የማድረግ ዘዴ

በአንድ የብሔራዊ የቴሌቪዥን ጣቢያ ላይ ለቃለ መጠይቅ ግብዣ ቢቀርብለዎት እና ስለፓርቲዎ ዓላማ እና እንቅስቃሴ ወይም ስለጠቅላላ አገራዊ ጉዳይ አስተያየት እንዲሰጡ ቢጠየቁ ለቃለ መጠይቁ የሚያደርጉ ዝግጅት እንዴት ያለ ነው?

በርካታ የፖለቲካ ፓርቲዎች ባሉበት እና በከፍተኛ ፉክክር በተሞላበት የኢትዮጵያ ፖለቲካ ምህዳር ውስጥ የመገናኛ ብዙኃን ቃለ-መጠይቆች ተራ ውይይቶች ብቻ አይደሉም። የመገናኛ ብዙኃን ቃለ መጠይቆች የፓርቲን መልዕክቶች ለማስተላለፍ፣ ፓርቲው ያለውን አቅም ለሕዝብ ለማሳየት፣ የፓርቲውን ገጽታ ለመገንባት እና የሕዝብን አስተያየት ለመቅረጽ ወርቃማ ዕድሎች ናቸው። ሆኖም ግን ሁሉም ጋዜጠኛ እርስዎ የፈለጉትን ብቻ ተናግረው እንዲሄዱ አፈቅድም። አንዳንድ የመገናኛ ብዙኃን ፕሮግራም ቅርጽ ሞጋች ሆነው የተቀረጹ በመሆናቸው እርስዎ ከሚናገሩትና ከሚያስተጋቡት መልዕክት በተቃራኒ ያሉ ሃሳቦች እና መረጃዎችን አቅርቦ ፈተና ሊጋርጥ ይችላል። አንዳንድ ጋዜጠኛች ደግሞ ጠንካራ ክርክር (hardtalk) የሆነ አቀራረብ ስለሚመርጡ ይዘውት የሚመጡት ጥያቄ ፈታኝ ይሆናል። ይህን መሰል ሙግቶችን ለመጋፈጥ ስልታዊ ዝግጅትን ይጠይቃል። ፖለቲከኞች ለሚናገሩትና ለሚሰጡት አስተያየት የሚሰጠው ትኩረት ከፍተኛ በመሆኑ ፓርቲዎች ለቃለምልልስ የሚያበቃ ዝግጅት እንዲኖራቸው ይመከራል። ከነዚህ ዝግጅቶች አንዱ የፓርቲ መሪዎች እና ቃል አቀባዮች የመገናኛ ብዙኃን ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነት በተመለከተ የክህሎት ሥልጠና ቢወስዱ ጠቃሚ እንደሆነ በባለሞያዎች ይመከራል።

4.2.1. የሚዲያ ስልጠና አስፈላጊነት

የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎችና ቃል አቀባዮች **የሚዲያ ስልጠና** ማግኘታቸው እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው። ተገቢ ዝግጅት ሳይደረግ ከጋዜጠኞች ጋር መገናኘት ከፍተኛ ስጋት አለው። አልፎ አልፎ እንደሚታየው፣ አንዳንድ የፓርቲ መሪዎች ለቃለ ምልልስ ሚዲያ ላይ ሲቀርቡ፣ የሚናገሩት ጠፍቷቸው ወይም ምን መናገር እንዳለባቸው ግራ ገብቷቸው ሲደናገሩ ይታያል። በሌላ ጊዜ ደግሞ አላስፈላጊ ክርክር ውስጥ ገብተው የፓርቲያቸውን ክብር ሊያጎድፍ በሚችል “ትርፍ” ንግግር ሲናገሩ ይስተዋላል።

ሚዲያ ላይ ለቃለ ምልልስ መቅረብ ራስንና ፓርቲን ለሕዝብ ፍርድ ማቅረብ ነው። አንዳንድ ጊዜ ሙገሳሲያስገኝ፣ በሌላ ጊዜ ደግሞ ትችትና ውግዘት ሊያስከትል ይችላል። በመሆኑም፣ ወደ ሚዲያ መቅረብ የሚፈጥረው ውጥረት የሚጠበቅ ነው። ልምድ ያላቸው ፖለቲከኞች እንኳን በጭንቀት ውስጥ ሆነው ሊሳሳቱ ይችላሉ። ይህ ደግሞ የተሳሳተ መረጃ እንዲሰጡ፣ ከመልዕክት ውጪ የሆነ ንግግር ሊያደርጋቸው ይችላል። በተለይ በማኅበራዊ ሚዲያ ስላቅና ትችት በሞላበት ዓለም ውስጥ የፖለቲካ መሪዎች ንግግር ወይም መጠነኛ የአነጋገር ስህተት ከአውድ ውጪ እየተወሰደ በአሉታዊ መንገድ ሲተረጎም ይስተዋላል። ይህን መሰሉን ችግር ለመከላከል የሚዲያ ስልጠና ወሳኝ መፍትሔ ነው።

የሚዲያ ስልጠና የፖለቲካ መሪዎችን ሚዲያ ላይ ሲቀርቡ ረጋ ብለው እንዲናገሩ፣ ስሜታዊ የሚያደርግ ጉዳይ እንኳን ቢከሰት ስሜታቸውን ተቆጣጥረው እንዲቆዩ፣ ቁልፍ መልዕክቶችን በግልጽ እንዲያስተላልፉ እና አስቸጋሪና ቀጥተኛ ጥያቄዎችን በልበ ሙሉነት እንዲቋቋሙ ያስችላቸዋል። በአግባቡ የተዋቀረ የስልጠና ፕሮግራም የሚከተሉትን ያስተምራል፦

ወደ ዋና ነጥቦች "መመለስ"	በጋዜጠኞች ወይም ቃለ መጠይቅ አድራጊዎች ሆን ተበለው የሚነሱ አስቸጋሪ ጥያቄን አምኖ መቀበል እና ብልሀት በተሞላው መንገድ ወደ ፓርቲው ማዕከላዊ አጀንዳና መልዕክቶች መመለስ። በዚህም ጉንጫ አልፋ ከሆኑ ሙግቶችና ስሜታዊ ከሚያደርጉ ክርክሮች እራስን ጠብቆ ሚዲያ ላይ የቀረቡበትን ዓላማ ለማሳካት በጥበብ ጥረት ማድረግን ያካትታል።
የተለመዱ ስህተቶችን ማስወገድ	ጋዜጠኞች ለማሳሳት ወይም “ማኖ ለማስነካት” የሚዘረጉትን ወጥመዶችን ለይቶ ማወቅና ማስወገድን መማር፣ ለምሳሌ በግምት ላይ የተመሰረቱ ጥያቄዎችን መመለስ፣ "ከቀረፃ ውጪ" ("off the record") መናገር ወይም በስሜት ተነሳስቶ ምላሽ መስጠት የመሳሰሉትን እንዴት መካላከልና ማስቀረት እንደሚቻል።
የአቀራረብ ዘይቤን ማስተካከል	በቃለም መጠይቅ ጊዜ ምላሽ የሚሰጡበት ድምጸት እና ይዘት ለተለያዩ ታዳሚዎችና የቃለ መጠይቅ አይነቶች መለያየት ስላለበት በዛ መልኩ እንዴት ምላሽን ማዘጋጀት እንደሚቻል ማወቅ። ለምሳሌ ለኢትዮጵያ ቴሌቪዥን (ኢቢሲ)፣ በአካባቢው ኤፍኤም ወይም የማህብረሰብ ሬዲዮ ፕሮግራም፣ በጋዜጣ ቃለ መጠይቅ ወይም በማኅበራዊ ሚዲያ የቀጥታ ጥያቄና መልስ ላይ ምላሽ የሚሰጡበት ዘይቤ እንዴት መሆን እንዳለበት።

4.2.2. በቀጣይ በሚዲያ ሲቀርቡ እንዴት ስኬታማ መሆን ይችላሉ?

በየትኛውም የመገናኛ ብዙኃን መድረክ በቃለ-መጠይቆች ስኬታማ መሆን በአጋጣሚ የሚመጣ አይደለም። የተሟላ ዝግጅት አቀራረብ ውጤት ነው። በዚህ የመመሪያ መጽሐፍ የፖለቲካ ፓርቲዎችና መሪዎች ለማንኛውም የሚዲያ ተሳትፎ እንዴት መዘጋጀትና ስኬታማ መሆን እንደሚችሉ ደረጃ በደረጃ የሚያሳይ ምክር ይሰጣል። ይህም መልዕክትዎ በግልጽና በውጤታማነት መደመጡን ያረጋግጣል[12]።

ምክር 1: ዓላማዎትንና ዋና መልዕክትዎን ይረዱ

አንድ የፓርቲ መሪ ወይም ቃል አቀባይ ለሚዲያ ቃለ-መጠይቅ ከመስማማቱ በፊት ለፓርቲው ተወካይ የመጀመሪያውና ወሳኝ የሆነው እርምጃ ፓርቲው በሚዲያ ሲቀርብ ምን ማሳካት እንደሚፈልግ በግልጽ ማወቅ ነው። ቃለ-መጠይቅ ዝም ብሎ ውይይት ብቻ አይደለም፤ ስልታዊ የመገናኛ መሳሪያ ነው። ለቃለ-መጠይቅ ከመቅረብዎ አስቀድመው የሚከተሉትን ጉዳዮች ያስቡባቸው።

ግልጽ አላማ ይያዙ	በሚዲያ ቀርበው ቃለ-መጠይቅ የሚሰጡበት ዓላማዎ ምንድን ነው? አዲስ ፖሊሲን ለማስተዋወቅ? የፓርቲውን አቋም ለማብራራት? ቀውስን ለመቆጣጠር? የተሳሳተ መረጃን ማረም እና ፓርቲዎን መከላከል? ወይስ የፓርቲውን ገጽታ ለማሳደግ? ወደ መገናኛ ብዙኃን የሚቀርቡበት ዓላማ የዝግጅትዎ እና የአቀራረብዎ እያንዳንዱን ገጽታ ይቀርጻል።
ዋና መልዕክቶችዎን ይለዩ	በዓላማዎ መሰረት፣ ምንም ይሁን ምን ማስተላለፍ ያለብዎትን ሁለት ወይም ሦስት ወሳኝ መልዕክቶች የትኞቹ ናቸው? እነዚህ መልዕክቶች ግልጽ፣ በቀላሉ የማይረሱ እና ከኢትዮጵያ መራጮች ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው መሆን አለባቸው (**ለበለጠ መረዳት ምዕራፍ ሦስት ክፍል 3.2 ወደኋላ መለስ በለው ይመልከቱ**)። ለምሳሌ፣ ዓላማዎ ስለ አንድ የመሬት ይዞታ ወይም አጠቃቀም ማሻሻያ ፖሊሲ የተሳሳተ መረጃን መከላከል ከሆነ፣ የእርስዎ ዋና መልዕክቶች ስለ ፖሊሲው ጥቅሞች እና ትክክለኛ ዝርዝሮች ላይ ማተኮር አለባቸው እንጂ ስለ ክሱ ራሱ መሆን የለበትም።
ትክክለኛውን ታዳሚ ይምረጡ	የሚዲያ ተቋሙ የሚደርስባቸውን ሰዎች ግምት ውስጥ ያስገቡ። ብሔራዊ ታዳሚ ያለው የመንግሥት የቴሌቪዥን ጣቢያ (ለምሳሌ ኢቢሲ) ነው ወይስ የአካባቢ ማኅበረሰብ ሬዲዮ ጣቢያ ወይም ልዩ ፍላጎት ያለው ማህበራዊ ሚዲያ? የሚሰጡትን ቃለ-መጠይቅ ተፅዕኖዎን ከፍ ለማድረግ ዓላማዎ ከሚዲያው ታዳሚ ጋር መጣጣም አለበት።

ሳጥን 4.10፡ የሚዲያ ቃለ-መጠይቅ ምሳሌ

ፓርቲዎ በአከባቢያዊ ምርጫ የወጣቶችን ድምፅ ለማግኘት አቅዷል እንበል። በወጣቶች ላይ በሚያተኩር ተወዳጅ የኦንላይን ማኅበራዊ ሚዲያ መድረክ ላይ ለቃለ-መጠይቅ ተጋብዘዋል። የእርስዎ ዓላማ በወጣቶች ሥራ አጥነት ጉዳይ ላይ የፓርቲዎን የያዘውን አቋም እና ታማኝነት ማረጋገጥ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ፣ ዋና መልዕክቶችዎ: "ፓርቲያችን ለሥራ ፈጠራ ግልጽና ተግባራዊ የሆነ ዕቅድ አለው" እና "በወጣቶች የሙያ ሥልጠና ላይ ኢንቨስት ለማድረግ ቁርጠኛ ነን" የሚሉ ይሆናሉ። ይህ ግልጽ ዓላማ እና የመልዕክቶች ስብስብ ለእያንዳንዱ ምላሽዎ መመሪያ በመሆን ትኩረት እንዲያደርጉ እና ስልታዊ የፖለቲካ ግቦችዎን እንዲያሳኩ ያግዝዎታል።

ምክር 2: የመገናኛ ብዙኃን ተተቋማት እና ጋዜጠኞችን መመርመር

በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁኔታ ውስጥ ይህ ምክር ለዝግጅት ብቻ አይደለም። ይልቁንም፣ የመገናኛ ብዙኃንን እና ቃለ መጠይቅ ሊሰጡት ያሰቡትን ጋዜጠኛ ማንነት፣ አቀራረብና ባህሪ መመርመር **ስትራቴጂያዊ የመገናኛ ብዙኃን አጠቃቀም** ወሳኝ አካል ነው። ስለመገናኛ ብዙኃኑ ተቋምና ጋዜጠኛው ከሚታወቀው ግንዛቤ ባሻገር ዘልቀው በመግባት የኢትዮጵያን የመገናኛ ብዙኃን ልዩ ባህሪያት በጥልቀት ማጥናት ይገባል።

የተቋሙን አቋም ይወቁ	ቃለ መጠይቅ ሊሰጡት ያሰቡትን ተቋም አቋምና ያለውን ልዩ አዝማሚያ ማወቅ ያስፈልጋል። በየኢትዮጵያ የመንግሥት እና የግል የመገናኛ ብዙኃን ብዙውን ጊዜ የተለየ የአርትዖት መስመር ወይም የፖለቲካ ዝምድና አላቸው። ተቋሙ በመንግሥት ደጋፊ፣ ከተቃዋሚ ፓርቲ ጋር የተሰለፈ ወይም ገለልተኛ አቋም ለመያዝ የሚሞክር መሆኑን መረዳት አለብዎት። ለምሳሌ፣ እንደ ኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን (ኢቢሲ) ወይም ፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት (ኤፍቢሲ) ያሉ የመንግሥት የመገናኛ ብዙኃን ስለ ልማት እና አገራዊ አንድነት ትረካዎች ላይ የበለጠ ትኩረት ሊያደርጉ ይችላሉ። በተቃራኒው፣ ሌሎች የግል ጣቢያዎች ስለ አስተዳደር እና ተጠያቂነት ወሳኝ ጥያቄዎችን ለመጠየቅ የበለጠ ሊያዘነብሉ ይችላሉ። የእርስዎ አቀራረብ እና መልዕክት በዚህ መሠረት መዘጋጀት አለበት።
የጋዜጠኛውን ዘይቤ ይመርምሩ	ቃለ መጠይቁን የሚሰጡት ማን ለተባለ ጋዜጠኛ ነው? በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ጋዜጠኞች ብዙውን ጊዜ በፖለቲካ፣ በንግድ ወይም በሰብአዊ መብቶች ጉዳዮች ላይ ልዩ ሙያ አላቸው። ስለ ጋዜጠኛው ያለፉ ሥራዎች ለማወቅ ጊዜ ይስጡና ይመርምሩ። ባለፉት ጊዜያት ፓርቲዎን ተችተዋል? አስቸጋሪ እና ተከታይ ጥያቄዎችን የመጠየቅ ዝንባሌ አላቸው? በምርመራ ጋዜጤኝነት ላይ የተመሰረተ አቀራረባቸው ይታወቃል? ዘይቤያቸውን ማወቅዎ ጥያቄዎችን አስቀድመው እንዲገምቱ እና ሐቀኛና የፖለቲካ ብልህነት ያላቸውን ምላሾች እንዲያዘጋጁ ያስችልዎታል። ይህ ማለት ጋዜጠኛውን ለማታለል መሞከር ማለት አይደለም። ይልቁንም ለተወሰኑ ፍላጎቶቻቸውና ጥያቄዎቻቸው በሙያዊና በራስ የመተማመን መንፈስ ለመመለስ ዝግጁ መሆን ማለት ነው።

ሳጥን 4.11፡ መገናኛ ብዙኃንን አስቀድሞ የመመርመር ምሳሌ

የመገናኛ ብዙኃን ተቋሙን እና ታዳሚዎችኑ መመርመር የግድ አስፈላጊ ነው። ተቋሙ የተለያዩ ቋንቋ ተነጋሪዎች ያለው ተመልካች ያለው ብሔራዊ የቴሌቪዥን ጣቢያ ነው ወይስ በተወሰነ ቋንቋ የሚያሰራጭ የክልል ሬዲዮ ጣቢያ ነው?

1. በኢቢሲ ወይም በፋና ቲቪ ፕሮግራም ላይ የሚደረግ ቃለ-መጠይቅ የከተማና የገጠር ድምፅ ሰጪዎችን ጨምሮ ሰፊ ብሔራዊ ታዳሚ ሊደርስ ይችላል። መልሶችዎ ከሁሉም የሕብረተሰብ ክፍሎች ካሉ ሰዎች ጋር እንዲስማማ ግልጽና ቀላል መሆን አለበት፣ የባለሙያ ቃላትን ማስቀረት ይመከራል።

2. በአዲስ አበባ የሚገኘው ሸገር ኤፍኤም ሬዲዮ ጣቢያ ላይ የሚናገሩ ከሆነ በከተማ ለሚኖሩ እና በፖለቲካው ውስጥ ለሚሳተፉ ታዳሚዎች የታወቀ ስለሆነ፣ ከፍተኛ የፖለቲካ ግንዛቤ እንዳላቸው መገመት ይችላሉ። መልሶችዎ የበለጠ ዝርዝር ሊሆኑ እና የዚያን ከተማ ነዋሪዎች ልዩ ፍላጎቶች ሊያሳዩ ይችላሉ።

ምክር 3፡ ዋና የፖለቲካ መልዕክቶችዎን ማዘጋጀት

ብዙውን ጊዜ ውጥረትና ፍረጃ በሚበዛበት የኢትዮጵያ የፖለቲካ ባህል ውስጥ የሚዲያ ቃለ-መጠይቆች ለተለያዩ ሐሳቦች የሙግት መድረክ ሊሆኑ ይችላሉ። ስኬታማ ለመሆን አንድ የፖለቲካ ፓርቲ **ለክስተቶች ምላሽ ሰጪ ብቻ መሆን የለበትም**። ይልቁንም፣ ስልታዊ መሆንና ዋና መልዕክቶቹን የማዘጋጀትና የማስተላለፍ ጥበብን መላበስአለበት። የፓርቲዎን የፖለቲካ ዓላማ መሠረት በማድረግ፣ በእያንዳንዱ ቃለ-መጠይቅ ወቅት ማስተላለፍ ያለብዎትን **ከ2 እስከ 3 ዋና መልዕክቶች ይለዩ**። እነዚህ መልዕክቶች የሚከተሉትን መመዘኛዎች ማሟላት አለባቸው፦

ግልጽ እና አጭር	በገጠር ከሚኖረው አርሶ እና አርብቶ አደሩ ገበሬ አንስቶ እስከ ከተማ ነዋሪው ምሁር ያሉ የተለያዩ ታዳሚዎች በቀላሉ የሚረዷቸውና የሚያስታውሷቸው መሆን አለባቸው።
በድርጊት ላይ ያተኮሩ	ፓርቲዎ በሚያምንበት ነገር ላይ ብቻ ሳይሆን በሚያደርገው ነገር ላይም ትኩረት የሚያደርጉ መሆን አለባቸው።
ለሕዝብ ተደራሽ	የኢትዮጵያ መራጮች በእውነት የሚጨነቁባቸውን ችግሮችና የሚፈልጓቸውን ጉዳዮች በቀጥታ የሚመልሱ መሆን አለባቸው።

እነዚህን ዋና ዋና ነጥቦች በመልሶቹ ውስጥ በተፈጥሮአዊ መንገድ ለማካተት ይለማመዱ። ይህ ዘዴ አንድ ጋዜጠኛ ጥያቄውን በፈለገው መንገድ ለመቅረጽ ቢሞክርም እንኳ ውይይቱን ወደ ፓርቲዎ አጀንዳ እንዲመልሱ ያግዝዎታል። ይህ ዘዴ በተለይ በኢትዮጵያ ወሳኝ ነው። ምክንያቱም አንዳንድ ጊዜ የጋዜጠኞች ጥያቄዎች በብሔር ወይም በፖለቲካ ተቀናቃኝነት ስሜት ሊመሩ ስለሚችሉ ነው። ስለዚህ ፓርቲዎ የራሱን ትርክት መቆጣጠር መቻሉ አስፈላጊ ነው።

ሳጥን 4.12፡ የዋና መልዕክቶች ምሳሌ

የፓርቲዎ ዓላማ የሀገሪቱን ኢኮኖሚያዊ ችግሮች መፍታት ከሆነ፣ ቁልፍ መልዕክቶችዎ የሚከተሉት ሊሆኑ ይችላሉ፦

- "የእኛ ኢኮኖሚያዊ ዕቅድ በግብርናና በቴክኖሎጂ ባሉ ቁልፍ ዘርፎች ላይ ኢንቨስት በማድረግ ወጣቶችን ያበረታታል እንዲሁም የሥራ ዕድል ይፈጥራል።" ይህ በቀጥታ የወጣቶች ሥራ አጥነትን ወሳኝ ጉዳይ ይፈታል።
- "የሕዝብ ሀብት ብከነትን ለመከላከል ሙስናን እንዋጋለን። እንዲሁም የሕዝብ ሀብቶች መሠረተ ልማቶችን ለመገንባትና ለሁሉም ኢትዮጵያውያን አስፈላጊ አገልግሎቶችን ለመስጠት ጥቅም ላይ መዋላቸውን እናረጋግጣለን።" ይህ ደግሞ ሕዝቡ በብቃት ማነስና በተጠያቂነት እጦት ያለበትን ብስጭት ይዳስሳል።

ምክር 4፡ አስቸጋሪ ጥያቄዎችን አስቀድሞ መገመትና መዘጋጀት

ብዙውን ጊዜ ጋዜጠኞች ፖለቲከኞችን ሲያገኙ አስቸጋሪና አሳሳቢ ጥያቄዎችን የመጠየቅ ልምድ አላቸው። ስለዚህ እርስዎም ለተለያዩ አስቸጋሪ ወይም ምቾት ለሚነሱ ርዕሰ ጉዳዮች መዘጋጀት ይኖርብዎታል። የፖለቲካ ፓርቲ ተወካይ እንደመሆንዎ መጠን ሊነሱ የሚችሉ ትችቶችን እና አወዛጋቢ ጉዳዮችን በጥንቃቄ ማሰብ እና ግልጽ፣ ሐቀኛምላሾችን ማዘጋጀት አለብዎት።

ምክር 5: ተረኮችንና ምሳሌዎችን ይጠቀሙ

እውነታዎች ይረሳሉ። ታሪኮች ግን ይደጋገማሉ። በፖለቲካ ጉዳዮች ላይ የተለያዩና ሰፊ የልምዶች ልዩነት ያላቸው ዜጎች ባሉበት የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁኔታ ውስጥ ለሕዝብ ልብ ቅርብ የሆኑ ተረኮች ከእውነታዎችና አሃዞች ዝርዝር የበለጠ የማይረሱና አሳማኝ ናቸው። እንደ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ስታቲስቲክስ ወይም ዝርዝር ስልታዊ ዕቅዶች ባሉ ምክንያታዊ ክርክሮች ላይ ብቻ መተማመን ማራኪ ቢመስልም የበለጠ ውጤታማ አቀራረብ ነጥቦቻችሁን ተዛማጅና ዘላቂ ለማድረግ ታሪክን፣ ምሳሌንና ተረኮችን መጠቀም ነው።

ሳጥን 4.14፡ በሚዲያ ተረኮችን የመናገር ምሳሌ፦

ስለ ፓርቲዎ የእርሻ ልማት ዕቅድ እየተወያዩ እንደሆነ ያስቡ። "የእኛ ዕቅድ የሰብል ምርትን በ15% ይጨምራል እንዲሁም የወጪ ንግድ ገቢን 20% ያሻሽላል" ብለው ብቻ ከማለት ይልቅ፣ ታሪክ መናገር ይችላሉ፦

"በቅርቡ በነበረን የመስክ ጉብኝት በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ አርሲ ዞን ውስጥ በአንድ ትንሽ መንደር ውስጥ ፋጡማ የምትባል ወጣትና ጎበዝ አርሶ አደር አገኘሁ። ከአባቷ ትንሽ መሬት ወርሳለች። የግብርና ምርቷን ለማሳደግና ለማሻሻል ከፍተኛ ምኞት አላት። ነገር ግን አሁንም ባህላዊና ጥንታዊውን የአስተራረስ ዘዴዎች ስለምትጠቀም እና የገበያ ትስስር እጥረት ስላጋጠማት የግብርና ሥራዋን ትርፋማ ለማድረግ ብትታገልም እንዳሰበችው አልተሳካላትም። የፓርቲያችን ዕቅድ ስለ ቁጥሮች ብቻ አይደለም። የኢኮኖሚ እድገትን የምንለካው በሰዎች ጎጆና ኪስ ውስጥ በሚታይ ተጨባጭ አውንታዊ ለውጥ ነው። ስለ ፋጡማ እና እንደ እርሷ ለሚታትሩ ሚሊዮን የአገራችን ወጣቶች፣ አርሶ አደሮች፣ አርብቶ አደሮች እና የከተማ ሰርቶ አደሮች ጭምር ነው። እሷንና እንደ እሷ ያሉ በሚሊዮኖዎች የሚቆጠሩ ገበሬዎችን ዘመናዊ መስኖ እና ብዙ ምርት የሚሰጡ ዘሮችን እንዲያገኙ እናደርጋለን። ዕቅዳችን በተጨማሪም ምርቷን በተመጣጣኝ ዋጋ መሸጥ እንድትችል ከኅብረት ሥራ ማኅበር ጋር ያገናኛታል። ይህ ስለ ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲ ብቻ አይደለም፤ ፋጡማ ለቤተሰቧ የተሻለ ሕይወት እንድትገነባ በማስቻል፣ የሀገራችንን የወደፊት ዕጣ ፈንታ ማጠናከር ነው።"

ስለ ፋጡማ የሚናገረው ይህ ታሪክ የተወሳሰበ ፖሊሲን ወደ ተዛማጅ የሰው ልምድ ይለውጠዋል። የፓርቲዎ ዕቅድ ጥቅሞች ግልጽ እና ስሜትን የሚነኩ እንዲሆኑ ያደርጋል፣ ይህም ከማንኛውም ቁጥራዊ መረጃ የበለጠ በድምፅ ሰጪዎች የመታወስና የመደጋገም ዕድሉ ከፍተኛ ነው።

ምክር 6፡ ይለማመዱ፣ ግን አይሸምድዱ

ኮስተር ያሉ የፖለቲካ ጉዳዮች የሚነሱባቸው የመገናኛ ብዙኃን ቃለ-መጠይቆች አስቸጋሪና ያልተጠበቁ ሊሆኑ ይችላሉ። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ተፈጥሯዊና እውነተኛ መሆን ከሕዝብ ጋር መተማመንን ለመገንባት ወሳኝ ነው። ዝግጅት አስፈላጊ ቢሆንም ቅንነት የጎደለው መስሎ መታየትን ማስወገድ ወሳኝ ነው። ይህን መሰሉን አቀራርብ ለማስቀረትቃለ-መጠይቆች ልምምዶችን አስቀድሞ ማድረግ ጠቃሚ ይሆናል።

የተግባር ቃለ-መጠይቆችን (Mock Interviews) ያካሂዱ	ለመዘጋጀት ምርጡ መንገድ ከሥራ ባልደረባ ወይም ከሙያተኛ የሚዲያ አሰልጣኝ ጋር የተግባር ቃለ-መጠይቆችን መለማመድ ነው። የሚጠበቁ፣ ፈታኝና ጠበኛ የሆኑ ጥያቄዎችን እንዲጠይቁ ያድርጉ። ይህ ቁልፍ መልእክቶችዎን ለማጥራት፣ የአነጋገር ዘይቤዎን ለመለማመድ እና አስቀድሞ በተዘጋጀ ጽሑፍ ላይ ሳይመሰረቱ ፈጣን ምላሽ የመስጠት ችሎታዎን ለማሻሻል ይረዳል።
በጹሑፍ በተያዘ ማስታወሻ ላይ ሳይደገፉ ቁልፍ ነጥቦች ላይ ያተኩሩ	ምላሾችዎን መለማመድ አስፈላጊ ነው፣ ነገር ግን ቃል በቃል ሸምድዶ መያዝ ስህተት ነው። በምትኩ፣ ማስተላለፍ በሚፈልጓቸው ዋና መልእክቶችና ቁልፍ ነጥቦች ላይ አፅንኦት በመስጠት ይለማመዱ። ይህ ባልተጠበቁ ጥያቄዎች ሲገጥሙ እንኳን መልእክትዎን በተፈጥሯዊ እና በውይይት መልክ ለማስተላለፍ ያስችላል።
ውስብስብ ጉዳዮችን ያብራሩ	የኢትዮጵያ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ጉዳዮች ውስብስብ ሊሆኑ ይችላሉ። ታዳሚዎቻችሁን በቴክኒካዊ ቃላት ወይም በፖለቲካዊ ቃላቶች ከመጫን ይቆጠቡ። እንደ የፊስካል ፖሊሲ ወይም የሕገ-መንግሥት ማሻሻያ ባሉ ውስብስብ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የፓርቲዎ አቋም አማካይ ዜጋ ሊረዳው በሚችል ግልጽ፣ ቀላልና ተዛማጅ ቋንቋ እንዲተረጎም ለማስቻል ከቃለ-መጠይቁ አስቀድመው እራስዎን ያሠለጥኑ።

ሳጥን 4.15፡ ለሚዲያ ቃለ-መጠይቅ የሚደረግ ልምምድ ምሳሌ፡

ስለ ፓርቲዎ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ዕቅድ በቴሌቪዥን ቃለ-መጠይቅ ለመቅረብ እየተዘጋጁ እንደሆነ ያስቡ። ዝርዝር የኢኮኖሚ አሃዞች ያለበትን ጽሑፍ በቃላችሁ ከመያዝ ይልቅ፣ ባልደረባዎ የሚከተሉትን የመሳሰሉ የተለያዩ ጥያቄዎችን በሚጠይቅበት የተግባር ቃለ-መጠይቅ ይለማመዱ፦

- "የኑሮ ውድነትን ለመዋጋት የፓርቲዎ ዕቅድ ምንድን ነው?"
- "ተቺዎች የፓርቲዎ የኢኮኖሚ ዕቅድ ከእውነታ የራቀ ነው ይላሉ። ምላሽዎ ምንድን ነው?"
- "ያቀረቧቸው ማሻሻያዎች በሰፊው የኢትዮጵያ ዜጋ ሕይወት ላይ ምን አይነት ተጨባጭ ተጽዕኖ ይኖራቸዋል?"

በእነዚህና መሰል ጥያቄዎች ላይ የተግባር ልምምዶች ማድረግ ቀጠትኛ መለስ ለመስጠት ለምሳሌ እንደ "በአነስተኛ ንግዶች ላይ ኢንቨስት ማድረግ፣" "ለወጣቶች የሥራ ዕድል መፍጠር፣" እና "የዋጋ ግሽበትን መቀነስ" የመሳሰሉ ቁልፍ ነጥቦችዎን በተፈጥሯዊና በራስ መተማመን ስሜት ለማቅረብ ያስቻላሉ። ይህ ልምምድ ጠያቂው ውይይቱን ወደ ሌላ አቅጣጫ ለመምራት በሚሞክርበት ጊዜም እንኳ በመልእክትዎ ላይ እንዲቆዩ ይረዳዎታል።

ምክር 7: የሰውነት ቋንቋዎን እና የድምጽ ድምጸት **ይቆጣጠሩ**

በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁኔታ የሚዲያ ቃለ-መጠይቆች በብሔራዊ ቴሌቪዥን እና ራዲዮ ወይም በምስል በሚታዩ ማኅበራዊ ሚዲያ (ለምሳሌ ዩቱዩብ) ላይ ሊተላለፉ በሚችሉበት ጊዜ፣ የቃል ያልሆነ የሰውነት ቋንቋ እና ድምጸት ልክ እንደ ቃላቶችዎ ወሳኝ ናቸው። የሰውነት ቋንቋዎ ከአለባበስ፣ የጸጉር አሰራር ወይም አቆራረጥ አንስቶ የፊት ገጽታዎ እና የድምጽ መልዕክትዎ በተለያዩ ታዳሚዎች ዘንድ እንዴት እንደሚቀበሉት አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። ድምፅ ሰጪዎች ብዙውን ጊዜ የመሪን ተአማኒነትና ቅንነት የሚገመግሙት በእነዚህ ምልክቶች ላይም በመመሥረት ነው።

ለቴሌቪዥን ቃለ-መጠይቆች	በማንኛውም በቪድዮ በመቀርጽ ቃለ-መጠይቅ ላይ ከአለባበስ አንስቶ የገጽታዎ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው። ዘና ያለ ሆኖም ቀጥ ያለ አቋም በመያዝ፣ ከቃለ-መጠይቅ አድራጊው ጋር ቀጥተኛ የዓይን ግንኙነት ያድርጉ። ይህ በራስ መተማመንና ሐቀኝነትን ያሳያል። እያዳመጡና እየተሳተፉ መሆንዎን ለማሳየት አልፎ አልፎ አንገትዎንያንቀሳቅሱ። እጆችዎን አለማጣመር ይመከራል። ምክንያቱም እጅ ማጣመር ራስን የመከላከል ወይም የተዘጋ አቋም ሊመስል ይችላል። እንዲሁም መንቀጥቀጥን ያስወግዱ። መቁነጥነጥ በተመልካች ዘንድ የፍርሃት ወይም ዝግጁ ያለመሆን ስሜት ሊፈጥር ይችላል። በቴሌቪዥን ቃለ-መጠይቅ ላይ የተረጋጋ፣ ጥንካሬንና ቁርጠኝነትን የሚያሳይ የሰውነት ቋንቋ ማሳየት ያስተላልፋል። እነዚህም በመሪነት ውስጥ በጣም የሚፈለጉ ባሕርያት ናቸው።
ለራዲዮና ፖድካስት ቃለ-መጠይቆች	በድምጽ ለሚተላለፉ ቃለ-መጠይቆች ድምጽዎ ዋነኛው ትኩረት ስለሆነ፣ የድምጽዎ ቃናና አቀራረብ የበለጠ አስፈላጊ ይሆናል። የሰዎችን ቀልብ ለመሳብ፣ ጉጉትና ርህራሄን ለማሳየት ድምጽዎን እንዴት እንደሚጠቀሙበት ይለማመዱ። ጠፍጣፋ ወይም ነጠላ በሆነ ድምጽ አወጣጥ (a flat or monotonous voice) ከመናገር ይቆጠቡ። ምክንያቱም ይህ አይነት አነጋገር አድማጮች ፍላጎታቸውን እንዲያጡና ቅንነት የጎደለው ሰው እንዲመስሉ ሊያደርግ ይችላል። በተመሳሳይ ድምጸት የሚነገር ነገርም መሰልቸትን ሊጋብዝ ይችላል። የፓርቲዎን ራዕይ በሚወያዩበት ጊዜ ስሜትን ለመግለጽ እና ከባድ ሀገራዊ ጉዳይን በሚመለከቱበት ጊዜ ጽኑነትን ለማሳየት ድምጽዎን ጎላ በማድረና አጽኖት ሰቶ ረገጥ አርጎ በመናገር ትኩረት ይሳቡ። ጠንካራ፣ ግልጽ እና በራስ የመተማመን ስሜት ያለው ድምጽ በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነትን እና መተማመንን ይገነባል።

የሰውነት ቋንቋዎን እና የድምጽ ቅላጼውን በመቆጣጠር የቃል ያልሆነ ግንኙነትዎ የፓርቲዎን መልዕክት እንደሚያጠናክር ማረጋገጥ ይችላሉ።

ምክር 8: ከዋናው መልዕክት ላለመውጣት መሸጋገርያ የመፍጠር ዘዴዎችን (Bridging Techniques) ይጠቀሙ

በሙግት በሚበዛባቸውና አወዛጋቢ በሆኑ የፖለቲካ ጉዳዮች ላይ በሚደረጉ የብዙኃን መገናኛ ቃለ-መጠይቆች፣ በቀላሉ ከፓርቲዎ ዋና አጀንዳ ወጥተው ትኩረት ወደሚበትኑ ወይም አግባብነት ወደሌላቸው ርዕሶች ሊያመሩ ይችላሉ። ይህ ሁኔታ ሲያጋጥም፣ **“መሸጋገሪያ”)** የሚባል ዘዴን መጠቀም ይቻላል። ይህ ዘዴ አንድን ጥያቄ እየተቀበሉ ውይይቱን ወደሚፈልጉት ዋና መልዕክትዎ በተረጋጋ ሁኔታ ለመመለስ የሚያስችል ወሳኝ ስልት ነው። በዚህም እያንዳንዱን የአየር ሰዓት ፓርቲዎ ዕቅዱን ለማስተዋወቅና ከታለመለት ታዳሚ ጋር ለመገናኘት እንዲጠቀምበት ያግዛል።

የመሸጋገሪያ ዘዴ ዋና ዓላማ መልስን ማምለጥ ወይም ትብብር የሌለው ሰው መስሎ መታየት አይደለም። ይልቁንም፣ ጥያቄውን በመቀበል፣ መሸጋገሪያ ሐረግ በመጠቀም፣ ከዚያም ውይይቱን ለፓርቲዎና ለሕዝቡ እጅግ በጣም አስፈላጊ ወደሆኑ ርዕሶች በመመለስ ስልታዊና ሥነ ምግባር ያለው ሰው መሆንን ያሳያል።

ምክር 9: እምነት ለመገንባት ሐቀኛ እና እውነተኛ ይሁኑ

መራጮች ብዙውን ጊዜ ተጠራጣሪና ለፖለቲካዊ ተስፋዎች ጥንቃቄ የሚያደርጉ በመሆናቸው የአንድ የፖለቲካ ፓርቲ ተአማኒነት በጣም ጠቃሚ ነው። ታዳሚዎች በተለይም ጋዜጠኞች ቅንነት የጎደለውና ጥያቄ የማምለጥ ባህሪን በፍጥነት ያውቁታል። ጋዘጤኞች እራሳቸውን ዝነኛ ለማድረግ እና “ትንታግ” ለማስባል ስለሚፈልጉ ነጥብ ለማስጣል ጥረት ያደርጋሉ። ስለዚህ ለፖለቲከኛ ስህተትን፣ ጉድለትን ወይም ውስብስብ እውነትን ማመን ማለት ቢሆንም እንኳ ሁልጊዜ ሐቀኛ መሆን ወሳኝ ነው። ይህ አቀራረብ ፓርቲዎን ከሌሎች የተለየ እንዲሆንና ከሕዝብ ጋር ጠንካራና እውነተኛ ግንኙነት እንዲፈጥር ሊያደርግ ይችላል።

በቃለ-መጠይቁ ወቅት መረጋጋትዎን ይጠብቁ። የተሳሳተ ግምት ወይም አስቸጋሪ የጥያቄ መስመር ከገጠመዎት፣ በጥልቀት ይተንፍሱ፣ እና ውይይቱን በዘዴ ወደ ዋና ዋና ነጥቦችዎ ይመልሱ። ያስታውሱ፣ ውጤታማ ቃለ-መጠይቅ ብዙ በመናገር ላይ የተመሰረተ አይደለም። ዋናው መልእክትዎን በሐቀኝነትና በብቃት ማስተላለፍ ላይ ነው።

ሳጥን 4.17፡ ምሳሌ፡-

አንድ ጋዜጠኛ ፓርቲዎ ስለገጠመው የቅርብ ጊዜ የፖሊሲ ውድቀት ወይም የሕዝብ ግንኙነት ችግር እንደጠየቀዎት ያስቡ። ተጠያቂነትን ከመካድ ወይም ሰበብ ከመደርደር ይልቅ፣ ችግሩን በስልታዊና ወደፊት በሚያይ ምላሽ አምኖ መቀበል ይችላሉ፡-

ጋዜጠኛ፡- "የፓርቲዎ የወጣቶች በፓርቲ ውስጥ የማብቃት ፕሮግራም ከስድስት ወር በፊት ቢጀመርም ግቦቹን ማሳካት ባለመቻሉ ከወጣት የፓርቲ አባላቱና ደጋፊዎቹ ትችት ቀርቦበታል። ለምን አልተሳካም?"

የፓርቲ መሪ፡- "የፕሮግራሙ የመጀመሪያ ትግበራ ከፍተኛ ችግሮች እንዳጋጠሙት እና የመጀመሪያ ግቦቻችንን እንዳላሳካን እናምናለን። በመጀመሪያው ዕቅዳችን ላይ ስህተቶችን ሠርተናል። እናም ሙሉ ኃላፊነቱን እንወስዳለን። ሆኖም ከዚያን ጊዜ ወዲህ ከወጣቶችና ከቅርንጫፍ የፓርቲ ጽሕፈት ቤት የፓርቲ መሪዎች የተሰጠውን አስተያየት ሰምተን በርካታ ለውጦችን አድርገናል። ፕሮግራሙን በማዕከል ደረጃ ከመተግበር ይልቅ በአካባቢው ላይ ይበልጥ እንዲያተኩር አሻሽለነዋል። በተጨማሪም የታቀደው ሥራ በፓርቲው አቅም ብቻ የሚተገበር ባለመሆኑ የበለጠ የሙያ ሥልጠና ዕድሎችን ለመስጠት አዳዲስ አጋርነቶችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተነጋግረን የትብብር ስምምነት ላይ ደርሰናል። ከስህተቶቻችን ለመማር እና ይህን ፕሮግራም ለፓርቲያችን ብሎም ለኢትዮጵያ ወጣቶች እውነተኛ ስኬት ለማድረግ ቁርጠኞች ነን።"

ይህ ምላሽ የፓርቲውን የዕቅድ አፈጻጸም ጉድለት በቀጥታ አምኖ ለተነሳው ጥያቄ ይመልሳል። ለተፈጠረው ችግር ኃላፊነት ይወስዳል። ከዚያም ችግሩን ለማስተካከል ፓርቲው ስላደረገው ነገር አዎንታዊ መልእክት ያስተላልፋል። ይህ ተጠያቂነትን እና ቀጣይነት ያለው መሻሻል ቁርጠኝነትን ያሳያል። ይህም መራጮች በአንድ መሪ ላይ ከፍ አድርገው የሚመለከቷቸው ባህሪያት ናቸው።

4.3. የፖለቲካ ፓርቲዎች ማኅበራዊ ሚዲያን የሚጠቀሙበት አግባብ

የማኅበራዊ ሚዲያ አዲሱ የፖለቲካ ፍልሚያ ግንባር ነው ይባላል። ለዚህም ነው ፖለቲካ ፓርቲዎች ማኅበራዊ ሚዲያን በአግባቡ መጠቀም ያለባቸው ስለሆነም ዘላቂ የሆነ የኮሚኒኬሽን ስትራቴጂ መፍጠር አስፈላጊ ነው ። ልክ በዓለም ሀጋራት የፖለቲካ ምህዳር ውስጥ እንድሚታየው ሁሉ በኢትዮጵያም ዲጂታል ቴክኖሎጂ እድገት ያስከተለው ለውጥ በዜጎችና በፖለቲካ መካከል ያለውን ግንኙነት በመሠረታዊነት እየቀየረው ነው። ከባህላዊውና ለዘመናት ከኖረው ከላይ ወደ ታች ይደረግ ከነበረው የመረጃ ፍሰትና የኮሚኔኬሽን ዘዴ (top-down communication model) ወደ ይበልጥ መስተጋብራዊ እና ያልተማከለ ዘዴ (interactive and decentralized) መቀየሩ ለፖለቲካ ፓርቲዎች ታይቶ የማይታወቅ ዕድል እና ትልቅ ፈተና ይዞ መጥቷል። ፓርቲዎች ተፈላጊ እና ምላሽ ሰጪ ሆኖ ለመቀጠል እንዲችሉ ማኅበራዊ ሚዲያን በአግባቡ የመጠቀም ግዴታ ውስጥ ገብተዋል። አንድ ፓርቲ ማኅበራዊ ሚዲያን የምርጫ ዘመቻ መሣሪያ ብቻ ከመቁጠር አልፎ የእለት ተዕለት የኮሚኒኬሽን ሥራዎችን ለማሳለጥ፣ ለውይይትና ለተሳትፎ ቀጣይነት ያለው መድረክ አድርጎ ሊቀበለው ይገባል።

- የእርስዎ ፓርቲ ማኅበራዊ ሚዲያን ምን ያህል ውጤታማ በሆነ መንገድ እየተጠቀመ ነው ብለው ያስባሉ?
- ማኅበራዊ ሚዲያን እንደ ኮሙኒኬሽን መሣሪያ በመጠቀም ምን ዓይነት ዕድሎች አግኝተዋል?
- በማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ረገድ ፓርቲዎ የገጠመው ፈተና አለ ብለው ያምናሉ?

ለብዙ ዘመናት በኢትዮጵያም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ የፖለቲካ ግንኙነት በአብዛኛው የአንድ-መንገድ (one-way traffic) ነበር። ፓርቲዎችና የፖለቲካ መሪዎች መልዕክቶቻቸውን ለማስተላለፍ ባህላዊ ሚዲያዎችን እና የሕዝብ ስብሰባዎችን ይጠቀሙ ነበር።

ይህ አቀራረብ ግን በርካታ ዜጎችን ከፖለቲካ ተወካዮቻቸው ጋር እንዲራራቁ አድርጓቸዋል። ፖለቲከኞች የዕለት ተዕለት ችግሮቻቸውን፣ ለምሳሌ የኑሮ ውድነት፣ የጸጥታ መደፍረስ፣ የትራንስፖርት እጥረት፣ የመሠረተ ልማት መጓደል፣ የሀብት ይገባኛል ግጭት ወይም የትምህርትና ጤና አገልግሎት አሰጣጥ መጓደል የመሳሰሉትን ጉዳዮች ሙሉ በሙሉ እንደማይረዱ እንዲሰማቸው አድርጓል። ይህም በሕዝብና በፖለቲከኞች መካከል ለስሜታዊ መራራቅ አስተዋጽኦ አድርጓል።

የማኅበራዊ ሚዲያ መምጣት ይህንን የፖለቲካ ኮሚኒኬሽን ባህልን በመሠረቱ ለውጦታል። እንደ ቴሌግራም፣ ፌስቡክ፣ ኤክስ (የቀድሞው ትዊተር) እና ቲክ ቶክ ያሉ መድረኮች ዜጎችን ከዝምተኛ አድማጮችነት ወደ ፖለቲካዊ ሂደት ንቁ ተሳታፊነት ቀይረዋቸዋል። የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይም ወጣቶች እና የኢንተርኔት አቅርቦት ባሉባቸው አከባቢዎች ለሚኖሩ የከተማ ነዋሪ ዜጎች እነዚህን መድረኮች ለሚከተሉት ጉዳዮች እየተጠቀሙባቸው ነው[13]፡-

ለፖለቲካ ተሳትፎ	በኦንላይን የሚደረጉ የቀጥታ የፖለቲካ ውይይቶች ላይ መሳተፍ፣ አስተያየቶችን ማጋራት እና በዲጂታል የሚካሄዱ የፖለቲካ ቅስቀሳ መካፈል።
መረጃ ማሰራጨት	ባህላዊ የሚባሉትን የሚዲያ ተቆጣጣሪዎችን በማለፍ ዜናዎችን፣ አስተያየቶችን እና በዜጎች የተፈጠሩ ይዘቶችን በፍጥነት ማጋራት። ብዙ ጊዜ እንደሚታየውም ከተለመዱት የዜና ማሰራጫዎች ቴሌቪዥን፣ ሬድዮ ወይም ጋዜጣ ቀድመው የማኅበራዊ ሚዲያዎች ከጥቃቅን አከባቢያዊ ጉዳዮች አንስቶ እስከትላለቅ ሀጋራዊ ጉዳዮች መረጃ ያሰራጫሉ።

የማኅበራዊ ሚዲያ አዲስ እውነታ ሆኖ መምጣት የፖለቲካ ፓርቲዎች የፕሬስ ኮንፈረንሶችን እና ይፋዊ መግለጫዎችን ለሕዝብ ለማጋራት እንዲችሉ እድል ፈጥሯል። ፓርቲዎች በፖለቲካ እንቅስቃሴያቸው ስኬታማ ለመሆን እና ከሕዝብ ጋር እያደገ የመጣውን የመራራቅ ስሜት ለመፍታት የማኅበራዊ ሚዲያ መድረኮችን መጠቀም አለባቸው። ይህም በምርጫ ጊዜ ብቻ ሳይሆን የፖለቲካ እንቅስቃሴያቸው ቀጣይነት ያለው አካል መሆን አለበት።

4.3.1. የማኅበራዊ ሚድያ፦ እድሎችና አደጋዎች

የማኅበራዊ ሚዲያ መስፋፋት ለኢትዮጵያ የፖለቲካ ምህዳርና ለፖለቲካ ፓርቲዎች ውስብስብ የሆነ ሁኔታን ፈጥሯል። በአንድ በኩል ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎን ለማጠናከር አስደናቂ አቅም ቢሰጥም በተመሳሳይ ጊዜ ለፖለቲካ አለመረጋጋትና የህዝብ ለህዝብ መስተጋበር ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ፈጥሯል። የፖለቲካ ፓርቲዎች ከማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም አንጻር ያለውን መልካም እድል እና የሚያስከትለውን አደጋ ጠንቀቀው እና ተንትነው ማወቅ ይጠበቅባቸውል።

- **ማኅበራዊ ሚዲያዎች ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጡ ዕድሎች፦**

ቀጥተኛ ውክልና	ማኅበራዊ ሚዲያ የዜጎችን ስጋቶች፣ ችግሮችና ፍላጎቶች በቀጥታ ለማዳመጥ፣ በፖሊሲዎች ላይ አስተያየት ለመሰብሰብ እና የመወከል ስሜት ለመፍጠር በቀደሙት ዘመናት ያልነበሩ ዕድሎችን ይሰጣል።
ቅስቀሳ እና ደጋፊ ማኅበረሰብ መገንባት	እንደ ቴሌግራም እና ፌስቡክ ያሉ መድረኮች ደጋፊዎችን ለማነቃቃት፣ ዝግጅቶችን ለማደራጀት እና በፓርቲው ዋና እሴቶች ዙሪያ ጠንካራና ቁርጠኛ ማኅበረሰብ ለመገንባት ኃይለኛ መሣሪያዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ ከድምፅ ሰጪዎች ተሳትፎ አልፎ የበጎ ፈቃደኞችን ምልመላ እና የሕዝብ ድጋፍን ማሰባሰብን ያጠቃልላል።
ከአዲሱ ትውልድ ጋር ለመጣጣም	እንደ ቲክቶክ እና ቴሌግራም ባሉ መድረኮች ላይ በንቃት በመሳተፍ፣ ፓርቲዎች ባህላዊ ፖለቲካን ብዙ ጊዜ ለሚጠራጠር ወጣት ትውልድ የበለጠ ቅርብ ለመሆን ያግዛል፣ ፓርቲዎን የበለጠ ከጊዜው ጋር ተዛማጅ እና ተራማጅ የሆነ ተደርጎ እንዲታይ ማድረግ ይችላሉ። ወጣት ድምጽ ሰጪዎችን ለመሳብም ያግዛል።
ግልጽነት እና ተጠያቂነት	ማኅበራዊ ሚዲያ ፓርቲዎች ስለ እንቅስቃሴዎቻቸው፣ ውሳኔዎቻቸው እና የፖሊሲ አቋሞቻቸው የበለጠ ግልጽ እንዲሆኑ ያስችላል። የተሳሳተ መረጃን ለማስተካከል እና ድርጊቶቻቸውን በቅጽበት ለማስተላለፍ ቀጥተኛ መድረክ ይፈጥራል።

- **ማኅበራዊ ሚዲያው ለፖለቲካ ፓርቲዎች የመጡት አደጋዎችና ኃላፊነቶች፦**

የተሳሳተ መረጃ እና የተዛባ መረጃ	የማኅበራዊ ሚዲያ ያልተማከለ ባህሪ (ተቆጣጣሪ ስለሌለው) የተሳሳተ መረጃ (Disinformation) እና የሐሰት ዜና (Mis-information) ለመሰራጨት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። ይህም ለፓርቲው ስም እና ለአጠቃላይ ፖለቲካዊ ውይይት ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል።
ፖለቲካዊ መከፋፈል እና ጨዋነት የጎደለው አነጋገር	የማኅበራዊ ሚዲያ ስልተ ቀመሮች (algorithms) ነባር እምነቶችንና መስተጋብሮችን የሚሸረሽሩ እና ፖለቲካዊ ክፍፍልን የሚያባብሱ ማዕቀፎችን መፍጠር ይችላሉ። በኢትዮጵያ ሁኔታ፣ ይህ አደጋ በተለይ በብሔር፣ በቋንቋ ተናጋሪዎችና የሃይማኖት ተከታዮች ላይ በኦንላይን ላይ በሚደረጉ የጥላቻ ንግግሮች፣ የሚለቀቁ ጹሁፎች፣ ሃሰት ትርክቶች እና ከፋፋይ መልዕክቶች ይበልጥ የተወሳሰበ ይሆናል።
የመልእክት ቁጥጥር ማጣት	ማኅበራዊ ሚድያ ለፓርቲዎች ከሕዝብ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት መፍጠሩ ጥቅም ቢሆንም፣ አንድ ፓርቲ በመልእክቱ ላይ ያለውን ቁጥጥር እንዲያጣ ሊያደርገው ይችላል። አስተያየቶች፣ ግብረመልሶችና፣ የሚጋሩ ተፃራሪ መልዕክቶች እና የሕዝብ ውይይቶች የፓርቲውን የታሰበ መልእክት በፍጥነት ሊጠለፉ፣ በተሳሳተ መልኩ እንዲጠቀሱ ወይም በስህተት ሊተረጉሙት ይችላሉ። ይህም ለፓርቲው የኮሚኒኬሽን ሥራዎች በአሉታዊ መልኩ ፈተና ሊያመጡ ይችላሉ።

የግል መረጃ ምስጢራዊነት መሸርሸር	የመረጃ መንታፊዎች ባሉበት አደገኛ ጊዜ የላቁ የዲጂታል መተግበሪያ ዘዴዎችን መጠቀም የግል መረጃ አያያዝን (privacy) በተመለከተ ስጋቶችን ሊፈጥር ይችላል። እንዲሁም ፓርቲዎች የግል መረጃን ለእውነተኛ ተሳትፎ ሳይሆን ለመቆጣጠር እየተጠቀሙበት ነው የሚል አስተሳሰብ ሊፈጠር ይችላል።

- እንደእርስዎ ፓርቲ ልምድ ደጋፊዎችን ለማሰባሰብ እና ወጣቶችን በማኅበራዊ ሚዲያ ለማሳተፍ ምን ስልት አላችሁ? የጥላቻ ንግግር እና ክፍፍልን ለመከላከል ምን ታደርጋላችሁ?

4.3.2. የፖለቲካ ፓርቲዎች በማኅበራዊ ሚዲያ ዘላቂ ተሳትፎ ለማድረግ የሚያስችሉ ስልቶች

በየጊዜው በሚለዋወጠው የፖለቲካ ምህዳር ውስጥ ማኅበራዊ ሚዲያ ከምርጫ ዘመቻ መሳሪያነት አልፏል። ለፖለቲካ ፓርቲዎች ዘላቂ የሆነ መገኘትን ለመፍጠር፣ ከሕዝብ ጋር ግንኙነት ለመገንባት እና በሀገራዊ ውይይቶች ውስጥ አስተዋፅኦ ለማድረግ ወሳኝና ዘላቂ መድረክ ነው። ማኅበራዊ ሚዲያዎችን በውጤታማነት የሚጠቀም ፓርቲ ለምርጫ ብቻ ሳይሆን በፓርቲው የፖለቲካ ሂደት ውስጥ (political lifecycle) ውጤታማ እንዲሆን ያግዘዋል። ማኅበራዊ ሚዲያን በተገቢው መንገድ መጠቀም መቻል ለፓርቲዎ ጠንካራ ስም ለመገንባት፣ ድጋፍ ለማሰባሰብ እና ለተከታዮቹ ተለዋዋጭ ፍላጎቶች ምላሽ ለመስጠት የተሻለ አቋም ይፈጥርለዎታል።

4.3.2.1. የማኅበራዊ ሚዲያ በአግባቡ ለመጠቀም ስልት ማዘጋጀት

የተሳካ የፖለቲካ ምርጫ ዘመቻ የሚጀምረው ዘመቻው ከመታወጁ ከረጅም ጊዜ በፊት ነው። ከምርጫ ጊዜ ውጪም ቢሆን የፖለቲካ ፓርቲዎች ማኅበራዊ ሚዲያዎችን በብቃት እንዲጠቀሙ የሚያስችሉ ቁልፍ ስልቶች ከዚህ በታች ቀርበዋል፦

ግልጽ የፖለቲካዊ ማንነት ይፍጠሩ	የተሳካ የፓርቲ ማንነት (brand identity)) የፓርቲውን ዋና እሴቶቹን፣ ራዕዩንና ተልዕኮውን የሚገልጽ ርዕዮተ ዓለማዊ ፊርማው ነው። ይህ ማንነት ከምርጫ ማስታወቂያ በፊት ለረጅም ጊዜ በሁሉም የመገናኛ ዘዴዎች ላይ በተከታታይ መገለጽ እና መተላለፍ አለበት። የፓርቲዎ ማንነት ኢኮኖሚያዊ ልማት፣ ማኅበራዊ ፍትህ ወይም የመሳሰሉት ላይ የሚያተኩር ቢሆንም፣ የተለየ የፖለቲካዊ እምነቱንና የታለመለትን ታዳሚ የሚያንጸባርቅ መሆን አለበት። • **የአጻጻፍ ስልት መመሪያ ያዘጋጁ (Style Guide)** ፦ የጸደቁ ቀለሞችን፣ የፊደል አጣጣል አይነቶችን፣ ምስሎችንና የመልዕክት ቅንብር ቅርጾችን የሚገልጽ ዝርዝር መመሪያ ያዘጋጁ። ይህም ከፌስቡክ ጽሑፍ እስከ ቴሌግራም፣ ከኤክስ (ትዊተር) እስከ ዩትዩብ ድረስ የሚተላለፉ መልዕክቶች ወጥነት ባለው ድም እንዲተላለፉ ያደርጋል። • **ዋና መልዕክትዎን ያጉሉ**፦ ፓርቲዎን ከሌሎች ተቀናቃኝ የፖለቲካ ፓርቲዎች በዋናነት የሚለዩ ሁለት ወይም ሦስት ቁልፍ መልዕክቶችን በጉልህ ይግለጹ። ለምሳሌ፣ የፓርቲዎ ዋና ትኩረት ግብርናን በዘመናዊ መንገድ ማልማት ከሆነ፣ እያንዳንዱ ይዘትዎ ከዚህ ማዕከላዊ ጭብጥ ጋር በተወሰነ መንገድ መያያዝ አለበት።
ቋሚ የዲጂታል ቡድን ማቋቋም	ዘመናዊ የፖለቲካ ፓርቲዎች የፓርቲያቸውን የማኅበራዊ ሚዲያ በቋሚነት የሚመራ እና የሚከታተል የዲጂታል ሚዲያም ለማስተዳደር የተለያዩ ዕውቀት ያላቸው ባለሙያዎችን የያዘ ቋሚ የዲጂታል ቡድን ያስፈልጋቸዋል። • **የዲጂታል ባለሙያዎችን መቅጠር**፦ ባለሞያዎችን ለመቅጠር አቅም ያላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች በይዘት ፈጠራ (content creation) ፣ የዲጂታል ማህበረሰብ አስተዳደር፣ በመረጃ ትንተና እና ከሁሉም በላይ ደግሞ በችግር ጊዜ የሚሰጥ ምላሽ (crisis communication) ላይ እውቀትና ልምድ ያላቸውን ባለሙያዎች ቢቀጥሩ ይመከራል። (ዲጂታል ሰርዊት እንደሚባለው ሰፊ ሃይል ባይሆንም ሁለት ወይም ሦስት ባለሞያዎችን መያዝ ጠቃሚነው) ። በኦንላይን የሚሰራጩ የሐሰት መረጃና የጥላቻ ንግግር የማያቋርጥ አደጋ በሆኑበት የፖለቲካ ምህዳር ውስጥ ፈጣን እና ስልታዊ ምላሽ ለመስጠት እንዲህ ያለው ቡድን በጣም አስፈላጊ ነው። • **ፈቃደኛ አባላትን ማሰልጠን**፦ ባለሞያ ለመቅጠር አቅም ውስንነት ያለባቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የቴክኖሎጂ ዕውቀት ያላቸውን ፈቃደኛ አባላትን መመልመልና ማሰልጠን ወሳኝ ነው። ወጥነትን ለማረጋገጥ እና ስህተቶችን ለመከላከል ሚናዎችን፣ ኃላፊነቶችን እና የይዘት ማጽደቅ ሂደቶችን የሚገልጽ ግልጽ የማህበራዊ ሚዲያ መመሪያ በፓርቲው ተዘጋጅቶ እንዲሰጣቸው በማድረግ የማኅበራዊ ሚዲያውን ጉዳይ እነሱ እንዲይዙት ማድረግ ያስፈልጋል።

የረጅም ጊዜና ተለዋዋጭ የማኅበራዊ ሚዲያ ስልት ይንደፉ	የማኅበራዊ ሚዲያ ስልትዎ ለፓርቲዎ ቀጣይ የፖለቲካ ተሳትፎ እና ንቅናቄ ዝርዝር ፍኖተ ካርታ (roadmap) መሆን አለበት። የማኅበራዊ ሚድያ አጠቃቀም ፍኖተ ካርታው የምርጫ ዘመቻን ጨምሮ ከምርጫ ባሻገር ላሉ የፓርቲው የኮሚኒኬሽን ሂደት የዕቅድ አካል መሆን አለበት። • **የይዘት መረሐግብር (Content Calendar) ማዘጋጀት**፦ ማኅበራዊ ሚዲያ ላይ የሚወጡ የመልዕክት ይዘትዎን አስቀድመው ያቅዱ። ወቅቱን እና ኩነቶችን የዋጁ እንዲሆኑ ያድርጉ። ለምሳሌ ከፌደራላዊ ፣ ክልላዊ ወይም አከባቢያዊ ኩነትና ዝግጅቶች፣ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወይም የክልል ምክር ቤቶች ሕግ የማውጣት ስብሰባዎችና ከቁልፍ የፖሊሲ ክርክሮች ጋር እንዲጣጣም ያድርጉ። በዋና ዋና የሕዝብና ብሔራዊ በአላት ላይ ፓርቲዎ የሚያስተላልፈውን መልዕክት ከወቅቱ ጋር አዛምዶ ምን መነገር እንዳለበት ያስቡ። • **መድረኮችን መዋጀት (Platform Specialization)** ፦ የተለያዩ የማኅበራዊ ሚዲያ መድረኮችን ለተለያዩ ዓላማዎች ይጠቀሙ። ፌስቡክ ፈጣን እና ይፋዊ ማስታወቂያዎችን ለመልቀቅና ብዙ ተከታዮችን ለመድረስ ሊያገለግል ይችላል። ቴሌግራም ማኅበረሰብ ለመገንባትና ዝርዝር ውይይቶችን ለማካሄድ ሊያገለግል ይችላል። ቲክቶክ ከወጣት ድምፅ ሰጪዎች ጋር ስለ ፓርቲዎ ራዕይ በሚናገሩ አጫጭርና ተዛማጅ ቪዲዮዎች ለመገናኘት ሁነኛ መሣሪያ ነው። ኤክስ (ትዊተር) ከጋዜጠኞች፣ ከአሳቢ መሪዎችና (thought leaders) ፣ ተጽኖ ፈጣሪዎች፣ ከፖለቲካ ተንታኞች ጋር ለመገናኘት ወሳኝ መድረክ ነው። • **ለስኬት የሚጠቅሙ መለኪያዎች**: ከድምፅ ሰጪዎች ቁጥር ባሻገር ለፓርቲው የማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ስኬታማነትን የሚጠቅሙ የተወሰኑ መለኪያዎችን ይወስኑ። የተሳትፎ መጠን (መውደዶች፣ ማጋራት፣ አስተያየቶች/(likes, shares, comments)፣ በቁልፍ ጉዳዮች ላይ ያለውን የሕዝብ ስሜት እና የተከታዮችዎን ዕድገት ይለኩ።
የፓርቲዎን ማኅበራዊ ሚዲያ ገጾች ማረጋገጥ (Verify ማድረግ)	በማኅበራዊ ሚዲያ ላይ የማንነት ስርቆትና የሐሰት አካውንቶች የተሳሳተ መረጃ (disinformation) ለማሰራጨት እና ልዩነት ለመፍጠር በሚውሉበት በዚህ ወቅት፣ የገጾች ይፋዊ ማረጋገጫ (verification) የግድ አስፈላጊ ነው። በትላልቅ ማኅበራዊ ሚዲያ መድረኮች ላይ የሚሰጡ የማረጋገጫ ምልክቶች (verification badges) አንድ ፓርቲ እንደ ታማኝና ትክክለኛ የመረጃ ምንጭ ራሱን ለማቋቋም ወሳኝ መሣሪያ ናቸው። • **በጊዜ ይጀምሩ**፦ ለሁሉም ይፋዊ የፓርቲዎ የማኅበራዊ ሚዲያ ገጾች የማረጋገጫ ለማግኘት ሂደቱን ቀድመው ይጀምሩ። በልምድ እንደሚታየው ማረጋገጫ ከማኅበራዊ ሚዲያ ባለቤቶቹ የማግኘት ሂደት ጊዜ ሊወስድ ስለሚችል። የተረጋገጠ የማኅበራዊ ሚዲያ ገጾች መኖሩ የፓርቲውን ዲጂታል ስም ለመጠበቅ መሠረታዊ መንገድ ነው። • **የተሳሳተ መረጃን ይቃወሙ**፦ ፓርቲው የተረጋገጠ የማኅበራዊ ሚዲያ አካውንት ሲኖረው በስሙ የሚወጡ ወይም የሚለጠፉ ሐሰተኛ መረጃዎችንና ትረካዎችን በብቃት ለመቋቋም ያስችሎታል። የተሳሳተ መረጃ ሲሰራጭ ከትክክለኛው የፓርቲዎ ማኅበራዊ ሚዲያ ምንጭ ያልወጣ መሆኑን ለሕዝብና ለድምፅ ሰጪዎች ማረጋገጫ በመስጠት በእርስዎ ፓርቲ ላይ እምነት እንዳይጎድል ለማድረግ በተረጋገጠ ገጽዎ ላይ ይፋዊ ምላሽ ለመስጠት መጠቀም ይችላሉ።
ታዳሚዎን ይመርምሩ እና ይረዱ	በየጊዜው የፓርቲዎን ማኅባራዊ ሚዲያ ታዳሚዎች ምርምር ያደጉና እነማን እንደሆኑ ይረዷቸው (Research and understand your target audience) ። ምን አይነት የሥነ ሕዝብ ስብጥር (የፆታ፣ የእድሜ፣ የትምህርት ደረጃ፣ የኢኮኖሚ ሁኔታ) እንዳላቸው ማወቅ ያስፈልጋል። • **ትንታኔዎችን ይጠቀሙ**፦ እንደ ፌስቡክ፣ ዩትዩብ እና ኤክስ (ትዊተር) ባሉ መድረኮች ላይ የሚቀርቡትን የትንታኔ መሳሪያዎች በመጠቀም የተከታዮችዎን ስነ-ሕዝብ (demographics)፣ በብዛት የሚወዱትን ይዘት እና መረጃ ወይም ይዘት ለመለጠፍ አመቺ የሆኑ ጊዜያትን በመደበኛነት ይረዱ። • **ማኅበራዊ ውይይቶችን ያዳምጡ**: ሰዎች ስለ ፓርቲዎ የሚሉትን ብቻ ሳይሆን ስለ ቁልፍ የፖሊሲ ጉዳዮች፣ ስለ ሌሎች ፓርቲዎች እና ስለ ሀገራዊ ክስተቶች የሚናገሩትን ለመከታተል የተራቀቁ የማኅበራዊ ሚዲያ መከታተያ ዘዴዎችን ይጠቀሙ። ይህ የፖሊሲ አቋምዎን እና የመገናኛ ስልቶችዎን ለማሳወቅ የሚያስችል ፈጣን የፖለቲካ መረጃ ይሰጥዎታል።

በግልና በፓርቲ አካውንቶች መካከል ግልጽ ልዩነትን ማስቀመጥ	የተቋማዊ፣ ሙያዊነትና ግልጽነትን ለመጠበቅ ይፋዊ የፓርቲ ገጾችን ከፓርቲው መሪዎች ወይም ማኅበራዊ ሚዲያውን ከሚመሩት የፓርቲው ባለሞያዎች የግል አካውንቶች መለየት ወሳኝ ነው። የግል ገጾች ፖለቲካዊ ጉዳዮች የሚተላለፉበት ቢሆንም እንኳን ብዙውን ጊዜ የግል መልከታዎች የሚንጸባረቅባቸው ወይም ማኅባራዊ ኩነቶች የሚተላለፉባቸው በመሆኑ የፓርቲውን የማኅባራዊ ሚዲያ ድረጃ ላይመጥኑ ይችላሉ። • **ተቋማዊ እና ግላዊ ድምጽን መለየት**፦ የፓርቲው ይፋዊ ገጽ የተቋሙን ድምጽ ማንጸባረቅ አለበት። ይኸውም መደበኛ ጉዳዮችና በፖሊሲ ላይ ያተኮረ እና መላውን ፓርቲ የሚወክል መሆን አለበት። የአንድ መሪ የግል አካውንት ደግሞ የበለጠ መደበኛ ያልሆነ ሊሆን ይችላል። ይህም የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎቻቸውን፣ ራዕያቸውን እና የግል አስተያየቶቻቸውን በራስ መንገድ ለማቅረብ ያስችላል። • **ግልጽ ወሰኖችን ማስቀመጥ**፦ በግልና በፓርቲ አካውንቶች መካከል ግልጽ ልዩነትን ማስቀመጥ አካውንቶቹን ለሚያስተዳድሩ ሠራተኞችም ግልጽ ወሰኖችን ይፈጥራል። ይህም የግል አስተያየቶች ወይም ይዘቶች በአጋጣሚ ከይፋዊ የፓርቲ መልዕክቶች ጋር እንዳይቀላቀሉ ያረጋግጣል።

4.3.2.2. የማኅበራዊ ሚዲያ ተከታዮችን ቁጥር ማሳደግ

ለፖለቲካ ፓርቲዎች ሰፊ ተደራሽነት እና ተጽኖ ፈጣሪ ለመሆን ከሚያስችሏቸው መገዶች አንዱ የማኅበራዊ ሚዲያ ተከታዮቻቸውን ቁጥር ማሳድግ እና ማስፋት ነው። በዚህ መንገድ የፖለቲካ ፓርትዎች የሚያስተላልፉት መልክት ለበርካታ ዜጎች እንዲደርስ እና የተጽኖ መጠኑም እንዲጨምር ማድረግ ይችላሉ። እንዴት የፓርቲዎን የማኅበራዊ ሚዲያ ገጾች ተከታዮችን እና የመረጃ ተጠቃሚዎችን ማሳደግ እንደሚችሉ ቀጥለን እንመልከት፦

የደጋፊዎችን መረብ ለመልዕክት ማሰራጨነት ይጠቀሙ	የፖለቲካ ፓርቲዎች የአባሎቻቸውን እና ደጋፊዎቻቸውን የማኅበራዊ ሚዲያ ገጾች ለፓርቲው የዲጂታል መልእክተኞች ማስተዋወቂያ እንዲሆኑ ማበረታታት አለባቸው። የኢንተርኔት ተደራሽነትና የንባብና ጽሑፍ ክህሎት ደረጃው በተለያየበት ሀገር ውስጥ ለሕዝብ ተደራሽ ለመሆን ግላዊ መረቦች (personal networks) ከፈተኛ ሚና አላቸው። ደጋፊዎች በስፋት ጥቅም ላይ በሚውሉ እንደ ፌስቡክና ቴሌግራም ባሉ መድረኮች ላይ የፓርቲው ማኅበራዊ ገጾች ላይ የሚወጡ መልዕክቶችን እንዲያጋሩ ያበረታቱ። ቁልፍ መፈክሮችን የያዙ ምስሎችን ወይም የፖሊሲ አቋሞችን የሚያብራሩ አጫጭር ቪዲዮዎችን በተለያዩ የአካባቢው ቋንቋዎች ተዘጋጅተው እንዲሰራጩ ማድረግ የአባልትን እና የደጋፊዎችን የማኅበራዊ ገጾች ተጠቅሞ መረጃ ለማሰራጨትና ተከታይ ለማብዛት ጠቃሚ ዘዴ ነው።
በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች (Platforms) ላይ የተቀናጀ አጠቃቀም	የማኅበራዊ ሚዲያ ገጾችዎ ብቻቸውን መሆን የለባቸውም። ይልቁንም የፓርቲዎ አጠቃላይ የኮሚኒኬሽን ስልት ማዕከላዊ አካል መሆን አለባቸው። ከፓርቲው ይፋዊ ድረ ገጽ እስከ የታተሙ በራሪ ወረቀቶች፣ ፖስተሮች እና ባነሮች ድረስ በሁሉም የኮሚኒኬሽን መገልገያ ቁሳቁሶች ላይ የፓርቲውን የማኅበራዊ ሚዲያ ገጾችዎን ማገናኛዎች (links) በግልጽ እንዲያሳዩ ያድርጉ። በታተሙ ቁሳቁሶች ላይ ሰዎች ገጾችዎን በፍጥነት እንዲከተሉ የሚያስችላቸውን ተወዳጅና ቀላል የሆነውን የQR ኮድ መጠቀም ያስፈልጋል እና ያስቡበት። ይህ እርስ በርስ የማስተዋወቅ ዘዴ ሰዎች ፓርቲዎን በየትኛውም ቦታ ሲያገኙት በኦንላይን ላይ ከእርስዎ ጋር ለመገናኘት ግልጽ መንገድ እንዲኖራቸው ያረጋግጣል።
የታለመ ማስታወቂያን መጠቀም	የፓሪቲውን ማኅበራዊ ሚዲያዎች ለማስተዋወቅ አነስተኛ በጀት እንኳን ቢኖር ስልታዊ ተሳትፎ ለመፍጠር ጠቃሚ መሳሪያ ሊሆን ስለሚችል የፓርቲውን ይፋዊ የማኅበራዊ ሚድያ ገጾች እንዲተዋወቅ ማድረግ። ለዚህም በአዋቂ እና ብዙ ተከታይ ባላቸው የማኅበራዊ ሚዲያዎች፣ በቴሌቪዥን እና ሬድዮ የፓርቲዎን ማኅበራዊ ሚድያ ገጾች እንዲተዋወቁ ማድረግ ተከታዮችን ሊያሰፋ ይችላል። ለምሳሌ እንደ ፌስቡክ ባሉ መድረኮች ላይ በመጠቀም በተወሰኑ የሕዝብ ክፍሎችን ኢላማ ያደረገ ማስታወቂያ በመስራት ስለፓርቲዎ ገጾች ማስተአውቅ ይቻላል። ለምሳሌ በከተማ ውስጥ ያሉ ወጣቶችን ወይም በተወሰኑ ክልሎች ያሉ የማኅበረሰብ አባላትን ታሳቢ ያደረጉ ማስታውቂያዎችን መልቀቅ ይቻላል። ሆኖም፣ ይህ በታላቅ ኃላፊነት መከናወን አለበት። የፖለቲካ ፓርቲዎች ማስታወቂያዎቻቸው ግልጽ፣ እውነት ላይ የተመሠረቱ መሆናቸውን እና የሐሰት መረጃዎችን ወይም የብሔር ግጭቶችን የሚያባብሱ አለመሆናቸውን ማረጋገጥ አለባቸው። በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁኔታ የመገናኛ ብዙኃን ሕጎችን ማክበር እና ለሰላማዊ መልእክት ማስተላለፍ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ይጠብቃል።
የቀጥታ ስርጭቶችን ማስተላለፍ	የፓርቲን ማኅበራዊ ሚዲያውች በሰፊው ለማስተዋውቅ ከሚያግዙ ዘዴዎች አንዱ ትኩረት ሳቢ የሆኑ ኩነቶችን ለምሳሌ የፓርቲውን ስብሰባዎች፣ ሰልፎች እና የማኅበረሰብ ጉብኝቶች በቀጥታ ስርጭቶች ማስተላለፍ ትኩረት ሳቢ ነው። እንደ ፌስቡክ ላይቭ እና ዩቱዩብ ያሉ ቻናሎች ለዚህ በጣም ምቹ ናቸው። ሰዎች ከፓርቲው ሩቅ ቢሆኑም እንኳን የሂደቱ ምን እንደሚመስል ለመታዘብ በሚያደርጉት ሙከራ ስለፓርቲው የበለጠ እንዲያውቁና ከማኅበራዊ ሚድያ ገፆቹም ጋር እንዲተዋወቁ ያደርጋል።

ምዕራፍ አምስት

የፖለቲካ ፓርቲዎች አካታችነት

ዘመናዊ ፖለቲካ፣ በውክልና የዲሞክራሲ ሥርዓት እና መንግሥት የሕዝቡን ፍላጎት ማንጸባረቅና ማገልገል አለበት በሚለው መርህ ላይ የተመሠረተ ነው። ይህም እውን የሚሆነው ከተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች የተውጣጡ ፖለቲከኞች የሕዝብን ጉዳይ ወክለው እንዲመሩ ተመርጠው የመንግስት ሥርዓትን መመሥረት ሲችሉ ነው።

ካለፉት ጥቂት አሥርት ዓመታት ወዲህ በበርካታ የዓለም ሀገራት ውስጥ አካታች የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ መከናወን በመቻሉ የፖለቲካ ባሕሉ በሂደት ከተናጥላዊ የወንድ ግሎማሶች መድረክነት ወደ ሁሉን አቀፍ አካታች ሥርዓት በመሸጋገር ላይ ነው። በኢትዮጲያም የፖለቲካ ሂደት ውስጥ የተጠበቀውን ያህል ባይሆንም እንኳን ሁሉን አቀፍ ወደሆነ የፖለቲካ ምህዳር ለመሸጋገር ጉልህ መሻሻሎችን ታይተዋል። በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 50 ንኡስ አንቀጽ 3 መሠረት የፌዴራል መንግሥቱ ከፍተኛ የሥልጣን አካል በሆነው የፌደራሉ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ ከሁሉም የሀገሪቱ ክፍል እና ከተለያዩ አስተዳደግ የመጡ ግለሰቦች ሕዝብን ወክለው በምርጫ መሰየማቸውን ተመልክተናል። በኢትዮጲያ በርካታ ቁጥር ያላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች መመሥረታቸውን ተከትሎ ሴቶች፣ ወጣቶች እና አካል ጉዳተኞች በፖለቲካው ውስጥ የመሳተፍ ምጣኒያቸው ጨምሯል። በመንግሥት የስልጣን መዋቅር ውስጥ ቁጥራቸው ቀላል የማባሉ ሴቶች በያዟቸው የስልጣን ቦታዎችም ከፍተኛ መሻሻል ታይቷል። በጉልህ በሚታይ መልኩ በገዢው ፓርቲ ውስጥ እና በከፍተኛ የመንግስት ደረጃዎች ላይ በርካታ ቁጥር ያላቸው ሴቶች ቁልፍ የስልጣን እርከኖችን መያዝ መቻላቸው በሂደት ለብዝሃነት ያለው ቁርጠኝነት እያደገ መምጣቱን ያመላክታል።

ይሁን እንጂ የታየው የአካታችነት የፖለቲካ ባሕል እድገት የሚያበረታታ ቢሆንም አሁንም የሴቶች፣ የወጣቶችና እየአካል ጉዳተኞች የፖለቲካ ተሳትፎና ውክልና ያልተመጣጠነ መሆኑ በጉል የሚታይ ጉዳይ ነው። በተለይ በፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ የነዚህ አካላት ተሳትፎ እና ወደ አመራር ደረጃ የማደግ እድል ውስንነት እንዳለበት ይሰተዋላል። እንደ ኢትዮጵያ ያለ የሥነ ሕዝብ ብዝሃነት ያለው ሃገር ውስጥ የሁሉም ድምጾች መሰማት እና የሁሉም ማንነቶች በትክክል መወከል የፖለቲካ ግብ ብቻ ሳይሆን የሀገር ህልውና ወሳኝ ጉዳይ ነው። የፖለቲካ ፓርቲዎች የሀገሪቱን ብዝሃ ማንነት በትክክል እንዲያንጸባርቁ ለማድረግ የሚደረገው ጥረት ገና አልተጠናቀቀም።

በዚህ የመመሪያ መጽሐፍ ምዕራፍ አምስት የፖለቲካ ፓርቲዎች ሁሉን አቀፍ ለሆነ ዲሞክራሲ ሥርዓት የመገንባት ኃላፊነታቸውን መወጣት እንዲችሉ የሚያግዙ ስልቶችን እና ምክረ ሀሳቦችን እንመለከታለን። የብዝሃነት መሠረቶች የሚገነቡት በፖለቲካ ፓርቲዎች አሳታፊነትና ውክልና የመሰጠት ሂደት ውስጥ ነው። ይህም ሴቶች፣ ወጣቶች፣ አካል ጉዳተኞች የተውጣጡ ግለሰቦች መካተት ብቻ ሳይሆን በሁሉም የፖለቲካ ሂደቶች ውስጥ ትርጉም ባለው መልኩ እንዲሳተፉ፣ እንዲወከሉና ለአመራርነት እንዲበቁ ማበረታታትን ይጨምራል።

5.1. ብዝሃነት ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መዳበር ያለው ፋይዳ

- ዲሞክራሲያዊ ሥርዓቶች የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን በትክክል የሚወክሉ መሆናቸውን እንዴት ማረጋገጥ እንችላለን?

የአንድን ሀገር ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመገንባትና ዘላቂና እውነተኛ ተወካይ እንዲሆን ለማድረግ እያንዳንዱ ዜጋ በፖለቲካ ሂደቶች ውስጥ እንዲሳተፍ እና ፍላጎቱ እንዲደመጥ መፍቀድ አለበት። ማንኛውንም ቡድን ከፖለቲካዊ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ማግለል ወደ ግጭትና አለመረጋጋት ሊያመራ ይችላል። አንድ ሀገር በፖለቲካዊ መገለል ምክንያት ወደ ግጭት ውስጥ የምትገባበት አጋጣሚ ሲፈጠር የዲሞክራሲያዊ ሽግግርና መጠናከርን ይገታል። ብዝሃነት ባለበት ሀገር ውስጥ ወካይ የዲሞክራሲ ሥርዓትን እውን ለማድረግ ውክልናን የሚያረጋገጥ መዋቅራዊ ሥርዓት መፈጠር አለበት። ለዚህም ነው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መዋቅር የተለያዩ ብሔር እና ክልላዊ ቡድኖችን ለማስተናገድ ታስቦ የተነደፈ በመሆኑ የፖለቲካ ተሳታፊነት እና ውክልና በፌዴራል እና በክልል ደረጃ እንዲኖር በማደረግ ለፖለቲካዊ መረጋጋትና ለማኅበራዊና እና ኢኮኖሚያዊ ለእድገት መረጋገጥ መሠረታዊ መርህ ነው።

የፖለቲካ ተሳታፊነት በኢፊድሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 25 እና በመንግስታቱ ድርጅት አባል ሀገራት የጸደቀው የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን ሰንድ አንቀጽ 2 ላይ እንደተቀመጠው በዘር፣ በብሔር፣ ብሔረሰብ፣ በቀለም፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በማኅበራዊ አመጣጥ፣ በሀብት፣ በትውልድ፣ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ሁሉ በዴሞክራሲያዊ ተቋማት ውስጥ በእኩል ዕድል እንዲሳተፍና የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያደርግ የሚያስችል ጽንሰ-ሐሳብ ነው። ይህ እሳቤና መርህ የሴቶች፣ የወጣቶችና የአካል ጉዳተኞች የፖለቲካ ተሳትፎንም ያጠቃልላል። ይህንን ተሳታፊነት ማስፈን ፈታኝ ነው።

በፖለቲካ ፓርቲዎችና በአመራር ውስጥ ብዝሃነትን እና አካታችነትን ማስፋፋት የሞራል ግዴታ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያን ዲሞክራሲ ለማጠናከር ስልታዊ አስፈላጊነትም ጭምር ያለው መሆኑን ማየት ያስፈልጋል። ብዝሃነት እና አካታችነትን ማረጋገጥ ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መዳበር ምን ይፈይዳል? የሚለውን ስንጠይቅ የሚከተሉትን እውነታዎች እንስተውላለን[1]።

5.1.1. ውክልና እና ፖሊሲ

የፖሊሲ አውጪዎች የአንድን ሀገር ሕዝብ ሙሉ በሙሉ በትክክል የማይወክሉ ከሆነ፣ ፖሊሲዎች ሁሉንም ቡድኖች ልዩ ፍላጎቶች እና ችግሮች ለመፍታት ብዙውን ጊዜ ይሳናቸዋል። በኢትዮጵያ ውስጥ ይህ በተለይ በገጠር ለሚኖሩ ወይም ከፖለቲካው ማዕከል ርቀው ለሚገኙ ማኅበረሰቦች እውነት ሊሆን ይችላል። እነዚህ ማኅበረሰቦችም አሳሳቢ ጉዳዮቻቸው ችላ የተባሉ እንደሆኑ ሊሰማቸው ይችላል። አካታች ያልሆነ የፖሊሲ ዝግጅትም እንዲሁ ነው። ሴቶችን፣ ወጣቶችን፣ አካል ጉዳተኛ ዜጎችን እና ሌሎች በፖለቲካ ምህዳር ውስጥ የተገለሉ ቡድኖች በትክክል ካልተሳተፉና ካተወከሉ ሁሉንም ቡድኖች ያማከለ ፖሊሲ ለመቅረጽ አዳጋች ይሆናል። ለምሳሌ በአንድ የስነ-ሕዝብ ቡድን ብቻ በተለይም በጎልማሳ ወንዶች የተያዘ የመንግሥት ወይም የፖለቲካ ፓርቲ አመራር በኢመደበኛ አነስተኛ ኢኮኖሚ ውስጥ ያሉ ሴቶችን፣ ሥራ የሚፈልጉ ወጣቶችን ወይም አሳታፊ ያልሆነ መሠረተ ልማት የሚያሰናክላቸውን የአካል ጉዳተኞችን ልዩ ችግሮች እና ፍላጎቶች ሙሉ በሙሉ ላይረዳ ይችላል።

ሴቶች	በታሪክ በመንግሥትና በፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ ያሉ ፖሊሲ አውጪ ቦታዎች በአመዛኙ በወንዶች የተያዙ ስለነበሩ የሴቶችን አመለካከትና ፍላጎቶች ችላ የሚሉ ሕጎችና ፖሊሲዎች እንዲፈጠሩ ሊያደርግ ይችላል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ይህ ሁኔታ ቢያንስ በሕግ አወጪው ምክር ቤቶች ከፍተኛ መሻሻሎች ታይተዋል። ለምሳሌ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሴት የምክር ቤት አባላት ቁጥር የ2013ን አጠቃላይ ምርጫ ተከትሎ ወደ 41.5% ከፍ ሊል ችሏል። ይህ እጅግ በጣም አበረታች እድገት ነው። ሆኖም ግን በፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ ያሉ አመራሮችን ስንመለከት አሁንም ከፍተኛ ክፍተት እንዳለ ለመገንዘብ ይቻላል። ከጥቂት ፓርቲዎች በቀር በከፍተኛ የፓርቲ አመራርነት ከፊት ረድፍ የሚቀመጡ ሴቶች ቁጥር እጅግ ዝቅተኛ ነው።
ወጣቶች	በመደበኛ የፖለቲካ ሂደት ውስጥ በተለይም በፖለቲካ ፓርቲዎች እና በመንግሥት መዋቅር ውስጥ የወጣቶች የፖለቲካ ተሳትፎ እና ውክልና በሚጠበቀው መጠን አይደለም። በርካታ ስታስቲካል መረጃዎች እንደሚያሳዩት ከኢትዮጵያ ሕዝብ ከፍተኛ ቁጥር ከ30 ዓመት በታች (ከሕዝቡ ከሦስት አምስተኛ በላይ የሚሆኑት ከ24 ዓመት በታች ናቸው) ነው። ወጣቶች ከውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ውስጥ መገለላቸው ቅሬታን ወደሚያባብስ ክፍተት ሊያመራ ይችላል። ወጣቶች በውሳኔ አሰጣጥ ውስጥ ሲካተቱ ዘላቂ ሰላምን ለማረጋገጥ፣ ቴክኖሎጂ እና የኢኮኖሚ ፈጠራ ባሉ ጉዳዮች ላይ ለአገሪቱ የወደፊት አቅጣጫ ወሳኝ የሆኑ አዲስ አመለካከቶችን ያመጣሉ ተብሎ ይታመናል። ወጣቶችን ያላካተቱ የፖሊሲ ቀረጻ ሂደቶች ከፍተኛ የአፈጻጸም ውስንነቶች ሊያጋጥማቸው ይችላል። የወጣቶች ውክልና በሕግ አውጪው ምክር ቤት እና በፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ ውስን መሆኑም የወጣቶችን አንገብጋቢ ጥያቄ የሆኑ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ እና የማኅበራዊ ጥያቄዎችን ለመፍታት የሚችሉ የፖሊሲና የሕግ ማዕቀፎች በበቂ ሁኔታ እንዳይኖሩ ሊያደርግ ይቻላል።
አካል ጉዳተኞች	የአካል ጉዳተኞች ፍላጎቶች ከከተማ ፕላን እስከ የሕዝብ አገልግሎቶች ድረስ በፖሊሲ ቀረጻ ውስጥ ብዙውን ጊዜ ችላ ይባላሉ። ለምሳሌ፣ አሳታፊ ያልሆነ መሠረተ ልማት ግንባታ በማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሕይወት ውስጥ አካል ጉዳተኞች ሙሉ በሙሉ እንዳይሳተፉ ሊያግዳቸው ይችላል። የስርዓት መሰናክሎችን የሚፈቱ እና እውነተኛ ተሳትፎን የሚያበረታቱ ፖሊሲዎችን ለመንደፍ ቀጥተኛ አስተዋፅኦአቸው ወሳኝ ነው። ለዚህም የአካል ጉዳተኞችን በፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉ ማድረግ እና በመንግሥት ሥርዓት ውስጥ እንዲወከሉ ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል።

5.2. ሴቶችን በፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ የማካተት ስትራቴጂ

- በእርስዎ የፖለቲካ ፓርቲ ውስጥ ሴቶች ያላቸው የተሳትፎን መጠን እንዴት ይለኩታል?
- በፓርቲያችሁ ውስጥ ሴቶች በምን ያህል ደረጃ የነቃ ተሳትፎ ያደርጋሉ?
- ምን ያህል ሴቶች በፓርቲው መዋቅር ውስጥ በአመራርነት ይሳተፋሉ?
- የእርስዎ ፓርቲ እጩዎችን ሲመለምል በምን ያህል ደረጃ ሴቶችን ያማከለ ነው?

እነዚህ ጥያቄዎች በሚገባ ተተንትነው መመለስ የሚገባቸው ናቸው።

በዴሞክራሲያዊ ስርዓቶች ውስጥ ሴቶችና ወንዶች እኩል መብቶች አሏቸው። ከአድልዎ የፀዱ የፖለቲካ ሥርዓት እውን በሆነባቸው ማኅበረሰብ ውስጥ ሴትና ወንድ በእኩል ድምጽ የመስጠት መብት ስለሚኖራቸው በፖለቲካ ውስጥ የሚኖራቸው ተሳትፎም በዚያው ልክ እኩልነት የሚያንጸባርቅ እንዲሆን ይጠበቃል። ሴቶች በፖለቲካ ውስጥ መሳተፋቸው ዴሞክራሲ ውጤታማ እንዲሆን ወሳኝ ግብዓት ነው። የሴቶች ፖለቲካዊ ተሳትፎ የፍትህ ጉዳይ ከመሆኑም በላይ የበለጠ ውጤታማ ፖለቲካዊ አስተዳደር ለመፍጠር ቁልፍ ሚና የሚጫወት ነው። በተለይም የሴቶች በፖሊሲ-አወጣጥ ሂደት ውስጥ መሳተፍ ጤና፣ ትምህርት፣ የሕፃናት እንክብካቤ፣ መሠረተ ልማት እና በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ማቆም በመሳሰሉ ወሳኝ ጉዳዮች ላይ ሕጎች እንዲወጡ ትልቅ አስተዋፅኦ አለው። ከዚህም በተጨማሪ ሴቶች በፖለቲካ

ምህዳር ውስጥ መሪ ሆነው መውጣት ሲጀምሩ ለታዳጊ ለሴት ልጆች ከፍ ያለ ትምህርት እንዲከታተሉ እና “የወንዶች ብቻ” የሚመስሉ ኃላፊነቶችን ለመቀበል ተነሳሽነት እንዲኖራቸው እንዲያሳድጉ አርአያ ሆነው ያገለግላሉ። ይሁን እንጂ በዓለማችን ውስጥ በሁሉም አካባቢዎች የሴቶች ድምጽ በውሳኔ አሰጣጥ ውስጥ ጉድለት አለበት[2]።

5.2.1. የሴቶች ፖለቲካዊ ተሳትፎን የገደቡ ጋሬጣዎች

ኢትዮጲያን ጨምሮ በበርካታ ታዳጊ ዲሞክራሲ ባለባቸው ሀገራት የፖለቲካ ምህዳሩ በወንዶች የተሞላ ነው። ለምን በርካታ ሴቶች የፓርቲ መሪ ሆነው ከፊት ረድፍ አይታዩም? ለምን በርካታ ሴቶች እጩ ሆነው ለምርጫ አይቀርቡም? ብዙ ጊዜ የሚነሱ ጥያቄዎች ናቸው።

እንደ ኢትዮጲያ ባሉ ታዳጊ የዲሞክራሲ ሥርዓት ጅማሬ ባለባቸው ሀገር ውስጥ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ወሳኝ “መግቢያ በር” (“gatekeepers”) ናቸው። የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎን ለማበረታታት ዓለም አቀፍ ቁርጠኝነቶች (የቤጂንግ የድርጊት መርሃ ግብር እና የዘላቂ ልማት ግቦች) እና ብሔራዊ ደረጃም ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌዎች እና ሌሎች የሕግ ማዕቀፎች ቢኖሩም፣ ሴቶች ወደ ፖለቲካ ለመግባት፣ ወደ ፓርቲ አመራርነት ለማደግ እና ወደ ሕዝብ ተወካይነት ደርሰው ወደ ፖሊሲ አውጭነትና ሀገር መሪነት ለማደግ የሚያደርጉት ጉዞ በከፍተኛ መሰናክሎች የተሞላ ነው።

የሴቶችን ተሳትፎ እና ተጽዕኖ ፈጣሪነት በብቃት ለመጨመር የፖለቲካ ፓርቲዎች ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። ብዙ የፖለቲካ ፓሪቲ መሪዎች በኢትዮጵያ ሲገሩ እንዲሚሰማው” የፓርቲዎች በር ለሴቶች ተሳትፎ ክፍት ነው።” ሆኖም ለምድን ነው የተሳትፏቸው መጠን አሁንም ዝቅተኛ የሆነው የሚለውን በኢትዮጲያ ማኅበራዊ፣ ባህላዊ እና ፖለቲካዊ አውዶች ውስጥ ስር የሰደዱትን የሴቶች ፈተናዎች መጀመሪያ መረዳትና በንቃት መጋፈጥ አለባቸው።

5.2.1.1. ማኅበራዊ እና ባህላዊ ሳንካዎች

የሴቶችን እኩልነትን የሚያረጋግጡ ኢትዮጲያ ፈርማ የተቀበለቻቸው ዓለም ዓቀፍ ሕጋዊ ማዕቀፎች ቢኖሩም በብዙ የኢትዮጵያ ማኅበረሰቦች ውስጥ የሚታየው ባህላዊ “የአባታዊነት” ወይም “የአባት-አምላኪነት አስተሳሰብ” (“patriarchal norms”) ዋነኛ እንቅፋት ሆኖ ቀጥሏል። እነዚህ አስተሳሰቦች ሴቶች በሕዝባዊ መድረኮች ከመሳተፍ ይልቅ በቤት ውስጥና በልጆች እንክብካቤ ላይ እንዲያተኩሩ የሚጠብቁ የተወሰኑ የፆታ ሚናዎችን ይደነግጋሉ። ይህም የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ፣ ውክልና እና ውሳኔ ሰጭነት እንዲወሰን አድርጎታል። አሁናዊ ጉዳዮችን ቀርብ ብለን ስንመለከት የሚከተሉትን ፈተናዎች እንጋፈጣለን፦

የተዛባ የፆታ አመለካከት	ብዙውን ጊዜ የመገናኛ ብዙኃን ያላቸው አቀራረብና ሥር የሰደዱ ማኅበራዊ አስተሳሰቦች ሴቶች ከወንዶች ያነሰ ብቃት ያላቸው ወይም ለሕዝብ አመራር የማይበቁ እንደሆኑ አድርገው የሚስሉ የተዛቡና አደገኛ አመለካከቶችን (Gender Stereotypes) ያሰራጫሉ። ይህ በሴት ዕጩዎች ላይ የሕዝብ ድጋፍ እንዲቀንስና የአመራር ችሎታቸውን በተመለከተ የጥርጣሬ ባህል እንዲፈጠር ያደርጋል። ይህም ሴቶች የፖለቲካ ቅቡልነትን በፓርቲያቸው እና በሕዝብ ውስጥ ለማግኘት ያለማቋረጥ እንዲታገሉ ያደርጋቸዋል።
ፆታዊ ጥቃቶች	በዓለም ዙሪያ እንዳሉ ሴቶች ሁሉ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ያሉም ሴቶች በተለያዩ አካላት ፆታ ላይ የተመሰረቱ ጥቃቶች ወይም ትንኮሳዎች (Gender-Based Violence (GBV)) ይደርስባቸዋል። ይህ ጥቃት አካላዊ፣ ሥነ ልቦናዊ፣ ወሲባዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ (ለምሳሌ የፓርቲ ሀብት ወይም የቢሮ ቦታ እንዳያገኙ መከልከል) ሊሆን ይችላል። የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ባደረገው ጥናት፣ በምርጫ ላይ የተሳተፉ ሴቶች የተለያዩ ሥነ ልቦናዊ፣ አካላዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቃቶች እንደገጠማቸው አረጋግጧል። ይህ ጥቃት በሕዝባዊ ቦታዎች ብቻ የተወሰነ አይደለም፤ በአካባቢ የመንግሥት ተቋማት፣ በማኅበረሰቦች ውስጥና በቤት ውስጥም ጭምር ሊከሰት ይችላል። ይህም ሴቶች በፍርሃት፣ በመሸማቀቅ፣ የራስ መተማመናቸውን እንዲያጡ በማድረግ በፖለቲካ ውስጥ የሚኖራቸው የተሳትፎ መጠናቸውን በእጅጉ ይወስነዋል።
ኦንላይን ትንኮሳ	የማኅበራዊ ሚዲያ መስፋፋት በአደባባይ የሚገለጡና በማኅበራዊና ፖለቲካ ጉዳዮች ላይ የጎላ ተሳትፎ የሚያደርጉ ሴቶችን ለማሸማቀቅ እና አስነዋሪ ለሆኑ ጥቃቶች አዳዲስ መንገዶችን ከፍቷል። በኢትዮጵያ ያሉ ሴት የፖለቲካ ሰዎች በተደጋጋሚ ለኦንላይን (Online Abuse) ጥቃቶች ይጋለጣሉ። እነዚህም የሞት ዛቻዎችን፣ የወሲባዊ ትንኮሳዎችን፣ ማስፈራሪያዎችን እና በአካላዊ ቁመናቸው፣ በአለባበሳቸው ወይም በግል ሕይወታቸው ላይ (physical appearance, attire, or personal life.) የሚያተኩር ፆታን ማዕከል ያደረገ (gender-motivated) የጥላቻ ንግግርን ያካትታሉ። ይህ ጠላትነት የተሞላበት የዲጂታል አካባቢ ሴቶች በሕዝባዊ ውይይቶች እንዳይሳተፉ ተስፋ፣ ወደ ፖርቲ ፖለቲካዎች ውስጥ እንዳይገቡ፣ ወደ ፖለቲካ መሪነት እንዳያድጉ ከፍተኛ ሥነ ልቦናዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል።

5.2.1.2. በፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ ያሉ ተቋማዊ እንቅፋቶች

በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ የፖለቲካ ውክልና የሚረጋገጠው በፖለቲካ ፓርቲዎች በሚኖር የነቃ ተሳትፎ ነው። የፖለቲካ ፓርቲዎች ለውክልና ዲሞክራሲ ዋና መሣሪያ እንደመሆናቸው መጠን የፓርቲዎቹ ውስጣዊ አሠራር የሴቶችን ፖለቲካዊ ስኬት የሚወስን ቁልፍ ነገር ነው። እንደ አለመታደል ሆኖ፣ ብዙ ፓርቲዎች ሳያውቁት ወይም ሆን ብለው የሴቶችን ተሳትፎ የሚያደናቅፉ ተቋማዊ አሠራሮች እና ባህሎች አሏቸው። የተለመዱትን የፓርቲዎች ውስጣዊ አሰራር አካል የሆኑ ተቋማዊ እንቅፋቶችን ስንመለከት የሚከተሉትን ጉልህ ጉዳዮች እናገኛለን፦

ግልጽ ያልሆኑ እና አድሎአዊ ሂደቶች	በፓርቲዎች ውስጥ የመሪዎች ምርጫ ሲደረግ፣ የእጩዎች ምልመላ፣ ምርጫ እና ወደ አመረራር የማሳደግ ሂደቶች ብዙውን ጊዜ ግልጽነት የጎደላቸው ናቸው። ይህም የሚሆነው ብዙውን ጊዜ በፓርቲዎች መተዳደርያ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ፖሊሲዎች ውስጥ ግልጽ የሆነ፣ ብቃት ላይ የተመሠረተ ሕግ አለመኖር፣ የፓርቲ መሪዎች ባህላዊ የአመራር ብቃት አላቸው ብለው የሚያስቧቸውን ወንዶችን በመሆኑ ወይም በወንዶች የበላይነት ውስጥ የገንዘብና ማኅበራዊ ትስስር ያላቸውን ወንድ እጩዎች እንዲመርጡ ሊያደርግ ይችላል። ሴቶች ብዙ ጊዜ ለዋና ዋና የውሳኔ አሰጣጥ ሚናዎች ችላ ይባላሉ። በምትኩ አነስተኛ የፖለቲካ ታዋቂነት ወደ ማያሰጡ ነገር ግን ብዙ ጊዜና ጉልበት ወደ ሚጠይቁ ቦታዎች ይገፋሉ።
ያልተመጣጠነ የሀብት ተደራሽነት	አብዛኛውን ጊዜ ሴቶች ለስኬታማ የፖለቲካ ሥራ የሚያስፈልጉ ወሳኝ ሀብቶችን የማግኘት ዕድላቸው አነስተኛ ነው። ይህም ከፓርቲ ለሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍ፣ የገንዘብ ለጋሾች እና የፖለቲካ ድጋፍ የሚሰጡ መደበኛ አባል ላልሆኑ ደጋፊዎች እና በጎፍቃደኞች ያላቸው ትስስር (ኔትዎርኮች) ወይም በተለምዶ እንደሚባለው "old boys' networks" ላይ ውስን ተደራሽነትን ይጨምራል። የምርጫ ቅስቀሳ ወጪ የሚበዛበት ሀገር ውስጥ፣ መጠነኛ የእጩዎች ምዝገባ ክፍያ እንኳን ትልቅ እንቅፋት ሊሆን ይችላል።
የተቋማዊ ድንጋጌዎች እጥረት	የብዙ ፓርቲዎች መመሥረቻ ሰነዶች እና መተዳደሪያ ደንቦች በፓርቲ መዋቅርና እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሴቶችን ውክልና ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ልዩ እርምጃዎች (ለምሳሌ የኮታ ውክልና) የላቸውም። እንደዚህ ዓይነት ድንጋጌዎች ቢኖሩም እንኳ፣ የወንዶች የበላይነት ያለበትን ነባራዊ ሁኔታ ለመቃወም የፖለቲካ ፍላጎት ስለሌለ በተግባር ሙሉ በሙሉ አይተገበሩም።

5.2.1.3. ጾታን ከግምት ውስጥ ያላስገባ የፓርቲ ባህል

የፖለቲካ ፓርቲዎች ልማዳዊ አመለካከት፣ አሰራር፣ አስተሳሰብ እና መደበኛ ያልሆነ ልምዶች ከህጎቻቸው ያላነሰ ተጽዕኖ ሊኖረው ይችላል። ጾታን ከግምት ውስጥ ያላስገባ የፓርቲ ባህል ሴቶችን ከመሳተፍና ከማደግ የሚያግድ የማይመችና ደጋፊነት የጎደለው ሁኔታ ይፈጥራል። እነዚህ የተለመዱ አመለካከቶች የሚከተሉትን ያካትታል፦

ጾታን መሠረት ያደረጉ ጥምር መለኪያዎች	ለወንድ የፖለቲካ ስኬት አዎንታዊና አስፈላጊ ተደርገው የሚታዩ ባሕርያት (ለምሳሌ ስልጣን ተኮር መሆን፣ የአደባባይ ተናጋሪ መሆን፣ ከፍተኛ ምኞት ማሳየት ወይም ቁርጠኝነት) በሴቶች ላይ ግን እንደ አሉታዊ ባሕርያት ይቆጠራሉ። ወንዶች ላይ ሲሆን ትክክለኛ የፖለቲከኛ መገለጫ የሚባሉ ጉዳዮች ወደ ሴቶች ሲመጡ “እዩኝ አዩኝ ባይ”፣ “ምላሰኛ”፣ "ጠበኛ" ወይም "ሥልጣን ፈላጊ" ተብለው ሊፈረጁ ይችላሉ። ይህም ጾታን መሠረት ያደረጉ ጥምር መለኪያዎች (Gendered Double Standards) እንዲኖር አድርጓል።
መደበኛ ያልሆኑ ግንኙነቶችና እንቅስቃሴዎች	የፖለቲካ ፓርቲዎች ማኅበራዊ ግንኙነቶች ብዙውን ጊዜ በመደበኛ ያልሆኑ ቦታዎች (ለምሳሌ በሆቴሎች፣ ባሮች፣ ጂም) ወይም በሌሊት ስብሰባዎች ላይ ይከናወናሉ። ይህ ደግሞ የቤተሰብ ኃላፊነት ያለባቸውን ሴቶች ወይም በወንዶች በሚመሩ ቦታዎች ላይ ምቾት የማይሰማቸውን ሴቶች ሊያገል ይችላል። ከመደበኛ የውሳኔ አሰጣጥ ቦታዎች መገለል የሴቶችን በፓርቲያቸው ውስጥ ሊኖራቸው የሚገባን የሥልጣን ወይም የሃላፊነት ዕድገት በእጅጉ ያደናቅፋል።

በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ያሉ የሴቶች ተግዳሮቶች ጥልቅ እና ብዙ ገጽታ ያላቸው ናቸው። እነዚህ ችግሮች የቁጥር ጉዳይ ብቻ ሳይሆኑ ሴቶችን እንደ እኩልና ብቃት ያላቸው የፖለቲካ ተዋናዮች ሙሉ በሙሉ ያልተቀበለ ሥርዓትና ባህል ውጤቶች ናቸው። እነዚህን መሰናክሎች መፍታት ይበልጥ አሳታፊና ጠንካራ ዲሞክራሲ ለመገንባት ቁርጠኛ የሆኑ የሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ኃላፊነት ነው። የሴቶችን ተሳትፎ በፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ ሊያሳዱግ የሚችሉ ስትራቴጂዎችን ምንድን ናቸው? የእርስዎ ፓርቲ ሴቶች አባላት የሚገጥማቸውን ተዳሮት ለመቋቋም የወሰደው አይነተኛ እርምርጃ አለ?

ከእነዚህ ስልቶች አንዳንዶቹ ወዲያውኑ ትልቅ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ ሲሆን ሌሎች ደግሞ ቀስ በቀስ ሊሳኩ የሚችሉ ናቸው። ያም ሆኖ ስትራቲጂዎቹ ስኬታማ ሆነዋል የሚባሉት በመካከለኛ እና የረዥም ጊዜ ውስጥ ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚያመጡት አጠቃላይ ውጤት ተመዝኖ የሚያሳየው ግልጽ የሆነ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ትርፍ መሆን አለበት[3]።

የፓርቲ መሪዎች ራሳቸው ወዲያውኑ የማሻሻያ ፍላጎት ወይም በካታችነት መርህ አስፈላጊነት ላይስማሙ ስለሚችሉ፣ ይህ የመመሪያ መጸሐፍ በዚህ ምዕራፍ የሚያቀርባቸው ስትራቴጂዎችና ምክረ ሀሳቦች ማሻሻያ ለማድረግ ለሚፈልጉ የፆታ እኩልነት ደጋፊዎች፣ ለውጥ እንዲያመጡ በፓርቲ መሪዎች ላይ ጫና ሊፈጥሩ ወይም ሊያበረታቱ ለሚችሉ ወትዋቾችና ጎትጓቾች (gender-equality advocates)፣ እንዲሁም በቀጥታ ለፓርቲ መሪዎች ግንዛቤ መፍጠርንና ማንቃትን ያለመ ነው። የፓርቲ መሪዎችን ማሳመን በሚያስፈልግበት ጊዜ ይህን መጸሐፍ ሲያነቡ የፆታ እኩልነት ደጋፊዎች የሚፈለጉትን ማሻሻያዎች እንዲጀምሩ ወይም እንዲያጸድቁ የፓርቲ መሪዎችን ሊያሳምኑ የሚችሉ መከራከሪያዎችና ተጨባጭ ስልቶች በእጃቸው ይኖራቸዋል። በተጨማሪም፣ የፓርቲ መሪዎች እነዚህን ስልቶች ለመተግበር ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል። በዚህም የፆታ እኩልነት ደጋፊዎች ስልቶቹን ለማቀድ፣ ለመተግበር እና ተጽዕኖውን ለመቆጣጠር መሪዎችን ለመርዳት ማቅረብ ይችላሉ።

እዚህ የተዘረዘሩት ብዙ ስልቶች ለሴቶች ወይም ለፆታ እኩልነት ደጋፊዎች ብቻ ሳይሆን ለሌሎች የፓርቲ አባላትም እንደሚጠቅሙ ማስታወስ ተገቢ ነው። የፓርቲ መሪዎችና የፆታ እኩልነት ደጋፊዎች የተጠቆሙትን ማሻሻያዎች ለመደገፍ በፓርቲዎች ውስጥ ያሉ ሌሎች ማንነት ላይ የተመሰረቱ ቡድኖችን ለምሳሌ ወጣትና አካል ጉዳተኞችን እንዴት ማሰባሰብ እንደሚችሉ እንዲያስቡ ይበረታታሉ። ለምሳሌ፣ የፓርቲ የሥነ-ምግባር ደንቦች ሁሉም የፓርቲ አባላት በተለይም የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዳህራቸው፣ የዘርና የቋንቋ ማንነታቸው፣ ዕድሜያቸው፣ አካላዊ ሁኔታቸው ወይም የትውልድ ቦታቸው ሳይለይ በፍትሐዊነትና ያለ አድልዎ እንዲታዩ ሊያደርጉ ይችላሉ።

5.2.2. ስትራቴጂ 1፡ የፆታ እኩልነትን በፓርቲ መዋቅሮች፣ ሂደቶች እና አሠራሮች ውስጥ ተቋማዊ ማድረግ

ምንም እንኳን የፖለቲካ ፓርቲዎች ደንቦች፣ ሂደቶች እና መዋቅሮች በእጅጉ ቢለያዩም፣ አብዛኛዎቹ ፓርቲዎች አሠራራቸውን የሚመሩባቸው መመሥረቻ ሰነዶችና የአሰራር መመሪያዎች አሏቸው። በተለይም በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 ምዕራፍ ሦስት ላይ ከአንቀጽ 71 እስከ 74 በተዘረዘረው መሰረት አንድ የፖለቲካ ፓርቲ የሚከተሉት ዋና ዋና ሰነዶች ይኖሩታል ተብለው የተዘረዘሩት የመመስረቻ ጽሑፍ፣ የፖለቲካ ፕሮግራም፤ የመተዳደሪያ ደንብ፣ እና የሃብትና ንብረት፣ የገቢና የወጪ ሰነዶች ናቸው። ስለዚህ እነዚህ የፓርቲ ሰነዶች አንድ ፓርቲ በይፋም ሆነ ይፋዊ ባልሆነ መንገድ እንዴት እንደሚሠራ፣ በፓርቲዎች ውስጥ ለወንዶችና ለሴቶች የፖለቲካ ዕድገት ምን ያህል እኩል ዕድሎች እንደተሰጠ ያሳያሉ። በዚህ መሠረት፣ ይህ ስትራቴጂ በፓርቲ ሰነዶች፣ ሂደቶች እና አሠራሮች ውስጥ የፆታ እኩልነትን እንደ መርህ እና የፆታ ሚዛንን እንደ ግብ ለማስተዋወቅ በሚረዱ ስልቶች ላይ ያተኩራል።

5.2.2.1. የፓርቲውን የሥርዓተ-ፆታ ኦዲት (Gender Audit) ያካሂዱ

ማንኛውም ጉዞ የሚጀምረው መነሻ ነጥብን በመረዳት ነው። የሥርዓተ-ፆታ ኦዲት ወይም “ራስን መገምገም” የሴቶችን የፖለቲካ ዕድገት ሊያደናቅፉ የሚችሉ ስውር ቦታዎችን እና አድሏዊ አሠራሮችን (መደበኛም ሆነ ኢመደበኛ) ለመለየት የሚያገለግል ጠቃሚ መሣሪያ ነው። እርስዎ የፓርቲ ዓባል ወይም መሪ ቢሆኑ ይህን መመሪያ ለመከተል ፍቃደኛ ነዎት? እንግዳውስ ይህን ስትራቴጂ ተግባራዊ ለማድረግ የሚከተሉትን ሂደቶች ይከተሉ።

ምን መመርመር ያስፈልጋል?	የፓርቲውን ሁሉም ሰነዶች ማለትም የመመስረቻ ጽሑፍ (ቻርተሩን)፣ የፖለቲካ ፕሮግራም፤ የመተዳደሪያ ደንብ፣ እና የሃብትና ንብረት፣ የገቢና የወጪ ሰነዶች፣ ፖሊሲዎችን እና የውስጥ ደንቦችን በጥልቀት ይመርምሩ። ከመደበኛ ደንቦች ባሻገር፣ መደበኛ ያልሆነውን የፓርቲ ባህል፣ የአባላትን ለሴት አመራሮች ያላቸውን አመለካከት፣ እንዲሁም ወንዶችና ሴቶች በተለምዶ የሚሠሯቸውን የሥራ ዓይነቶች ይፈትሹ። ኦዲቱ ከተለያዩ ብሔሮች፣ ክልሎች ወይም ማኅበራዊ-ኢኮኖሚያዊ አስተዳደግ የመጡ ሴቶች እንዴት እንደሚወከሉ ወይም እንደሚስተናገዱ ያለውን አድሏዊነት መፈተሽ አለበት።
እንዴት ማካሄድ ይቻላል?	በጣም ውጤታማ የሆኑ ግምገማዎች ሴቶች የተካተቱበት በፓርቲው ከፍተኛ አመራሮች፣ ቁልፍ የሥራ አስፈጻሚ አባላት እና የሥርዓተ-ፆታ ባለሙያዎችን ባካተተ የውስጥ የሥራ ቡድን (ኮሚቴ) ይመራሉ። ይህ የሥራ ቡድን አመራሮችን ማካተት ያስፈለገው የአመራሩን ድጋፍ የሚያረጋግጥ ሲሆን ፓርቲው በኦዲት ግኝቶቹ ላይ ተመስርቶ አስፈላጊ የማስተካከያ እርምጃ የመውሰድ ዕድሉን ይጨምራል። የውስጥ ቡድን ማቋቋም የማይቻል ከሆነ፣ የፓርቲው የሴቶች ክንፍ ይህንን ጥረት ሊመራ ይችላል ወይም የውጭ የሥርዓተ-ፆታ ተንታኝ መቅጠር ይቻላል።
መቼ ማካሄድ ይመከራል?	የሥርዓተ-ፆታ ኦዲት ለማድረግ ከምርጫ በፊትና በኋላ ያለው ጊዜ ተስማሚ ነው። ከምርጫ በፊት፣ ሕጎችን መገምገም እና የዘመቻ ዕቅድዎን ለማሳወቅ የአባላትን አስተያየቶች መሰብሰብ ይችላሉ። ከምርጫ በኋላ ደግሞ፣ የሴት ዕጩዎቻችሁ ምን ያህል እንደሠሩና ምን ቃል ኪዳኖች እንደተፈጸሙ ለማየት የድምፅ ውጤቶችን እና የመራጮችን አስተያየቶች ከሥርዓተ-ፆታ አንፃር መተንተን ይችላሉ።

እንዲህ አይነት ኦዲቶችን ሲያደርጉ ፓርቲዎ በእውነት ለሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ምን ያህል ምቹ እንደሆኑ ያሳያል። ክፍተቶች እንኳን ቢኖሩ ለማሻሻያ የሚያስፈልጉትን መረጃዎች ይሰጥዎታል።

ሳጥን 5.1: ሥርዓተ-ፆታ-ተኮር ለሆኑ ፓርቲዎች መመዘኛዎች ማረጋገጫ ዝርዝር (Checklist)

- የፖለቲካ ፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ ወንዶችና ሴቶች በሁሉም የፓርቲ ውሳኔ ሰጪ አካላት፣ በፓርቲ የምርጫ ዝርዝሮች እና ለሁሉም በሚሾሙና በሚመደቡ ቦታዎች ላይ ሚዛናዊ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያረጋግጣል።
- የፆታ እኩልነት በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ፣ ፖሊሲዎች እና ፕሮግራሞች ውስጥ እንደ መሠረታዊ የፓርቲ እሴት ተጠቅሷል።
- ፓርቲው የአካባቢ፣ የክልል እና የፌደራል ደረጃ አባላትን እንዲሁም የሥራ አስፈፃሚ አባላትን የያዘ ወቅታዊ መረጃ አለው፤ ሁሉም መረጃ በፆታ ተለይቶ (ወንድ እና ሴት) ተቀምጧል።
- ፓርቲው ሴቶችን የሚጎዱ ሂደቶችን እና ልማዶችን ለመለየት፣ እንዲሁም የፆታ እኩልነት ላይ ያለውን እድገት ለመገምገም መደበኛ የፆታ ኦዲት ያካሂዳል።
- የተወሰኑ የፆታ እኩልነት ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች በግልጽ ተቀምጠዋል፤ ከእነዚህ ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ጉዳዮች መካከል አንዳንዶቹ በፓርቲው የምርጫ ቅስቀሳዎችና ቃልኪዳኖች ውስጥ ተካትተዋል።
- ተጽኖ የማይደረግበት (autonomous)፣ ንቁ እና ለሕዝብ በሚታይ መልኩ የተዋቀረ የፆታ እኩልነትን የሚደግፍ መዋቅር (ለምሳሌ፣ የሴቶች ክፍል ወይም ክንፍ) በፓርቲው ውስጥ ተቋቁሟል፣ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ያደርጋል እንዲሁም በማርቲዎ አካላት ይከበራል።
- የፓርቲው የፆታ እኩልነት መዋቅር (ክፍል ወይም ክንፍ) በየጊዜው በፓርቲው ውስጥና በሕዝብ መካከል ስለ ፆታ እኩልነት ጉዳዮች ውይይት በነጻነት ማካሄድ ይችላል።
- የፓርቲው የሴቶች ክፍል ወይም ክንፍ የፓርቲው እና በሲቪል ማኅበረሰብ፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ በፓርላማና በመንግሥት ውስጥ ባሉ የሴቶች መካከል እንደ አገናኝ ድልድይ ሆኖ ያገለግላል።
- የፓርቲው ሀብቶች በሴትና በወንድ አባላትና ዕጩዎች መካከል በፍትሃዊነት ይሰራጫል።
- የፖለቲካ ፓርቲው በጀቱ ውስጥ ለፆታ እኩልነት ዘዴና በፓርቲው ውስጥ ለሚኖሩ የፆታ እኩልነት ፖሊሲዎች/ስትራቴጂዎች የገንዘብ ድጋፍን ይጨምራል።
- ፓርቲው ወንዶችም ሆኑ ሴቶች በፆታ ላይ የተመሰረቱ የሥነ ምግባር ጉድለቶች ወይም አድሎዎችን ለፓርቲው ትኩረት እንዲያደርሱ የሚያስችል የቅሬታ አቀራረብ ዘዴና አሰራር አቋቁሟል።

5.2.2.2. የፓርቲ የሥርዓተ-ፆታ የድርጊት መርሃ ግብር (Gender Action Plan) ማዘጋጀትና መተግበር

የሥርዓተ-ፆታ ተዋጽኦን ኦዲት/መገምገም (gender audit) በራሱ ፍጻሜ አይደለም። ግኝቶቹ ለለውጥ ግልጽ የሆነ ፍኖተ ካርታ ለማዘጋጀት ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው። የፓርቲ የሥርዓተ-ፆታ ተዋጽኦ የድርጊት መርሃ ግብር በኦዲት ላይ የተለዩትን ክፍተቶች ለማስተካከል የተወሰኑ፣ በጊዜ የተገደቡ እርምጃዎችን የሚያስቀምጥ ስልታዊ ሰነድ ነው። ይህም ፓርቲው የፆታ እኩልነትን ለማሳደግ የሚረዱትን ፖሊሲዎች፣ ስልቶች፣ የአሰራር ሂደቶች፣ መዋቅሮች እና እንቅስቃሴዎች ለማሻሻል የሚያስፈልገውን መረጃ ያቀርባል።

ምን ማካተት አለበት?	የማሻሻያ የሥራ ዕቅዱ ለምሳሌ የሚከተሉትን ጉዳዮችን ተጨባጭ ለውጦችን ማቅረብ አለበት፡- • የሴቶችን ውክልና ለማረጋገጥ የፓርቲውን ደንቦች ማሻሻል፤ • የፆታዊ ትንኮሳና መድልኦን በፓርቲው ውስጥ ለመከላከል አዲስ የስነምግባር መመሪያ ማስተዋወቅ፤ • እምቅ አቅም ያላቸውን ሴት አባላት ለመሪነት ለማብቃት የሚያስችሉ የመሪነት ልምምድ ለመስጠት፣ ለመምከርና ለማሰልጠን የአቅም ግንባታ ፕሮግራም ማዘጋጀት፤ • ሴቶች የምርጫ ቅስቀሳ ሀብቶችን በእኩልነት ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ ስልቶችን መዘርጋት።
ተቀባይነትን እንዴት ማግኘት ይቻላል?	የሥርዓተ-ፆታ ተዋጽኦን ኦዲት ያካሄደው የሥራ ቡድን ዕቅዱን የማዘጋጀት ሂደቱን መምራት አለበት። ዕቅዱ በሁሉም የፓርቲው አባላት ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ፣ ረቂቆች ለሁሉም አባላት አስተያየትና ውይይት እንዲቀርቡ መደረግ አለበት። ይህ አሳታፊ ሂደት ግንዛቤ ለመፍጠርና ለስኬታማ ትግበራ የሚያስፈልገውን የፓርቲ-አቀፍ ቁርጠኝነት ለማረጋገጥ ይረዳል።

ሰነዱ ከጸደቀ በኋላ፣ የፓርቲው አመራር በሁሉም ደረጃ የሚገኙ የፓርቲው አባላት የሥርዓተ-ፆታ የድርጊት መርሃ ግብር እንቅስቃሴዎችን እና ዓላማዎችን ሙሉ በሙሉ እንዲረዱ እና እንዲያከብሩ ማድረግ አለበት። ከዚህ በታች ያለው ሠንጠረዥ የፓርቲ ሥርዓተ-ፆታ የድርጊት መርሃ ግብርን ሊያካትቱ የሚችሉ የተለያዩ ክፍሎችን ለይቶ ለምሳሌ ያህል ያብራራል።

ሰንጠረዥ 5.1፡ የፓርቲ የሥርዓተ-ፆታ የድርጊት መርሃ ግብር፡ ሊያካትታቸው የሚችል ቁልፍ ጉዳዮች

የትግበራ አይነት	ትግበራ
የውስጥ የፓርቲ አሰራሮችን የሥርዓተ-ፆታ ኦዲት ማድረግ	• የፓርቲውን ቁልፍ ሂደቶች እና ተግባራት፣ በፆታ እኩልነት ጉዳዮች ላይ ያለውን አመለካከት፣ እንዲሁም በፓርቲው ውስጥ ያለውን የሥራ እና የሥልጣን ክፍፍል በፓርቲ አባላት ጾታ መሰረት እራስን መገምገም ወይም የሥርዓተ-ፆታ ኦዲት ማድረግ።
ለፆታ እኩልነት የሥራ እቅድ የፓርቲ አመራር ድጋፍ መፍጠር እና ማጎልበት	• የሥርዓተ-ፆታ ኦዲት ግኝቶች ላይ ተመስርቶ ለፓርቲው የተለየ የሥራ ክፍሎች የፆታ እኩልነት የሥራ እቅድ ማዘጋጀት። • የፓርቲው መዋቅር ዋና ዋና አካላት የዚህን የሥራ እቅድ ትግበራ ቢያንስ በየአራት ዓመቱ አንድ ጊዜ እንዲወያዩበት እና በተደረገው መሻሻል ላይ በመመርኮዝ አዲስ የሥራ እቅዶችን ለማዘጋጀት እንዲስማሙ ማድረግ።
የፓርቲ መመስረቻ ሰነዶችን ማጠናከር	• በፓርቲው የሕጎ ሰነዶች ውስጥ ሴቶች በፓርቲው የተለያዩ መዋቅር ውስጥ እና በተለይም በፓርቲ የውሳኔ አሰጣጥ አካላት እና ሂደቶች ውስጥ ዝቅ ቢል ከዚህ ማነስ የለበትም የሚባለውን ውክልና (ensure minimum representation) እንዲኖራቸው የሚያስችሉ ድንጋጌዎችን ማካተት። • በፆታ ላይ የተመሰረተ መድልዎ እና ትንኮሳን ለመከላከል የሚያስችሉ የውስጥ ፓርቲ የስነ-ምግባር ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን ማካተት ወይም ማጠናከር።
የሴቶች ክፍልን በፓርቲ ሕጎች/ደንቦች ውስጥ ማካተት	• በፓርቲው ውስጥ የራሳቸውን የቻሉ ሆነው የፓርቲ መዋቅር አካል የሆኑ የሴቶች አደረጃጀቶችን ወይም ክፍሎችን ("የሴቶች ክንፍ") ማቋቋም ወይም ማጠናከር። • የሴቶች ክፍል/ ክንፍ በውሳኔ አሰጣጥ አካላት እና ሂደቶች ውስጥ ውክልና እንዲኖረው የሚጠይቁ ድንጋጌዎችን በፓርቲ ሕጎች ወይም ደንቦች ውስጥ ማካተት።
የፓርቲውን የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት መዋቅርን/የሴቶች ክፍልን መደገፍ	• የሴቶች ክፍፍል/ክንፍ ሊያከናውኗቸው የሚችሉ የተወሰኑ ተግባራትን ማዘጋጀት። ለምሳሌ የምክር ፕሮግራሞችን፣ ሥልጠናዎችን፣ የልምድ ልውውጥ መድረኮችን ወይም ክፍት ውይይቶችን መረሐ ግብሮችን ማዘጋጀጥ • የሴቶች ክፍል/ክንፍ እነዚህን ተግባራት ለማከናወን የሚያስችል በቂ ሀብት ማግኘታቸውን ማረጋገጥ።
በፆታ የተከፋፈለ መረጃ (sex-disaggregated data) መሰብሰብ	• በፆታ የተከፋፈለ የአባልነት ስታቲስቲክስን (sexdisaggregated data) በመደበኛነት መሰብሰብ እና ማከማቸት። ይህም በአካባቢ እና በክልል ደረጃ ያሉ መረጃዎችን ይጨምራል።
የፓርቲ የሥራ ሂደቶችን ይበልጥ ግልፅ እና ፍትሃዊ በማድረግ የውስጠ ፓርቲ ዲሞክራሲን ማጎልበት	• የፓርቲ አባላትን ምልመላ፣ የአባላትን እድገት፣ የዕጩዎች ምርጫን፣ የውሳኔ አሰጣጥን እና የሃብት ክፍፍልን በተመለከተ ያሉትን የውስጠ ፓርቲ ሂደቶችን በግልጽ እና ግልፅ በሆነ መንገድ እና በዲሞክራሲያዊ መርሆዎች መሰረት እንዲተገበሩ ማበረታታት። • የፓርቲ የሥራ ሂደቶች በግልፅ እና ለፆታ እኩልነት ስሜታዊነት ባለው መንገድ መፃፋቸውን ማረጋገጥ። • እንደ አዲስ ተመልምለው ፓርቲውን ለተቀላቀሉ ወንድ እና ሴት የፓርቲ አባላት በሙሉ፣ ስለ ፆታ እኩልነት በፖለቲካ ፓርቲው ውስጥ የሚያስተምር ሞጁልን ጨምሮ የማስተዋወቂያ ስልተናዎችን መስጠት።
ሴቶችን እንደ ፓርቲ መሪዎች እና የምርጫ እጩዎች ለማብቃት የውስጠ ፓርቲ እርምጃዎችን መውሰድ	• በፓርቲው ውስጥ በፓርቲው ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚ ደረጃ ላይ እና በቁልፍ የፓርቲ ሚናዎች ውስጥ የሴቶችን ድርሻ ከጊዜ ወደ ጊዜ ለመጨመር የሚያስችል የሥራ እቅድ መከተልና ተግባራዊ ማድረግ። ይህም የሴቶችን ድርሻ በፓርቲው የአባልነት ቁጥር ላይ የሚያንፀባርቅ መሆን አለበት። • በፓርቲው ውስጥ የሴቶችን ውክልና ለመጨመር ጊዜ-ገደብ ያላቸው መለኪያዎችን (set time-bound benchmarks)፣ ዒላማዎችን ወይም ኮታዎችን በፈቃደኝነት ማውጣት።

ሥልጠና እና አመራር አቅም ማጎልበቻ ዶጋፎችን ማደራጀት	• ለሴት አባላት የተለየ የሥልጠና ዓይነቶችን ማዘጋጀት (በአመራር ክህሎት ማጎልበት፣ ሴቶችን እንደ ዕጩ ማዘጋጀት፣ ወዘተ)።
የውስጠ ፓርቲ ግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን ማካሄድ	• ስለ ፆታ እኩልነት የፓርቲውን ፖሊሲ ለሁሉም የፓርቲ አባላት ግንዛቤ ማስጨበጥ። • የፓርቲውን የፆታ እኩልነት ዓላማዎች እና ፖሊሲ ለወንድ እና ለሴት የፓርቲ አክቲቪስቶች፣ አባላት እና ባለሥልጣናት፣ ለፓርቲው እና የሕዝብ የሚጫወቱትን ሚና ጨምሮ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ሴሚናሮችን ማዘጋጀት።
በፆታ እኩልነት ጉዳዮች ላይ ተጨባጭ የፓርቲ አቋሞችን ማዘጋጀት	• ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች መወሰን እና የተወሰኑ የፆታ እኩልነት ጉዳዮችን እና ተግዳሮቶችን የሚመለከቱ ተጨባጭ የፓርቲ አቋሞችን ማዘጋጀት። • ፓርቲው ተቃዋሚ ሲሆን (የፓርቲው የሴቶች ክንፍ ብቻ ሳይሆን) እንደዚህ ያሉ አቋሞችን እና ፖሊሲዎችን ለማስተዋወቅ ዘመቻዎችን ማደራጀት አለበት። ፓርቲው ገዥ ፓርቲ ሲሆን ደግሞ እንደዚህ ያሉ አቋሞችን እና ፖሊሲዎችን የማስተዋወቅ ሂደቱን መምራት እና በትግበራቸው መፅናት አለበት።

5.2.2.3. የሴቶችን ተዋጽኦ በፓርቲ በመዋቅሮች ውስጥ መወከላቸውን በሕጎች ማረጋገጥ

ሴቶች ከአባልነት ወደ ፓርቲው የአመራርነት የሥልጣን ቦታዎች እንዲሸጋገሩ ለማድረግ፣ ፓርቲው በሁሉም ቁልፍ የውሳኔ አሰጣጥ አካላት እና ሂደቶች ውስጥ መገኘታቸውን የሚያረጋግጡ ዝርዝር ደንቦችን ማውጣት አለበት። እነዚህን በፓርቲው የመዋቅር አካላት ውስጥና የሥራና የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ አስገብተን ልናያቸው እንችላለን።

በመዋቅር አካላት ውስጥ ውክልና	የፓርቲዎ ሕግ ሴቶች በአመራር ቦታዎች ላይ ቢያንስ በተወሰነ ቁጥር እንዲገኙ የሚያስችሉ ድንጋጌዎችን ያካተተ ይሁን። ይህ ማለት ለአስፈፃሚ ኮሚቴው ከ30-40% የሴቶች ኮታ፣ በቁልፍ ኮሚቴዎች (ለምሳሌ፡ ፋይናንስ፣ አስተዳደር እና የእጩዎች ምልመላ) ውስጥ ዝቅተኛ ውክልና፣ ወይም ደግሞ በጀርመን አረንጓዴ ፓርቲ ጥቅም ላይ እንደሚውለው አንድ ወንድና አንዲት ሴት በጋራ ሊቀመንበር የሚሆኑበት "ሁለትዮሽ አመራር" ሞዴል ሊሆን ይችላል።
በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ውክልና	ሴቶች በአመራር ቦታዎች ላይ ብቻ ሳይሆን በሁሉም የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ውስጥም ጠንካራ ድምጽ እንዲኖራቸው ያረጋግጡ። ለምሳሌ፣ በፓርቲ ኮንግረሶች፣ ጉባኤዎች እና ዓመታዊ ጠቅላላ ስብሰባዎች ላይ የሴቶች ውክልና ከፓርቲው አባላት ቁጥር ጋር እንዲመጣጠን አስገዳጅ ደንብ ያውጡ። ይህ አመለካከታቸው በሁሉም ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ተሰምቶ እንዲከራከርበት ዋስትና ይሰጣል።

ሳጥን 5.2: የሴቶችን ተዋጽኦ በፓርቲ በመዋቅሮች እና የውሳኔ ሰጪ አካላት ውስጥ መወከላቸውን የሚያረጋግጡ ዓለም አቀፍ ተመኩሮዎች

በመዋቅር አካላት ውስጥ ውክልና	በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ውክልና
በተለያዩ የአውሮፓ ሀገራት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች በውስጥ ደንባቸው ውስጥ ሴቶች በፓርቲያቸው ውሳኔ ሰጪ የመዋቅር አካላት ውስጥ እንዲወከሉ የሚያስችል ድንጋጌዎችን ያካተቱ ሲሆን የሴቶች ውክልና የሚያስፈልግባቸውን የሥራ መደቦች የሚገልጹ አንቀጾችን አስቀምጠዋል። ከእነዚህም መካከል፦ • **የእንጊሊዝ የሰራተኞች ፓርቲ (United Kingdom Labour Party)**፦ ፓርቲው በሀገር አቀፍ ደረጃ 24 አባላት ያሉት ሲሆን ከነዚህ መካከል ሦስቱ የፓርላማ አባላት መሆን አለባቸው። ከሦስቱ የፓላማ አባላት እና የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተወካዮች መካከል ቢያን አንዷ ሴት መህን አለባት። • **የጀርመን ክርስቲያን ዴሞክራቲክ ዩኒየን (German Christian Democratic Union)**፦ ለፓርቲ የሥራ አስፈፃሚ ወይም ኃላፊዎች 33 በመቶ የሴቶች ኮታ ተግባራዊ ያደርጋል። ይህ ገደብ ካልተሟላ የውስጥ ምርጫዎች እንደገና ይካሄዳሉ። • **የኖርዌይ ክርስቲያን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (KrF)** የእጩዎች አቀራረብ መመሪያዎች በማንኛውም የምርጫ ክልል ውስጥ ከሚቀርቡት ዋናዎቹ ሦስት እጩዎች መካከል አንድ ሴት፣ አንድ ወንድ እና አንድ ወጣት መሆን እንዳለባቸው ይገልጻል።"	ፓርቲዎች በሕጎቻቸው ወይም በመተዳደሪያ ደንቦቻቸው ውስጥ በእያንዳንዱ በውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች እና እንቅስቃሴዎች ውስጥ እንዲኖር ዝቅተኛ የሚባለውን የጾታ ውክልና ለማረጋገጥ (ensure minimum representation) ለማድረግ አንቀጾችን ማካተት ይችላሉ። ለምሳሌ የሚከተሉትን ፓርቲዎች እንመልከት፦ • **የካናዳ የኦንታሪዮ ሊበራል ፓርቲ (Liberal Party of Ontario)**፦ በዓመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ የሴቶች እና የወንዶች እኩል ውክልና እንዲኖር ይጠይቃል። (ከ18 የምርጫ ክልል ውስጥ ካሉ የ አባላት ማህበር ውስጥ ከእያንዳንዱ አራት ሴቶች እና አራት ወንዶች እንዲወከልይ ይደረካል)። • **የእንጊሊዝ የሰራተኞች ፓርቲ (United Kingdom Labour Party)**፦ወደ ፓርቲው ልዩ ልዩ ጉባኤ እና ወደ አመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ በሚላኩ ልዑካን መካከል የፆታ እኩልነትን ለማረጋገጥ እርምጃዎችን ይወስዳል። • **የአሜሪካን ዴሞክራቲክ ፓርቲ (United States Democratic Party)**፦ ብሔራዊ ኮንቬንሽኑ በወንዶችና በሴቶች እኩል የተከፋፈሉ ልዑካንን ያቀፈ ነው። • **የአሜሪካን ሪፐብሊካን ፓርቲ (United States Democratic Party)**፦ እያንዳንዱ ግዛት ወደ ሪፐብሊካን ብሔራዊ ኮንቬንሽን በሚላኩ ልዑካኖቹ መካከል የወንዶችና የሴቶች እኩል ውክልና እንዲኖር ይጥራል”

5.2.2.4. የፓርቲውን የሴቶች ክፍል ወይም ክንፍ ማጎልበት

የፖለቲካ ፓርቲዎች የሴቶች ክፍል ወይም ክንፍ በፓርቲ ውስጥ የፆታ እኩልነትን ለማስፈን ዋነኛ አቅሞች ሊሆኑ ይችላሉ። የሴቶች ክንፍ በፓርቲው ውስጥ የሴቶችን ሰፊ ተሳትፎ ለማመቻቸት ሊቋቋም የሚችል የውስጥ ፓርቲ አካላት ናቸው። የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ ለማሳደግ ወሳኝ ሚና መጫወት ይችላል። ይህም የአባላትን የጋራ ጉዳዮች በማስተባበር፣ የሴቶችን የአመራር ክህሎት በማጎልበት፣ አዳዲስ አባላትና እጩዎችን ለመምረጥ በመርዳት እንዲሁም ለፓርቲ መሪነት ምርጫ በሚወዳደሩ ሴቶች ላይ ግብዓቶችንና/ወይም ድጋፍ በማቅረብ አይነተኛ ሚና የሚጫወት ነው። ክንፎቹን እንዴት ማጎልበት ይቻላል?

የሴቶች ክንፍ ተቋማዊ	የሴቶች ክንፍ በፓርቲው መተዳደሪያ ደንቦችና መመሪያዎች ውስጥ በይፋ እውቅና እንዲያገኝ ያድርጉ። የሴቶች ክንፍ ግልጽ የሆነ ተልዕኮ፣ የራሱ የሆነ በጀት እና የውሳኔ ሃሳቦቹን ለፓርቲው አመራር የሚያደርስበት መደበኛ የግንኙነት መስመሮች እንዳሉት ያረጋግጡ።
ክንፉን ከሁሉም የፖሊሲ ዘርፎች ጋር ያዋህዷቸው	የሴቶችን ክንፍ "በሴቶች ጉዳይ" ብቻ አይገድቡት። በፆታ እኩልነት እይታ ኢኮኖሚን፣ ግብርናን ወይም የውጭ ጉዳይን ጨምሮ በተለያዩ የፖሊሲ ዘርፎች ላይ ዕውቀታቸውን እንዲያካፍሉ እና ምርምር እንዲያደርጉ ያጎልብቷቸው።
ውክልና እንዲኖራቸው ያድርጉ	የሴቶች ክንፍ ኃላፊዎች በፓርቲው ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እና ሌሎች ቁልፍ አካላት ውስጥ ስልጣን ያላቸው አባላት መሆናቸው ያረጋግጡ። ይህ ክንፉ እንዳይገለል ለመከላከል እና ግብዓቶቹ በሁሉም የፓርቲ ውሳኔዎች ላይ ትርጉም ያለው ተጽዕኖ እንዲኖራቸው ለማድረግ ወሳኝ እርምጃ ነው።

5.2.3. ስትራቴጂ 2፡ የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ ለማሳደግ በፈቃደኝነት እርምጃዎችን መውሰድ

የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎን መሻሻል የተገደበው በፓርቲው ኦፊሴላዊ ሰነዶች ውስጥ ተሳትፏቸውን ለመደገፍ የሚያስችሉ ልዩ እርምጃዎች ባለመኖራቸው ወይም ለተወሰኑ የፓርቲ አደረጃጀቶች ድጋፍ ባለመኖሩ ብቻ አይደለም። ሴቶች በፖለቲካ ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ ውስን የሆነው የሀብት፣ የመረጃ እና የምርጫ ዘመቻ ማካሄጃ መሳሪያዎች የማግኘት እድል የተገደበ ስለሆነም ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት ወንዶች በፖለቲካው ዓለም “የቅድሚያ ጅማሬ” (“head start”) እድል ስላላቸው ነው። በሁሉም የኢትዮጲያ የፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥም ሆነ በፌዴራል የሕዝብ ተውካዮች ምክር ቤት እና የክልል ምክርቤቶች ውስጥ የወንዶች ውክልና ከሴቶች እጅግ የላቀ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ወንዶች በፓርላማ ውስጥም ሆነ በፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ በውሳኔ ሰጪ መዋቅሮች ውስጥ የበላይነት አላቸው። ይህም የሆነበት ምክንያት ወንዶች ሀብት በማሰባሰብ እና የፖለቲካ አውታረ መረቦችን (ኔትዎርኮችን) በሚገባ ለመቆጣጠር በመቻላቸው ነው። ለዚህም ነው በበርካታ ሀገራት ውስጥ የፖለቲካ “የወንዶች ጉዳይ”ተብሎ የሚገለጸው። ይህ ሁኔታ እንዴት መለወጥ ይችላል?

5.2.3.1. የፓርቲውን ሴት አባላት ማወቅ

ማንኛውንም ምልመላ ከማካሄዱ በፊት አንድ የፖለቲካ ፓርቲ አስቀድሞ በውስጡ ያሉትን የሰው ሀብት መረዳት አለበት። ብዙ ፓርቲዎች ስለ ሴት አባላቶቻቸው ያላቸው መረጃ ውስን ነው። የፖለቲካ ፓርቲውች የሴት አባልት ቁጥራቸውን፣ በፓርቲ ውስጥ ያላቸውን የሥራ ድርሻ፣ የትምህርት ደረጃ፣ ልዩ ክህሎቶቻቸውን እና ብቃቶቻቸውን ጨምሮ በቂ ሁኔታ የተደራጀ መረጃ የላቸውም። ሆኖም ይህን መሰል መረጃ በተደራጀ መልኩ መኖር ለፓርቲው እምቅ አቅም ያላቸው መሪዎችን፣ አማካሪዎችን እና ዕጩዎችን ለመለየት ወሳኝ ግብዓት ነው።

አንድ ፓርቲ ይህን አስፈላጊ መረጃ ለመሰብሰብ የፆታ ኦዲት ማካሄድ አለበት። የፓርቲው የሴቶች ክንፍ ወይም ለፆታ እኩልነት የተቋቋመ ኮሚቴ ይህንን ጥረት ሊመራው ይችላል። ኦዲቱ ስለ ሴት አባላት ከቀላል ቁጥሮች በላይ መሆን አለበት። በጥቅሉ ፓርቲያችን ይህን ያህል የሴት አባላት አሉት ከማለት ባሻገር ቢቻል የሚከተሉትን መረጃዎች ማካተት ይኖርበታል፡-

ፓርቲውን ለመቀላቀል የመረጡበት ምክንያት	ፓርቲውን የተቀላቀሉት ለምንድን ነው? የፖለቲካ ፍላጎታቸው ምንድን ነው?
አሁን ያሉባቸውና ያለፉባቸው ሚናዎች	በፓርቲው መዋቅር ውስጥና በማኅበረሰባቸው ውስጥ ምን አይነት የኃላፊነት ቦታዎችን ይዘው ነበር?
ክህሎቶችና ሙያዊ ብቃት	ያላቸው ሙያዊ ብቃት፣ የትምህርት ዝግጅት እና ልዩ ክህሎቶች ምንድናቸው?
ተሳትፎና ሀሳቦች	በማኅበረሰብ ማኅበራት ውስጥ ይሳተፋሉ? በፓርቲው ውስጥ የሴቶችን ተሳትፎ ለመጨመር ያላቸው ሀሳቦች ምንድናቸው?

ይህ መረጃ ከአባላት ከምልመላ እስከ እጩዎች ምርጫ ድረስ የፓርቲውን ስልት በሁሉም ገጽታዎች ላይ መረጃ ለመስጠት ጥቅም ላይ መዋል አለበት።

5.2.3.2. አዳዲስ ሴት አባላትን መመልመል እና በፓርቲው ውስጥ ማቆየት

ብዙ ሴቶችን መመልመል ወደፊት ሊኖሩ የሚችሉ ሴት እጩዎችን፣ ካድሬዎችን፣ ታጋዮችን እና መሪዎችን ቁጥር ለማስፋት ወሳኝ እርምጃ ነው። በዓለም ዙሪያ በብዙ ቦታዎች የፓርቲ አባልነት እየቀነሰ በመምጣቱ፣ ይህ ስልት የፓርቲን የረጅም ጊዜ ጤና ለመጠበቅ በጣም አስፈላጊ ነው። አንድ ፓርቲ ለሴቶች ተስማሚ በሆነ ቁጥር፣ ለተለያዩ ሴቶች የበለጠ ማራኪ ይሆናል።


ንቁ የምልመላ ስልቶች (Active Recruitment)	የፓርቲ መሪዎች እና የፆታ እኩልነት አቀንቃኞች ሴቶችን ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች በንቃት መፈለግ አለባቸው። ይህ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፡- • የሴቶች የሙያ ማኅበራትን፣ ዩኒቨርሲቲዎችን እና የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች ውስጥ ያሉ ሴቶችን ማነጋገር እና የፓርቲ አባል እንዲሆኑ ማሳመን። • በሕግ፣ በኢኮኖሚክስ እና በማኅበረሰብ አደረጃጀት ዘርፎች የተለየ ክህሎት ያላቸውን ሴቶች “ማደን” (Head-hunting) እና ለፓርቲ አባልነት መመልመል። • ተመልማይ ሴቶችን ለይቶ ለማወቅ እና ፓርቲውን እንዲቀላቀሉ ለማበረታታት ብቻ የሚያተኩር "የሴቶች ምልመላ ዳይሬክተር/ ክፍል" ማደራጀት። • የፓርቲውን የሴቶች ክንፍ በመጠቀም ሌሎች ሴቶችን እንዲሳተፉ የሚያበረታቱ ግላዊ ደብዳቤዎችን ወይም ኢሜይሎችን እንዲጽፉ ማድርግ።
ተዛማጅ የምልመላ ስልቶች (Passive Recruitment)	አዳዲስ ሴት የፓርቲ አባላትን ለመልመል ፓርቲዎች ሰፋ ያሉ እና ይፋዊ ዘዴዎችንም መጠቀም ይችላሉ፡- • በሕትመት ወይም በሬዲዮና ቴሌቪዥን ብዙኃን ሚዲያዎች ላይ ለምልመላ ጥሪ ማውጣት፣ ሴቶች ፓርቲውን እንዲቀላቀሉ በግልጽ ጥሪ ማቅረብና ማበረታታት። • የፓርቲው አባል ያልሆኑ ነገር ግን በፖለቲካዊ ተሳትፎ ላይ ፍላጎት ያላቸውን የሴት ባለሙያዎችና መሪዎች የሚመዝግብ የፓርቲውን የመረጃ ቋት መፍጠር። • ሴቶች ስለ ፓርቲው ዓላማ እንዲያውቁና እንዴት አስተዋጽኦ ማድረግ እንደሚችሉ የሚማሩበት የማኅበራዊ ሚዲያ ዘምቻ ማካሄድ ወይም የአንላይን መድረኮችን ማዘጋጀት።

5.2.3.3. የእጩዎች ምልመላ ሂደቶችን ፍትሐዊና ግልጽ እንዲሆን ማድረግ

የእጩዎች ምልመላ ሂደት ለሴቶች የፖለቲካ ዕድገት ትልቁ እንቅፋት ከሆኑ ጉዳዮች አንዱ ነው። በዚህ ሂደት ውስጥ ሊንሰራፋ የሚችለውን መደበኛ ያልሆነውን “የቀድሞ የወንዶች ክበብ” (old boys’ club) ተጽእኖ ለመቀነስ፣ አንድ ፓርቲ ደንቦቹንና የአሠራር ሂደቶቹን መደበኛ ማድረግ አለበት።

ሂደቱን መደበኛ ማድረግ	የእጩዎች ምለመላ ሂደትን ግልጽ በሆነና በጽሑፍ በተዘጋጀ መግለጫ በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ ማካተት ያስፈልጋል። ይህም የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፡- • ለዕጩነት የሚያበቁ ዝቅተኛ መስፈርቶች። • የዕጩ ምለምላ ሂደት ዝርዝርና የጊዜ ሰሌዳ በይፋ ማሳወቅ። • መደበኛ ባልሆኑ ግንኙነቶች ላይ ያልተመሰረቱ የእጩዎች የግምገማ መስፈርቶች።
የጾታ ሚዛንን ማረጋገጥ	የእጩ ምልመላ ኮሚቴው አባላት ስብጥር ራሱ ወሳኝ ነው። የፓርቲ መሪዎች እነዚህ አካላት በጾታ ሚዛናዊ እንዲሆኑ ደንቦችን ማውጣት አለባቸው። ሙሉ በሙሉ ከወንዶች የተውጣጣ የምርጫ ኮሚቴ የሴት እጩዎችን ልዩ ብቃትና አመለካከቶች የመረዳት ዕድሉ በጣም አናሳ ነው።
በፈቃደኝነት የኮታ ሥርዓትን ግምት ውስጥ ማስገባት	ፓርቲዎች የተወሰነ መቶኛ የሴት እጩዎች እንዲኖሩ ለማድረግ በፈቃደኝነት በሕገ ደንባቸው ውስጥ የኮታ ሥርዓት (quotas) ሊያካትቱ ይችላሉ። ይህ ለጾታ እኩልነት ያላቸውን ጠንካራና ተቋማዊ ቁርጠኝነት ያሳያል። እነዚህ ኮታዎች ለምርጫ ለሚቀርቡ የፓርቲ ዝርዝሮች እንዲሁም እንደ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ባሉ ቁልፍ የውስጥ ውሳኔ አሰጣጥ መዋቅሮች ላይ ተግባራዊ ሊደረጉ ይችላሉ።

ምስል 5.1፡ የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ ለመጨመር የሚረዱ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረቱ እርምጃዎች



5.2.4. አቅምን መገንባትና ድጋፍ መስጠት

ብዙ ሴቶች የፖለቲካ ሥልጣን ለመያዝ የሚያስችላቸው ችሎታና ብቃት አላቸው። ነገር ግን ወንዶች ለረጅም ጊዜ ሲጠቀሙባቸው እንደነበሩት ዓይነት መደበኛ ያልሆኑ ሥልጠናዎችና አውታረ መረቦች (ኔትዎርኮች) የማግኘት ዕድላቸው ጠባብ ነው። አንድ ፓርቲ ይህንን ክፍተት በንቃት መሙላት አለበት። እንዴት?

የአማካሪነት ፕሮግራሞች	የሴቶችን አቅም በፓርቲ ውስጥ ለማጎልበት መደበኛ የሆነ የአማካሪነት ፕሮግራም (Mentorship Programs) መመስረት ያስፈልጋል። አዳዲስ ሴት የፓርቲ አባላትን ልምድ ካላቸው ወንድ ወይም ሴት የፓርቲ መሪዎች ጋር ማጣመር ይመከራል። እነዚህ መሪዎች ምክር ሊሰጡ፣ የተሳካላቸው ስልቶችን ሊያካፍሉ እና የፖለቲካውን መስክ እንዲረዱ ሊረዷቸው ይችላሉ። ይህ ደጋፊ የሆነ አውታረ መረብ ይፈጥራል እንዲሁም ክህሎቶችን ይገነባል።
ዒላማ ያደረገ ሥልጠና	እንደ ንግግር ችሎታ፣ የምርጫ ቅስቀሳ ዕቅድ ዝግጅት፣ ከመገናኛ ብዙኃን ጋር ግንኙነት መፍጠር እና የገንዘብ ማሰባሰብ ባሉ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ለሴቶች ልዩ የአቅም ግንባታ ሥልጠና መስጠት (Targeted Training) ያስፈልጋል። ፓርቲዎች እነዚህን ፕሮግራሞች ለማካሄድ ከአካባቢው የሲቪል ማኅበራት ወይም ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር መሥራት ይችላሉ።
ሴቶችን ለእጩነት ማበረታታት	አንድ ፓርቲ ሴቶች ወደ ፊት እንዲወጡ በንቃት ማበረታታት አለበት። ለሥልጣን መወዳደር ከፍተኛ የሆነ ግላዊና ሙያዊ አደጋን እንደሚያካትት መቀበል ያስፈልጋል። የፓርቲ አመራሮች ሴቶች ሙያዊና ግላዊ ግዴታዎቻቸውን እንዲያመዛዝኑ የገንዘብና የሎጅስቲክስ ድጋፍ እንደሚያደርጉ ግልጽ ማድረግ አለባቸው።
ግላዊና ሙያዊ ሕይወትን ማመዛዘን	ለፆታ እኩልነት በእውነት ቁርጠኛ የሆነ ፓርቲ ደጋፊ የሆነ አካባቢ ለመፍጠር ይሰራል። ለብዙ ሴቶች መደበኛ የወሊድ ፈቃድ ፖሊሲዎች ከፖለቲካ ሕይወት ጋር ለመተግበር አስቸጋሪ ሊሆኑ ቢችሉም አንድ ፓርቲ ለስብሰባዎች እና ለዝግጅቶች ተለዋዋጭ የሆነ የጊዜ ሰሌዳ ለመያዝ ቁርጠኛ ሊሆን (Balance Personal and Professional Life) ይችላል። ይህ ሴቶች (እና ወንዶች) የሚገጥሟቸውን ተግዳሮቶች እንደሚረዳ እና የበለጠ አሳታፊና ለቤተሰብ ተስማሚ የሆነ ባህል እንደሚፈጥር ያሳያል።

5.2.4. ስትራቴጂ 3፡ የሀብት ፍትሐዊ ተደራሽነትን ማረጋገጥ

በኢትዮጵያ ልክ እንደሌሎች የዓለም ክፍሎች የፖለቲካ ተሳትፎና ስኬት ብዙውን ጊዜ ከገንዘብ አቅም ጋር የተያያዘ ነው። ለሴቶች፣ ለወጣቶች እና ለአካል ጉዳተኞች ለኢኮኖሚያዊ ሀብቶች እኩል ተደራሽነት አለመኖር ለፖለቲካ ተሳትፏቸው ከፍተኛ እንቅፋት ይፈጥራል። ይህም ተወዳዳሪ ዘመቻዎችን የማካሄድ አቅማቸውን ይገድባል። በመሆኑም ፆታን መሠረት ያደረገ የአድሎ ችግርን በፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ መቅረፍ ከሚቻልባቸው መንገዶች አንዱና ዋነኛው የገንዘብና የግብአት እኩል ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ነው። የገንዘብ ማሰባሰብ እና አሁን ያሉ ግብዓቶችን በአግባቡ ማከፋፈል በፖለቲካ ውስጥ የፆታ እኩልነትን ለማምጣት ቁልፍ ሚና እንዳለው ከዚህ ቀደም በተሰሩ ጥናቶች ተለይቷል።

የፓርቲ መሪዎች የገንዘብ ማሰባሰብ ስልቶችን በማጋራት እና ከወንዶች ጋር እኩል መወዳደር የሚያስችላቸውን በቂ ገንዘብ እንዲያሰባስቡ በመርዳት ሴቶች እነዚህን ገደቦች እንዲያሸንፉ ማበረታታት አለባቸው። የፖለቲካ ፓርቲዎች እና አመራሮቻቸው ለሴት እጩዎች እጅግ በጣም አስፈላጊ ደጋፊዎች መሆን አለባቸው። ከዚህ አንጻር የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚከተሉትን ስልቶች መከተል ይችላሉ፦

5.2.4.1. የፋይናንስ እና የአይነት ድጋፍን በፓርቲ ውስጥ ተቋማዊ ማድረግ

እኩል የመወዳደሪያ ሜዳ ለመፍጠር፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች መደበኛ ካልሆነ ድጋፍ አልፈው ውክልና ለሌላቸው እጩዎች የገንዘብ ድጋፍን ተቋማዊ ማድረግ አለባቸው። የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/11 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ለፓርቲዎች የመንግሥት የገንዘብ ድጋፍ የሚመድብበትን ሁኔታ በምዕራፍ አምስት አንቀጽ 100 ያብራራል። በተለይም በንዑስ አንቀጽ 2 ሐ እና መ ላይ እንደተደነገገው "ፓርቲው ለውድድር የሚያቀርባቸው የሴት እጩዎች ብዛት" እና "የፓርቲው የሴቶች አባላት ብዛት እና የሴቶች አመራር አባላት ብዛት" አንድ የፖለቲካ ፓርቲ የሚያገኘው የገንዘብ ድጋፍ መጠን በሚከተሉት መስፈርቶች መካከል ሆነው ተቀምጠዋል። ይህ ለፓርቲዎች ለሴቶች በሚያደርጉት የፋንናስ ድጋፍ ላይ አንውታዊ እርምጃ እንዲወስዱ ግልጽ ማበረታቻ ይሰጣል።

ፓርቲዎች የገንዘብ ድጋፍን እንዴት ማካተት እና በሥርዓትና ደንቦቻቸው ውስጥ መደበኛ ማድረግ ይችላሉ?

ግልጽ የሆነ የሀብት ክፍፍል ደንቦችን ማቋቋም	የፓርቲው የውስጥ ደንቦች የገንዘብ ሀብቶች ለእጩዎች እንዴት እንደሚከፋፈሉ በግልጽ ማሳወቅ አለባቸው። እነዚህ ደንቦች በፍትሐዊነትና ግልጽነት መርሆዎች ላይ የተመሠረቱ መሆናቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው። ይህ ደግሞ በዝምድና የመደገፍ ክሶችን ለመከላከልና በሁሉም አባላት መካከል መተማመንን ለመገንባት ወሳኝ ነው።
ልዩ ፈንዶችንና የገንዘብ ማበረታቻዎችን መፍጠር	• **የእጩነት ምዝገባ ክፍያ**፦ በፓርቲው የውስጥ አሰራር መሰረት የዕጩነት የምዝገባ ክፍያ ካለ ለሴት፣ ለወጣቶችና ለአካል ጉዳተኞች የውስጥ የእጩነት ምዝገባ ክፍያ አሠራርን ማስቀረት ወይም እነዚህን ወጪዎች ለመሸፈን ልዩ ፈንድ ማቋቋም። • **የተመደበ ሀብት**፦ ለሴት፣ ለወጣትና ለአካል ጉዳተኞች ቡድኖች፣ ለአቅም ግንባታና ለምርጫ ቅስቀሳ ድጋፍ እንዲሆን ከፓርቲው ገቢ (ከመንግሥት የሚሰጥን ገንዘብ ጨምሮ) የተወሰነውን ክፍል መደበኛ በሆነ መንገድ መመደብ። • **የገንዘብ ማሰባሰቢያ አውታረ መረቦች (ኔትዎርኮች)**፦ ውክልና የሌላቸውን ቡድኖች እጩዎችን ለመደገፍ ልዩ የገንዘብ ማሰባሰቢያ ኮሚቴዎችን ወይም ዝግጅቶችን መፍጠር። ለእነዚህ እጩዎች የፓርቲውን የለጋሾች ዝርዝር የማግኘት ዕድል መስጠት እና የራሳቸውን የገንዘብ ማሰባሰቢያ አውታረ መረቦች እንዲገነቡ ክህሎቶችን መስጠት።

የፖለቲካ ፓርቲዎች የአይነት ድጋፍን (In-Kind Support) በደንባቸውና በአሰራራቸው ውስጥ ማካተት የሚችሉባቸው መንገዶች

የዓይነት አስተዋጽኦዎች	የገንዘብ አቅማቸው ውስን ለሆኑ ዕጩዎች (በተለይም ሴት፣ ወጣት እና አካል ጉዳተኞች) ወሳኝ ሊሆን የሚችል፣ ተግባራዊና ገንዘብ ነክ ያልሆነ (In-Kind Contributions) ድጋፍ መስጠት ነው። ይህም የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፦ • ለስብሰባዎችና ለዝግጅቶች የፓርቲው ንብረት የሆኑ ቦታዎችን በነጻ መጠቀም፤ • ከፓርቲው ጋር ግንኙነት ባላቸው የመገናኛ ብዙኃን ላይ በነጻ የአየር ሰዓት ወይም ገጾች መመደብ፤ • በማዕከላዊነት የተዘጋጁ፣ ሙያዊ የቅስቀሳ ቁሳቁሶችን (ፖስተሮች፣ በራሪ ወረቀቶች) በቅናሽ ወይም በድጎማ ዋጋ ማቅረብ።
ዒላማ ያደረገ ሥልጠናና አማካሪነት አገልግልቶች	ወጪ ቆጣቢ የምርጫ ቅስቀሳ፣ የሕዝብ ንግግር እና የገንዘብ ማሰባሰብ ላይ ልዩ ሥልጠናና ምክር መስጠት። ውክልና የሌላቸው ቡድኖች ውስጥ የሚገኙ ተስፋ ሰጪ ዕጩዎችን ልምድ ካላቸው አማካሪዎች ጋር ማገናኘት። እነዚህ አማካሪዎች የምርጫ ቅስቀሳ የገንዘብ ጉዳዮችን በራስ መተማመን እንዲያስተዳድሩ ሊረዷቸው ይችላሉ።
‘አስተማማኝ የምርጫ ክልል’ ስልትን ማጤን	የረጅም ጊዜ መፍትሄ ባይሆንም፣ የፓርቲ አመራሮች ተስፋ ሰጪ ዕጩዎችን ውድድሩ አነስተኛ በሆነባቸው ክልሎች፣ እንደ አስተማማኝ የምርጫ ወረዳዎች ወይም በፓርቲ ዝርዝሮች ላይ ባሉ ከፍተኛ ቦታዎች ላይ በስልታዊ መንገድ ሊያስቀምጡ ይችላሉ። ይህ ዕጩዎቹ ከፍተኛ የገንዘብ ወጪ ሳይጠይቅ ጠቃሚ ልምድና የሕዝብ ዕውቅና እንዲያገኙ ያስችላቸዋል። **ሁኔታዎች አመቺ ሲሆኑ እና የሕግ ጉዳዮች በሚሟሉባቸው ሁኔታ ውስጥ ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ስልት ነው።**

5.2.4. ስትራቴጂ 4፡ ሥርዓተ-ፆታን በፓርቲ የኮሚኒኔሽን ተግባራት ውስጥ በስልታዊ መንገድ ማካተት

ለአንድ የፖለቲካ ፓርቲ የፆታ እኩልነትን በመሠረታዊ ስልቶቹና ኮሚኒኬሽኑ ውስጥ ማካተት ምርጫ ብቻ አይደለም። ይልቁንም ስልታዊና ብዙውን ጊዜ አሸናፊ የሆነ የምርጫ አካሄድ ነው። መራጮች ለሀገር ዘመናዊና አሳታፊ ራዕይን በተጨባጭ የሚያሳዩ ፓርቲዎችን እየፈለጉ ድጋፍ የሚያደርጉበት እድል ሰፊ ነው። ይህም ከንግግር ባለፈ በሁሉም የፖለቲካ የእንቅስቃሴ ደረጃዎች ሴቶችን የሚያበረታቱ ተጨባጭ፣ የሚታዩ እና አስተማማኝ ተግባራትን ይጠይቃል። ከዚህ ረገድ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚከተሉትን ስልቶች ተግባራዊማድረግ ይችላሉ፦

ሴቶችን እንደ ፖለቲካ መሪ በግልጽ ማሳየት	አንድ ምስል ከሺህ ቃላት በላይ ይናገራል። ወንድ የፓርቲ መሪዎች በፖስተሮች፣ በማኅበራዊ ሚዲያ እና በመገናኛ ብዙኃን ላይ የበላይ ሆነው የመታየታቸውን የተለመደ አሠራር ይለውጡ። የሴት እጩዎቻችሁን፣ የምርጫ ዘመቻ አስፈጻሚዎቻችሁንና የፓርቲ አባላችሁን በፓርቲው ድረ ገጽ፣ በምርጫ ፖስተሮቻችሁ እና በሁሉም የመገናኛ ብዙኃን መልዕክቶቻችሁ (ከቴሌቪዥንና ሬዲዮ ስርጭቶች እስከ ኦንላይን መድረኮች ድረስ) በጉልህ ያሳዩ። ሴቶችም በራስ መተማመን ያላቸውና ብቃት ያላቸው የፓርቲው መሪዎች እና ቃል አቀባዮች መሆናቸውን ያሳዩ።
በአደባባይ ትይንተ ሕዝቦች እና ክርክሮች ላይ ሴቶችንማብቃት	በፖለቲካ ሰልፎችና በማኅበረሰብ ዝግጅቶች ወቅት ለሴት እጩዎችና መሪዎች ተመጣጣኝ የመናገር ጊዜ ይስጡ። በቴሌቪዥን በሚተላለፉ የክርክር መድረኮችና በፓርቲ የማኅበራዊ ሚድያዎች ስርጭቶች ላይ ሴት እጩዎችና የፓርቲ መሪዎች እንዲሳተፉ መጋበዝዎንና መደገፍዎን ያረጋግጡ። ይህ ሴቶቹ እጭዎችና መሪዎች ስማቸው እንዲታወቅና ፓርቲው በአመራራቸው ላይ እምነት እንዳለው ያሳያል።
ዒላማ ያደረጉ የመራጮች ትምህርት ዘመቻዎች ማስጀመር	ሴቶችን ድምጽ እንዲሰጡ ለማበረታታትና የፖለቲካ መብቶቻቸውን ለማሳወቅ በተለየ ሁኔታ የተነደፉ የመራጮች ትምህርት ዘመቻዎችን ይንደፉና ተግባራዊ ያድርጉ። እነዚህ ዘመቻዎች ለተለያዩ ባህሎች ተስማሚ መሆን አለባቸው። እንዲሁም በኢትዮጵያ የተለያዩ ክልሎች ውስጥ ያሉ የተለያዩ ቋንቋዎችን፣ የትምህርት ደረጃዎችንና ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው። ከሁሉም በላይ ደግሞ እነዚህ ዘመቻዎች ውጤታማና የሴቶችን የሕይወት ተሞክሮ የሚያንጸባርቁ እንዲሆኑ ሴቶች በዕቅድ ዝግጅቱ፣ በልማቱና በአተገባበሩ ላይ መሳተፍ አለባቸው።
ከምርጫ ጋር የተያያዙ የፆታ ትንኮሳዎችን በይፋ ማውገዝ	ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በምርጫ ጊዜ የሚፈጸሙትን ማንኛውንም ዓይነት ፆታዊ የጥቃት እና የትንኮሳ ድርጊቶችን **በግልጽ እና በማያሻማ ቋንቋ በማውገዝ** መግለጫ መስጠት አለበት።

ሳጥን 5.3: የእንጊሊዙ ኮንሰርቫቲቭ ፓርቲ ለሴቶች እኩልነት የገባው ቃል ኪዳን

የእንጊሊዙ ኮንሰርቫቲቭ ፓርቲ ይፋዊ ድረ-ገጽ ለሴቶች የተዘጋጀ ክፍል አለው። በዚህ ክፍል ውስጥ ፓርቲው **አጠቃላይ ቁርጠኝነቱን** እንደሚከተለው አስቀምጧል፦

- ለጾታ እኩልነት አሁንም ያሉትን እንቅፋቶች ለማስወገድ ቁርጠኞች ነን።
- በተጨማሪም በሴቶች ላይ የሚደርስን ጥቃት ለማስቆም እርምጃ እየወሰድን ነው።

ይህም ከዚህ በታች በተዘረዘሩት **ልዩ ቁርጠኝነቶች** አስቀምጧል፦

- በከፍተኛ ኩባንያዎች ውስጥ የሴት ተወካዮችን ቁጥር መጨመር፤
- ጾታ-ተኮር ክፍያ ልዩነትን መቀነስ፤
- ሴት ሥራ ፈጣሪዎችን ማበረታታት፤
- ተለዋዋጭ የወላጅነት ፈቃድ ማስተዋወቅ፤
- በሴቶች ላይ የሚደርስን ጥቃት መከላከል።

እያንዳንዱ ቁርጠኝነት እስካሁን ፓርቲው የወሰዳቸውን እና በዚህ ረገድ **ለማድረግ ያቀዳቸውን እርምጃዎች** ይገልጻል፣ ለምሳሌ፦

በሴቶች ላይ የሚደርስን ጥቃት መከላከል እስካሁን የተወሰዱ እርምጃዎች፦

- በሴቶች ላይ የሚደርስን ጥቃት ለመከላከል የመንግስት ስትራቴጂ አውጥተናል።
- ለአስገድዶ መድፈር ተጠቂዎች የእርዳታ ማዕከላት (rape crisis centres) የገንዘብ ድጋፍ በዓመት 9.8 ሚሊዮን ፓውንድ በመስጠት ለረጅም ጊዜ እንዲረጋጋ አድርገናል።
- የቤት ውስጥ ጥቃት ፍቺ ከ16 እስከ 18 ዓመት የሆናቸውን ልጆች እና አስገዳጅና ተቆጣጣሪ ባህሪን እንዲጨምር አስፋፍተናል።
- ማስፈራራት እና ጥቃት የመፍራት ስሜት በሚኖርበት ጊዜ ማሳደድን (stalking) ወንጀል አድርገናል።
- አስገዳጅ ጋብቻን ወንጀል ስለማድረግ ምክክር አድርገናል።

5.3. ወጣቶችን በፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ የማካተት ስትራቴጂ

በበርካታ ሀገራት ወጣቶች መደበኛ በሚባሉ የፖለቲካ ሂደት ውስጥ ንቁ ተሳታፊ አይደሉም። ለምሳሌ በርካታ ወጣቶች በምርጫ ሂደቶች ውስጥ እንደ እጩና እንደ መራጭ ተሳታፊ አይደሉም። በርካታ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወጣቶችን እጩ አድርገው አያቀርቡም። ለዚህ ማሳያው የሚሆነን ዓለም አቀፉ የፓርላማዎች ሕብረት (Inter-Parliamentary Union(IPU)) ያወጣው የጥናት ሪፖርት ነው። በሕብረቱ የቅርብ ጊዜ ሪፖርት መሠረት ከ30 ዓመት በታች የሆኑ የፓርላማ አባላት ዓለም አቀፋዊ ምጣኔ በትንሹ አድጎ 2.6 በመቶ ደርሷል። ይህ ጭማሪ ከጥቂት ዓመት በፊት ከነበረው ጋር ሲነጻጸር የ0.4 በመቶ ጭማሪ ያሳያል። ሆኖም የዓለም ሕዝብ ግማሽ ያህሉ (50 በመቶው) ከ30 ዓመት በታች መሆኑን ሪፖርቱ የሚያመለክት ሲሆን፣ ይህ የፖለቲካ ውክልና ላይ ያለውን ከፍተኛ ክፍተት ያጎላል[4]። በኢትዮጲያም ከዚህ የተለየ ሁኔታ የለም። በ2013 ዓ.ም በተደረገው ሀገራዊ ምርጫ በፓርቲያቸው ተወክለው በምርጫ በመወዳደር አሸንፈው ወደ ሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት የገቡ እድሚያቸው ከ30 ዓመት በታች የነበሩ ወጣት የህዝብ ተወካዮች ከአጠቃላይ የምክር ቤቱ መቀመጫ አንፃር ከ3 ከመቶ እንብዛም ያለበለጠ ነበር። ከ60 ከመቶ በላይ ወጣቶች እንዳላት በሚገመት ሀገር ውስጥ የወጣቶች ውክልና በእጁጉ አንስተኛ መሆን እጅግ አሳሳቢ ነው።

5.3.1. ለምን ወጣቶችን?

በሌላ በኩል ዘመናዊ ዲሞክራሲያዊ ሀገራት ከሚያሳስቡ ጉዳዮች መካከል አንዱ ወጣቶች በድምጽ ሰጪነት ያለመሳተፋቸው ነው። እንደ ድምጽ መስጠትና የምርጫ ቅስቀሳን በመሳሰሉ የፖለቲካ ተሳትፎዎች ላይ የወጣቶች ዝቅ እያለ የመጣ የተሳትፎ ምጣኔ ከሌሎች የእድሜ ቡድኖች ጋር ሲነጻጸሩ ከመራጭነት የመታቀብ ሁኔታዎች በስፋት ይስተዋላል። ይህ አዝማሚያ በአንጻሩ መደበኛ ባልሆኑ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ በተለይም ሀይልን በቀላቀለ የፖለቲካ ግጭቶች እና የአመጻ ተግባራት ውስጥ ለመሳተፍ እድል ስለሚፈጥር አሳሳቢ ይሆናል።

1. ውክልና ያለው እና ህጋዊ የፖለቲካ ስርዓት ማስፈን

ወጣቶችን ያገለለወይም ችላ የሚል የፖለቲካ ሥርዓት ውክልና የጎደለው ነው። የአንድ ሀገር የሕዝብ ቁጥር ጉልህ ክፍል በሕይወታቸው ላይ ተጽዕኖ በሚያሳድሩ ውሳኔዎች ላይ ድምፅ እንደሌላቸው ሲሰማቸው፣ በፖለቲካ ተቋማት ላይ ያላቸው እምነት እየተሸረሸረ የዴሞክራሲያዊ መንግሥት ህጋዊነትን ያሳጣል።

በመሆኑም ፓርቲዎች ወጣቶችን በዓላማ በማሳተፍ የሚያቀርቧቸው ዕቅዶችና ፖሊሲዎች የመላውን ኅብረተሰብ የተለያዩ ፍላጎቶችና ጉዳዮች የሚያንጸባርቁ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይችላሉ። ይህ ደግሞ በኢትዮጵያ ውስጥ ብቅ እያሉ ያሉትን ዲሞክራሲያዊ ተቋማት መሠረት ያጠናክራል። በተጨማሪም ወደ ግጭትና አመጻ የሚገቡ ወጣቶችን ቁጥር ለመቀነስ አይነተኛ አስተዋፆ ማድረግ ይችላሉ።

2. የመገለል ቀውስን ማስወገድ

ወጣቶች ድምጻቸው እንዳልተሰማ (disenfranchisement) ወይም ከቁም ነገር እንዳልተወሰደ ሲሰማቸው ኃላፊነት ከመውሰድ ይርቃሉ። በዚህም ከመደበኛ የፖለቲካ ሂደቶች ሊገለሉ ይችላሉ። ይህ ደግሞ ክብ የሆነ ችግር (circular problem) ይፈጥራል። ፓርቲዎች የወጣቶችን ድምጽ ማግኘት አንችልም ብለው ካሰቡ የወጣቶችን ምኞቶች ለመመለስ ፍላጎት ያጣሉ፤ ይህም በተራው በወጣቶች ዘንድ የበለጠ መገለልንና የፖለቲካ ግዴለሽነትን ያባብሳል። በኢትዮጵያ ወጣቶች ለፖለቲካ ለውጥ በተደረጉ እንቅስቃሴዎች ግንባር ቀደም ሆነው ሲታገሉ ስለነበር፣ ይህ ሁኔታ በተለይ አደገኛ ሊሆን ይችላል። ሰልፎችን መርተው ከነበረ በኋላ በአዳዲስ መደበኛ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች መገለል የዲሞክራሲያዊ ለውጡን ሊያናጋ እና ግጭትን ሊያባብስ ይችላል።

3. ዋነኛውን የህዝብ ክፍል መሳብ

ከአገሪቱ ሕዝብ ውስጥ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ከ30 ዓመት በታች በመሆኑ ወጣቶች ልዩ የፍላጎት ቡድን ብቻ አይደሉም። ይልቁንም ትልቁና ከፍተኛ ተጽዕኖ ፈጣሪ የሆኑ የሕዝብ ክፍል ናቸው። የስታስቲክስ መረጃዎች እንደሚያሳዩት፦

- በአለም የሥነ ሕዝብ ስታስቲክስ ሪፖርት መሠረት በኢትዮጵያ ያለው የሕዝብ ዕድሜ አማካይ (median age) 19.1 ዓመት ብቻ መሆኑ የአገሪቱን እጅግ ወጣት ሕዝብ ያሳያል።

በከተሞች ያለው የወጣቶች የሥራ አጥነት መጠን ከፍተኛ ሲሆን፣ በአንዳንድ ግምቶች ከ25% በላይ እንደሚደርስና የሴት ወጣቶች መጠን ደግሞ ከወንዶች በእጥፍ እንደሚበልጥ ያሳያል[5]።

ይህንን የሕዝብ ክፍል ችላ ማለት ስልታዊ ስህተት ብቻ ሳይሆን ኃላፊነትን መካድም ጭምር ነው። የወጣቶችን ፍላጎት በተሳካ ሁኔታ መግለጽና መሟገት የሚችል ፓርቲ ወሳኝና ዘላቂ የምርጫ የበላይነትን ሊያስገኝ ይችላል።

4. ዘላቂ ድጋፍ ሰጪ መሠረት መገንባት

በፖለቲካ ውስጥ መሳተፍ ብዙውን ጊዜ የዕድሜ ልክ ልማድ ይሆናል። አንድ ፓርቲ ዛሬ በወጣቶች ላይ ኢንቨስት በማድረግና በማብቃት፣ ለአንድ ምርጫ ብቻ ድምፅ አያገኝም። ይልቁንም ለሚቀጥሉት አስርት ዓመታት ታማኝ ድጋፍ ሰጪ መሠረት እየገነባ ነው። ወጣቶችን በፖሊሲ ቀረጻ፣ በበጎ ፈቃድ ሥራ እና በውስጣዊ የፓርቲ አመራር ውስጥ ትርጉም ባለው መልኩ በማሳተፍ ፓርቲዎች አዲስ ትውልድ ያፈራሉ። እነዚህም ለረጅም ጊዜ ድርጅቱን የሚያስቀጥሉ ቁርጠኛ አባላት፣ የወደፊት እጩዎችና ታማኝ ድምፅ ሰጪዎች ይሆናሉ። ይህ ደግሞ ውጤታማ የምርጫ ቅስቀሳዎችን ለማካሄድና ሌሎች የፓርቲ ተግባራትን ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን "አካላዊና አእምሯዊ ኃይል" ("muscle and brainpower") ያለማቋረጥ እንዲኖር ያደርጋል።

5. አዳዲስ ሀሳቦችንና ማኅበራዊ ፍትህን ወደ ፖለቲካዊ ውይይቶች ማምጣት

ወጣቶችን በፖለቲካ ፓርቲ ውስጥ ማቀፍና ማሳተፍ ባላቸው የሕዝብ ቁጥር አብላጫነት ብቻ አይደለም። ይልቁንም ወጣቶችን ወደ ፓርቲ መድረክ መሳብ ትውልዱን የዋጀ የአዳዲስ ሀሳቦች ምንጭና ለፈጠራ ወሳኝ ኃይል መሆናቸውንም ያገናዘበ ነው። ወጣቶች በፍጥነት በሚለዋወጥ ኢኮኖሚ ውስጥ ሥራ ከማግኘት ተግዳሮቶች አንስቶ እስከ ማኅበራዊ እኩልነትና ፍትህ ጥያቄዎች ድረስ፣ የራሳቸውንና የእኩዮቻቸውን ችግሮችና እውነታዎች የመረዳት ልዩ ግንዛቤ አላቸው። በፓርቲ ውይይቶች ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ ለትውልዳቸው ፍላጎት ምላሽ የሚሰጡ ዘላቂና ማኅበራዊፖሊሲዎችን ለመፍጠር የሚያስፈልገውን ግብዓት ይሰጣል። ወደፊት ተኮር የሆኑ አመለካከቶቻቸው (forward-looking perspectives) እና ነባራዊውን ሁኔታ ለመቃወም ያላቸው ፍላጎት ፓርቲዎች የአጭር ጊዜ የፖለቲካ ትርፍን ትተው ለሁሉም ሰው ይበልጥ አሳታፊና የዳበረ የወደፊት ዕጣ ፈንታ ላይ እንዲያተኩሩ ይገፋፋቸዋል።

5.3.2. የወጣቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ የሚወስኑ ሦስት ምሰሶዎች

ወጣቶችን በፖለቲካ የማሳተፍ ዘዴዎች ተለውጠዋል። ያም ሆኖ የወጣቶች በፖለቲካ ውስጥ የመሳተፍ መሠረታዊ ምክንያቶች በሦስት ዋና ዋና ነጥቦች ላይ የተመሠረቱ ናቸው። እነዚህም **ሀብቶች፣ ፍላጎት እና ምልመላ** ናቸው። የፖለቲካ ፓርቲዎች ከወጣቶች ጋር ውጤታማ ግንኙነት ለመፍጠር እነዚህን ሦስቱን ምሰሶዎች ትኩረት መስጠት አለባቸው።

1. ሀብቶች (የ"አይችልም" ምክንያት/(The "Cannot" Factor))

ይህ ነጥብ አንድ ወጣት በፖለቲካ ውስጥ ለመሳተፍ የማይችልበትን የአቅም ውስንነትን ይመለከታል። በኢትዮጵያ ውስጥ ይህ የሚከተሉትን ያጠቃልላል።

ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ	ድህነትና ሥራ አጥነት ወጣቶች በፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ ለመሳተፍ እንዳይችሉ የሚገድባቸው ዋና ዋና እንቅፋቶች ናቸው። ኢኮኖሚያዊ ሕልውናውን ለማስቀጠል የሚታገል ወጣት ለፖለቲካዊ ተሳትፎ የሚያስችል ጊዜ ወይም ጉልበት አይኖረውም። ለምሳሌየኢትያጲያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ከናሽናል ዴሞክራቲ ኢንስቲትዩት (NDI) ጋር በመሆን በ2016 በኢትዮጵያ ወጣቶች ላይ የተደረገ አንድ ጥናት እንደሚያሳየው ዝቅተኛ የፖለቲካ ተሳትፎ እንዲኖር ዋና ዋና ምክንያቶች ዘላቂ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ዋንኛ ምክንያቶች ሆነው ቀርበዋል።
ትምህርትና ዕውቀት	የፖለቲካ ዕውቀት እና የስነ–ዜጋ ትምህርት በፖለቲካ ጉዳዮች ላይ ለመሳተፍ ጠንካራ መለያዎች ናቸው። ብዙ ወጣቶች የፖለቲካ ተቋማት እንዴት እንደሚሠሩ ወይም እንዴት የፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ መሳተፍ እንደሚችሉ አያውቁም።
ዲጂታል ተደራሽነት	ዛሬ ላይ በአመዛኙ የፖለቲካ ተሳትፎ ከኢንተርኔትና ከስማርት ስልኮች ተደራሽነት ጋር በእጅጉ የተሳሰረ ነው። የኢንተርኔት ተደራሽነት እያደገ ቢሆንም፣ በተለይ በገጠርና በሩቅ አካባቢዎች ፈተና ሆኖ ቀጥሏል።

2. ፍላጎት (“አልፈልግም” የሚለው ምክንያት/The “Don’t Want to” Factor)

ብዙውን ጊዜ ወጣቶች ካላቸው ውስን የፖለቲካ ውክልና እና ውሳኔ ሰጭነት ሚና ጋር ያላቸው ዝቅተኛ ተሳትፎ ምክንያት በፖለቲካ ምህዳር ውስጥ “የአንፈልግም” ስሜት እንዲፈጠር ያደርጋል። ይህ ክፍል የሚያተኩረው ወጣቶች ከፖለቲካ ጋር ባላቸው ሥነ-ልቦናዊ ግንኙነት ላይ ነው።

የፖለቲካዊ ተጽዕኖ ፈጣሪነት ስሜት	ብዙ ወጣቶች ድምፃቸው ወይም ሐሳባቸው ለውጥ እንደማያመጣ ይሰማቸዋል። ይህ የፖለቲካ ተጽዕኖ ፈጣሪነት ስሜት (political efficacy) ማጣት ለመሳተፍ ዋነኛ እንቅፋት ነው።
በፖለቲካ ላይ መተማመን ማጣት	በፖለቲከኞች እና በፖለቲካዊ ሥርዓቱ ላይ ወጣቱ የፈጠረው አለመተማመንና ተጠራጣሪነት (political trust) አንዱ ፈተና ነው። ይህን አስቸጋሪ ሁኔታ ለመሻገር እውነተኛ እና ግልጽ የፖለቲካ የተሳትፎ መደረክ መፍጠር ወሳኝ ጉዳይ እንዲሆን አርጎታል።
የቀድሞ ልምድ	ከዚህ በፊት የነበረ አሉታዊ የፖለቲካ ተሳትፎ ልምድ (የቤተሰብና የአከባቢን ጨምሮ) በቀጣይ ወጣቶች በፖለትካ ውስጥ መደበኛ በሆነ መልኩ እንዳይሳተፉ ሊገታቸው ይችላል።

3. ምልመላ (“አልተጠየቅንም” የሚለው ምክንያት/The “Weren’t Asked” Factor)

የፖለቲካ ፓርቲዎች ወጣቶችን በንቃት ወደ ፓርቲያቸው እንዲቀላቀሉ በማነሳሳትና በመጋበዝ ወሳኝ ሚና የሚጫወቱበት ቦታ ነው።

አዳዲስ የማንቀሳቀሻ መንገዶች	የ። ፓርቲዎች ትኩረታቸውን ወደ ዲጂታል ተደራሽነትና ተሳትፎ መቀየር አለባቸው። ለፓርቲዎች የሚነሳው ጥያቄ ወጣቶች አሁንም ፍላጎት አላቸው ወይ የሚለው ሳይሆን፣ ፓርቲዎቹ ምልመላ ስልታቸውን ወጣቶች ወዳሉበት ቦታ በተለይም ወደ ኦንላይን እና ማኅበራዊ ሚዲያ ለመቀየር ፈቃደኛ ናቸው ወይ የሚለው ነው።

5.3.3. ለተለያዩ የወጣቶች ክፍሎች የተዘጋጀ) ስልት

ሁሉም ወጣቶች አንድ አይነት አይደሉም። ወጣቶችን ለመመልመል የፖለቲካ ፓርቲዎች ሲንቀሳቀሱ ሰፋ ያለ እና ለተለያዩ የወጣቶች ክፍሎች የተዘጋጀ የግንኙነት ስልት (a tailored strategy) እንደሚያስፈልጋቸው መገንዘብ አለባቸው። በተለይም በፖለቲካው ንቁ ተሳትፎ ለሚያደርጉትና ፍላጎት ለሌላቸው ወጣቶች የተለየ አቀራረብ ያስፈልጋል።

ንቁ ተሳትፎ ላላቸው ወጣቶች	ይህ ቡድን በማኅበራዊ ሚዲያ ላይ ንቁ ተሳታፊ ሲሆን በተወሰኑ ጉዳዮች ላይም የራሱ የሆነ ጠንካራ አቋም አለው። ፓርቲዎች በእነዚህ የመሣሪያ ስርዓቶች ላይ በቀጥታ ሊያነጋግሯቸው ይገባል። የምናዳምጣችሁ ነን የሚለውን መልእክት ማሳየት እና እንደ ሥራ አጥነት፣ ሰላም እና ሙስና ባሉ ጉዳዮች ላይ ግልጽና አሳማኝ የፖሊሲ አቋሞችን ማቅረብ ይገባል።
ተሳትፎ ለሌላቸው ወጣቶች	ይህ ቡድን ወይ ግድ የለሽ ነው፣ ወይ መረጃ የሌለው ነው ወይም በፖለቲካው ላይ እምነት የሌለው ሊሆን ይችላል። እዚህ ቡድን ውስጥ ያሉ ወጣቶችን ለመሳብ ፓርቲዎች እምነትን በመገንባት እና ፖለቲካን ከዕለት ተዕለት ሕይወታቸው ጋር በማዛመድ ላይ ማተኮር አለባቸው። ይህ ደግሞ ስለ ፖለቲካው ሂደት ግልጽና በቀላሉ ሊደረስበት የሚችል መረጃ መስጠት፣ ለውይይት የሚያመቹ መድረኮችን መፍጠር እና ውጤታማ የአመራርና የአገልግሎት አሰጣጥ ታሪክ ማሳየትን ሊያካትት ይችላል።

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ዲሞክራሲ የወደፊት ዕጣ ፈንታ የሚወሰነው በወጣቶች ትርጉም ባለው ተሳትፎ ላይ ነው። በዚህ ረገድ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከ”ተለመደው አሠራር” በመውጣትና የወጣቶችን ተሳትፎ አዲስ እውነታ በመቀበል ወሳኝ ሚና መጫወት አለባቸው። ጥያቄው ወጣቶች በፖለቲካ ውስጥ ፍላጎት አላቸው ወይ የሚለው ሳይሆን፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች በወጣቶች ላይ እውነተኛ ፍላጎት አላቸው ወይ እናም እምነታቸውን ለማግኘት ፈቃደኛ ናቸው ወይ የሚለው ነው። ይህን ከማድረግ ረገድ የሚከተሉትን ስትራቴጂዎችን ማጤን ለፖለቲካ ፓርቲዎች ጠቃሚ ይሆናል።

5.3.3.1. ስልት 1፡ ሁሉን አቀፍና ወጥ የሆነ የወጣቶች ስትራቴጂ ማዘጋጀት

ወጣቶች በፓርቲው ውስጥ እንዲካተቱ ብቻ ሳይሆን በፓርቲ አመራርነት ስልጣን እንዲኖራቸው ለማድረግ የሚከተሉት ስልቶች ለኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተጨባጭ ሁኔታ ተስማሚ በሆነ መልኩ ተዘጋጅተዋል[6]። ወጣቶችን ለመሳብ ይድረስ ይድረስ በድንገት የሚዘጋጁ ስልቶች እምብዛም ስኬታማ አይሆኑም። አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ሁሉን አቀፍ የሆነ የወጣቶች ስትራቴጂ መንደፍ እና መተግበር አለበት። ይህ ስትራቴጂ የፓርቲውን ሁሉም ገጽታዎች ማካተት አለበት። ስትራቴጂው ከፓርቲው ውጪ ካሉ ወጣቶች ጋር በቅርበት በመተባበር መዘጋጀት ይኖርበታል። ይህ ደግሞ ከፓርቲው ውጪ ያሉ ወጣቶች አስተያየት ለዕቅዱ መሠረት መሆኑን ያረጋግጣል። በተጨባጭ ወጣቶች ምን ይፈልጋሉ፣ ስጋታቸው ምንድን ነው በምን መልኩ በፖለቲካ ውስጥ መሳተፍ ይፈልጋሉ የሚሉትን ሃሳቦች በተጨባጭ ያገናዘበ ዕቅድ ለማዘጋጀት ይጠቅማል።

ዋና ሰነድ ያድርጉት	የፓርቲውን ወጣቶችን የማካተት ስትራቴጂ የተለየ ሰነድ ብቻ ሳይሆን በፓርቲው መተዳደርያ ደንብ፣ መመሪያ፣ በውስጥ ደንቦችና በዋና ዋና የፖሊሲ መግለጫዎች ውስጥ መጠቀስ አለበት። ይህም ወጣቶች የፓርቲው ማንነት ቋሚና ዋና አካል እንደሆኑ እንጂ ጊዜያዊ ጉዳይ እንዳልሆኑ ግልጽ መልእክት ያስተላልፋል።
ለተለያዩ ወጣት አይነቶች እውቅና ይስጡ	ወጣትነት በእድሜ መለኪያዎች ተመሳሳይ ማንነት የሚጠቃልል ቢሆንም በወጣነት ውስጥ ብዝሃነት እንዳለ ማስታወስ ያስፈልጋል። በመሆኑም ስትራቴጂው ከተለያዩ ብሔሮችና ክልሎች ወይም አከባቢዎች የመጡ ወጣቶችን፣ እንዲሁም ወጣት ሴቶችንና አካል ጉዳተኞችን ጨምሮ የኢትዮጵያ ወጣቶችን የተለያዩ እውነታዎች ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት። ዕቅዱ በእነዚህ የተለያየ አስተዳደግ ባላቸው ንዑስ-ቡድኖች መካከል ያለውን የእውቀትና ዕድል አለመመጣጠን ለመፍታት የተወሰኑ እርምጃዎችን ማካተት አለበት።

5.3.3.2. ስልት 2፡ ጠንካራ እና በራሱ መወሰን የሚችል የወጣቶች ክንፍ ማደራጀት

የአንድ ፓርቲ የወጣቶች ክንፍ ለምርጫ ቅስቀሳ የሚውል “ከባዱን ሥራ የሚሰራ እግረኛ ሰራዊት” (“foot soldiers”) ወይም ግብረ ኃይል ከመሆን የዘለለ መሆን አለበት። በፓርቲው አመራርና በፓርቲው ውስጥ ካሉ ወጣቶች ሲልም ደግሞ በሀገሪቱ ካሉ የተለያዩ ወጣቶች መካከል ወሳኝ ድልድይ ሆኖ የሚያገለግል ራሱን የቻለ፣ ጠንካራ እና የተከበረ ክንፍ መሆን ይኖርበታል። የወጣቶች ክንፍ የፓርቲው መዋቅር አካል ሆኖ ወጣቶችን የተመለከቱ ጉዳዮችን አቅዶ የሚፈጽም እንዲሆን አቅም ሊፈጠርለት ይገባል።

ለወጣቶች ክንፍ የመወሰን ስልጣን መስጠት	ፓርቲው በስሩ ለሚቋቋም የወጣት ክንፍ ኃላፊነትን ከመወሰን ስልጣን ጋር አጣምሮ መሰጠት (granting autonomy) ይጠበቅበታል። ይህም ለወጣቶች በጣም ጠቃሚ የሆኑ ጉዳዮችን የመለየት እና ያለማቋረጥ የመመራት ፍርሃት ሳይኖርባቸው መፍትሄዎችን የማፍለቅ ችሎታን ይጨምራል። የወጣቶች ክንፍ ለአዳዲስ ሀሳቦች ማጎልበቻ እና ለውስጣዊ ክርክር ገንቢ ቦታ ሆኖ በማገልገል፣ ፓርቲው ጊዜውን ያገናዘበ ተለዋዋጭና ጠቃሚ ሆኖ እንዲቀጥል ሊረዳው ይችላል።
ብዝሃነት ያለው አመራር ማፍለቅ መጠቀም	ፓርቲዎች ጠንካራ እና አሳታፊ የወጣቶች ክንፍ ሲያደራጁ የአዳዲስ የፓርቲ መሪዎች መፍለቂያ እንዲሆን ያስችሉታል። በተለይም የፓርቲዎች የወጣቶች ክንፍ ብዝሃነትን የጠበቀ ሲሆን የተለያዩ ብሔር፣ ክልልና ጾታ ያላቸውን ወጣት መሪዎች ለመለየትና ለማፍራት እጅግ ውጤታማ ዘዴ ሊሆን ይችላል።

ሳጥን 5.4. ፓርቲዎች እነዚህን አምስት መርሆች በመከተል ወጣት-ተኮር ፓርቲዎችን መገንባት ይችላሉ[7]	
የውስጥ ደንብ (Bylaws) ማሻሻል እዎነተኛ አካቶን	ያሉትን የፓርቲ ደንቦች በማሻሻል ወጣቶች በእጩ ዝርዝሮች፣ በፓርቲው የውስጥ አመራር ቦታዎች እና አስፈላጊ ኮሚቴዎች ውስጥ ቦታ እንዲያገኙ ማረጋገጥ። እነዚህ ደንቦች በአግባቡ መተግበራቸውን ማረጋገጥ።
ንዑስ ክፍሎችን (Units) ማቋቋም	ለወጣቶች የተሰሩ ክንፎችንና ሌሎች ወጣቶች ላይ ያተኮሩ ንዑስ ክፍሎችን መፍጠርና መደገፍ። ይህ ደግሞ በሌሎች ተጽዕኖ ፈጣሪ ክፍሎች ውስጥ ንዑስ ኮሚቴዎችን ማቋቋም ሊያካትት ይችላል። ለምሳሌ፣ የፓርቲውን ፖሊሲ ለሚያዘጋጀው ኮሚቴ ወጣቶች ላይ ያተኮረ ንዑስ ኮሚቴ ማከል ይቻላል።
ተጽዕኖ (Impact) ማረጋገጥ	ለወጣቶች የተሰጡት ቦታዎች የፓርቲውን ውሳኔ አሰጣጥ፣ ማንነት እና የፖሊሲ አወጣጥ ላይ ተጽዕኖ ማሳደራቸውን ማረጋገጥ። የይስሙላ ተሳትፎ (Tokenism) ማስወገድ። ፓርቲዎች በተለምዶ የሚሰሩት ስህተት ለወጣቶች የሚሰጡት ቦታ ምሳሌያዊ ወይም "ስራውን ሰራሁ" ለማለት ብቻ የሚሆን ማድረግ ነው።
አመራር (Leadership) እድል መፍጠር	ወጣት መሪዎች እንደ የውይይት መድረኮች (talk shows) ወይም ጋዜጣዊ መግለጫዎች (press conferences) ባሉ ባህላዊ የመገናኛ ብዙኃን እንዲሁም በማህበራዊ ሚዲያ ንቁ ተሳትፎዎች ላይ የፓርቲው ፊት እንዲሆኑ እድሎችን መፍጠር። ወጣት አክቲቪስቶች የህግ አውጪ ተነሳሽነቶችን፣ አባላትን የመመልመል ስራዎችን፣ የገንዘብ ማሰባሰቢያ እንቅስቃሴዎችን እና ሌሎች አስፈላጊ ተግባራትን እንዲመሩ መፍቀድ።
ማብቃት (Develop)	ለፓርቲው ወጣት አክቲቪስቶች ጠቃሚ ክህሎቶችን እንዲያዳብሩ እና እንዴት ተግባራዊ እንደሚያደርጓቸው እንዲገነዘቡ የሚያግዙ የስልጠና ክፍለ ጊዜዎችን ማዘጋጀት። ወጣት አክቲቪስቶችን ልምድ ካላቸው የፓርቲ መሪዎች ጋር የሚያገናኝ ፕሮግራም (mentorship program) መፍጠርና መደገፍ።

5.3.3.3. ስልት 3፡ በፓርቲ መዋቅር ውስጥ እውነተኛ የወጣቶች ውክልና ማረጋገጥ

ፓርቲዎች ወጣቶች በፓርቲያቸው ውስጥ ትርጉም ባለው መንገድ አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ ዕድል ለመስጠት የውስጥ አደረጃጀቶቻቸውን፣ ሂደቶቻቸውን እና ተቋሞቻቸውን ማስተካከል ወይም ማሻሻል አለባቸው። ይህ ፓርቲዎች ጊዜ ያለፈባቸው አደረጃጀቶችን ማሻሻልን ይጨምራል። በተጨማሪም የወጣቶች ፍላጎት በትክክል እንዲወከል ወጣቶች በፓርቲው ቁልፍ የውሳኔ መስጫ አካላት ውስጥ መኖርና ስልጣን ሊሰጣቸው ይገባል። ተምሳሌታዊና ውስን ተጽዕኖ ያለው ውክልና ጥርጣሬንና አለመተማመንን ይፈጥራል።

ወጣቶች በኮታ እንዲወከሉ ማድረግ	በፓርቲው ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ውስጥ፣ በፓርቲው የቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት፣ በፖሊሲ አውጫ ኮሚቴዎች እና በእጩዎች ምልመላ ፓነሎች ውስጥ የወጣቶችን ተሳትፎ ለማረጋገጥ እንዲቻል ወጣት ተወካዮች በተወሰነ ምጣኔ መሳተፋቸውን ለማረጋገጥ እንዲቻል የኮታ አሰራሮችን የመሳሰሉ እርምጃዎችን መተግበር ያስፈልጋል። እነዚህ የወጣቶች ውክልና ለይስሙላ እንዳይሆኑ ሙሉ የድምጽ መስጠት መብት እና እንደሌሎች አባላት ሀሳብ የማቅረብና የመወያየት ሥልጣን ሊኖራቸው ይገባል።
ወጣቶች እጩ የምርጫ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማስቻል	ወጣቶች ከፓርቲያቸው ውሳኔ አሳላፊ ስልጣን ተጋሪነት ባሻገር እንደ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወይም የክልል ምክር ቤቶች ባሉ ምርጫዎች ላይ የወጣት እጩዎች ሆነው እንዲሳተፉ የፖለቲካ ፓርቲዎችን በበጎ ፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ኮታዎችን ማስተዋወቅ ያስፈልጋል። እነዚህ ኮታዎች ትርጉም ያላቸው መሆን አለባቸው። ይህም ወጣት እጩዎች በድምፅ መስጫ ወረቀቱ ላይ ለይስሙላ የሚካተቱ ብቻ ሳይሆኑ እንደሌሎች እጩዎች ተመሳሳይ ቅድሚያ በመሰጠት ሊመረጡ በሚችሉ ቦታዎች ላይ መቀመጣቸውን ያረጋግጣል። የወጣት እጩዎች የሀገሪቱን የወጣት ብዝሃነት የሚያንጸባርቁ መሆን አለባቸው።

5.3.3.4. ስልት 4፡ የወጣቶች ማሰልጠኛ ተቋማት እና የአመራር ፕሮግራሞችን ማቋቋም

ወጣቶች በውጤታማነት እንዲሳተፉ እና እንዲመሩ ለማድረግ፣ ፓርቲዎች በችሎታቸውና በእውቀታቸው ላይ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስ አለባቸው።

ዘላቂ የወጣቶች አካዳሚ መፍጠር	በፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ ለወጣት አባላት እና ለወደፊት የፓርቲው እጩ ተወዳዳሪዎች አቅም ማጎልበቻ የሚሆን ዘላቂ የሆነ የሥልጠና አካዳሚ መፍጠር እና መደገፍ ያስፈልጋል። ይህ አካዳሚ ስለ ፓርቲ እሴቶች ግንዛቤ ከመስጠት ባለፈ፣ ወጣቶችን በፖለቲካ ውስጥ ስኬታማ ለመሆን የሚያስፈልጉ ተግባራዊ ክህሎቶችን ማስታጠቅ አለበት። እነዚህም የሕዝብ ንግግር፣ ድርድር፣ ከመገናኛ ብዙኃን ጋር ግንኙነት መፍጠር፣ የምርጫ ቅስቀሳ አስተዳደር፣ እንዲሁም የኢትዮጵያን ሕገ-መንግስታዊና ፌዴራላዊ ስርዓት በጥልቀት መረዳትን ሊያካትት ይችላል።
የወጣቶችን አካዳሚ አካታች ማድረግ	በፓርቲዎች ውስጥ የሚቋቋሙ የማሰልጠኛ አካዳሚዎችን የወጣት ወንድ ፓርቲ አባላት ማሰልጠኛ ላለማድረግ በአካታችነት መርህ እንዲመራ ማድረግ ያስፈልጋል። የአካዳሚው ፕሮግራሞች የወደፊቱን ጊዜ በእውነት የተለያየ እና ሁሉን አቀፍ የአመራር የሚፈልቅበት ለማድረግ ሴቶችን፣ የተልያዩ ቋንቋ ተናጋሪዎችን፣ አካል ጉዳተኛ ወጣቶችን ያከተተ መርህ መከተል ይኖርበታል።

5.3.3.5. ስልት 5፡ የወጣቶችን አመለካከት በሁሉም የፓርቲ ፖሊሲዎች ውስጥ ማካተት

የወጣቶች ጉዳዮች በአንድ የፓርቲ መግለጫ ውስጥ ብቻ ተገድበው መቅረት የለባቸውም። የወጣቶች አመለካከት የሁሉም የፓርቲ ፖሊሲዎች ማዕከላዊ መነፅር መሆን አለበት። የወጣቶችን ጉዳዮች በፖለቲካ ፓርቲዎች መድረኮች እና ፖሊሲዎች ውስጥ ለማካተት መቻል ፓርቲዎቹ የወጣቶችን ጥቅም ለማስጠበቅ ያላቸውን ቁርጠኝነት ያሳያሉ። ወጣቶች ቅድሚያ የሚሰጧቸውን ነገሮች በበለጠ ለመረዳት እና ተጨባጭና ትርጉም ያለው የፖሊሲ መፍትሄ ለማምጣት ፓርቲዎች ወጣት አክቲቪስቶች ሃሳባቸውን የሚገልጹበት እና የሂደቱ ባለቤት የሚሆኑበት ሁሉን ያካተተ የፖሊሲ ዝግጅት ሂደት መፍጠር ይችላሉ።

የተለያዩ ዘርፎችን መተንተን	የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚያዘጋጁት ማንኛውንም ሕዝባዊ ፖሊሲ (ለምሳሌ፦ የግብርና፣ የኢኮኖሚ ልማት፣ የትምህርት ወይም የውጭ ጉዳይ ግንኙነት) በሚቀረጽበት ጊዜ ፓርቲው በወጣቶች ላይ ሊኖረው የሚችለውን ተፅዕኖ መገምገም (cross-sectoral analysis) አለበት። ለምሳሌ፣ የኢኮኖሚ ፖሊሲ በትላልቅ ኢኮኖሚያዊ አመልካቾች ላይ ብቻ ሳይሆን፣ የወጣቶችን ሥራ አጥነት እንዴት እንደሚፈታና ዕድሎችን እንዴት እንደሚፈጥር ላይም ማተኮር አለበት።
የፓርቲ እሴቶችን ማደስ	የፓርቲውን ዋና እሴቶችና ተልዕኮ ዘመናዊ ለማድረግ ከወጣቶች ክንፍ ጋር በመነጋገር የአዲሱን ትውልድ ምኞቶችና ስጋቶች የሚያንፀባርቁ መሆናቸውን (rejuvenate party values) ማረጋገጥ። ይህ ፓርቲው ያለፈው ጊዜ ውስጥ እንዳልተቀረቀረ፣ ይልቁንም ወደፊት የሚመለከት ድርጅት መሆኑን ያሳያል።

ሳጥን 5.5: ወጣቶችን በሕዝብ ፖሊሲዎች በተሻለ መንገድ ለማገልገል፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች እነዚህን አምስት መርሆዎች መከተል አለባቸው	
የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ	ወጣቶች ምን እንደሚያሳስባቸው ለማወቅ ምርጡ መንገድ በቀላሉ መጠየቅ ነው። የተለመዱ ዘዴዎች ባህላዊ የሕዝብ አስተያየት ጥናቶችን እንደ ድምጽ መስጫ (polling) እና የትኩረት ቡድኖች (focus groups) ፣ በማኅበራዊ ሚዲያ ላይ የሚደረጉ የኦንላይን ጥናቶች እና በሕዝባዊ ዝግጅቶች ላይ የሚታደሉ ቀላል የዳሰሳ ጥናቶችን ያካትታሉ። ይህ ደግሞ ከአጋር ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ሊከናወን ይችላል።
ወጣቶችን በሂደቱ ውስጥ ማካተት	የፓርቲውን ወጣት አክቲቪስቶችን በፓርቲው የፖሊሲ መድረክ ዝግጅት ሂደት ውስጥ ማካተት ያስፈልጋል። የቡድኑ አካል እንዲሆኑ ማድረግ፣ በፖሊሲ አወጣጥ ሂደት ውስጥ ቁልፍ የውሳኔ ሰጪ ቦታዎች ላይ ማስቀመጥ እና የትኞቹን ጉዳዮች ቅድሚያ መስጠት እንዳለባቸው፣ ምን መፍትሄዎች ማቅረብ እንዳለባቸው እና እንዴት በተሻለ መንገድ ማሳወቅ እንዳለባቸው ድምጽ እንዲያሰሙ መፍቀድ ተገቢ ነው።
መደበኛ አስተያየት መቀበል	በፖሊሲ ዝግጅት ሂደት ውስጥ በሁሉም ደረጃዎች ከሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች እና ወጣት አክቲቪስቶች መደበኛ ግብዓት መጠየቅ። የፖሊሲ ሀሳቦች ሲዘጋጁ ወጣት መሪዎች አስተያየት የሚሰጡበት ዕድል ሊሰጣቸው ይገባል። አስተያየታቸውን ማካተት እና እንደተደመጡ ማሳየት አስፈላጊ ነው።
የተለያዩ ድምጾችን ማሰባሰብ	የተለያየ አስተዳደግና ማንነት ያላቸው ወጣቶች በፖሊሲ ቅድሚያዎች ላይ ከፓርቲ አባላት ጋር እንዲሳተፉ ዕድል መስጠት። በተለይም በባህላዊ መንገድ ለተገለሉ፣ ለተገፉና ውክልና ላላገኙ ማኅበረሰቦች ቅድሚያ መስጠት ያስፈልጋል። ምሳሌዎች ወጣቶችን የሚያሳትፉ የአዳራሽ ስብሰባዎችና (town halls) ወጣቶች በቀላሉ ሊደርሱባቸው በሚችሉ ቦታዎች የሚካሄዱ ጉባዔዎችን ያካትታሉ።
ወጣቶች ሀሳባቸውን እንዲገልጹ ዕድል መስጠት	የፓርቲው ወጣት መሪዎች የፖሊሲ መድረኩን ፊት እንዲሆኑ ዕድል መስጠት። ምሳሌዎች የቀጥታ የኦንላይን ስርጭቶችን፣ ቀደም ሲል የተቀረጹ ቪዲዮዎችን፣ የቴሌቪዥን የውይይት መድረኮችን እና ትላልቅ ሕዝባዊ ዝግጅቶችን ያካትታሉ። ይህ ወጣቶች በፓርቲው ውስጥ የባለቤትነት ስሜት እንዲሰማቸው ያደርጋል። እንዲሁም ወጣቶችን የሀገሪቱን አጠቃላይ ዕይታ ለማስተላለፍ የገጽታ ግንባታ እንዲሆኑ የፓርቲው ፊት ሆነው እንዲታዩ በመጠቀም ፓርቲው ከወጣቶች ጋር እንዲቀራረብ ይረዳዋል።

5.4. አካል ጉዳተኞችን በፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ የማካተት ስትራቲጂ

የአካል ጉዳተኞችን በፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ ለማሳተፍ ውጤታማ ስልቶችን ምንድናቸው የሚሉትን በዝርዝር ከማየታችን በፊት የፖለቲካ ፓርቲዎች በመጀመሪያ ይህ ሰፊ የኅብረተሰብ ክፍል የሚያጋጥሙትን ልዩ ሁኔታዎችና ተግዳሮቶች መረዳት አለባቸው። የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ ያለ እውነታ ሲሆን እ.ኤ.አ 2013 የዓለም አቀፉ የሰራተኞች ድርጅት (International Labour Organization)[8] ባወጣው ሪፖርት መሰረት በኢትዮጲያ የአካል ጉዳተኛ ዜጎች ቁጥር 15 ሚሊዮን ወይም 17.6% የሚሆነውን ሕዝብ እንደሚይዝ ይገመታል። ይህም አሃዝ የአካል ጉዳተኛ ዜጎችን ትልቅና ወሳኝ የድምጽ ሰጪ አካል ያደርጋቸዋል። አካል ጉዳተኛ ዜጎች ደጋግመው እንደሚወተዉቱት በወረቀት ላይ ጠንካራ የሕግ እና የፖሊሲ ማዕቀፎች ቢኖሩም፣ የፖለቲካ ተሳትፎአቸውን እና ማኅበራዊ ተጠቃሚነታቸውን የሚገድቡ ከፍተኛ እንቅፋቶች አሁንም አሉ።

5.4.1. ዋና ዋና የሕግ ማዕቀፎች

የኢትዮጵያ መንግሥት ለአካል ጉዳተኞች መብት ቁልፍ በሆኑ የሕግና የፖሊሲ ሰነዶች አማካኝነት መደበኛ ቁርጠኝነቱን (formal commitment) አሳይቷል። ከነዚህ መካከል የሚከተሉትን ማስታወስ ይቻላል፦

ዓለም አቀፍ ስምምነቶች	ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ. በ2010 የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአካል ጉዳተኞች መብቶች ስምምነት (UN Convention on the Rights of Persons with Disabilities (UNCRPD)) የመጀመሪያ ፈራሚና አጽዳቂ ነበረች። በተጨማሪም የአካል ጉዳተኞችን መብት የሚደግፉ ሌሎች ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን አጽድቃለች።
ሀገራዊ ሕጎች	የ1987ቱ ሕገ-መንግሥት (አንቀጽ 41(5)) መንግሥት የመልሶ ማቋቋምና የድጋፍ አገልግሎት የመስጠት ኃላፊነት እንዳለበት ያመለክታል[9]። በ 2000 ዓ.ም የወጣው የአካል ጉዳተኞች የሥራ ስምሪት መብት አዋጅ ቁጥር 568/2000 አካል ጉዳተኞች ተገቢውን ሥልጠና፣ የሥራ ዕድል እና ደመወዝ እንዲያገኙ መብታቸውን ይጠብቃል እንዲሁም በሥራ ቦታ የሚደርስባቸውን መድልዎ ለመከላከል ታስቦ ነው[10]። የ2001 የሕንጻ ግንባታ አዋጅ ቁጥር 624/2001 ያሉ ሌሎች ሕጎች በሥራ ቦታ የሚፈጸም አድልኦንና የሕንፃዎች ተደራሽነትን የመሳሰሉ ልዩ ጉዳዮችን ይመለከታሉ[11]። የአካል ጉዳተኞችን የፖለቲካ ተሳትፎን ለማበረታታት የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/11 ለአካል ጉዳተኞች የሚደረጉ የተለዩ ድጋፎችን ዘርዝሯል[12]።
የፖሊሲ ማዕቀፎች	የአካል ጉዳተኞችን የማካተት ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር እና የኢትዮጵያ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (GTP) ጨምሮ ዋና ዋና የፖሊሲ ሰነዶች የአካል ጉዳትን ሁሉን አቀፍ የልማት ጉዳይ አድርገው ይገልጻሉ።

5.4.2. የአካል ጉዳተኞች የፖለቲካ ተሳትፎ እንቅፋቶች

በሕግ እና በፖሊሲ ደረጃ መሻሻሎች ቢኖሩም በኢትዮጵያ የሚኖሩ አካል ጉዳተኞች በፖለቲካው ውስጥ ሙሉ በሙሉ እንዳይሳተፉ የሚገድቡ ሥርዓታዊ እንቅፋቶች ያጋጥሟቸዋል። የፖለቲካ ፓርቲዎች እነዚህን እንቅፋቶች መረዳትና ለማስወገድ በንቃት መሥራት እንዳለባቸው በአካል ጉዳተኞች አዘውትሮ ጥያቄ ይቀርብባቸዋል። የኢትዮጲያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት የአካል ጉዳተኞች ክንፍ ከተለይዩ አካል ጉዳተኛ ተቋማት እና ባለደርሻ አካላት ጋር በመተባበር አካል ጉዳተኞች በፖለቲካ ጉዳዮች ንቁ ተሳትፎ እንዳይኖራቸው የሚያደርጉ ጉዳዮችን ለይቷል። እነዚህ የተለዩ ፈተናዎች ለኢትዮጲያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ቦርድ “የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/11ማሻሻያ ምክረ ሐሳቦች” ሰነድ ላይ አካቶ ያስረከበ ሲሆን ሰነዱ የሚከተሉትን ቁልፍ ጉዳዮች በጥቅል ማየት ይቻላል።

ተደራሽነት የሌላቸው የፖለቲካ ሂደቶች	የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅ አንዳንድ መሻሻሎችን ቢያሳይም፣ አሁንም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን (UNCRPD) ደረጃዎችን አያሟላም። ብዙ የምርጫ ጣቢያዎች በአካል ተደራሽ አይደሉም። የምርጫ አፈጻጸም የአካል ጉዳተኞችን ፍላጎት ከግምት ውስጥ አያስገባም። አንዳንድ ድንጋጌዎች ደግሞ የስነ-አእምሮ እና የአእምሮ እክል ያለባቸውን ግለሰቦች ያደርጋሉ። ይህም ሁሉን አቀፍ የሕግ አቅም መርሆዎችን ይጥሳል።
ከማኅበራዊ-ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች መገለል	አብዛኛዎቹ በኢትዮጵያ የሚኖሩ አካል ጉዳተኞች በገጠር አካባቢዎች የሚኖሩ ሲሆን፣ ከፍተኛ ድህነት፣ የተገደበ የትምህርት ዕድል እና የመሠረታዊ አገልግሎቶች እጥረት ይገጥማቸዋል። ይህ ማኅበራዊ-ኢኮኖሚያዊ መገለል በፖለቲካዊ ሕይወት ውስጥ የመሳተፍ ችሎታቸውን በቀጥታ ይጎዳል። ብዙዎች በቤተሰብ ወይም በምጽዋት ላይ ጥገኛ ለመሆን ይገደዳሉ። ይህም የፖለቲካ ተሳትፎን የሩቅ ቅድሚያ ጉዳይ ያደርገዋል።
ደካማ የሆነ የሲቪል ማኅበራት አካባቢ	የአካል ጉዳተኞች ድርጅቶች (DPOs) እና ሌሎች ለሥራቸው ወሳኝ የሆኑ የሲቪል ማኅበራት እንቅስቃሴዎች በሕግ ማዕቀፎች፣ በማኅበራቱ የትብብር ድክመት፣ በሀብት ጉድለት እና መሰል ሳንካዎች አካላ ጉዳተኞችን ለፖለቲካ ተሳትፎ ለማንቃት እናይችሉ እንዲገደቡ አድርጓቸዋል። አሳታፊነትን ለማስፈን ቁርጠኛ የሆነ የፖለቲካ ፓርቲ የአካል ጉዳተኞች ድርጅቶችን እንደ ተፎካካሪ ሳይሆን፣ በእውነተኛ ተወካይ ዲሞክራሲ ለመገንባት ሥራቸው ወሳኝ የሆኑ ቁልፍ አጋሮች አድርጎ ሊመለከታቸው ይገባል።
አጠቃላይ የሆነ የሕግ ክፍተት	አንድ አጠቃላይ የአካል ጉዳተኞች ሕግ አለመኖሩ ድንጋጌዎች በተለያዩ የሕግ ሰነዶች ላይ ተበታትነው እንዲገኙ አድርጓል። ይህ መበታተን በሁሉም ዘርፎች ወጥ የሆነ የመብት ጥበቃ እና ውጤታማ አፈጻጸም ለማረጋገጥ አስቸጋሪ ያደርገዋል።

- የእርስዎ የፖለቲካ ፓርቲ በምን ያህል ደረጃ አካል ጉዳተኛ ዜጎችን በፓርቲው መዋቅር ውስጥ አካቶ ያሳትፋል?
- በእርስዎ አመለካከት አካል ጉዳተኛ ዜጎችን የፓርቲዎ አባል አድርጎ ውክልና እንዲኖራቸው እና ወደ ፓርቲ አመራርነት እንዲመጡ ማስቻል ለመን ይጠቅማል በለው ያማናሉ?

5.4.3. የፖለቲካ ፓርቲዎች አካል ጉዳተኞችን ለምን ያሳትፋሉ?

ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለማጠናከር የሚቻለው የዜጎችን ሁለንተናዊ የፖለቲካ ተሳትፎ በመገንባት ላይ እንደሚመሠረት አስቀድመን አይተናል። አካል ጉዳተኞችም ዜጎች ናቸው። የአካል ጉዳተኞች ተሳትፎ ዲሞክራሲን የሚያጠናክረው ለምንድን ነው?

ለአንድ የፖለቲካ ፓርቲ የአካል ጉዳተኞችን በፖለቲካ ሂደቶች ውስጥ ማካተት የልግስና ተግባር ሳይሆን (is not an act of charity) መሠረታዊ ሰብአዊ እና ህገ መንግስታዊ መብታቸውን ማረጋገጥ ነው ነው። ለዲሞክራሲያዊ መርሆዎች ቁርጠኛ እንደሆነች ሀገር፣ የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት እና ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ስምምነቶችን ማፅደቋ ሁሉም ዜጎች ሙሉና እኩል ተሳትፎ እንዲኖራቸው ጠንካራ የሕግ መሠረት ይሰጣል። ይሁን እንጂ የሕግ ማዕቀፎች ብቻ በቂ አይደሉም። **የፖለቲካ ፓርቲዎች የአካል ጉዳተኞችን በፖለቲካ ሕይወት ውስጥ ትርጉም ባለው መንገድ እንዳይሳተፉ የሚያግዱ ማኅበራዊ መሰናክሎችን ለማስወገድ በንቃት መሥራት አለባቸው**[13]።

1. አካታችነት የተሻለ ፖሊሲን ያመጣል

ከአጠቃላይ ሕዝቡ አንፃር ወደ 20 ከመቶ የተጠጋ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሰዎች የአካል ጉዳት ያለባቸው በመሆናቸው፤ አካል ጉዳተኞች ትልቅ የሚባል የሕዝብ አካልን የሚሸፍኑ ሲሆኑ እና ብዙ ጊዜ ያልተነካ ድምጽ ሰጪ ቡድን ናቸው። የፖለቲካ ፓርቲዎች አካል ጉዳተኞችን በአወቃቀራቸው ውስጥ በእውነት (genuinely) ሲያካትቱ፣ መላውን መራጭ ሕዝብ ለመወከል ያላቸውን ቁርጠኝነት ያሳያሉ። ይህ ደግሞ **ከፍተኛ ድጋፍ እንዲያገኙ ሊያደርግ ይችላል**። በተጨማሪም፣ አካታች የፖለቲካ ፓርቲ የበለጠ እውቀት ያለውና ውጤታማ ይሆናል።

ልዩ እውቀት	አካል ጉዳተኞች በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ሲካተቱ፣ ፓርቲዎች ብዙ ጊዜ ችላ ከተባለ የሕይወት ተሞክሮና እውቀት ተጠቃሚ ይሆናሉ። በተደራሽነት፣ በትምህርት እና በሥራ ዕድል ዙሪያ ያላቸው ቀጥተኛ እውቀት ለሕዝቡ ትልቅ ክፍል እውነተኛ ፍላጎት ምላሽ የሚሰጡ ጠንካራና ውጤታማ ፖሊሲዎችን ለመፍጠር የላቀ ጠቀሜታ አለው።
ብዝሃነት ያለው አመለካከት	አካል ጉዳተኞች ወደ ውይይት የሚያመጡት የተለያየ አመለካከት የፓርቲውን አቋም እና የፖሊሲ ማዕቀፎችን ያጠነክራል። አንድ ፖሊሲ የተለያየ ችሎታ ባላቸው ሰዎች ላይ ሲተገበር እንዴት እንደሚጠቅም ወይም እንደሚጎዳ ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ ፓርቲው ለመላው ማኅበረሰብ የበለጠ ሁሉን አቀፍ፣ ፍትሃዊ እና የመቋቋም አቅም ያላቸው መፍትሄዎችን ማዘጋጀት ይችላል።

2. አሳታፊነት የሕዝብን ግንዛቤ እና ተዓማኒነት ያሳድጋል

የሕዝብ አመኔታ ወሳኝ በሆነበት የፖለቲካ ሁኔታ ውስጥ በግልጽና በእውነተኛነት አሳታፊ የሆነ ፓርቲ ጎልቶ ይታያል። የአካል ጉዳተኞች መብትና ተሳትፎ በንቃት ሲያስተዋውቅ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ የዲሞክራሲያዊ መርሆችን ለመጠበቅና ሕገ መንግሥቱን ለማክበር ያለውን ቁርጠኝነት ያሳያል። ይሄም የሚከተሉትን ጥቅሞች ያስገኙለታል፦

የሕዝብ አመኔታ ማግኘት	አሳታፊ የሆነ ፓርቲ የበለጠ ዲሞክራሲያዊ፣ ግልጽና የሀገሪቱን ልዩነት የሚያንጸባርቅ ሆኖ ይታያል። ይህ የሕዝብን ግንዛቤ በከፍተኛ ሁኔታ ሊያሳድግ፣ በድምጽ ሰጪዎች ዘንድ ተዓማኒነትን ሊገነባ እና አዎንታዊ የመገናኛ ብዙኃን ትኩረትን ሊስብ ይችላል።
የገንዘብ ድጋፍ እና ሀብቶች ለማሰባሰብ	በብዙ አገሮች እና በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁኔታ የአንድ ፓርቲ ለአሳታፊነት ያለው ቁርጠኝነት የመንግሥት የገንዘብ ድጋፍን ለማግኘት ወይም ከዓለም አቀፍ አጋሮችና ከሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች ድጋፍን ለመሳብ እንደ አንድ ምክንያት ሊወሰድ ይችላል። ለምሳሌ የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/11 አንቀጽ 100 ንዑስ አንቀጽ 2 ሠ እና ረ በግልጽ እንዳስቀመጠው አንድ የፖለቲካ ፓርቲ የሚያገኘው የመንግሥት የገንዘብ ድጋፍ መጠን ከሚለኩ መስፈርቶች መካከል “ፓርቲው ለውድድር የሚያቀርባቸው የአካል ጉዳተኛ እጩዎች ብዛት” እና “የአካል ጉዳተኞች አባላት እና የአካል ጉዳተኛ አመራሮች ብዛት” ዋንኞቹ ናቸው።

3. “እኛ የሌለንበት ነገር ሁሉ ስለእኛ አይደለም” የሚለውን መርህ ለማክበር

ዓለም አቀፍ የአካል ጉዳተኞች እንቅስቃሴ መሪ ቃል የሆነው **“እኛ የሌለንበት ነገር ሁሉ ስለእኛ አይደለም” (Nothing About Us Without Us)** ለፖለቲካ ፓርቲዎች አካል ጉዳተኞችን ለማሳተፍ እጅግ አስፈላጊ መርህ ነው። አሳታፊነት ትርጉም ያለው እንዲሆን፣ አካል ጉዳተኞች በፓርቲው ሥራ ውስጥ በሁሉም ደረጃዎች በውይይቱ ጠረጴዛ ላይና በክፍሉ ውስጥ መገኘት አለባቸው።

ትርጉም ያለው ተሳትፎ	አካል ጉዳተኞችን ለይስሙላ ያህል በአንድ ቦታ ላይ ማስቀመጥ ብቻ በቂ አይደለም። ትርጉም ያለው ተሳትፎን እውን ለማድረግ በፓርቲው ውስጥ እውነተኛ ሥልጣንና ተጽዕኖ ሊኖራቸው ይገባል። ከፓርቲ መመሥረቻ ሰነዶችን ከመገምገም አንስቶ ፖሊሲዎችን እስከመቅረጽ እና እጩዎችን እስከመመልመል እና መምረጥ ድረስ በሁሉም የፓርቲው እንቅስቃሴ ውስጥ ገጽታዎች መታየት፣ ድምጻቸው መሰማትና መከበር አለበት።
በማኅበረሰቡ ውስጥ ያለውን ልዩነት ማወቅ	አንድ ፓርቲ አካል ጉዳተኝነት ውስብስብ ክስተት መሆኑን ማስታወስ አለበት። የአይነ ስውር ፍላጎት መስማት የተሳነው ወይም የመንቀሳቀስ ችግር ካለበት ሰው ፍላጎት በእጅጉ ይለያል። ስለዚህ፣ ፓርቲው የአካል ጉዳተኛ የማኅበረሰቡን ፍላጎት የተሟላና ጥልቅ ግንዛቤ ማግኘት እንዲችል ከተለያዩ የአካል ጉዳተኛ ቡድኖች ተወካዮችን ለማካተት መጣር አለበት።

5.4.4. የአካል ጉዳተኞችን በፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ ለማሳተፍ የሚረዱ ስልቶች

በኢትዮጵያ አውድ ዘላቂና እውነተኛ ዲሞክራሲዊ ሥርዓትን የአካል ጉዳተኞችን ሙሉና ትርጉም ባለው ተሳትፎ ሳያካትት ማሳካት አይቻልም። ኢትዮጵያ የአካል ጉዳተኞችን መብቶች የሚደግፉ ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌዎችና ብሔራዊ የሕግ ማዕቀፎች ቢኖሯትም፣ በፖሊሲና በተግባር መካከል ያለው ክፍተት አሁንም ሰፊ ነው። የፖለቲካ ፓርቲዎች ይህንን ክፍተት ለመሙላት ወሳኝ ሚና አላቸው። ይህ ሚና የአካል ጉዳተኞችን መብቶች ከመደገፍ ባለፈ በንቃት በራሳቸው መዋቅርና እንቅስቃሴዎች ውስጥ ማካተትንም ይጨምራል። የሚከተሉት ስልቶች የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የአካል ጉዳተኞችን እውነተኛና ዘላቂ ተሳትፎ እንዲያሳድጉ የሚረዳ ፍኖተ ካርታ ያቀርባሉ[14]።

ስልት 1፦ አካታችነትን ለማረጋገጥ ተጨባጭ እርምጃዎችን መውሰድ

አካታችነት ከወሬ የዘለለ እንዲሆን፣ በፓርቲ ሰነዶችና መዋቅሮች ውስጥ በሕግ መልክ መቀመጥ አለበት።

አካላዊ ተደራሽነት	የፓርቲ ቢሮዎችና የስብሰባ ቦታዎች በአካል ተደራሽ መሆናቸውን ያረጋግጡ። ይህ እንደ ተንሸራታች መንገዶች (ramps)፣ ግልጽ የእግር መንገዶች እና ተደራሽ መጸዳጃ ቤቶችን የመሳሰሉትን ያካትታል። የሕዝብ ቦታዎች፣ ለምሳሌ የምክር ቤት ስብሰባ አዳራሾች፣ ሙሉ በሙሉ ተደራሽ እንዲሆኑ በንቃት ይስሩ። በተጨማሪም ስለ ቦታዎቹ ተደራሽነት ለሁሉም አባላት ግልጽ በሆነ መንገድ ያሳውቁ።
የኮሚኒኬሽን ዘዴዎች ተደራሽነት	ሁሉም የፓርቲ ድረ ገጾች እና ዲጂታል አገልግሎቶች ተደራሽ መሆናቸውን ያረጋግጡ። የታተሙ ጽሑፎች ቀላልና ግልጽ ቋንቋን፣ ጥሩ የቀለም ውህደትንመጠቀም አለባቸው። በሚቻልበት ጊዜም ወደ ብሬይል (Braille) ጽሑፍ መቀየር ይመከራል። ሁሉም ዋና ዋና ማስታወቂያዎችና ዝግጅቶች የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ እንዲኖራቸው ያድርጉ።
የመጠባበቂያ ድልድል (Quotas) እና የተጠበቁ መቀመጫዎች	በፓርቲው ብጎ ፍቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ለውስጥ ፓርቲ የሥራ ቦታዎች እና ምርጫዎች የእጩዎች ዝርዝር ለአካል ጉዳተኞች የመጠባበቂያ ድልድል ኮታ ማስተዋወቅ። እነዚህ እርምጃዎች በተለይም በጊዜያዊነት፣ የሚታይ ውክልና ለማረጋገጥ እና አካል ጉዳተኞች የሥልጣን ቦታዎችን መያዝ እንደሚችሉ ለማሳየት ሁነኛ መንገድ ሊሆኑ ይችላሉ።
ደህንነትና ጥበቃ	በስብሰባዎችና በዝግጅቶች ላይ የሁሉም አካል ጉዳተኞች፣ በተለይም የአካል ጉዳተኛ ሴቶች፣ ደህንነት የተጠበቀ መሆኑን ያረጋግጡ። በፆታ ላይ የተመሰረተ ማንኛውንም ዓይነት ጥቃት ወይም ትንኮሳ የፈጸሙ ሰዎችን ለመለየትና ተጠያቂ ለማድረግ ጥብቅ የሆነ ፖሊሲ እና አሰራር ያዘጋጁ።

ስልት 2፦ በግንዛቤ ማስጨበጫ እና ሥልጠና ይጀምሩ

ብዙ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ልክ እንደ መላው ማኅበረሰብ፣ ስለ አካል ጉዳተኝነት እና አካል ጉዳተኞች ስለሚገጥሟቸው ስልታዊ መሰናክሎች ጥልቅ ግንዛቤ የላቸውም። ትርጉም ያለው አሳታፊነትን ለመፍጠር የመጀመሪያው እርምጃ ይህንን የእውቀት ክፍተት ከፓርቲው ውስጥ መፍታት ነው።

የእውቀት ኦዲት ያድርጉ	ፓርቲው በመጀመሪያ በራሱ ውስጥ ያሉትን የእውቀት ክፍተቶች መለየት እና አካል ጉዳተኞች ለመሳተፍ የሚያጋጥሟቸውን ነባር መሰናክሎች መረዳት አለበት። በመቀጠልም ከታችኛው የሥራ ዘርፍ አባላት እስከ ከፍተኛ አመራሮች ድረስ ላሉ የፓርቲው አባላት ሁሉ አጠቃላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘመቻ ማድረግ ያስፈልጋል።
አካል ጉዳተኛ አባላትን ያበረታቱ	ብዙ አካል ጉዳተኞች ሥር በሰደዱ ባህላዊ አመለካከቶች፣ ማኅበራዊ መድሎ እና መገለሎች ምክንያት ከአደባባይ ጉዳዮች ተገልለዋል። እንዲሁም በፖለቲካ ፓርቲ መዋቅሮች ውስጥ በራስ መተማመን ወይም ልምድ ሊያጡ ይችላሉ። ፓርቲው አካል ጉዳተኛ ለሆኑ አባላቱ እንደ ንግግር ችሎታ፣ የፖሊሲ ትንተና እና የፖለቲካ ሂደቶችን መረዳት ባሉ ጉዳዮች ላይ አቅማቸውን ለመገንባት የሚያስችሉ ልዩ የሥልጠና ፕሮግራሞችን ማቅረብ አለበት። ጠንካራና ውጤታማ አቀራረብ "ከእኛ ለእኛ" የሚለው ሞዴል ("from us to us") ሲሆን፣ በዚህ ሞዴል አካል ጉዳተኞች ለራሳቸው እኩዮች አሰልጣኝ እንዲሆኑ ሥልጠና ተሰጥቷቸው ሊበረታቱ ይገባል።

ስልት 3፦ ከአካል ጉዳተኞች ማኅበራት (OPDs) ጋር ጠንካራ አጋርነት መፍጠር

የፖለቲካ ፓርቲዎች የአካል ጉዳተኝነት ጉዳይ ላይ ብቸኛ ባለሙያ መሆን የለባቸውም። ይልቁንም፣ የራሳቸውን ማኅበረሰብ ፍላጎቶችና ጉዳዮች ጠንቅቀው የሚያውቁ የአካል ጉዳተኞች ማኅበራት (OPDs) ያለቸውን እውቀት ማወቅና መጠቀም አለባቸው።

መደበኛ የትብብር መድረኮችን መፍጠር	የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች ከተለያዩ የአካል ጉዳተኞች ማኅበራት መሪዎች ጋር በየጊዜው የሚገናኙበት መድረክ ሊፈጥሩ። ይህ ለግልጽ ውይይት፣ ለጋራ ሥልጠና እና ለቅስቀሳ ዘመቻዎች የጋራ እቅድ ማውጣት ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል። ይህ አቀራረብ መተማመንን እና እርስ በርስ ያለውን ሚናና እሴት የጋራ ግንዛቤ ለመገንባት ይረዳል።
የቅስቀሳ ጥረቶችን አንድ ማድረግ	የአካል ጉዳተኞች ቡድኖች የተለያዩ በመሆናቸው እና ፍላጎቶቻቸውም ስለሚለያይ፣ የጋራ መድረክ ቁልፍ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ድምጻቸውን አንድ ለማድረግ ይረዳል። የፖለቲካ ፓርቲዎች ለዚህ ውይይት እንደ አጋዥ በመሆን፣ የአካል ጉዳተኞች ማኅበራት የጋራ አቋም እንዲይዙ እና የጋራ መልእክታቸውን እንዲያስተጋቡ ሊረዱ ይችላሉ።

ስልት 4፦ ለአካል ጉዳተኞች ተሳትፎ እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮችን ማሸነፍ

አካል ጉዳተኞች ብዙውን ጊዜ ለፖለቲካ ፍላጎት አላቸው። ነገር ግን ከማኅበራዊ መገለል አንስቶ እስከ ተግባራዊ ችግሮች ድረስ ልዩ የሆኑ እንቅፋቶች ይገጥሟቸዋል። የፖለቲካ ፓርቲዎች እነዚህን እንቅፋቶች ለማስወገድ በንቃት መሥራት አለባቸው።

የገንዘብ ችግሮችን መፍታት	ብዙ አካል ጉዳተኞች የኢኮኖሚ ችግር ያጋጥማቸዋል። የፖለቲካ ፓርቲዎች የአባልነት እና የእጩነት ክፍያዎችን ለአካል ጉዳተኞች እንዲቀንሱ ወይም ሙሉ በሙሉ እንዲያነሱ የሚያስችል ፖሊሲ ሊያስቡበት ይገባል። በተጨማሪም ለማንኛውም ዕጩ ከፍተኛ ወጪ ለሚያስከትለው የምርጫ ቅስቀሳ የገንዘብ ድጋፍ ለመስጠት የፓርቲ ፈንድ ማቋቋም ይችላሉ።
መገለልን መዋጋት	ማኅበራዊ መገለልን እና አካል ጉዳተኞች ተደራሽ ያልሆኑ ቦታዎችን (ለምሳሌ የፓርቲውን ቢሮ፣ የስብሰባ ቦታዎች) ወይም እንቅስቃሴዎችን እንደ መደበኛ ነገር አድርገው የሚቀበሉበትን "ውስጣዊ አድሎአዊነት" መቀበል ("internalized discrimination") እና በንቃት ማስወገድ ያስፈልጋል። ፓርቲው አካል ጉዳተኞች ሸክም ሳይሆኑ የፖለቲካ ማኅበረሰቡ ጠቃሚና ዋነኛ አካል መሆናቸውን በተከታታይ ማስተላለፍ አለበት። ይህ ቤተሰቦቻቸውና ማኅበረሰባቸው የፖለቲካ ምኞታቸውን እንዲደግፉ ማበረታታትንም ያጠቃልላል።

ሳጥን 5.6:ከፍተኛ 10 የተለመዱ እንቅፋቶች

እያንዳንዱ ሀገር እና የፖለቲካ ፓርቲ የተለያየ ቢሆንም የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች የሚያጋጥሟቸው አንዳንድ የተለመዱ ማነቆዎች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል። እነዚህ ማነቆዎች ሁሉም የአካል ጉዳት ያለባቸውን ሰዎች በተመሳሳይ መልኩ አይነኩም።

1. የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች በፖለቲካ ውስጥ ፍላጎት የላቸውም ወይም የአመራር ሚናዎችን መውጣት አይችሉም የሚል የተሳሳተ አመለካከት።
2. ለአካል ጉዳተኞች በቂ የሥልጠና ዕድሎች አለመኖር እንዲሁም አስፈላጊ የሥልጠና ቁሳቁሶች ተደራሽ አለመሆን።
3. አንዳንድ የሕግ ድንጋጌዎች የአካል ጉዳተኞችን ተሳትፎ እና ድምጽ የመስጠት መብት ሊገድቡ ይችላል።
4. የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች እና የድምጽ መስጫ ሥርዓቶች ተደራሽ አለመሆን።
5. የፖለቲካ ፓርቲዎች ዝግጅቶች እና ስብሰባዎች አካላዊ ተደራሽነት በሌላቸው ቦታዎች መዘጋጀት። በተጨማሪም፣ ወደ እነዚህ ቦታዎች የሚወስደው የሕዝብ ትራንስፖርት ብዙውን ጊዜ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ አይደለም።
6. የፖለቲካ ፓርቲዎች የኮሚኒኬሽን ዘዴዎች እና የሚጠቀሙት ቋንቋ ተደራሽ አለመሆን።
7. ድህነት። ብዙ የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች ለምርጫ ዘመቻ እና ክፍያዎች እኩል የገንዘብ አቅም የላቸውም።
8. ሥራ መልቀቅ ግዴታ መሆን። በአንዳንድ አገሮች አሠሪዎች ሠራተኞች ለተመረጡ የሥራ መደቦች የምርጫ ዘመቻ መጀመር ከፈለጉ ሥራቸውን እንዲለቁ ሊጠይቋቸው ይችላሉ።
9. የፖለቲካ ጥቃት። በብዙ አገሮች የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች አካላዊ እና ሥነ ልቦናዊ ጥቃት ይደርስባቸዋል።
10. ሌላ ዓይነት መድልኦ። ብዙ የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች በጾታቸው፣ በብሔራቸው፣ በዘራቸው ወይም በሌሎች ምክንያቶች የተነሳ ብዙ ዓይነት መድልኦ ይገጥማቸዋል።

ሳጥን 5.7:የአካል ጉዳተኞችን በፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ የማካተት ዝቅተኛ መስፈርቶች (Minimum Standards on Inclusion)

በኬንያ የፖለቲካ ፓርቲዎች አካል ጉዳተኞችን በፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ የማካተት ዝቅተኛ መስፈርቶች ዝርዝር አዘጋጅተዋል። እነዚህ መስፈርቶች የተዘጋጁት ለኬንያ ነባራዊ ሁኔታ ቢሆኑም በኢትዮጲያ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተፈፃሚ ላይሆኑ ይችላሉ። አካል ጉዳተኞችን በፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ ለማካተት የወጡ ዝቅተኛ መስፈርቶች (Minimum Standards) ምሳሌዎች ፦

1. አካል ጉዳተኞች በፖለቲካ ፓርቲዎች ሂደት ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ የሚመለከቱ ቁልፍ ሕጎችን፣ ፖሊሲዎችን እና መመሪያዎችን ማክበር።
2. የአካል ጉዳተኞችን የሚያካትቱ የፓርቲ ፖሊሲዎች፣ ማንፌስቶ፣ መተዳደርያ ደንብ እና የምርጫ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ምልመላና መምረጫ ደንቦች መኖር።
3. ሁሉንም ያካተተ የፓርቲ አመራርና የአስተዳደር መዋቅር መፍጠር (ለምሳሌ የፓርቲ ኮሚቴዎች፣ የአካል ጉዳተኞች ክንፍ ወይም ሊግ ወዘተ)።
4. አካል ጉዳተኞች መረጃዎችን፣ ግንኙነቶችን፣ የቢሮ ህንፃዎችን እና አገልግሎቶችን ማግኘት/መድረስ እንዲችሉ ማድረግ።
5. ለአካል ጉዳተኞች ፍትሃዊ እና ግልጽነት ያለው የፓርቲ እጩ ተወዳዳሪዎች ምልመላ እና መምረጫ ዝርዝር ሂደት መዘርጋት።
6. የፓርቲ ውስጥ አለመግባባቶችን ለመፍታት ሁሉን ያካተተ የቅሬታ እና የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት መዘርጋት።
7. አካል ጉዳተኞች በፓርቲ የሥራ ሂደቶች እና የምርጫ ቅስቀሳዎች ውስጥ ሙሉ በሙሉ እንዲሳተፉ ማድረግ።
8. ለአካል ጉዳተኞች እንቅስቃሴዎች ሁሉን ያካተተ ፋይናንስ እና ተጠያቂነት መኖር።
9. የአካል ጉዳተኞችን ተሳትፎ የሚያሳይ መረጃ መሰብሰብ እና መከታተል (Data and monitoring)።
10. አካል ጉዳተኞችን እንደ ፓርቲ አባላት መመልመል እና በፓርቲው ውስጥ እንዲቆዩ ማበረታታት።

እነዚህን ስልቶች በመተግበር አንድ የፖለቲካ ፓርቲ በእውነትም አሳታፊ እና ለወደፊት የሚያስብ ድርጅት እንደሆነ ስም መገንባት ይችላል። ይህም የአካል ጉዳተኞች አስተዋፅዖ የሚደገፍበት ብቻ ሳይሆን፣ ለሀገሪቷ ስኬት ወሳኝ እንደሆነ የሚታይበትን ባህል ያዳብራል።

5.5. የካታችነት የፖለቲካ ባሕል ግንባታ

የኢትዮጲያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት የአካታችነትን ባህል በኢትዮጲያ የፖለቲካ ምህዳር ውስጥ ለመገንባት ያሳየው ቁርጠኝነት እና የወሰዳቸው እርምጃዎች በብዙ ሀገራት በምሳሌነት ሊጠቀስ የሚችል ነው። የጋራ ምክር ቤቱ የፖለቲካ አካታችነትን እውን ለማድረግ አስቀድሞ የሴቶች፣ የወጣቶች እና የአካል ጉዳተኞችን ክንፍ በማዋናው ጽሕፈት ቤት ሥር እንዲቋቋሙ አድርጓል። በመቀጠልም በሁሉ የክልል የጋራ ምክር ቤቶች ሥር ሦስቱ ክንፎች እንዲዋቀሩ በማድረግ የካታችነት ባህል በፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ እንዲተዋወቅ ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል።

የጋራ ምክር ቤቱ መተዳደርያ ደንቡን ሲያረቅ እና ሲጸድቅም የሴቶች፣ የወጣቶች እና የአካል ጉዳተኞች በይፋ እውቅና እንዲያገኙ ከማድረግ ባሻገር የራሳቸው መመሪያ የማውጣት ሥልጣን በመስጠት ጭምር ክንፎቹ በጋር ምክር ቤቱ ሥር ሆነው እራሳቸውን የቻሉ፣ በራሳቸው አቅደው የሚፈጽሙ ሙሉ ስልጣን ያላቸው (autonomous) ክንፎች እንዲሆኑ አስችሏቸዋል። ይህንም ተከትሎ ሦስቱም ክንፎች የአደረጃጀት እና የአሰራር መመሪያ አውጥተው በጠቅላላ ጉባኤያቸው በማጸደቅ ወደ ሥራ ገብተዋል። ከዚህ አንጻር የጋራ ምክር ቤቱ የካታችነት ባህልን ለመገንባት ተራማጅ እና ቁረጠኛ መሆኑን በተጨባጭ አስመስክሯል። አክታችነትን በተምለከተ የጋራ ምክር ቤቱ መተዳደርያ ድንብ ይዘትን በአጭሩ ለመቃኘት እንሞክር።

መተዳደሪያ ደንቡ ለጋራ ምክር ቤቱ ሦስቱ ክንፎች (የሴቶች፣ የወጣቶች እና የአካል ጉዳተኞች) በዝርዝር እውቅና የሰጠው በአንቀጽ 35 ነው። ይህ 12 ያህል ዝርዝር ንዑስ አንቀጾች ያሉት አንቀጽ የክንፎቹን አደረጃጀት እና ተግባር በግልጽ አስቀምጧል። የአንቀጹ ዋና ጭብጥ የጋራ ምክር ቤቱ ክንፎች አደረጃጀትና ተግባር ሲሆን፣ የሚከተሉትን ነጥቦች ይዟል[15]:-

የመመስረት ዓላማ	ክንፎቹ የተቋቋሙት ወጣቶች፣ ሴቶች እና አካል ጉዳተኞች የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ መብቶቻቸውን ለማስከበር የሚያስችል መድረክ ሆነው እንዲያገለግሉ ነው።
የሥራ ግንኙነት እና ተጠያቂነት	ክንፎቹ ለጋራ ምክር ቤቱ ራዕይ፣ ዓላማ እና ተልዕኮ መሳካት የበኩላቸውን ሚና ይወጣሉ። የክንፎቹ ስራ አስፈጻሚዎችም በየደረጃው ካሉ የጋራ ምክር ቤቶች ጋር በቋሚነት ይሰራሉ።
የፖለቲካ ተሳትፎን ማጠናከር	እያንዳንዱ ክንፍ የሚወክለውን አካል በፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ የፖለቲካ ተሳትፎ እና ውሳኔ አሰጣጥ ድርሻ እንዲጠናከር ይሰራል፤ ድምፁ እንዲሰማም ያግዛል።
የድጋፍ አሰጣጥ	የጋራ ምክር ቤቶች (ሀገራዊው እና የክልል የጋራ ምክርቤቶች) ለክንፎቹ በጀት፣ የአቅም ግንባታ እና ሌሎች ድጋፎችን እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ።
የአመራርና አደረጃጀት	ክንፎቹ ሰባት የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት እንደሚኖራቸው እና የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ለጋራ ምክር ቤቱ ስራ አስፈፃሚ እንደሚያቀርቡ ተደንግጓል።
ራስን የማስተዳደር መብት	እያንዳንዱ ክንፍ ከዚህ መተዳደሪያ ደንብ ጋር የማይቃረን ዝርዝር የአሰራር መመሪያ የማዘጋጀት እና በጠቅላላ ጉባኤያቸው የማፅደቅ መብት አለው።

መተዳደሪያ ደንቡ ከአንቀጽ 36 እስከ 38 ድረስ የእያንዳንዱን ክንፍ (የሴቶች፣ የወጣቶች እና የአካል ጉዳተኞች) ተግባርና ኃላፊነት በዝርዝር ያስቀምጣል። እነዚህ አንቀጾች ክንፎቹ ለሚወክሉት አካል መስጠት ስላለባቸው ዝርዝር ኃላፊነቶች ይገልጻሉ። የአንቀጾቹ ዋና ጭብጥ የሴቶች፣ የወጣቶች እና የአካል ጉዳተኞች ክንፎች ዋና ተግባራትና ኃላፊነቶች የሚሉ ናቸው። ሁሉም ክንፎች የሚጋሯቸው ዋና ተግባራት የሚከተሉት ናቸው:-

ማስተባበር እና ማጠናከር	አባላቶቻቸው ለመብቶቻቸው እንዲታገሉ ማስተባበር እና የጋራ ምክር ቤቱ አባል ፓርቲዎች ውስጥ እንዲደራጁና እንዲጠናከሩ መርዳት።
የፖለቲካ ተሳትፎን ማሳደግ	የአባላቶቻቸውን የፖለቲካ ተሳትፎ እና ውሳኔ ሰጪነት ሚና ማሳደግ።
የመሪነት አቅም ማጎልበት	አባላቶቻቸው በፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ የመሪነት ብቃታቸው እንዲያድግ ድጋፍ ማድረግ።
ሌሎች ኃላፊነቶች	ከሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው እና ከጠቅላላ ጉባኤ የሚሰጣቸውን ሌሎች ተግባራት መፈጸም።

መተዳደሪያ ደንቡ ተጠሪነትን አስመልክቶ በዝርዝር ያስቀመጠ ሲሆን፣ በአንቀጽ 64 ንዑስ አንቀጽ 7 ላይ የሁለትዮሽ ተጠሪነትን ሞዴል አስተዋውቋል። ይህ ሞዴል የፖለቲካ ፓርቲዎች በፓርቲዎቻቸው መዋቅር ውስጥ የሚደራጁ የሴቶች፣ የወጣቶች እና የአካል ጉዳተኛ ክንፎች የፓርቲው አካል እንደመሆናቸው ራሳቸውን ችለው መንቀሳቀስ የሚችሉበትን አሰራር ያስቀምጣል። የዚህ አንቀጽ ዋና ጭብጥ የክንፎቹ ተጠሪነትና የሥራ ግንኙነት ሲሆን፣ የክንፎቹን የሥራ ተጠያቂነት በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፍለዋል፦

ለመረጣቸው አካል (የክንፎቹ ጠቅላላ ጉባኤ)	ክንፎቹ የሥራ አስፈጻሚ ምርጫን፣ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርቶችን፣ የሥራ ዕቅዶችን እና የአሠራር መመሪያዎችን ማጽደቅን ወይም ማሻሻልን በሚመለከት ለጉባኤው ተጠሪ ይሆናሉ።
በየደረጃው ላሉ የጋራ ምክር ቤቶች የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴዎች	የዕለት ተዕለት ሥራዎችን፣ ረቂቅ የሥራ እቅዶችን፣ የበጀት አመዳደብን እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ያላቸውን ግንኙነት በሚመለከት ለኮሚቴዎቹ ተጠሪ ይሆናሉ።
ተጠሪነታቸው ከታች ወደ ላይ ነው	ክንፎቹ የሥራ አፈጻጸማቸውን በተመለከተ ተጠሪነታቸው በቅድሚያ ለታችኛው መዋቅር ማለትም ለመረጣቸው አካል (ጠቅላላ ጉባኤያቸው) እና ከዛም በላይ ለጋራ ምክር ቤቱ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴዎች ይሆናል።

ምዕራፍ ስድስት

በኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ውስጥ ውጤታማ ተሳትፎ ማድረግ

በአለም ባሉ ሀራት የፖለቲካ ፓርቲዎች ስብስብ ውስጥ እንብዛም ባለተመደ መልኩ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎችም በአንድ የጋራ መድረክ ላይ ተሰባስበው ቁልፍ አገራዊ ጉዳዮችን የሚመክሩበት ሥርዓት መፍጠር ችለዋል። የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች መጋቢት 5 ቀን 2011 ዓ.ም. በተፈራረሙት የቃል ኪዳን ሰነድ እና በምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/11 አንቀጽ 141 መሠረት "በኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት" ተብሉ ተመስርቷል። የጋራ ምክር ቤቱ ከተመሠረተበት ጊዜ አንስቶ በርካታ ተግባራትን አከናውኗል። ምክር ቤቱ ከፈፀማቸው ዋና ዋና ተገባራት መካከል የሚከተሉት ጉዳዮች በምሳሌትነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው፦

- በፓርቲዎች መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን በውይይት መፍታት፤
- በፓርቲዎች እና በመንግሥት ተቋማት መካከል ውይይቶች እንዲካሄዱ መድረኮችን ማመቻቸት፤
- ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የፓርቲዎችን የአቅም ግንባታ (በስልጠናና የልምድ ልውውጥ) መደገፍ፤
- የክልልና የከተማ አስተዳደር የጋራ ምክር ቤቶች እንዲመሰረቱ በማስተባበር መዋቅሩን ማስፋፋት፤
- የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክክር (inter-party dialogues) ፤
- አካታች የፖለቲካ ባህልን ለማስረጽ የሴቶች፣ የወጣቶችና የአካል ጉዳተኞች ክንፎች እንዲቋቋሙ ማድረግ፤
- ፓርቲዎች እንዲቀራረቡና በጋራ ጉዳዮች ላይ የጋራ አቋም እንዲይዙ መድረክ መፍጠር።

የጋራ ምክር ቤቱ ተቋማዊ አቅሙን ለማሳደግ እና በሕግና በሥርዓት እንዲመራ ለማድረግ የመተዳደሪያ ደንብ አውጥቷል። ይህ ደንብ በምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ ከፀደቀ በኋላ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ዕውቅና ተሰጥቶት ወደ ትግበራ ገብቷል። የኢትዮጲያ ፖለቲካ ፓርቲዎች በጋራ ምክር ቤቱ ውስጥ ንቁና ወሳኝ ሚና እንዲወጡ፣ የመተዳደሪያ ደንቡን በሚገባ መረዳት እና ከምክር ቤቱ ጋር የተሳካ ግንኙነት መፍጠር ወሳኝ ነው።

6.1. የጋራ ምክር ቤቱ አወቃቀር እና ኃላፊነት

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት የተመሠረተበት ዋነኛ ዓላማ በሀገሪቱ ዘላቂ ሰላም፣ ዲሞክራሲ፣ የሕግ የበላይነት እና የሕዝቦች አብሮነት እንዲሰፍን የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማድረግ ነው። የመተዳደሪያ ደንቡ መግቢያ ላይ እና አንቀጽ 13 ላይ እንደተዘረዘረው፣ የጋራ ምክር ቤቱ ተግባር እና ኃላፊነት (mandates) የሚከተሉትን ዋና ዋና ነጥቦች ያካትታል[1]፦

ጠንካራ ዲሞክራሲን መገንባት	የጋራ ምክር ቤቱ ጠንካራ፣ ዘላቂና እውነተኛ የዲሞክራሲና የመድብለ-ፓርቲ ሥርዓት በሀገሪቱ እንዲኖር ለማስቻል የፖለቲካ ፓርቲዎች በጋራ ድምጽ የሚሰሙበት መድረክ ሆኖ ያገለግላል።
የሕዝብ አብሮነትን ማጠናከር	የጋራ ምክር ቤቱ የሕዝቦችን አብሮነት፣ መቻቻል፣ መተሳሰብ እንዲሁም ሕገ-መንግሥታዊ እና ሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች አስተዋጽኦ የሚያደርጉበትን ሁኔታ ያመቻቻል።
የፖለቲካ ባህልን ማሻሻል	በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል መግባባት፣ መከባበር እና ጤናማ ውድድር የሰፈነበት የፖለቲካ ባህል እንዲዳብር የጋራ ምክር ቤቱ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር በመተባበር ይሰራል።
ብሔራዊ ጉዳዮችን መደገፍ	በሀገሪቱ ዘላቂ ሰላም፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት እንዲረጋገጥ፣ የሕግ የበላይነት እንዲከበር እና መልካም አስተዳደር እንዲጎለብት የፓርቲዎችን የጋራና የትብብር ጥረቶችና እንቅስቅሴዎችን ያበረታታል።
የምርጫ ሥርዓቱን ማሳደግ	የጋራ ምክር ቤቱ በኢትዮጲያ የሚካሄዱ ምርጫዎች አሳታፊ፣ አካታች፣ ነፃ፣ ፍትሃዊ እና ሰላማዊ እንዲሆኑ የሚያስችል የምርጫ ሥርዓት እንዲፈጠር ፓርቲዎች በጋራ እንዲሰሩ ያግዛል።
የፖለቲካ ፓርቲዎችን አቅም መገንባት	የፖለቲካ ፓርቲዎችን አቅም ለማጎልበት፣ ዘመናዊ አሰራሮችን ለማስፋት እንዲሁም የውይይትና የልምድ ልውውጥ መድረኮችን ከሚመለከታቸው ባልደርሻ አካላት ጋር በመተባበር ያመቻቻል።
የግጭት አፈታት	በፓርቲዎች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶችን በውይይትና በምክክር እንዲፈቱ የጋራ መድረክ ሆኖ ያገለግላል።
ምርምርና የልምድ ለውውጥ	በፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ጥናትና ምርምር በማካሄድ በፓርቲዎች መካከል የእውቀት ሽግግር እንዲኖር ያበረታታል።
ደንቦችን መከታተልና ማስፈጸም	የቃል ኪዳን ሰነዱ እና መተዳደሪያ ደንቡ በሁሉም አባል ፓርቲዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፤ ጥሰት ሲፈጠርም የማጣራትና ውሳኔ የመስጠት ስልጣን አለው።
ግልጽነትና ተጠያቂ	የጋራ ምክር ቤቱን የጋራ ውሳኔዎችን እና መግለጫዎችን በመገናኛ ብዙኃን ለሕዝብ ይፋ ያደርጋል።

ሳጥን 6.1: የጋራ ምክር ቤቱ ተልዕኮ

ዴሞክራሲያዊነት፣ አካታችነት፣ እኩልነት፣ ተቋማዊ ነፃነት፣ ፍህታዊነት፣ ሰላማዊነት፣ እና ተጠያቂነት የሰፈነበት የፖለቲካ ባህል እንዲፈጠር የፖለቲካ ምህዳሩን በማስፋት እና ዘላቂ በማድረግ የፖለቲካ ፓርቲዎች በመድበለ ፓርቲ ሥርዓት ውስጥ ገንቢ በሆነ መንገድ ለመሳተፍ ያላቸውን አቅም ማሳደግ፤ በፓርቲዎች መካከል እንዲሁም ከመንግስት አካላት ጋር የሚፈጠሩ አለመግባባቶች በውይይት ወይም በድርድር እንዲፈቱ የሚያስችል መድረክ ሆኖ ማገልገል ነው።

የጋራ ምክር ቤቱ መተዳደርያ ደንቡ ከምክር ቤቱ ተግባር እና ኃላፊነት (mandates) በተጨማሪ ዘጠኝ ያህል ዝርዝር ዓላማዎች እንዳሉት አስቀምጧል።

ሳጥን 6.2: የጋራ ምክር ቤቱ ዓላማዎች

1. የፖለቲካ ፓርቲዎችን አቅም በመገንባት የዴሞክራሲ እና የመድብለ ፓርቲ ስርዓት ግንባታን ማጠናከር፤
2. በፓርቲዎች መካከል ሊነሱ የሚችሉ ፖለቲካዊ አለመግባባቶችን በውይይት እና በእርስ በርስ መግባባት እንዲፈቱ የጋራ መድረክ ሆኖ ማገልገል፤
3. በፖለቲካ ፓርቲዎች እና በመንግስት አካላት፣ በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን ለመፍታት የውይይት እና የምክክር መድረኮችን በማመቻቸትና በማማከር የመግባቢያ መድረክ ሆኖ ማገልገል፤
4. በሀገራዊ፣ ዓለም አቀፋዊ እና አከባቢያዊ ጉዳዮች ላይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የውይይት መድረኮችን ማመቻቸት፤
5. የህግ የበላይነትን በማስፈን ሰላምና መረጋጋት እንዲኖር ለማስቻል፣ የዜጎች ህገ-መንግስታዊ መብት እንዲከበርና እንዲረጋገጥ የፖለቲካ ፓርቲዎች በሃላፊነት እንዲንቀሳቀሱ ለማድረግ የሚያስችል የጋራ መድረክ መፍጠርና ስልት መንደፍ፤
6. ምርጫዎች ጊዜያቸውን የጠበቁ፣ ሰላማዊ፣ ነጻ፣ ፍትሃዊ እና ተዓማኒ እንዲሆኑ በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ከዝግጅት እስከ ድህረ-ምርጫ ባለዉ ሂደት የፖለቲካ ፓርቲዎችን ተሳትፎና ሚና ማጎልበት፣
7. መንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ሀገር አቀፍ እና አለም አቀፍ ተቋማት ጋር በጋራ ጉዳዮች በትብብር መስራት፤
8. ጠንካራ የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት ለመመስረት ለሚደረገው ጥረት ትርጉም ያለው ሚና መጫወት፤

ለዜጎች የምርጫ፣ የሲቪክና የፖለቲካ ግንዛቤ ማሳደጊያ ተግባራትን መካናወን ናቸው።

6.1.1. የጋራ ምክር ቤቱ አደረጃጀት

የጋራ ምክር ቤቱ የተጣለበትን ኃላፊነት፣ ተልዕኮ እና ዓላማ ለማስፈጸም የሚያስችል ዝርዝር መዋቅር አደራጅቷል። የመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 12 ላይ እንደተቀመጠው፣ የምክር ቤቱ አደረጃጀት ስምንት ዋና ዋና ክፍሎችን ያካተተ ነው፦

ሳጥን 6.3: የጋራ ምክር ቤቱ አደረጃጀት

- ጠቅላላ ጉባኤ፦
- የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ
- የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ
- ጽሕፈት ቤት
- ቋሚ ኮሚቴዎች
- የወጣቶች ክንፍ
- የሴቶች ክንፍ
- የአካል ጉዳተኞች ክንፍ

ከዚህ በተጨማሪም፣ ምክር ቤቱ በክልል እና/ወይም በከተማ አስተዳደሮች የጋራ ምክር ቤቶች እንዲኖሩት የመተዳደሪያ ደንቡ ይፈቅዳል። እነዚህ ቅርንጫፍ ምክር ቤቶችም ጠቅላላ ጉባኤ፣ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እና ሌሎች መዋቅሮችን ሊያካትቱ ይችላሉ። እስካሁን ባለው ተሞክሮ፣ አብዛኞቹ የክልልና የከተማ አስተዳደር የጋራ ምክር ቤቶች ጠቅላላ ጉባኤ፣ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እና ሦስቱን ክንፎች አካተው እንደተዋቀሩ መገንዘብ ይቻላል።

የመተዳደሪያ ደንቡ ለእያንዳንዱ የጋራ ምክር ቤቱ መዋቅር ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነት መድቧል። ለምሳሌ ያህል ከፍተኛ ሥልጣንና ኃላፊነት ያላቸውን የጠቅላላ ጉባኤውን እና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴውን አወቃቀርና ተግባር ቀጥለን እንመለከታለን (እነዚህ ዝርዝሮች በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 14 እስከ 20 ድረስ ተካተዋል)።

ጠቅላላ ጉባኤ

የጋራ ምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ ከፍተኛው የሥልጣን አካል ሲሆን፣ እያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ በአንድ ሰው የሚወከልበት ስብስብ ነው።

ዋና ተግባራትና ኃላፊነቶች፦

- ***ፖሊሲና ደንብ ማውጣት***፦ ምክር ቤቱን የሚመሩ የቃል ኪዳን ሰነዶችን፣ ፖሊሲዎችን፣ ደንቦችን እና ስትራቴጂክ ዕቅዶችን ያወጣል፣ ያሻሽላል ወይም ይሰርዛል።
- ***አመራሮችን መምረጥና ማሰናበት***፦ የምርጫ ኮሚቴ፣ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ፣ የቋሚ ኮሚቴ እና የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ አባላትን ይመርጣል እንዲሁም አመኔታ ሲያጣ ከኃላፊነት ያነሳል።
- ***የፓርቲ አባልነትን መውሰን***፦ አዳዲስ ፓርቲዎች የአባልነት ጥያቄ ሲያቀርቡ መርምሮ ይወስናል።
- ***ዕቅድ፣ የሪፖርትና ግምገማ***: በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እና በኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ የሚቀርቡ ዓመታዊ የሥራና የበጀት ዕቅዶችን እንዲሁም የኦዲት ሪፖርቶችን መርምሮ ያጸድቃል።
- ***የፖለቲካ ውሳኔ መስጠት***፦ የፖለቲካ ውሳኔ በሚፈልጉ አገራዊ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ የመፍትሔ ሐሳብና አቅጣጫ ያስቀምጣል።

የስብሰባ አደረጃጀትና ሂደት

- ***የስብሰባ ጊዜ***፦ ጠቅላላ ጉባኤው በየአራት ወሩ፣ በዓመት ሦስት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያካሂዳል። አስቸኳይ ጉዳይ ሲያጋጥም ደግሞ በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ወይም በ1/3ኛው የአባላት ጥያቄ መሠረት አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።
- ***ምልዓተ ጉባኤ***፦ ከጠቅላላ አባላት መካከል 50%+1 አባላት ሲገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል።
- ***የውሳኔ አሰጣጥ***፦ የጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ የሚተላለፈው በስምምነት ነው። ስምምነት ላይ መድረስ ካልተቻለ ግን በ3/4ኛው የድምፅ ብልጫ ውሳኔ ይሰጣል።

የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ

በመተዳደርያ ደንቡ መሠረት የጋራ ምክር ቤቱ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ከጠቅላላ ጉባኤ ቀጥሎ ከፍተኛው አስፈጻሚ አካል ነው።

የአደረጃጀትና የሥራ ሂደት፦

- ***የአባላት ቁጥርና ምርጫ***፦ ኮሚቴው 7 (ሰባት) አባላት ያሉት ሲሆን፣ በጠቅላላ ጉባኤ ይመረጣሉ። ገዥው ፓርቲ ግን በየደረጃው በሚገኙ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴዎች ውስጥ በቀጥታ አባል ይሆናል።
- ***የአባላት ብቃትና ስብጥር***፦ አባላቱ ብቁ፣ መልካም ስነምግባር ያላቸው እና የጋራ ምክር ቤቱን ደንብ የሚያከብሩ መሆን አለባቸው። በተጨማሪም፣ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ስብጥር ጾታን፣ አካል ጉዳተኝነትን እንዲሁም የሀገራዊና የክልላዊ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ውክልና ያማከለ መሆን አለበት።
- ***የስብሰባ ጊዜና ውሳኔ***፦ ኮሚቴው በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል። አስቸኳይ ስብሰባም ሊጠራ ይችላል። ምልዓተ ጉባኤ የሚሆነው 50%+1 አባላት ሲገኙ ሲሆን፣ ውሳኔዎች የሚተላለፉት በተባበረ ድምጽ ወይም በ3/4 ድምፅ ነው።

ዋና ተግባራትና ኃላፊነቶች፦

- ***የስራ እቅድና በጀት***፦ ዓመታዊ የሥራ እቅድ እና በጀት አዘጋጅቶ ለጠቅላላ ጉባኤ በማቅረብ ያስወስናል፣ እንዲሁም ተግባራዊነቱን ያስፈጽማል።
- ***የፕሮግራሞች ትግበራ***፦ በጠቅላላ ጉባኤው የሚወሰኑ ፖሊሲዎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል።
- ***ክትትልና ቁጥጥር***፦ የክልልና የከተማ አስተዳደር የጋራ ምክር ቤቶችን ያደራጃል፣ ያስተባብራል፣ ይከታተላል። የቋሚ ኮሚቴዎችን፣ የሴቶች፣ የወጣቶችና የአካል ጉዳተኞች ክንፎችን የሥራ አፈጻጸም ይቆጣጠራል።
- ***የአቅም ግንባታና ድጋፍ***፦ ለአባል ፓርቲዎች ስልጠናና ሌሎች የአቅም ግንባታ ስራዎች በፍትሃዊነት እንዲዳረሱ ያደርጋል እንዲሁም ከአገር ውስጥና ዓለም አቀፍ አጋር አካላት ጋር በትብብር ይሰራል።
- ***የጽሕፈት ቤት አመራር***፦ የጋራ ምክር ቤቱን ዋና ጽሕፈት ቤት በበላይነት ይመራል፣ ሰራተኞችን ይቀጥራል፣ ያሰናብታል እንዲሁም የፋይናንስ አሰራር መመሪያ ያወጣል።

ከሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በተጨማሪ የጋራ ምክር ቤቱ ስድስት ቋሚ ኮሚቴዎች አሉት። እነዚህ ኮሚቴዎች እያንዳንዳቸው ሦስት አባላት ያሏቸው ሲሆን፣ ከጠቅላላ ጉባኤ አባላት መካከል ይመረጣሉ። ቋሚ ኮሚቴዎቹ የሚከተሉትን ባህሪያት ይኖራቸዋል፦

- እያንዳንዱ ኮሚቴ ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢና ጸሐፊ በመመደብ የሥራ ክፍፍል ያደርጋል።
- የክልልና የከተማ አስተዳደር የጋራ ምክር ቤቶች እንደአስፈላጊነቱ ቋሚ ኮሚቴዎችን የማቋቋም ሥልጣን አላቸው።
- ለቋሚ ኮሚቴ አባልነት የሚመረጡ እጩዎች አግባብነት ያለው የትምህርት ዝግጅትና የሥራ ልምድ፣ እንዲሁም መልካም ስነምግባር ሊኖራቸው ይገባል። በተጨማሪም፣ የጋራ ምክር ቤቱን ሕገ-ደንብ የሚያከብሩ እና ለመሪነት የሚያስፈልጉ ሌሎች መስፈርቶችን የሚያሟሉ መሆን አለባቸው።

የመተዳደሪያ ደንቡ ከአንቀጽ 28 እስከ 33 ድረስ የእያንዳንዱን ቋሚ ኮሚቴ ተግባር እና ኃላፊነት በዝርዝር ያስቀምጣል።

ሳጥን 6.4: የጋራ ምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች ዝርዝር	
• የምርጫ እና ምክክር ቋሚ ኮሚቴ • የአቅም ግንባታ ቋሚ ኮሚቴ • የሕግ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ	• የአስተዳደርና የፋይናንስ ቋሚ ኮሚቴ • የጥናት፣ የምርምርና የፖሊሲ ቋሚ ኮሚቴ • የአደረጃጀት ቋሚ ኮሚቴ

የጋራ ምክር ቤቱ መዋቀሮች እና አደረጃጀቶች የተዋቀሩት የምክር ቤቱን ተልዕኮ፣ ተግባራት እና አላማማዎች ለማስፈፀም በሚያስችል መልኩ በመሆኑ በርካታ ጠቃሚ ተግባራትን ለማከናዎን አስችሎታል።

6.1.2. የጋራ ምክር ቤቱ መመሥረት ለዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ የሚፈጥረው እድል

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ለትብብርና ለውይይት የተፈጠረ መድረክ እንደመሆኑ ለፖለቲካ ፓርቲዎች ተቀራርቦ መሥራት እና መተባበር ትልቅ በር ከፍቷል።

- የጋራ ምክር ቤቱ ከመመሥረቱ በቀደምመው ጊዜ የፖለቲካ ፓርቲዎች የነበራቸውን ግንኙነት ካለዎት ልምድ በመነሳት እንዴት ይገመግሙታል?

በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ በፓርቲዎች መካከል ያለው ፉክክር ከትብብር ይልቅ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ሆኖ ቆይቷል። ይህ ሁኔታ አንዳንድ ጊዜ በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል አለመተማመንንና አለመረጋጋትን ሲያስከትል ቆይቷል። በኢትዮጲያ የፖለቲካ ለውጥና ማሻሻያ ከተጀመረ 2010 ዓ.ም ወዲህ በፓርቲዎች መካከል በጋራ አጀንዳዎች ላይ የጋራ ስምምነት ላይ ለመድረስ ሁኔታዎችን የሚያመቻች ሁኔታ መፍጠር በመቻሉ የጋራ ምክር ቤቱ በበርካታ የፓርቲ መሪዎች የለውጡ ሂደት ስኬት ወሳኝ አካል እንደሆነ ተደርጎ የሚቆጠር ነው። ከፖለቲካ ጉዳዮች ውስብስብነት እና በማኅበራዊ-ፖለቲካዊ ልዩነት ጥልቀት ምክንያት በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል ግልጽ፣ በመረጃ ላይ የተመሠረተና ቀጣይነት ያለው ውይይት ማድረግ አስፈላጊ ነው። የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ወሳኝ ሚና የሚጫወት የሚጠበቅበት እዚህ ላይ ነው።

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ለፓርቲዎች ትብብርና ተሳትፎ እንደ መዋቅር ገለልተኛና ወሳኝ መድረክ ሆኖ ያገለግላል። የተለያዩ የርዕዮተ ዓለም የሚከተሉ ሀገራዊ እና የክልል ፓርቲዎች ተሰባስበው ገንቢ በሆኑ ውይይቶች እንዲሳተፉ፣ የጋራ ጉዳዮች ላይ የጋራ ፕሮጀክቶች እንዲያዘጋጁ እና ለዲሞክራሲያዊ ማሻሻያዎች ድምጽ እንዲያሰሙ መድረክ ይሰጣል። ከተልዕኮ መግለጫው ለማየት እንደሚቻለው ዴሞክራሲያዊነት፣ አካታችነት፣ እኩልነት፣ ተቋማዊ ነፃነት፣ ፍህታዊነት፣ ሰላማዊነት፣ እና ተጠያቂነት የሰፈነበት የፖለቲካ ባህል በኢትዮጲያ እንዲፈጠር ማስቻል ነው። ይህም ሊሳካ የሚችለው የፖለቲካ ምህዳሩን በማስፋት፣ የእርስ በእርስ መተማመን ባህልን በመገንባት እና በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የጋራ ባለቤትነት ስሜት የሚጨምር የትብብር ሁኔታን ማሳደግ ነው።

የጋራ ምክር ቤቱ ተልኮ እና አላማዎች እንዲሳኩ ትኩረት የተሰጠባቸው ቁልፍ መርሆች እና ተግባራት የሚከትሉትን ጉዳዮች ያካተተ መሆኑ ከመተዳደሪያ ደንቡ እና ከተግባራዊ እንቅስቃሴዎቹ ለመረዳት ይቻላል።

1. አካታችነትን እና መግባባትን ማጎልበት

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ለአካታችነት ያለው ቁርጠኝነት ውጤታማነቱ መሠረት ነው። ምክር ቤቱ በይፋ እውቅና የተሰጣቸው ፓርቲዎች በሙሉ (ሀገራዊ እና የክልል፣ ነባር እና አዳዲስ ፓርቲዎችን ጨምሮ) በምክር ቤቱ ውስጥ በእኩል ደረጃ እንዲሳተፉ በመፍቀድ ሰፋ ያሉ አመለካከቶች መደመጣቸውን ያረጋግጣል። በምክር ቤቱ ውስጥ እያንዳንዱ ፓርቲ እኩል አንድ ድምጽ የላው በመሆኑ “ለትናንሽ” እና “ለትልቅ” ወይም ለገዢው እና ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ድምጽ

በመስጠት ረገድ ልዩነት የማደረግ መሆኑ ሁሉም ፓርቲዎች ከወሳኝ ሀገራዊ ውይይቶች እንዳይገለሉ ይከላከላል። በዚህም የበለጠ ውክልና ያለው የፖለቲካ ምህዳር በምክር ቤት ውስጥ ይፈጥራል። ፓርቲዎች በዚህ መድረክ በኩል በጣም የተለያዩ አመለካከቶች ካሏቸው ሌሎች ፓርቲዎች ጋር ለመደራደር መገደዳቸውን በቀጥታ እንዲለማመዱ ያደርጋል። ይህ ደግሞ ለበሰለ ዲሞክራሲ ወሳኝ ክህሎት መገንብያ እድል የፈጠረ ነው።

2. ለግጭት/አለመግባባት ለመፍታት ወሳኝ ዘዴ መፍጠር

የፖለቲካ ውጥረትና ዋልተኝነት ባለበት የፖለቲካ ምህዳር (polarized political landscape) ውስጥ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል ሊነሱ የሚችሉ ግጭቶችን ለመከላከል እና ለመፍታት የሚያስችል ስልቶችን በመተግበር ሰላማዊ የፖለቲካ ግንኙነት እንዲኖር ውሳኝ መድረክ ሆኖ ያገለግላል። ለምሳሌ በመተዳደርያ ደንቡ ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው የሕግ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ዋና ተግባርና ኃላፊነቶች ዋንኛዎቹ በአባል ፓርቲዎች መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችንና ቅሬታዎችን በሕጋዊ መንገድ መፍታት ነው። ይህንንም ሲፈጽም ቋሚ ኮሚቴው በፓርቲዎች መካከል የሚነሱ ግጭቶችንና ቅሬታዎችን ይመረምራል፣ አስፈላጊ ሲሆን ክርክር ይሰማል፣ እንዲሁም ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የውሳኔ ሐሳብ ያቀርባል። በተጨማሪም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ወደ ምክር ቤቱ የሚመራቸውን የፓርቲዎች አለመግባባቶች እልባት እንዲያገኙ ይሰራል። ይህንንም ለማከናወን የሚያግዘውን የቅሬታ አቀራረብና የግጭት አፈታት ሂደትን የሚመራ ዝርዝር መመሪያ ያዘጋጃል። የጋራ ምክር ቤቱ ግልጽ የመገናኛ መንገዶችን በማጎልበት መድረኩ ሊከሰቱ የሚችሉ ግጭቶችን ቀድሞ ለመለየት ያስችላል። ይህም ፓርቲዎች አወዛጋቢ ጉዳዮችን ወደ ከፍተኛ ደረጃ ከማደጉ በፊት እንዲፈቱ ያስችላቸዋል።

ይህ ተግባር በተለይ እንደ ቅድመ-ምርጫና ድህረ-ምርጫ ባሉ አስቸጋሪ ወቅቶች ወሳኝ ነው። በእነዚህ ጊዜያት የፖለቲካ ፉክክር በቀላሉ ወደ ትላልቅ ግጭቶች ሊያድግ ይችላል። የጋራ ምክር ቤቱ ለውይይት አስተማማኝና የተዋቀረ የግጭት አፈታት ዘዴ በመፍጠር፣ ግጭቶች እንዳይባብሱ ስምምነት መፍጠር ባቃታቸው ፓርቲዎችን መካክል ጣልቃ በመግባት ችግሮቻቸውን በውይይት እንዲፈቱ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ እንዲሁም ፓርቲዎች አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ነገሮችን በጋራ እንዲለዩና እንደ የጋራ መግለጫ መስጠት ወይም ሽምግልና ባሉ የመከላከያ እርምጃዎች ላይ እንዲስማሙ ያስችላቸዋል። ለግጭት አፈታት ይህ ቅድመ-ተከላካይ (proactive) እንጂ ምላሽ-ተኮር (reactive) ያልሆነ አካሄድ ለፖለቲካ ፓርቲዎች ሰላማዊ ግንኙነት ብሎም ለኢትዮጵያ መረጋጋት በጣም አስፈላጊ ነው።

3. መደበኛ ያልሆነ ውይይት ሚና መጫውት

የፖለቲካ ተሳትፎ በተለምዶ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መደበኛ አውድ ውስጥ የሚካሄድ ቢሆንም የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት በመደበኛ ባልሆነና ተለዋዋጭ ሁኔታ ውስጥ በፓርቲዎች መካከል ውይይት (inter-party dialogue) በማመቻቸት ወሳኝ አማራጭ ይሰጣል። ይህ መድረክ የፓርቲ ተወካዮች በመደበኛ የሕግ አውጭነት ሂደቶች ውስጥ ወይም በከፍተኛ የሕዝብ ቁጥጥር ሥር ለመነጋገር አስቸጋሪ ሊሆኑ የሚችሉ ስሱ ጉዳዮችን እንዲወያዩ ያስችላቸዋል። በዚህ ግልጽ በሆነ አካባቢ፣ ፓርቲዎች የጋራ መግባባትን ማግኘት፣ የጋራ መረዳዳትን ማዳበር እና አዳዲስ ሀሳቦችን ያለ ጠላትነት መንፈስ መሞከር ይችላሉ። ይህ መደበኛ ያልሆነ ትብብር የፓርላማን ሥራ ከማሟላት ባለፈ፣ በፓርቲዎች መካከል የትብብርና የጋራ ተጠያቂነትን ባህል በማስፋፋት የፖለቲካ ሥርዓቱን የመቋቋም አቅም ያጠናክራል።

- የጋራ የምክር ቤቱን አደረጃጀት ተልዕኮ፣ አላማ፣ ተግባርና ኃላፊነት እዚህ የመምሪያ መፀሐፍ ላይ እና ከመተዳደርያ ደንቡ ሲመለክቱ ምን ተገነዘቡ?

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ካለው አወቃቀር፣ ይዞት ከተነሳው ተልዕኮ፣ ዓላማ፣ ተገባርና ኃላፊነት አንፅር ስንገምግመው ምክር ቤቱ የተመሠረተው ለመነጋገርያ መድረክ ለመሆን ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያ ለዲሞክራሲያዊ አስተዳደር መሠረታዊ ምሰሶ ነው። በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል መተማመንን፣ ትብብርን እና ቁልፍ የሆነ የግጭት መከላከያ መሣሪያ በመሆን በረጅም ጊዜ የተረጋጋ፣ አሳታፊና ትብብር የተሞላበት የፖለቲካ ባህል ለመገንባት አይነተኛ ሚና የሚጫውት ነው።

6.2. በጋራ ምክር ቤቱ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ ለፓርቲዎች የሚሰጠው ፋይዳ

- የእርስዎ ፖለቲካ ፓርቲ የኢትዮጲያ የፖለቲካ ፓርቲዎች ያጋራ ምክር ቤት አባል የሆነበትን ምክንያቶች አሁንም ያስታውሷቸዋል?
- ፓርቲዎ አባል በመሆኑ ምን ተጠቀመ? አባል በመሆን አጣነው የሚሏቸው ጉዳዮች አሉ?

በዚህ ክፍል የምንመለከተው የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤቱ አባል በመሆን ሊያገኛቸው የሚችሉ የጋራ እና የተናጠል ጥቅሞችን ነው። የምክር ቤቱ መተዳደርያ ደንብ በምዕራፍ አምስት አንቀጽ 56 የፖለቲካ ፓርትዎች የጋራ ምክር ቤቱ አባል ሲሆኑ ስለሚኖራቸው መብቶች ዘርዝሮ ያስቀምጣል።

ሳጥን 6.5: የአባል ፓርቲዎች መብት	
1. በምክር ቤቱ ውስጥ የመምረጥና የመመረጥ መብት አላቸው፤ 2. በጋራ ምክር ቤቱ ስብሰባዎች ላይ በመሳተፍ ሀሳብና አስተያየት የመስጠት መብት አላቸው፤ 3. የአቅም ግንባታና ሥልጠና ድጋፍ በፍትሐዊነት የማግኘት መብት አላቸው፤	1. አቤቱታዎችን፣ ቅሬታዎችንና ጥያቄዎችን ለጋራ ምክር ቤቱ በማቅረብ የመሰማትና ውሳኔ የማግኘት መብት አላቸው፤ 2. የጋራ ምክር ቤቱ የማህበራዊና መደበኛ ሚዲያዎች በእኩልነትና ፍትሐዊነት የመጠቀም መብት አላቸው፤ 3. በሀገር ውሰጥ እና ከሀገር ውጭ በሚደረጉ የልምድ ልውውጥ፣ የጉብኝት፣ የስልጠና፣ የትምህርት እና ተዛማጅ እድሎች በፍትሀዊነትና የመሳተፍ መብት አላቸው።

በጋራ ምክር ቤቱ ውስጥ የአባል ፓርቲዎች ተጨማሪ ውክልና እና መብቶችን ለማወቅ የመተዳደሪያ ደንቡን አንቀጽ 55 መመልከት ይቻላል። ይህ አንቀጽ የአባል ፓርቲዎችን ውክልና እና ተጨማሪ መብቶችን በተመለከተ የሚከተሉትን ይደነግጋል፦

ቋሚ ተወካይ	እያንዳንዱ አባል ፓርቲ በምክር ቤቱ ውስጥ በአንድ ቋሚ ተወካይ ይወከላል። ቋሚ ተወካዩ በማይገኝበት ጊዜ ደግሞ ፓርቲው ተለዋጭ ሰው በሕጋዊ ደብዳቤ ወክሎ መላክ ይችላል።
የእኩል ድምጽ መብት	እያንዳንዱ አባል ፓርቲ በምክር ቤቱ ውስጥ እኩል አንድ ድምጽ አለው።
አካታች ውክልናን ማበረታታት	የጋራ ምክር ቤቱ አካታችነትን ለማረጋገጥ ሲባል፣ ፓርቲዎች ሴት፣ ወጣት እና አካል ጉዳተኛ አባላትን እንዲወክሉ ያበረታታል።
የስብሰባ አደረጃጀት	በየደረጃው በሚደረጉ ስብሰባዎች የፓርቲው እና የተወካዩን ስም የሚገልጽ መለያ በጠረጴዛው ላይ ይቀመጣል። በክልል፣ ከተማ፣ ዞን፣ ክፍለ ከተማ እና ወረዳ ደረጃ ባሉ ምክር ቤቶች ደግሞ የፓርቲዎችን ቁጥር ታሳቢ ባደረገ መልኩ እኩል ውክልና እንዲኖር ይወሰናል።

1. በፓርቲዎች መካከል ለውይይት እና ለጋራ መግባባት የሚሆኑ ዕድሎች መፍጠር

እንደ ኢትዮጵያ የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት ውስጥ በርዕዮተ ዓለምና በታሪክ ላይ የተመሠረቱ ልዩነቶች በፓርቲዎች መካከል ትብብርን ሊያደናቅፉ ይችላሉ። የፖለቲካ ፓርቲዎች ካላቸው የቁጥር ብዛት የተነሳም የፖለቲካ ፓርቲዎች እርስ በርስ የማይተዋወቁበት እድል ሰፊ ነው። የጋራ ምክር ቤቱ መተዳደርያ ደንብ ውስጥ ተደጋግሞ እንደተገለፀው ምክር ቤቱ ጠንካራ የዴሞክራሲ እና የመድብለ ፓርቲ ስርዓት እንዲጠናከር ፓርቲዎች የጋራ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ያበረታታል። ለዜጎች ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች መከበርም በጋራ እንዲሰሩ ያግዛል። ለዚህም ተልዕኮ መሳካት የጋራ ምክር ቤቱ ወሳኝና የገለልተኛ ውይይት የሚያካሂድ መድረክ በመሆኑ የተለያዩ አመለካከቶች ያላቸው ፓርቲዎች አንድ ላይ እንዲመጡና የጋራ መግባባት እንዲያገኙ እድል በመፍጠር ላይ ይገኛል። ስለሆነም የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤቱ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ሲያደርጉ ገዢውን ፓርቲ ጨምሮ ሁሉንም በሕጋዊ መንገድ ተመዝግበው የሚንቀሳቀሱ የሀገሪቱን ፓርቲዎች በአንድ መድረክ የማግኘት እድላቸው ይሰፋል። የፖለቲካ ፓርቲዎች በዚህ የጋራ መድረክ (የጋራ ምክር ቤት) መሳተፍ መቻላቸው ለሚከተሉት ጉዳዮች ተስማሚ ነው፦

አንገብጋቢ **ጉዳዮችን መፍታት**	ፓርቲዎች እንደ የፌዴራሊዝም ሞዴሎች፣ የሥራ ቋንቋ፣ የሰንደቅ አላማ አጠቃቀም፣ የብሔራዊ ደህንነት፣የሕገ መንግሥት ማሻሻያ እና ሌሎችም አክራካሪ እና አንገብጋቢ ጉዳዮችን ግልጽና ጠላትነት በሌለበት ሁኔታ ተቀራቦ መወያየት፣ አንዱ የሌላውን ስጋት፣ ፍልጎት አማራጭ ሃሳብ መስማት ይችላሉ።
የጋራ መግባባትን መገንባት	የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች በተድጋጋሚ የጋራ ምክር ቤቱ በሚያመቻቸው መድረኮች ላይ የመገናኘትና እና የመላመድ እድል ይፈጥራል። በዚህም መደበኛ እና መደበኛ ያልሆኑ ውይይቶች ሲካሄዱ በፓርቲ ተወካዮች መካከል የጋራ መከባበርና መግባባት እንዲያዳብሩ ያግዛል። ይህም ጥልቅ የፖለቲካ ልዩነቶችን ለማጥበብ ይረዳል፣ በርቀት ከመራረጅ እና የጥላቻ ስሜት ለማርገብ ይጠቅማል።
አዳዲስ እና አማራጭ ሀሳቦችን መሞከር	የጋራ ምክር ቤቱ ለአዳዲስና አማራጭ የፖሊሲ ሀሳቦች ማፍለቂያ እና ውስብስብ ችግሮች በጋራ ለምፍታት ለትብብር መፍትሔዎች መፈጠሪያ መድረክ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል። ይህም ፓርቲዎች የየራሳቸውን የፓርቲ መርሆች ገደብ ሳይደረግባቸው አዳዲስ አቀራረቦችን እንዲሞክሩ ያስችላል።

2. በምርጫ ማሻሻያዎችና በዲሞክራሲያዊ ጉዳዮች ላይ ፓርቲዎች በጋራ እንዲሟገቱ እድል ያመቻቻል

የጋራ ምክር ቤቱ ምርጫ እና የምርጫ ነክ ጉዳዮች የፓርቲዎች የተናጠል እና የጋራ ጉዳይ መሆኑን እውቅና በመስጥት በጋራ ምክር ቤቱ አደረጃጀት ውስጥ ልዩ ትኩረት በመስጠት የምርጫ እና ምክክር ቋሚ ኮሚቴ አደራጅቷል። በተጨማሪም ምክር ቤቱ በተልዕኮው፣ ተገባር እና ሃላፊንቱ ላይ በዝርዝር እንዳስቀመጠው ከቅድመ-ምርጫ ዝግጅት እስከ ድህረ-ምርጫ ሂደት ድረስ የምርጫ እንቅስቃሴዎችን በመከታተል፣ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን በማመቻቸት እና የምርጫ ሥነ-ምግባር ደንቦችን በማስከበር ለፓርቲዎች አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል። በተጨማሪም፣ በምርጫ ወቅት የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን በመከታተል መፍትሄ እንዲያገኙ ይረዳል። ከዚህ ጉዳይ ጋር ተያይዞ የፖለቲካ ፓርቲዎች በምክር ቤቱ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ሲያደርጉ በሚከተሉት ጉዳዮች ተጠቃሚነታቸውን ያሰፋሉ፦

ለሕግ ማሻሻዎች የጋራ ጥረት ማድረግ	የጋራ ምክር ቤቱ ፓርቲዎች ለመሠረታዊ የምርጫ ማሻሻያዎች እንዲተጉ የተባበረ ግንባር እንዲፈጥሩ ያስችላቸዋል። ለምሳሌ፦ የተመጣጠነ የውድድር ምህዳር ማረጋገጥ፣ ፍትሐዊና ግልጽ ምርጫዎችን ማረጋገጥ፣ እንዲሁም የፖለቲካ ተዋናዮች መብቶችን መጠበቅን ያካትታል።
ዲሞክራሲያዊ ተቋማትን ማጠናከር	የጋራ ምክር ቤቱ ስጋቶችን በጋራ በማንሳትና መፍትሄዎችን በማቅረብ መንግሥትንና ሌሎች ተቋማትን ተጠያቂ ሊያደርግ ይችላል። በዚህም የዲሞክራሲያዊ ሥርዓቱን ራሱን ያጠናክራል።
የብዝኃነትን እና አካታችነትን ማጉላት	የጋራ ምክር ቤቱ የፖለቲካ ብዝኃነትን እና አካታችነትን በጋራ የሚጠብቅ ጠባቂ ሆኖ ያገለግላል። ለጤናማ ዲሞክራሲ ወሳኝ የሆነውን የሰላማዊ ውድድርና ውይይት መብትን ይከላከላል። በዚህም የፖለቲካ ፓርቲዎች በተናጠላዊ አቅማቸው ማሳካት የማችሉትን በጋራ ኃላቸውን አሰባስበው እውን ማድረግ ይችላሉ።

3. ለፓርቲ አባላት ሀብት መጋራት፣ እውቀት ሽግግር እና አቅም ግንባታ

በኢትዮጵያ ያሉ ብዙ የፖለቲካ ፓርቲዎች ውስን በሆነ የገንዘብ፣ የሰውና የቴክኒክ ሀብት ነው የሚንቀሳቀሱት። የጋራ ምክር ቤቱ ይህንን በመረዳት ለአቅም ግንባታ ድጋፎች የተለየ ትኩረት በመስጠት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ ካላት ጋር በመተባበር የፖለቲካ ፓርቲዎችን እያሳተፈ የሚገኘው። በመተዳደርያ ደንቡ የተለያዩ አንቀጾች ላይ ተዳጋግሞ እንደተተጠቀሰው የምክር ቤቱ አባል ፓርቲዎች በምክር ቤቱ ውስጥ የነቃ ተሳትፎ ሲያደርጉ ስልጠናዎችን ያገኛሉ። እንዲሁም በፓርቲ አመራሮች እና አባላት መካከል የልምድ ልውውጥና ትምህርታዊ ጉብኝቶች እንዲኖሩ ምቹ ሁኔታዎች ይፈጠርላቸዋል። በዚህም ምክር ቤቱ ፓርቲዎች ያላቸውን ውስን ሀብት ተግዳሮትን ለመቃቋም የሚያስችል እድል ፈጥሯል። የምክር ቤቱ አባል መሆን ሀብት መጋራትንና የጋራ አቅም ግንባታን የሚያስችል ዘዴ በመፍጠር ሁነኛ መፍትሔ ይሰጣል። በዚህም የፖለቲካ ፓርቲዎች በጋራ ምክር ቤቱ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ሲያደርጉ፦

ሀብት ማሰባሰብ	አባል ፓርቲዎች እንደ የምርምር መረጃዎች፣ የፖሊሲ ዕውቀትና የሥልጠና ቁሳቁሶችን በመጋራት (pooling resources) ውስን በጀታቸውን በአግባቡ መጠቀም ይችላሉ።
እውቀት መለዋወጥ	ይህ መድረክ የፓርቲ አባላት እርስ በእርስ እንዲማማሩ (knowledge exchange) ያመቻቻል። ፓርቲዎች እንደ ድርጅታዊ አስተዳደር፣ መሠረታዊ የሕዝብ ቅስቀሳ እና ውጤታማ የኮሚኒኬሽን ዘዴዎች ባሉ ዘርፎች የላቀ አሠራሮችን ሊለዋወጡና ከሌሎች ተሞክሮዎች ሊማሩ ይችላሉ። የፓርቲ ተውካዮች በሥራ አስፈፃሚ እና በቋሚ ኮሚቴዎች ውስጥ እና በክንፎች ውስጥ የነቃ ተሳትፎ ሲያደርጉ በርካታ ክህሎቶችን እና እውቀቶችን እርስ በርስ መለዋወጥ ይችላሉ።
ዒላማ ያደረገ ሥልጠና	የጋራ ምክር ቤቱ ከተመሠረተበት ጊዜ አንስቶ በበርካታ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች (targeted training) ለፓርቲ ተውካዮች እንዲሰጡ ከበልድርሻ አካልት ጋር በምተባበር ሁኔታዎችን ሲያመቻች ቆይቷል። ከበርካታ ዕርሶች መካከል በድርድር፣ ሀገራዊ ምክክር፣ በሕዝብ ግንኙነት፣ ግጭት አፈታት፣ የፖለቲካ አመራር፣ ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ አካታችነት እና በዘመናዊ የቅስቀሳ ስልቶች ላይ ያተኮሩ የሥልጠና አውደ ጥናቶችን በማዘጋጀት ለአባል ፓርቲዎች ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመወዳደርና በኃላፊነት ለማስተዳደር የሚያስፈልጉ ክህሎቶችን ሲያስታጥቅ ቆይቷል። አባል ፓርትዎች በምክር ቤቱ ውስጥ በሚቆዩበት ጊዜ ሁሉ መሰል ስልጠናዎች የምግኘት እድላቸው ይሰፋል።

4. የፖለቲካ ፓርቲዎችን የጋራ ድምፅ ማጎልበት

የጋራ ምክር ቤቱ በመተዳደርያ ደንቡ ውስጥ አጉልቶ እንዳሚጠቅሰው በሀገራዊ፣ ዓለም አቀፋዊ እና አከባቢያዊ ጉዳዮች ላይ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ አቋም በመያዝ ተባብሮ ለመስራት እና ለሕዝብ መግለጫ ለመስጠት የሚችሉበትን እድል ያመቻቻል። ይህም አንድ ፓርቲ በሆነ ወቅታዊ ጉዳይ ላይ የሚያሰማው ድምጽ ተደማጭነቱ የተወሰነ ሊሆን የሚችል ሲሆን በጋራ የሚያሰሙት ድምጽ የፓርቲዎችን የፖለቲካ ተፅዕኖ ያጎለብታል። በመሆኑም የጋራ ምክር ቤቱ በተለያዩ ፓርቲዎች መካከል ትብብርን በመፍጠር የሚጫወተው ሚና የአባላቱን ሕጋዊነት ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያ ያለውን የብዝሃ-ፓርቲ የፖለቲካ ሥርዓት ሕጋዊነት ያሳድጋል። የፖእልቲካ ፓርቲዎች ተሰባስበው ድምጻቸውን ለማሰማት ሲሞክሩ የሚከተሉትን ጥቅሞች የበለጠ ያሰፋሉ፦

የሕዝብን አመኔታ መገንባት	ዜጎች ተቀናቃኝ ራዕይ ያላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች ገንቢ በሆነ ውይይት ሲሳተፉ እና ለጋራ ግቦች ሲሰሩ ሲመለከቱ፣ በፖለቲካዊ ሂደቱ ላይ ያላቸው የሕዝብ አመኔታ፣ ቅቡልነት እእና እምነት ይሰፋል። ይህ ፖለቲካ ዜሮ ድምር ጨዋታ ነው የሚለውን አመለካከት ይቀንሳል እንዲሁም የዜጎችን ሰፊ ተሳትፎ ያበረታታል።
የተባበረ ድምጽ ማሰማት	በዋና ዋና ጉዳዮች ላይ የጋራ ስምምነት ላይ በመድረስ፣ የጋራ ምክር ቤቱ ለሕዝብም ሆነ ለመንግሥት ተቋማት የተባበረ እና የጎላ ድምፅ ያሰማል። ይህ የጋራ ጥንካሬ የፖለቲካ ተቃዋሚዎች ስጋቶችና ሃሳቦች በቁም ነገር እንዲታዩ እና በብሔራዊ ፖሊሲ ላይ ተጽዕኖ የማድረግ ዕድላቸው ከፍ እንዲል ያረጋግጣል።
ዲሞክራሲያዊ ደንቦችን ማጠናከር	የጋራ ምክር ቤቱ አባላት በተቀናጀ ጥረታቸው፣ በሥልጣኔ የተሞላ ጤነኛ ውድድርና ስምምነትን በማሳየት ጥሩ ምሳሌ ይሆናሉ። ይህ ደግሞ ዲሞክራሲያዊ ደንቦችን የሚያጠናክር ሲሆን፣ ለኢትዮጵያ የተረጋጋና ብዝሃነት ያለው የፖለቲካ የወደፊት ዕጣ ፈንታ የጋራ ቁርጠኝነትን ያሳያል።

የፖለቲካ ፓርቲዎች በጋራ ምክር ቤቱ አባል በመሆን የሚያገኟቸው መብቶችና ጥቅሞች እንዳሉ ሁሉ፣ ግዴታዎችና ኃላፊነቶችም እንዳሉባቸው መዘንጋት የለበትም። የመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 57 የአባል ፓርቲዎችን ግዴታዎች በዝርዝር ያስቀምጣል። በተጨማሪም፣ አንቀጽ 58 የአባል ፓርቲዎች ከምክር ቤቱ ሊሰናበቱ የሚችሉባቸውን ሁኔታዎች ዘርዝሯል።

ሳጥን 6.6፡ የአባል ፓርቲዎች ያሉባቸው ግዴታዎች እና ሊያሰናብቱ የሚችሉ ምክንያቶችና ሁኔታዎች

የአባል ፓርቲዎች ግዴታ እና የአባልነት ክፍያ	ከአባልነት ሊያሰናብቱ የሚችሉ ምክንያቶችና ሁኔታዎች
1. የቃል ኪዳን ሰነዱን፣ ይህንን የመተዳደሪያ ደንብና ምክር ቤቱ የሚያወጣቸውን ደንቦችና መመሪያዎች በሙሉ የማክበር፤ 2. የምክር ቤቱን አባላት እርስ በርስ ግንኙነት የሚያውኩ፣ የጋራ ምክር ቤቱን አንድነት እና ጥንካሬ ከሚሸረሽሩ ማናቸውም ዓይነት አፍራሽ ድርጊቶች የመቆጠብ፤ 3. የጋራ ምክር ቤቱ አባል የፖለቲካ ፓርቲዎችን የአባልነት መዋጮ የመክፈል፤ 4. አባልነት ክፍያ በወቅቱ ያልከፈለ አባል የፖለቲካ ፓርቲ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ እንዲከፍል በደብዳቤ ይጠየቃል። ያለ በቂ ምክንያት በተሰጠው አንድ ወር ጊዜ ውስጥ ያልከፈለ ፓርቲ ክፍያውን እስኪፈጽም ድረስ ከአባልነት ይታገዳል። እገዳ የተጣለበት ፓርቲ ክፍያ እስኪፈጽም ጊዜ ድረስ የአባልነት መብቱን ያጣል።	1. ያለ በቂ ምክንያት የአባልነት መዋጮን በተከታታይ ስድስት ወራት ጊዜ አለመክፈል፤ 2. የቃል ኪዳን ሰነዱን፣ ይህን የመተዳደሪያ ደንብ እና የጋራ ምክር ቤቱን ደንቦችና መመሪያዎች አለማክበር፤ 3. ፓርቲው ህጋዊ ሰውነቱን ሲያጣ፤ 4. በራስ ፈቃድ የጋራ ምክር ቤቱን አባልነት ሲለቅ ይሆናል።

6.3. አዳዲስ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤቱ አባል የሚሆኑበት መንገድ

የጋራ ምክር ቤቱ ለመሥራች ፓርቲዎች ብቻ ክፍት የሆነ ተቋም አይደለም። በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ተመዝግበው ሕጋዊ ሰውነት ያገኙ አዳዲስ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ እንዲሁም ቅንጅቶች ወይም ግንባሮች የጋራ ምክር ቤቱ አባል መሆን ይችላሉ።

ሆኖም፣ አባል ለመሆን አመልካች ፓርቲዎች፣ የፓርቲዎች ቅንጅት ወይም ግንባሮች ማሟላት ያለባቸው አንዳንድ ሂደቶች አሉ። የጋራ ምክር ቤቱ መተዳደሪያ ደንብ ምዕራፍ አምስት አንቀጽ 55 ላይ የጋራ ምክር ቤቱ አባል የሚኮንበትን ሥርዓት በዝርዝር አስቀምጧል።

የአባልነት ማመልከቻ	ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባል ለመሆን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የሰጠውን ሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ ቅጂ ማቅረብ አለበት። በተጨማሪም የጋራ ምክር ቤቱን የቃል ኪዳን ሰነድና መተዳደሪያ ደንብ መቀበሉን የሚያረጋግጥ የጽሑፍ ማስረጃ ከማመልከቻው ጋር ማያያዝ ይጠበቅበታል።
የውሳኔ አሰጣጥ	የአባልነት ጥያቄው በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ከተቀበለ በኋላ ለጠቅላላ ጉባኤ ይቀርባል። ጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ ሲሰጥ፣ ፓርቲው ከተወሰነበት ቀን ጀምሮ ሙሉ አባል ይሆናል።

6.4. በጋራ ምክር ቤቱ ውስጥ በምን መልኩ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ

የጋራ ምክር ቤቱ ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች መብታቸው ተጠብቆላቸው በነፃነት መሳተፍና አስተዋጽኦ ማድረግ የሚችሉበት የጋራ መድረክ ነው። ፓርቲዎች በምክር ቤቱ የጠቅላላ ጉባኤ አባል ከመሆን በተጨማሪ፣ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በአመራር መዋቅሩ ውስጥ በቀጥታ የመሳተፍ ዕድል አላቸው። ይህም የሆነበት ምክንያት፣ የጋራ ምክር ቤቱ መዋቅር ለሁሉም አባላት ሰፊ ተሳትፎን በሚያመቻች መልኩ የተቀረጸ በመሆኑ ነው። ለምሳሌ በሀገራዊው የጋራ ምክር ቤት ውስጥ ያለውን የሚከተለውን አወቃቀር እና እያንዳንዱ መዋቅር ሊያሳትፍ የሚችለውን የፓርቲዎች ብዛት መልከት ይቻላል።

የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ	ሰባት የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚወከሉበት መዋቅር ነው።
ቋሚ ኮሚቴዎች	ስድስት ቋሚ ኮሚቴዎች ያሉት ሲሆን፣ እያንዳንዱ ኮሚቴ ሦስት አባላት (ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢና ጸሐፊ) አሉት። በዚህም በአጠቃላይ 18 የፖለቲካ ፓርቲዎች ይወከላሉ።
የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ	ይህ ኮሚቴ ሦስት አባላት ያሉት ሲሆን፣ ሦስት የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚወከሉበት ነው።
ክንፎች	የጋራ ምክር ቤቱ ሦስት ክንፎች (የሴቶች፣ የወጣቶች እና የአካል ጉዳተኞች) አሉት። እያንዳንዱ ክንፍ ሰባት አባላት ያሉት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እና ሦስት አባላት ያሉት የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ ያደራጃል። በዚህም በእያንዳንዱ ክንፍ ውስጥ 10 ያህል ፓርቲዎች ይወከላሉ።

በጋራ ምክር ቤቱ ውስጥ በአመራርነት ሊሳተፉ የሚችሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቁጥር ከፍተኛ ነው። ክንፎችን ሳይጨምር፣ እስከ **28 የሚደርሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች በአገር አቀፍ ምክር ቤቱ አመራር ውስጥ** የመሳተፍ ዕድል አላቸው። ከዚህ በተጨማሪ፣ ፓርቲዎች በሦስቱ ክንፎች (የወጣቶች፣ የሴቶችና የአካል ጉዳተኞች) በኩል ተጨማሪ ተወካዮች ሊወክሉ ይችላሉ።

በተጨማሪም፣ የጋራ ምክር ቤቱ በሁሉም ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች (የትግራይ ክልልን ሳይጨምር) ቅርንጫፎችን አዋቅሯል። እነዚህ የክልልና ከተማ ምክር ቤቶች ከአገር አቀፍ ምክር ቤቱ ጋር በተመሳሳይ መልኩ የተደራጁ ናቸው (ቋሚ ኮሚቴዎች እንደአስፈላጊነቱ የሚዋቀሩ ሆነው) ። እያንዳንዱ የክልል ምክር ቤት አምስት የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚወከሉበት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴዎች አሉት። በሁሉም ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች የወጣቶች፣ የሴቶችና የአካል ጉዳተኞች ክንፎችም ተቋቁመዋል። ይህም ለበርካታ የፖለቲካ ፓርቲዎች በአመራርነት የመሳተፍ ዕድል ይሰጣል።

ጋራ ምክር ቤቱ መተዳደሪያ ደንብ ለሁሉም አባል ፓርቲዎች እኩል ዕድል ለመስጠት በማሰብ ተደራራቢ ኃላፊነትን ይገድባል። ይህ ደንብ አንድ ፓርቲ ወይም የአንድ ፓርቲ ተወካይ ከአንድ የኃላፊነት ቦታ በላይ እንዳይይዝ የሚከለክል ሲሆን ሁሉም ፓርቲዎች በፍትሃዊነት እንዲወከሉ ለማድረግ እንደ ዋነኛ መሣሪያ ያገለግላል። ይህ ገደብ በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 62 ላይ እንደሚከተለው ተቀምጧል፦

ዋና መርህ	ይህ ገደብ የተጣለው የሥራ መደራረብን ለመቀነስ፣ ለሁሉም ፓርቲዎችና አመራሮች ፍትሃዊ ተሳትፎ ለመስጠት፣ ልምድ እንዲቀስሙ ለማድረግና በምክር ቤቱ ውስጥ የፖለቲካ ሚዛንን ለማስጠበቅ ነው።
ተደራራቢ ኃላፊነትን መከልከል፦	• በዋናው የጋራ ምክር ቤት ውስጥ የሥራ አስፈጻሚ፣ ቋሚ ኮሚቴ ወይም ክንፍ አመራር የሆነ ሰው በክልል ወይም በከተማ አስተዳደር ምክር ቤት ውስጥ ተመሳሳይ ኃላፊነት መያዝ አይችልም። • በማንኛውም የጋራ ምክር ቤት አደረጃጀት ውስጥ አንድ አባል ከአንድ የሥራ ክፍል በላይ አመራር መሆን አይችልም። • አንድ ፓርቲ በየደረጃው ከሚገኙ የጋራ ምክር ቤቶች ከአንድ የአመራር አካል በላይ መሳተፍ አይችልም። • በክልል/ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት ውስጥ አመራር የሆነ ሰው በዞን/ክፍለ ከተማ ወይም ወረዳ ደረጃ የአመራር አባል መሆን አይችልም።
ሚዛናዊነት	ፓርቲዎች በፈጠሩት ቅንጅት ወይም ግንባር ምክንያት ከአንድ ፓርቲ ከአንድ ሰው በላይ የአመራር አባል ሆኖ መመረጥ አይችልም።
ገዢ ፓርቲን በተመለከተ	ገዥው ፓርቲ በየደረጃው ባሉ የጋራ ምክር ቤት የሥራ አስፈጻሚና አስተባባሪ ኮሚቴዎች ሰብሳቢ መሆን አይችልም።
መረጃ አያያዝ	ተደራራቢ ኃላፊነትን ለመቆጣጠር የጋራ ምክር ቤቱና የክልል/ከተማ አስተዳደር ምክር ቤቶች የአመራር አባላትን ዝርዝር የያዘ የመረጃ ቋት ያዘጋጃሉ።

የፖለቲካ ፓርቲዎች የተመቻቸላቸውን መልካም አጋጣሚ በአግባቡ ለመጠቀምና የፓርቲያቸውን ጥቅም ለማስከበር፣ እንዲሁም የጋራ ምክር ቤቱን የጋራ ዓላማዎች ለማሳካት፣ ቁርጠኝነት፣ ብቃትና መልካም ሥነ ምግባር ያላቸውን አባላት መወከል ይኖርባቸዋል።

በእርስዎ እይታ ፓርቲውን ወክሎ በጋራ ምክር ቤቱ ውስጥ የሚሳተፍና ወደ አመራርነት ሊመጣ የሚችል ሰው ምን ዓይነት ብቃቶች ሊኖሩት ይገባል ብለው ያስባሉ?

6.4.1. በጋራ ምክር ቤቱ የሚወከሉ አባልነት ብቃት

የጋራ ምክር ቤቱ ለውይይት፣ መግባባት ለመፍጠር እና ዲሞክራሲያዊ እሴቶችን ለማስፋፋት እንደ ወሳኝ የመድብለ ፓርቲ መድረክ ሆኖ እያገለገለ ነው። ለአንድ የፖለቲካ ፓርቲ፣ ተወካዮቹ በጋራ ምክር ቤቱ ውስጥ በንቃት እና ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲሳተፉ ማድረግ ስልታዊ አስፈላጊነት (strategic necessity) አለው። ይህን መስለ ምክር ቤት ኢትዮጲያን በመሰሉ ታዳጊ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት የሚጥሩ ሀጋራት የላቸውም። በመሆኑም የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ድምጽ የሚያሰሙበት መድረክ መሆኑን አመነው "በቁመንገር ሊወስዱት ይገባል ("it has to be taken seriously") ። በምክር ቤቱ ውስጥ የሚሳተፉ የፓርቲ አባላት በራሳቸው ፓርቲ ውስጥ ከሚኖራቸው ባሻገር ለሀገራዊ የፖለቲካ ሕይወት አስተዋፅዖ ለማድረግ እና የአመራር ብቃቱን ለማሳየት ጥሩ አጋጣሚ ነው። ቀጥለን የምንመለከተው በጋራ ምክር ቤቱ ውስጥ ፓርቲያቸውን ወክለ የሚሳተፉ አባላት የጋራ ምክር ቤቱ መዋቅር እንዲረዱ፣ እንዲሳተፉ እና በመጨረሻም እንዲመሩበት የሚያስችሉ ስልቶችን ያብራራል።

1. የጋራ ምክር ቤቱን አወቃቀርን፣ ኮሚቴዎችና የሥራ ቡድኖችን መረዳት

ውጤታማ ተወካይ ለመሆን አንድ ሰው በመጀመሪያ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት አወቃቀርን መረዳት አለበት። ምክር ቤቱ የተዋቀረው ለተቀናጀ ተግባር ሲሆን፣ በተለምዶ በጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባዎችና በተለያዩ ልዩ የሥራ ቡድኖች ወይም ኮሚቴዎች አማካኝነት ይንቀሳቀሳል። የምክር ቤቱ ዝርዝር ሥራ የሚከናወነው በእነዚህ ኮሚቴዎች ውስጥ ሲሆን፣ የፓርቲ ተወካዮችም ቀጥተኛ ተፅዕኖ ማሳደር የሚችሉት እዚሁ ነው።

ቁልፍ ኮሚቴዎች	የጋራ ምክር ቤቱ በጊዜ ሂደት የሚለውጥ ሊሆን የሚችል ቢሆንም በአጠቃላይ በሀገራዊ ወሳኝ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ የሥራ ቡድኖች ወይም ኮሚቴዎች አሉት። የሥራ አስፈጻሚና ስድስት ቋሚ ኮሚቴዎች አሉት። እነዚህ ኮሚቴዎች በምርጫ፣ በምክክር፣ በሕግ፣ የፓርቲዎችን አቅም በመገንባት፣ በግጭት አፈታት፣ በአደረጃጀት፣ አስተዳድርና ፋይናንስ፣ በፖሊሲ ጥናት እና ምርምር ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ናቸው።
የኮሚቴዎቹ ሚና	የጋራ ምክር ቤቱ ኮሚቴዎች ለውይይት፣ ለድርድር እና የጋራ ውሳኔዎችን ለማዘጋጀት ዋና መድረኮች ናቸው። ፓርቲዎች እንደ በምርጫዎች ውስጥ የእኩልነት ሁኔታን ማረጋገጥ ወይም በሀገራዊ ውይይት ተነሳሽነት ላይ የጋራ አቋም መፍጠርን የመሳሰሉ ውስብስብ ጉዳዮችን በጥልቀት እንዲመረምሩ ያስችላቸዋል።

2. ለአመራርነት የሚያበቁ ንቁ የተሳትፎ ዕድሎችን መለየት

እንደ የጋራ ምክር ቤት ባለ የብዙ ባህርያት ፓርቲዎች የሚሳተፉበት እና አንድ ፓርቲ አንድ ድምጽ በሚሰጠበት መድረክ ውስጥ አመራር ለመሆን የሚያበቃው ብዙ ጊዜ የትብብር፣ የጋራ አቋም እና በብቃትና እውቀት ላይ የተመሠረተ ስብእና እንጂ ወክለው የመጠበት ፓርቲ መጠን (ትልቅ ወይም ትንሽ አሊያም ሀገራዊ ወይም ክልላዊ ፓርቲ) ላይ የሚደገፍ አይደለም። የፓርቲ ተወካይ በምክር ቤቱ የጋራ ግቦች ላይ ወጥ የሆነ ብቃትና ቁርጠኝነት በማሳየት ወደ አመራርነት ቦታ ሊወጣ ይችላል። አንድ የፓርቲ ተወካይ በጋራ ምክር ቤቱ ውስጥ ብቃቱን እና ቁርጠኛ (committed) መሆኑን ለማሳየት መገዶች መካከል የሚከተሉት ሊታዩ ይቻላሉ፦

በቋሚ ኮሚቴዎች/ በሥራ ቡድኖች ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ	በግራ ምክር ቤቱ ውስጥ በንቃት ለመሳተድ በጣም ቀጥተኛው መንገድ ከፓርቲዎ መርህ ጋር በሚስማማ ኮሚቴዎች/የሥራ ቡድን ውስጥ በንቃት መሳተፍ ነው። ለምሳሌ፣ የፓርቲዎ ዋና ትኩረት ግጭት ማስቀረት እና የሰላም ግንባታ ላይ ከሆነ፣ ተወካይዎ በምርጫ እና ውይይት ጉዳዮች ላይ በሚሠራ ቋሚ ኮሚቴ ውስጥ የአመራር ሚና መፈለግ አለበት። በዚህ ቋሚ ኮሚቴ ውስጥ የሚያሳየው ተነሳሽነት፣ ብቃት እና ውጤት በምክር ቤቱ ውስጥ እውቅና እንዲኖረው ያደርጋል፣ ከፍ ላለ ኃላፊነቶች እንዲታጭ ያደርገዋል።
የአመራር ሚናዎችን መውሰድ	እንደ ቋሚ ኮሚቴ ሊቀመንበር ወይም ምክትል ሊቀመንበር፣ ጸሐፊ ወይም ለአንድ የተወሰነ ጉዳይ ቃል አቀባይነት ያሉ የአመራር ቦታዎች በጋራ ምክር ቤቱ ሥራ ሂደት ወሳኝ ናቸው። በነዚህ የሥራ ኃላፊነቶች ላይ ለመመረጥ ፍቃደኛ መሆን እና ጥረት መድረግ ከፓርቲ ተውካዮች ይጠበቃል። አንድ የፓርቲ ተወካይ ግልጽ፣ ታማኝና ውጤታማ አስተባባሪ በመሆን የሚታወቅ ከሆነ ለእነዚህ ሚናዎች ሊመረጥ ወይም ሊሾም ይችላል።
የተለያዩ የአመራር ቡድኖችን መገንባት	የጋራ ምክር ቤቱ የተለያዩ እውቀት እና ክህሎት ያላቸውን አባላት በተለየዩ ኮሚቴዎች ውስጥ የጠቀማል። አንድ የፓርቲ ተወካይ ለግል አመራር ብቃት ግንባታ ከመትጋት ባለፈ፣ ባለው እውቀትና ክህሎት ሌሎች የፓርቲ ተወካዮች ያሉበትን ኮሚቴዎች እና ቡድኖች አቅም ለማሳደግ በጎ ፍቃደኛ መሆን አለበት። ለምሳሌ የሕግ ትምህርት እና ልምድ ያለው አባል የሕግ ቋሚ ኮሚቴ አባላትን ብቃት የበለጠ ለማሳደግ በፍቃደኝነት ማማከር እና ሞያዊ ድጋፍ ሊሰጥ ይችላል። ይህ ደግሞ መላውን ምክር ቤት የሚጠቅም የጋራ አመራር ባህልን ያዳብራል።

6.4.2. በጋራ ምክር ቤት መዋቅሮች ውስጥ ለውጤታማ አስተዋፅዖ እና ውክልና የሚረዱ መንገዶች

የፖለቲካ ፓርቲዎች በጋራ ምክር ቤቱ ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ ዓላማ ያለው መሆን ይጠበቅበታል። ዓላማ የሌለው ተሳትፎ ለፓርቲው የሀብት ብክነት ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ፓርቲው በጋራ ምክር ቤቱ ውስጥ የተካተተበትን ዓላማ ለማሳካት እና ውጤታማ ተሳትፎ ለማድረግ የፓርቲ ተወካዮች ተገቢ ክህሎቶችና ብቃቶች ሊኖራቸው ይገባል። እንዲሁም መሠረታዊ መርሆችን ማክበር ይጠበቅባቸዋል።

የአንድ ፓርቲ ተወካይ ለወከለው ፓርቲ ታማኝ ከመሆኑ በተጨማሪ፣ በምክር ቤቱ ውስጥ ከሌሎች ፓርቲዎች ተወካዮች ጋር መቻቻልን፣ መግባባትን እና መደራደርን መሰረት ያደረገ አብሮ የመስራት ክህሎት ሊኖረው ይገባል። የፖለቲካ ፓርቲን ወክለው በጋራ ምክር ቤቱ የሚሳተፉ አባላት በሚከተሉት ክህሎትና እውቀቶች ላይ የተሻለ አቅም ማጎልበት ይጠበቅባቸዋል[2]፦

1. ስለዎከሉት የፖለቲካ ፓርቲ ጥልቅ ግንዛቤ ይኑሮዎት

በጋራ ምክር ቤቱ ውስጥ ፓርቲዎን ወክለው ከመሳተፍዎና ውይይቶችን ከመጀመርዎ በፊት፣ እንደ ፓርቲ ተወካይ የፓርቲዎን **ዓላማ፣ ግብ፣ መርህ፣ እሴትና መሠረታዊ ሐሳቦች** ጠለቅ ያለ ግንዛቤ ሊኖርዎ ይገባል። ይህ በወሳኝ ጉዳዮች ላይ የፓርቲውን አቋም በግልጽ ለመግለጽና የውስጥ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደቱን ለመረዳት ያስችሎታል። ይህ ዝግጅት ከሌለ፣ በየትኞቹ ጉዳዮች ላይ ፓርቲዎን ወክለው መወሰን እንዳለብዎ የመረጃ ክፍተት ሊገጥምዎት ይችላል። በዚህም የተነሳ፣ መወሰን በማይገባዎ ጉዳይ ላይ ውሳኔ እንዲያስተላልፉ ወይም መወሰን ባለብዎት ጉዳይ ላይ አቋም እንዳይዙ ሊያደርግ ይችላል። እንዲህ ያለው ሁኔታ የፓርቲዎን ጥቅም ከመጉዳት ባለፈ፣ የምክር ቤቱን የውይይት ሂደት ሊያስተጓጉል ይችላል።

2. የኮሚኒኬሽንና የድርድር ክህሎቶችን ማዳበር

በጋራ ምክር ቤቱ ውስጥ የምካሄዱ በርካታ ውይይቶች፣ የሃሳብ ልውውጦች፣ ክርክሮች እና ድርድሮች ይኖራሉ። በነዚህ ህደቶች ላይ ፓርቲዎችን ወክለው ሲገኙ የተሻለ የኮሚኒኬሽን እና የድርድር ክህሎት እንዲኖሮዎት ይጠበቃል እና እነሱን ለማሳደግ ጥረት መድረግ ይኖርበታል።

ግልጽ አገላለጽን መጠቀም	አንድ ተወካይ የፓርቲውን አቋም በጽሑፍም ሆነ በንግግር በአማርኛ ወይም በሌሎች የምክር ቤቱ የሥራ ቋንቋዎች በግልጽና በአጭሩ ማቅረብ መቻል አለበት።
ንቁ አዳማጭ መሆን	ምንም እንኳን መሠረታዊ የሆነ ርዮተ ዓለማዊ እና የአመለካከት አለመግባባት ካለባቸው ፓርቲዎች ጋር ቢሆንም፣ በክር ቤቱ ውስጥ የፖርቲ ተወካዮች የሚወያዩት የሌሎች ፓርቲዎችን አመለካከቶች ማዳመጥና በእውነት መረዳት መቻል (genuinely under-stand)፣ ለውጤታማ ውይይትና የጋራ መግባባት ላይ ለመድረስ ወሳኝ ነው።
የጋራ መገባባት መፍጠር	በዙውን ጊዜ በጋራ ምክር ቤቱ ውስጥ የሚደረጉ ውይይቶች እና ድርድሮች በጋራ ጉዳዮች እና ሀገራዊ አጀንዳዎች ላይ ነው። ይህን መስለ ንግግሮች፣ ውይይቶች ወይም ድርድሮች ስምምነት መፈለጉ ናቸው። አንድ ብቃት ያለው የፓርቲ ተወካይ የጋራ ግቦችን ለመለየትና በእነሱ ዙሪያ መግባባት ለመፍጠር ይጥራል።

3. ለዲሞክራሲያዊ መርሆዎች ተገዢ መሆን

በጋራ ምክር ቤቱ ውስጥ እና በፖለቲካዊ ሂደት ውስጥ የዲሞክራሲ መርሆችን ማክበር የግራ ምክር ቤቱን አሰራር እና ዓላማዎች ውጤታማና ህጋዊ ሆኖ እንዲሰሩ ወሳኝ ነው። በመሆኑም በጋራ ምክር ቤት ውስጥ ፓርቲያቸውን ወክለው የሚሳተፉ አባላት ለዲሞክራሲያዊ መርሆዎች እና አሰራሮች ተገዢ መሆን ይጠበቅባቸዋል።

አክብሮትና ሙያዊነት	በጋራ ምክር ቤቱ ውስጥ የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች የፖለቲካ ትስስራቸው ወይም የፓርቲያቸው መጠን ምንም ይሁን ምን ሁሉንም ተሳታፊዎች በአክብሮትና በሙያዊ ብቃት ማስተናገድ አለባቸው።
ደንቦችን ማክበር	የጋራ ምክር ቤቱ በቃል ኪዳን ሰነድ፣ የመተዳደርያ ደንብ፣ መምሪያዎችና በሥነ-ሥርዓት ደንቦች የሚሠራ ነው። አንድ ተወካይ ፍትሃዊነትንና ግልጽነትን ለማረጋገጥ እነዚህን መመሪያዎች በጥብቅ መከተል አለበት።
ተጠያቂነት	የፖለቲካ ፓርቲ ተወክዮች በፓርቲያቸውና በጋራ ምክር ቤቱ እና በወከሉት ፓርቲ መካከል አገናኝ ድልድይ ናቸው። በመሆኑም የምክር ቤቱን እንቅስቃሴዎችና ውሳኔዎች በማሳወቅ ለፓርቲያቸው አመራርና አባላት ተጠያቂ መሆን አለባቸው።

4. ጠንካራ የውክልና ክህሎቶች ማዳበር

በጋራ ምክር ቤት ውስጥ የፓርቲ ተወካዮች ፓርቲያቸውን በብቃት ለመወከል እና በዲሞክራሲያዊ ስርዓት ውስጥ ለመስራት የተለያዩ ክህሎቶች ያስፈልጓቸዋል። እነዚህ ክህሎቶች በአመራር፣ በኮሙኒኬሽን፣ በአደረጃጀትና በስትራቴጂክ እቅድ የማውጣት ብቃት ሊጠቃለሉ ይችላሉ። የፓርቲ ተወካዮች በጋራ ምክር ቤቱ ውስጥ በሚኖራቸው ተሳትፎ የውክልና ኃላፊነቶች ለመወጣት የሚከተሉት ጉዳይች ላይ ክህሎት ማዳበር ይጠይቃል፦

የድምጽ ሰጪዎችን ፍላጎት ማስከበር	በጋራ ምክር ቤት ውስጥ የሚሳተፉ ተወካዮች የፓርቲያቸው ደጋፊዎች ፍላጎቶችና ስጋቶች ሊያውቁና እነርሱን በብቃት ለመወከል መትጋት አለባቸው።
መተማመንን መገንባት	በብዙ ፓርቲዎች መድረክ ውስጥ መተማመን በጣም ውድ ነገር ነው። አንድ የፓርቲ ተወካይ ወጥ፣ ግልጽ እና የጋራ ጥቅምን ቅድሚያ በመስጠት ከሌሎች ፓርቲዎች ጋር መተማመንን ለመገንባት መሥራት አለበት።

5. የቅንጅት/የጋራ አመራር ክህሎቶችን ማዳበር

የጋራ ምክር ቤቱ በተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች በጋራ የሚመራ ነው። ይህም የተቀናጀ አመራር (collective leadership) ይጠይቃል። በቅንጅት ውስጥ ያሉ ውጤታማ መሪዎች ክፍት አስተሳሰብ ያላቸው (open-minded)፣ በሥራ ላይ ያተኮሩ እና ለቡድኑ ግቦች ደጋፊ መሆን አለባቸው። በሥራ ላይ የሚያጋጥሙ ግጭቶችን እና አለምግባቶችን የጋራ መግባባት ለመፍጠር እንደ ዕድል የሚመለከቱ እና ጠንካራ የግጭት አፈታት ችሎታዎች ሊኖራቸው ይገባል። በተጨማሪም፣ ትኩረትን ከሌሎች ጋር መጋራትና እያንዳንዱ አባል አስተዋፅዖው ለምክር ቤቱ ስኬት አስፈላጊ እንደሆነ እንዲሰማው ማድረግ መቻል አለባቸው።

የጋራ ምክር ቤቱ መተዳደሪያ ደንብ በአንቀጽ 51 ላይ፣ በምክር ቤቱ የኃላፊነት ቦታዎች ለእጩነት የሚያበቁ መስፈርቶችን በዝርዝር አስቀምጧል። እነዚህ መስፈርቶች ማንኛውም ለኃላፊነት ቦታ ለመመረጥ እጩ ሆኖ የሚቀርብ ሰው ሊያሟላቸው የሚገቡ የብቃት ማረጋገጫዎች መሆናቸውን የገለጸ ሲሆን፣ እጩዎች ለጉባኤው ሲቀርቡ እነዚህን መስፈርቶች ማሟላት እንዳለባቸው መተዳደሪያ ደንቡ ያዛል።

ሳጥን 6.7፡ በጋራ ምክር ቤቱ የኃላፊነት ቦታዎች ለእጩነት የሚያበቁ መስፈርቶች

1. የአመራር ብቃትና ልምድ ያለው፤
2. የጋራ ምክር ቤቱን ጥቅም ማስከበር የሚችል፤
3. የጋራ ምክር ቤቱን ለማገልገል ፍላጎት ያለው፣ ለሥራው ተደራሽና ፊቃደኛ የሆነ፤
4. የጋራ ምክር ቤቱን ከባለድርሻ አካላት ጋር አስተባብሮ መሥራት የሚችል፤
5. የጋራ ምክር ቤቱን የቃል ኪዳን ሰነድ፣ መተዳደሪያ ደንብ እና አሠራሮችን አክብሮ የሚያስከብር፤
6. የጋራ ምክር ቤቱን ሰነዶችና ሚስጢሮች ማስጠበቅ የሚችል፤
7. ኃላፊነትና ተጠያቂነትን ለመውሰድ ዝግጁ የሆነ፤
8. መልካም ስነምግባር ያለው ይሆናል።

6.5. የጋራ ምክር ቤቱ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት

በኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት የመተዳደሪያ ደንብ መሠረት፣ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቱ ሁለት ዋና ዋና ደረጃዎችን ይከተላል። የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት የሚከተሉትን መርሆች ይከተላል። ይህ አይነት የውሳኔ አሰጣጥ አሠራር በሁሉም የጋራ ምክር ቤቱ መዋቅሮች ውስጥ የሚተገበር ነው።

በስምምነት መወሰን	የጋራ ምክር ቤቱ ዋና መርህ ማንኛውም ውሳኔ በሁሉም አባል ፓርቲዎች ስምምነት መተላለፍ አለበት የሚል ነው። ይህ አካሄድ በፓርቲዎች መካከል መግባባትንና መተማመንን ለመፍጠር ያለመ ነው።
በ3/4ኛ ድምጽ መወሰን	በሆነ ምክንያት በስምምነት ውሳኔ ላይ መድረስ ካልተቻለ፣ እንደ አማራጭ በጠቅላላ ጉባኤው እና በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ላይ ውሳኔው **በ3/4ኛ የድምጽ** ብልጫ ሊተላለፍ ይችላል።

ይህ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት የመተዳደሪያ ደንቡን ለማሻሻልም ጭምር የሚያገለግል ሲሆን፣ ማሻሻያው በስምምነት ካልተደረሰበት በ3/4ኛ ድምጽ ሊወሰን እንደሚችል ደንቡ ያስቀምጣል። ይህ የሚያሳየው ምክር ቤቱ አብዛኛው የፓርቲዎችን ድምጽ በመያዝ ወሳኝ ጉዳዮችን የማስፈጸም ስልጣን እንዳለው ነው።

6.5.1. በጋራ መግባባት እና ማመቻመች ስላላቸው ልዩነቶ

በጋራ ምክር ቤት ውስጥ የጋራ መግባባት (Consensus building) እና ማመቻመች (compromise) የተባሉ እሳቤዎችን ተግባራዊ ማድረጊያ ስልቶችን ከመመልካታችን አስቀድመን የሁለቱን ጽንሰ ሐሳቦች አንድነት እና ልይነት በአጭሩ እንምለከታለን።

የጋራ መግባባት (Consensus building) እና ማመቻመች (compromise) የጋራ ግብ እና ሁለቱም ተመሳሳይ ባህሪያት ስላሏቸው በቀላሉ ሊምታቱ ይችላሉ። ስለዚህም ሁለቱን መለየት አስፈላጊ ነው። እንደ በጋራ መግባባት ሁሉ ማመቻመችም በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል ለአለመግባባት ወይም ለግጭት ሲከሰት ሊሰጥ የሚችል ምላሽ ነው። ሁለቱም አለመግባባትን ለመፍታት ከሚረዱ የመፍትሄ መንገዶች መካከል ሊካተቱ ይችላሉ። በዚህም እንደ አለመግባባት ወይም ግጭት ባሉ ነባራዊ ሁኔታዎች ውስጥ ከመቆየት ለመውጣት እና ወደ ስምምነት ለመድረስ ይረዳሉ። ምንም እንኳን ማመቻመች እና በጋራ መግባባት በፓርቲዎ መካከል ለሚነሱ ለአለመግባባቶች መፍትሄዎች ቢሆኑም፣ የአፈታት መንገዳቸው አንድ አይነት አይደለም።

ከጋራ መግባባት በተለየ መልኩ ማመቻመች (compromise) አለመግባባት ውስጥ ያሉ ወገኖች በአከራካሪው ጉዳይ ላይ ያላቸውን አቋም እንዲቀይሩ አይጠይቅም። በመሰረታዊ መልኩ ማመቻመች ማለት የሚጋጩ አመለካከቶችን ወይም ፍላጎቶችን ለማስተናገድ ያለመ የውል አይነት ነው። በማመቻመች ውስጥ ተከራካሪ ወገኖች የየራሳቸውን ተቃራኒ አመለካከቶች ይዘው የሚቀጥሉበት ሁኔታ አለ። ተስማሚ ወገኖች "አቋም ከቀየሩ እንደ ስምምነት አይቆጠርም" ("it does not count as a compromise when you change your mind.") የሚባለው ለዚህ ነው። በማመቻመች ውስጥ ተከራካሪ ወገኖች የሌላኛውን ወገን ፍላጎት ከፊል በመቀበል ይስማማሉ እንጂ ከሌላኛው ወገን ፍላጎት ጋር ሙሉ በሙሉ አይስማሙም። በዚህም ምክንያት፣ በፖለቲካዊ ንድፈ ሃሳብ ውስጥ ማመቻመች በፖለቲካ እና በማህበረሰብ ውስጥ ያሉ አለመግባባቶችን ለመፍታት ትክክለኛ እና ተቀባይነት ያለው ዘዴ እንደሆነ ይነገርለታል።

በጋራ መግባባት (Consensus building) ሁሉም የቡድኑ አባላት ሊደግፉት የሚችሉበትን ስምምነት ላይ ለመድረስ በጋራ የመሥራት ስልታዊ ሂደት ነው። ይህ አቀራረብ የተለያዩ አመለካከቶችን፣ ፍላጎቶችን እና ስጋቶችን በማቀናጀት ለሁሉም ተሳታፊዎች ተቀባይነት ያለው ውሳኔ ላይ ለመድረስ የሚያስችል የጋራ ውሳኔ አሰጣጥ ዘዴ ነው። የመግባባት ሂደት የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ፍላጎትና እሴት ለመረዳትና ለመመለስ ቅድሚያ የሚሰጥ ሲሆን፣ በብዙኃን ድምፅ ላይ ተመሥርቶ ውሳኔ ላይ ከመድረስ ይልቅ፣ በአንድነት ወይም በአንድነት አቅራቢያ ያለ ስምምነት ላይ ለማድረስ ያለመ ነው። በጋራ መግባባት ላይ ሲደረስ አለመግባባት ውስጥ የነበሩ ወገኖች የተደረሰበትን ስምምነት ከመጀመሪያ አቋማቸው የተሻለ (ወይም ቢያንስ እኩል) እንደሆነ አድርገው ይወስዳሉ።

6.5.1.1. በጋራ ምክር ቤት ውስጥ በጋራ መግባባት እና ማመቻመች ተግብራዊ ማድረግ

በጋራ መግባባት (consensus building) በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ባለ የተለያየ እና ውስብስብ ሕዝብ ፍላጎትች ባለባት ሀገር ውስጥ ለጤናማ የፖለቲካ ሥርዓት መሠረት ነው። የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት በተፎካካሪ ፓርቲዎች መካከል ለሚደረግ ውይይትና ትብብር እንደ መድረክ በመሆኑ በጋራ መግባባት ልምምድ ለማበረታታት ተስማሚ ነው።

ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ ያለው የፖለቲካ ሁኔታ ለመግባባት ልዩ ፈተናዎችን ያቀርባል። ከብዙ ምዕራባዊ ዲሞክራሲዎች በተለየ እዚህ ያለው የፖለቲካ ምህዳር ብዙውን ጊዜ በታሪካዊ ቅሬታዎች፣ በጥልቅ ሥር በሰደዱ በብሔር ማንነት ላይ በተመሠረቱ ርዕዮተ ዓለማዊ ልዩነቶች እንዲሁም ውጤቱ ስለ ፖሊሲ ብቻ ሳይሆን ስለ አገሪቱ አንድነትና ማንነት ጭምር በሚሆንበት ከፍተኛ ፉክክር የሚታወቅ ነው። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ማመቻመች (compromise) የፖለቲካ መሳሪያ ብቻ ሳይሆን፣ የሀገር ፍላጎት ነው (it's a national necessity)[3]። ስለዚህ ማመቻመች ላይ አተኩረን እንቀጥል።

6.5.1.2. ከተለያዩ የፖለቲካ ፍላጎቶች ጋር ውጤታማ ድርድር እና ስምምነት ለማድረግ የሚያስችሉ ስልቶች

ስልት 1፡ የጋራ ብሔራዊ ጥቅሞችን መለየት

በእርስዎ እመነት በጋራ ምክር ቤቱ ውስጥ ሁሉም ፓርቲዎች የጋራ የሆኑ አጀንዳዎች ምን ምን ናቸው? ፓርቲዎች ስለተወሰኑ ፖሊሲዎች ከመወያየታቸው በፊት፣ በመጀመሪያ ሁሉም የሚጋሯቸውን መሠረታዊ ጥቅሞች መለየት አለባቸው። በኢትዮጵያ ሁኔታ የጋራ አጀንዳዎች ሊሆኑ ከሚችሉ ጉዳዮች መካከል ሀገራዊ ሰላም፣ ሉዓላዊነት፣ ኢኮኖሚያዊ ልማት እና ፖለቲካዊ መረጋጋትን ሊያካትቱ ይችላሉ። ሁሉም ፓርቲዎች የተለያዩ አቀራረቦች ቢኖራቸውም ወደ እነዚህ የጋራ ግቦች እየሰሩ መሆናቸውን መቀበል ለድርድር ወሳኝ መነሻ እና የመተማመን መሠረት ሊሆን ይችላል።

ስልት 2፡ የተለያዩ አመለካከቶችን መረዳት

ውጤታማ ስምምነት የተቃራኒ አመለካከቶችን በጥልቀት መረዳት ይጠይቃል። ይህ ማለት የአንድ ፓርቲን የፖሊሲ አቋም ከላይ ከመመልከት አልፎ ከበስተጀርባ ያሉትን ታሪካዊ፣ ባህላዊ እና ርዕዮተ ዓለማዊ ምክንያቶችን መመርመር ማለት ነው። ለምሳሌ፣ የአንድ ፓርቲ በፌደራሊዝም ላይ ያለው አቋም ከታሪካዊ የመገለል ትረካዎች የመነጨ ሊሆን ሲችል። የሌላኛው ፓርቲ በማዕከላዊ መንግስት ላይ ያለው አቋም ደግሞ ለብሔራዊ አንድነት ካለው ስጋት የመነጨ ሊሆን ይችላል። የጋራ ምክር ቤቱ ፓርቲዎች እነዚህን መሠረታዊ አመለካከቶች በአስተማማኝና ጠብ-አልባ በሆነ ሁኔታ (non-confrontational setting) እንዲካፈሉ የሚያስችሉ የሥራ ላይ ውይይቶችን እና የተዋቀሩ ውይይቶችን ማመቻቸት ይችላል።

ስልት 3፡ ሥርዓታዊ ፍትሃዊነትንና ግልጽነትን ማስፈን

በማንኛውም ጊዜ በጋራ ምክር ቤት ውስጥ ውይይት እና ድርድር ሲካሄድ ሂደቱ ለሁሉም ተሳታፊዎች ፍትሃዊና ግልጽ እንደሆነ መታየት አለበት። ይህ ከሌለ ፓርቲዎች (የተለየ የአደረጃጀት ባህሪ የያዙ ፓርቲዎች) እንደተገለሉ ይሰማቸዋል። ይህም አይነት ሁነኢታ መተማመንን ሊያፈርስ ይችላል። የጋራ ምክርር ቤቱ ውይይቶች እንዴት እንደሚካሄዱ፣ ሀሳቦች እንዴት እንደሚቀርቡ እና ስምምነቶች እንዴት እንደሚደረስባቸው ግልጽ ደንቦችን መረዳት ከሁሉም ፓርቲዎች ይጠበቃል። ተጨማሪ ሥርዓቶች ካስፈልጉም የጋራ ምክር ቤቱ ማውጣት አለበት። ይህም ሁሉም ፓርቲዎች የመደመጥ እኩል ዕድል ማግኘታቸውን እና ውሳኔዎች በዝግ በር ውስጥ አለመወሰናቸውን ማረጋገጥን ያካትታል።

ስልት 4፡ ከርዕዮት ዓለም ይልቅ ተግባራዊ (Pragmatic) ማመቻመችን ማስቀደም

ፖለቲካዊ ልዩነት እና ዋልተኝነት ባለበት አካባቢ በጥልቅ ከተያዙ ርዕዮተ ዓለማዊ መርሆዎች ይልቅ በተግባራዊና በሥነ-ምግባር ነክ ባልሆኑ ጉዳዮች (non-moral issues) ላይ የጋራ መግባባት መፈለግ የበለጠ የሚቻል ነይሆናል። እንደ ክልላዊ ራስ ገዝ አስተዳደር ወይም የመንግስት አወቃቀር ያሉ ጉዳዮች መሠረታዊ ቢሆኑም

የፖለቲካ ፓርቲዎች በጋራ ምክር ቤት ውስጥ አቋም ለመያዝ ያዳግታቸው ይሆናል። ከዚያ ይልቅ ወቅታዊ እና ፓርቲዎች ተጨባጭና አስቸኳይ ችግሮች ናቸው በሚሏቸው ጉዳዮች ላይ ከመነጋገር ቢጀምሩ ጉዳዮችን ለማመቻመች እና ለመስማማት ወደ ሚያስችላቸው ደረጃ ማደግ ስለሚችሉ በሂደት በጋራ ምክር ቤቱ ውስጥ ልዩነቶችን በውይይት ለመፍታትና በመስማማት ችግሮችን የመፍታት የተሳካ ታሪክ መገንባት ይችላሉ። ለምሳሌ፣ የፖለቲካ የሥራ አጥነትን ለመፍታት፣ የሕዝብ አገልግሎቶችን ለማሻሻል ወይም ለተፈጥሮ አደጋ ምላሽ ለመስጠት የጋራ ስትራቴጂ ላይ ሊስማሙ ይችላሉ። በእነዚህ ዘርፎች የሚገኝ ስኬት በኋላ ላይ የበለጠ አከራካሪ ጉዳዮችን ለመፍታት የሚያስፈልገውን መተማመን ሊገነባ ይችላል።

6.5.2. በጋራ ምክር ቤት ውስጥ ገንቢ የውይይት ባህልን ማዳበር

ማመቻመች (compromise) የአንድ ጊዜ ክስተት ብቻ አይደለም። ይልቁንም ዘላቂ የሆነ የውይይት እና የጋራ መከባበር ባህል ውጤት ነው። ለኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ይህ ባህል የፖለቲካ ፉክክርን ከአንድ ወገን አሸናፊነት ወደ ትብብር ሂደት ለመቀየር ቁልፍ ነገር ነው። በመሆኑም በጋራ ምክር ቤቱ ውስጥ ገንቢ የውሕት ባህልን ለማዳበር የሚከተሉትን ጉዳዮች ላይ ማተኮር ያስፈልጋል፦

1. ከጋራ መግባባት (Consensus) አልፎ ወደ መርህ-ተኮር ማመቻመች (Principled Compromise) መሸጋገር

ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ሙሉ በሙሉ የሚስማሙበት የጋራ መግባባት (consensus) ክቡር እና የሚፈለግ ግብ ቢሆንም በተለያዩ የፖለቲካ ሁኔታዎች ውስጥ ግን ብዙውን ጊዜ ከእውነታ የራቀ ነው። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች የበለጠ ተግባራዊ እና መርህ-ተኮር አቀራረብ መርህ-ተኮር ማመቻመች (principled approach is principled compromise) ነው። ከታክቲካል ስምምነት በተለየ ይህ ፓርቲዎች አሁንም የልይነት አመለካከታቸውን እንደያዙ መፍትሄ ላይ እንዲስማሙ ያደርጋል። ለምሳሌ፣ አንድ ፓርቲ በአንድ የተወሰነ ፖሊሲ ጉዳይ ላይ ሙሉ በሙሉ ባያምንም፣ የተቃዋሚውን ፓርቲ አቋም ሕጋዊነት ስለሚያከብር እና የፖለቲካ አለመግባባትን ማስወገድ ትልቅ ጥቅም እንዳለው ስለሚያውቅ፣ የፖሊሲ ሃሳቡን ሙሉ በሙሉ ባይገዛውም ስምምነት ላይ ለመድረስ ሲባል አቋሙን ሳይለውጥ በማመቻመች የቀረበውን ፖሊሲ ለመደገፍ ይችላል። ይህ የጋራ ምክር በኢቱ አባል ፓርቲዎች ሊረዱት እና ሊቀበሉት የሚገባ ወሳኝ ልዩነት ነው።

2. የጋራ ምክር ቤቱን እንደ “ሞራላዊ የውይይት” መድረክ መጠቀም

የጋራ ምክር ቤቱን መድረክ የመሸናነፍያ “የድርድር መድረክ” (“horse-trading) ብቻ ሳይሆን የሞራላዊ ውይይት (moral deliberation) ቦታ መሆን አለበት። ይህም ማለት ፓርቲዎች ፍላጎቶቻቸውን ብቻ ከመለዋወጥ ይልቅ ለአቋሞቻቸው ምክንያቶችን መለዋወጥ አለባቸው። ይህ ደግሞ ፓርቲዎች ዋና እሴቶቻቸውንና ስጋቶቻቸውን እንደ ድክመት ይወሰድብኛል ብለው ሳይፈሩ በግልጽ የሚያወሩበት አካባቢ ይጠይቃል።

3. አለመግባባትን መቀበል እና ማክበር

ገንቢ የውይይት ባህል ማለት እያንዳንዱ ጉዳይ ላይ “ሁለቱም አሸናፊ የሚሆኑበት” መፍትሄ (“win-win” solution) ሊኖረው አይችልም የሚለውን መቀበል ነው። በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ አለመግባባት እንዲኖር መፍቀድ እና ወደ ግጭት እንዳያመራ መከላከል ነው። የጋራ ምክር ቤቱ የፖለቲካ ተቃዋሚዎች የጥልቅ ልዩነቶቻቸውን አምነው መቀበል የሚችሉበት መድረክ ነው። ሆኖም ግን ለሀገር እና ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ለትብብር የጋራ መግባባት የሚያገኙበት መድረክ ሆኖ ሊያገለግል ይገባል።

ምዕራፍ ሰባት

ሀገራዊውን እና በክልል/ ወይም ከተማ አስተዳደር የጋራ ምክርቤቶችን ማስተባበር

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት አደረጃጀት የፌደራል አወቃቀርን ተከትሎ የተዋቀረ ነው። በሀገር አቀፍ ደረጃ የተደራጀ ዋናው የጋራ ምክር ቤት ሥር የክልል እና/ወይም የከተማ አስተዳደር የጋራ ምከር ቤቶች እንዲዋቀሩ ተደርገዋል። በክልል እና/ወይም በከተማ አስተዳደር የጋራ ምከር ቤቶች ሥር የዞን እና /ወይም የክፍለ ከተማ የጋራ ምክር ቤቶች ይኖራሉ። በዞን እና /ወይም በክፍለ ከተማ የጋራ ምክር ቤቶች ሥር የወረዳ የጋራ ምክር ቤቶች እንደሚዋቀሩ የጋራ ምክር ቤቱ መተዳድርያ ደንብ ይደነግጋል።

በኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት እና በክልል እና/ወይም የከተማ አስተዳደር የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤቶች መካከል የሚኖር ውጤታማ ግንኙነት ባለብዙ ደረጃ አስተዳደርን (multi-level governance) የጋራ መደጋገፍን እና አጠቃላይ አፈጻጸምን ለማጠናከር ወሳኝ ነው። ለዚህ ግንኙነት ግልጽ የሆኑ መመሪያዎችን ማዘጋጀት በእነዚህ የተለያዩ ደረጃዎች መካከል ውጤታማ ቅንጅትና ትብብር ለመፍጠር የሚያስችል ማዕቀፍ ለመዘርጋት ይረዳል። እነዚህ መመሪያዎች ባለብዙ ደረጃ አስተዳደርን ለማጠናከር እና በኢትዮጵያ ውስጥ የመድብለ ፓርቲ ዲሞክራሲን ለማራመድ ወሳኝ ናቸው።

7.1. የጋራ ምክር ቤቶችን ለማስተባበር የመመርያ አስፈላጊነትን

የሀገራዊውን እና በክልል/ ወይም ከተማ አስተዳደር የጋራ ምክር ቤቶች የሚኖራቸውን ሚና፣ የሚከተሏቸውን የአሰራር ዘዴዎች፣ በመካከላቸው የሚኖረውን ግንኙነት ለመዘርዘር እና ምርጥ ተመኩሮዎች ለመለዋወጥ የሚያስችሉ ግልጽ መመሪያዎች ያስፈልጋሉ። በምክር ቤቶቹ ውስጥ የሚካሄዱ እንቅሳሴዎስ የሚያስተባብር መመርያ መኖር የተደጋገሙ ጥረቶችን ለመቀነስ የሚያስችል ሲሆን በምክር ቤቶቹ ውስጥ ቀልጣፋ የትብብር፣ የተጠያቂነት እና የእውቀት መለዋወጥ ሂደቶችን ተቋማዊ ያደርጋል።

ትብብርን ተቋማዊ በማድረግ ምክር ቤቶቹ በሚገባ በተዘረዘሩ ሚናዎች እና ደረጃውን የጠበቀ የቅንጅት፣ የእቅድ ዝግጅት፣ የትግበራና የግምገማ ሂደቶች አማካኝነት ያላቸውን የጥቅም ብልጫ መጠቀም ይችላሉ። መመሪያዎቹ በመደበኛ ውይይትና ውክልና አማካኝነት የጋራ መግባባትንና ለክልሎች እና እና/ወይም የከተማ አስተዳደር ምክር ቤቶች የራስን የማስተዳደር (autonomy) አክብሮትን ያጎለብታሉ። ከሁሉም በላይ ደግሞ፣ ይህ ደረጃውን የጠበቀ አቀራረብ በአካባቢው የሕዝብ ፍላጎትና በብሔራዊ ደረጃ ቅድሚያ በሚሰጣቸው ጉዳዮች ላይ በመመሥረት የአቅም ግንባታን፣ የሀብት አጠቃቀምን እና የተሳትፎ ጥረቶችን በማሻሻል፣ በጋራ የሚተገበሩ ፕሮግራሞችን ውጤታማነት፣ ተፅዕኖ፣ ቀጣይነትና ዘላቂነት ያሳድጋል።

የጋራ ምክርቤቶቹን ለማስተባበር መመሪያ ዓላማ የሚከትሉትን ጉዳዮችን ያካትታል፦

ተጠያቂነትን ማሳደግ	በጋራ ምክርቤቶቹ የተቀናጁ ፕሮግራሞችና የሀብት አጠቃቀም ላይ በመደበኛ ሪፖርት ማቅረብ።
አንድነትን ማጎልበት	በጋራ ምክርቤቶቹ መካከል ግልጽ ውይይት በማድረግ እና ጥረቶችን በማስተባበር በምክር ቤቶቹ መካከል አብሮ የመሥራት ስምምነትን እና ልምድን ማጎልበት።
ድጋፍ መስጠት	የክልል/ ወይም የከተማ አስተዳደር የጋራ ምክርቤቶችን በሚለዩ ፍላጎቶች ላይ በመመሥረት የተለየ ድጋፍና የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎችን መስጠት።
የጋራ እቅድ ማዘጋጀት	በተለያየ የአስትዳደር እረከኖቹ የሚፈጸሙ ተነሳሽነቶችን በጋራ ማቀድ፣ መከታተልና መገምገም።
መቀናጀት	በጋራ ምክርቤቶቹ መካከል ግልጽ ሚናዎችን በመዘርዘርና ተግባራትን በማስተካከል ቅድምያ ለሚሰጣቸው ጉይዳዮች በትብብርና በመናበብ መሥራት።

7.1.1. የጋራ ምክር ቤቶች መካከል ውጤታማ ትብብር እንዴት መፍጠር ይቻላል?

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት እና በክልል እና/ ወይም ከተማ አስተዳደር ምክር ቤቶች መካከል የሚኖረው ትብብር ስኬታማ ለማድረግ፣ ሁለቱን አካላት እንደ አንድ የተሳሰረ የመድበለ-ፓርቲ ሥርዓት ግንባታ ሂደት አስተባባሪ ተቋም አርጎ መመልከት ወሳኝ ነው። ይህ የተቀናጀ አሠራር የጋራ የዲሞክራሲያዊ ግቦችን ለማሳካት ቀጣይነት ያለው ሂደት ነው።

በምክር ቤቱ መተዳድርያ ደንብ ላይ እንድተመለከተው የፌደራሉ የጋራ ምክር ቤት እንደ ዋና አካል አጠቃላይ አመራርና ስትራቴጂያዊ አቅጣጫዎችን ሲሰጥ በሌላ በኩል የክልል እና/ ወይም የከተማ አስተዳደር ምክር ቤቶች ደግሞ ከአካባቢው ፍላጎት ጋር የተጣጣሙ ፕሮግራሞችን በብቃት እንዲተገበሩ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው። በመሆኑም የሁለቱ አካላት ውጤታማ ትብብር እጅግ አስፈላጊ ነው።

ውጤታማ ቅንጅት ከሌለ፣ የሀገራዊው እና የክልል እና/ ወይም ከተማ አስተዳደር ምክር ቤቶች አሠራር እርስ በእርሱ ሊጣረስ፣ ያላቸውን አንጻራዊ አቅም በአግባቡ መጠቀም ሊሳናቸው፣ እንዲሁም የጋራ አሠራራቸው ሊዳከም ይችላል። ስለሆነም የዋናው የጋራ ምክር ቤት እና በክልል እና/ ወይም በከተማ አስተዳደር ምክር ቤቶች መካከል የሚፈጠረው ትብብር በሚከተሉት መርሆዎች ሊመራር ይገበዋል፦

በዕቅድ ዝግጅት ወቅት ወጥ አሠራር መከተል	በዋናው የጋራ ምክር ቤት እና በክልል እና/ ወይም ከተማ አስተዳደር የጋራ ምክር ቤቶች መካከል የሚፈጠሩ ትብብሮች በዕቅድ ዝግጅት ወቅት መጀመር አለባቸው። ይህም የሥራ ዕቅዶች በሁሉም የጋራ ምክር ቤቱ ተሳትፎ እና መናበብ የተዘጋጁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ይረዳል።
ቀጣይነት ያለው ትብብር	በጋራ ምክርቤቶቹ መካከል የሚኖረው ትብብር በቀጣይነት እንዲኖረው ዋናው የጋራ ምክር ቤት ለክልል እና/ ወይም ለከተማ አስተዳደር የጋራ ምክር ቤቶች የዕቅድ አፈጻጸም ሁኔታዎችን ከስልታዊ ማዕቀፎች አንጻር በመከታተል በመደበኛ ግብረመልስ (feedback) ለክልል እና/ ወይም ለከተማ አስተዳደር የጋራ ምክር ቤቶች መስጠት ይኖርበታል።
ቀጥተኛ ግንኙነት	በዋናው የጋራ ምክር ቤት እና በክልል እና/ ወይም በከተማ አስተዳደር የጋራ ምክር ቤቶች የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴዎች መካከል መደበኛ የመወያያ እና ልምድ ልውውጥ ማድረጊያ መድርኮችን መፍጠር ያስፈልጋል። በየአመራሩ መካከል የሚፈጠሩ ግልጽ የመገናኛ መስመሮች እና ቀጥተኛ መድረኮች ግንኙነቶችን ለመገንባትና ችግሮችን ለመፍታት ያግዛል።
በምክር ቤቶች መካከል መስተጋብርን ማጠናከር	አሳታፊነትን ማዕከል ያደረገ የጋራ ምክር ቤቶች ትብብር በመክር ቤቶች መካከል የሚኖረውም መስታግበር (interdependence) እውቅና ከምስጠት በላይ በዋና ምክር ቤት የሚወሰኑ ማንኛውም ውሳኔዎች በክልል እና/ ወይም ከተማ አስተዳደር የጋራ ምክር ቤቶች ላይ የሚያሳድሩትን ተጽዕኖ ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው።
የጋራ ስምምነት ያላቸውን ግቦች ማስቀመጥ	በዋናው እና በክልል እና/ ወይም ከተማ አስተዳደር የጋራ ምክር ቤቶች መካከል በየዓመቱ ሊያሳኳቸው የሚያልሟቸውን የግራ ስምምነት ያላቸውን ግቦች (mutually agreed goals) በግልጽ ማስቀመጥ። እንደዚህ አይነት ግቦች የመድብለ ፓርቲ ዲሞክራሲዊ ሥርዓትን ለመገንባት እና በጋራ ምክር ቤቱ ውስጥ የካታችነትን ባህል ለመገንባት የሚደረጉ ጥረቶችን ከፍ ሊያደርጉ ይቻሉ።
የመረጃ ፍሰት	በጋራ ምክር ቤቶቹ መካከል ጠንካራ ትብብር መፍጠርም ይሁን ማስቀጠል የሚቻለው በዋናው ምክር ቤቶ እና በክልል እና/ ወይም ከተማ አስተዳደር መካከል ቀጠትኛ እና የጎንዮሽ የመረጃ ልውውጥ ሲፈጠር ነው። ስለዚህ በመረጃ ልውውጥ መስመሮች በቂ መረጃ እንዲፈስ ማድረግ ያስፈልጋል። በጋራ በሚካሄድ ሁኔታዊ ትንተና ላይ ተመስርቶ ሥራዎችን በማቀናጀት እና አስፈላጊ የሆኑ ግብረመልሶችን በመስጠት በጋራ ምክር ቤቶቹ መካከል የሚኖረውን ትብብር ዘላቂ ያደርገዋል።

7.2. በጋራ ምክርቤቶች መካከል ውጤታማ ኮሚኒኬሽን እና የትብብር መፍጠርያ ዘዴዎች

በጋራ ምክር ቤቶቹ መካከል ጠንካራ የግንኙነት (ኮሚኒኬሽን) እና የትብብር ሥርዓት መፍጠር፣ በሁሉም ደረጃ ያሉ መዋቅሮችን እና የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን ለማቀናጀት መሠረታዊ ነው።

በዋናው የጋራ ምክር ቤት እና በክልል እና/ ወይም ከተማ አስተዳደር ምክር ቤቶች መካከል መደበኛ የግንኙነት መስመር ሲኖር ፈጣን፣ ቀጥተኛ እና ወቅታዊ መረጃዎችን ለመለዋወጥ፣ የጋራ ውሳኔዎችን ለማሳለፍ፣ ሀብት ለመጋራት እና ሞያዊ ድጋፍ ለመለዋወጥ እጅግ አስፈላጊ ነው። በተጨማሪም፣ በክልል እና/ ወይም ከተማ አስተዳደር ምክር ቤቶች መካከል የጎንዮሽ መረጃ መለዋወጥ፣ ልምድ መካፈል እና ስጋቶችን መወያየትና ማስተካከል እንዲቻል የጋራ ምክር ቤቶቹን የሚያገናኝ መደበኛ የግንኙነት መስመር መፈጠር አለበት።

በዋናው የጋራ ምክር ቤት እና በክልል እና/ ወይም ከተማ አስተዳደር ምክር ቤቶች ሥር የተዋቀሩ የሴቶች፣ የወጣቶች እና የአካል ጉዳተኛ ክንፎች መካከል የተሻለ ትብብርና መናበብ እንዲኖር ውጤታማ የግንኙነት ሥርዓት መፍጠር ተገቢ ይሆናል። ይህ አሠራር የጋራ ምክር ቤቶችን ለማስተባበርና የተቀናጀ እንቅስቃሴ ለማካሄድ እጅግ ጠቃሚ መሣሪያ ነው። ለዚህም ዋናው የጋራ ምክር ቤት በሚያወጣው የግንኙነት መመሪያ መሠረት፣ ሁሉም የጋራ ምክር ቤቶች ከአካባቢያዊ ጉዳዮች ጋር ያላቸውን ትስስር ለማጠናከር እና ግንኙነቱ እንዳይቋረጥ ስልታዊ የመገናኛ ደንቦችን መጠቀም አለባቸው ። በጋራ ምክር ቤቶቹ መካከል ውጤታማ ግንኙነት እና ትብብር ለመፍጠር የሚከተሉትን ስልቶች ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፦

1. መደበኛ ስብሰባዎች፣ የጋራ አውደ ጥናት እና የመረጃ መለዋወጫ መድረኮች (Platforms)

በዋናው የጋራ ምክር ቤት እና በክልል/ከተማ አስተዳደር የጋራ ምክር ቤቶች፣ እንዲሁም በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴዎቻቸው፣ ክንፎቻቸው እና ሌሎች የሥራ ቡድኖች መካከል ጠንካራ የሥራ ግንኙነት መፍጠር ወሳኝ ነው። ይህም የጋራ ግቦችን ለማሳካት ዕቅድ ለማውጣት፣ የሥራ ሂደቶችን ለመከታተል፣ ግብረመልስ ለመለዋወጥ፣ አቅምን ለማስተባበር፣ ክትትልና ግምገማ ለማድረግ እና እርስ በርስ ለመማማር የሚያስችሉ መድረኮችን ይፈጥራል። ይህንን ለማሳካት የሚከተሉትን ዘዴዎች ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል፦

የመረጃ መለዋውጫ መድርኮች ማስተዋወቅ	በዋናው የጋራ ምክር ቤት ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እና በክልል እና/ ወይም ከተማ አስተዳደር የጋራ ምክር ቤቶች የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴዎች መካከል እንዲሁም በዋናው ምክር ቤት እና በክልል እና/ ወይም ከተማ አስተዳደር የጋራ ምክር ቤቶች ስር የተዋቀሩ ክንፎች አመራሮች መካከል መደበኛ መረጃ መውልዋወጫ የማኅበራዊ ሚድያ ገፆችን (Information-Sharing Platforms) (ቴሊ ግራም፣ ዋትስ አፕ፣ ፌስ ቡክ ጉሩፕ) በመክፈት በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋል።
የግማሽ ዓመትና ዓመታዊ የግምገማ ስብሰባዎች	በዋናው የጋራ ምክር ቤት ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እና በክልል እና/ ወይም ከተማ አስተዳደር የጋራ ምክር ቤቶች የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴዎች መካከል እንዲሁም በዋናው ምክር ቤት እና በክልል እና/ ወይም ከተማ አስተዳደር የጋራ ምክር ቤቶች ስር የተዋቀሩ ክንፎች አመራሮች መካከል የዕቅድ ዝግጅት፣ የአፈጻጸም ክትትል እና ግምገማ ማድረጊያ የሚያግዙ በየስድስት ወሩ መገናኘት እና የጋራ ስብሰባዎችን ማካሄድ። እነዚህ ስብሰባዎች መሻሻልን ለመተንተን፣ ስልታዊ ቁጥጥር ለማድረግ እና ከአዳዲስ ፈተናዎች ጋር ለመላመድ መድረክ ይሰጣሉ።
የልምድ ልውውጥ መድረኮች	እነዚህ ክፍለ-ጊዜዎች በግምገማ ስብሰባዎች ወቅት ተጨማሪ ቀኖችን ወስዶ የሚካሄዱ ሊሆኑ ይችላሉ። ከጋራ ምክር ቤቶቹ አመራሮች በተጨማሪ ባለድርሻ አካላት በመጋበዝ በቀጥታ እንዲሳተፉ ማድረግ፣ ጥያቄዎችን እንዲጠይቁ እና በጋራ እንዲመክሩ ያስችላሉ። ዓላማው በመስክ የተገኘውን እውቀት ለመጠቀም እና መልካም ልምዶችን ለማስቀጠል፣ እውቀትን፣ ክህሎትንና ግንዛቤዎችን በጋራ ለመለዋወጥ ነው።

2. ሥራዎችን በርቀት ለማስተባበር የቴክኖሎጂ ግብዓቶችን በአግባቡ መጠቀም

ዘመኑ የደረሰበት የቴክኖሎጂ እድገት ደረጃ በርቀት ሆነን ሥራን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማስተባበር እና ለማስፈጸም የሚያስችል ነው። የዋናው የጋራ ምክር ቤት እና በክልል እና/ወይም በከተማ አስተዳደር የጋራ ምክር ቤቶች መካከል ያለው የሥራ ቅንጅት እንዲሻሻል አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የቴክኖሎጂ መሳሪያዎችም አሉ። ለምሳሌ፣ የቪዲዮ ኮንፈረንስ ፊት ለፊት ለመነጋገር ያስችላል። ፈጣን የመልዕክት መላላኪያ እና የትብብር መሣሪያዎች (እንደ ቴሌግራም ወይም ኢሜል) በቀጥታ ለመነጋገር (real-time communication) እና ፋይሎችን ለማጋራት ያግዛሉ። በተጨማሪም፣ የፕሮጀክት ማኔጅመንት ሶፍትዌሮች የሥራ ድርሻን ለመመደብና የሂደቱን ለውጥ ለመከታተል ያገለግላሉ። የጋራ ምክር ቤቱ ሊጠቀሙ የሚችሉ የመገናኛ መንገዶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፦

ዲጂታል የሥራ ቦታዎች	ዲጂታል የሥራ ቦታዎች (Digital Workspaces) የምንላቸው እንደ ስላክ (Slack)፣ ቴሊግራም፣ ዋትስ አፕ (WhatsApp) ያሉ መድረኮች በጽሐፍ መለክት፣ በድምጽ ወይም በቪዲዮ ጥሪ አማካኝነት በድንገት ለሚመጡ ጉዳዮች አፋጣኝ መመሪያዎችን ለመስጠት፣ የወዲያው መረጃዎች ልውውጥ፣ ሰንድ መላኪያ ሆነው ሊያገለግሉ ይችላሉ። እንዚህን ገጾች ለሚመልከታቸው አካላት በማስተዋወቅ፣ ቡድን በመፍጠር እና ሥርዓት ያለው የአጠቃቀም መመሪያዎችን በመከተል ሥራን ማቀናጀት ይቻላል።
የጋራ መገልገያ መሳሪያዎች	የጋራ መገልገያ መሳሪያዎች (Collaborative Tools) የጋራ ምክር ቤቶች መዋቅሮች እንደ Google Drive እና Microsoft OneDrive ያሉ መሳሪያዎች ብዙ ተጠቃሚዎች በአንድ ሰነድ ላይ በተመሳሳይ ጊዜ እንዲሰሩ ያስችላሉ። ይህም የጋራ ፕሮጀክቶችን ለማስተባበር፣ ሪፖርት ለማዘጋጀት፣ ዴታ ቤዝ ለገንባት በጥሩ ሁኔታ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ። እነዚህን ኦን ላይን ላይ ሰንደ የሚያስተባብሩ (Cloud-based document collaboration) መሳሪያዎችን መጠቀም የጋራ ሥራን ውጤታማ ያደርጋል እንዲሁም የተለያዩ የሰነድ ቅጂዎች (version control) እንዳይፈጠሩ ይከላከላል።
ቪዲዮ ኮንፈረንስ	የጋራ ምክርቤቶቹ አማራሮች በአካል ተገናኝቶ ሥብሰባዎችን ማድረግ በማይችሉበት ሁኔታ Zoom፣ Google Meet እና Microsoft Teams በመሳሰሉ የኦንላይን መድረኮች ፊት ለፊት በቪድዮ እየተያዩ ስብሰባዎችን ለማካሄድ ያስችላሉ። ይህ ደግሞ በውይይት ወቅት የፊት ገጽታዎችንና የሰውነት እንቅስቃሴዎችን ለመረዳት ስለሚያግዝ፣ ግንኙነቱን የበለጠ ውጤታማ ያደርገዋል።
ኢሜይል (Email)	እንደ ቴሌግራም እና ዋትስ አፕ ፈጣን የመልዕክት መላላኪያ ባይሆንም፣ ኢሜይል መደበኛ ለሆኑ ኮሚኒኬሽኖች በተለይም ለጽሑፍ ልውውጥ እና ለሰነድ ማጋራት አሁንም የተለመደ የመገናኛ ዘዴ ነው። በተለይም መልስ ወዲያውኑ በማይጠበቅበት ጊዜ (asynchronous communication) ጠቃሚ ነው።

3. ግልጽ ሚናዎችንና ኃላፊነቶችን መወሰን

ግልጽ ሚናዎችና ኃላፊነቶች በጋራ ምክር ቤቶቹ መካከል መመደብ ለውጤታማ ትብብር እና ለቅንጅታዊ አሠራሮች በጣም አስፈላጊ ናቸው። የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት እንደ ዋና አካል አጠቃላይ አመራርን፣ ሥትራቲጂካዊ ግቦችን ማስቀመጥ፣ ስልቶችንና አቅጣጫዎችን ይሰጣል። የክልል እና/ወይም የከተማ አስተዳደር የጋራ ምክር ቤቶች ደግሞ ከክልሎቹ ወይም የከተማ አስተዳሮቹ ተጨባጭ ሁኔታዎች እና አባል የፖለቲካ ፓርቲዎች ፍላጎት ጋር የተጣጣሙ ፕሮግራሞችን የመተግበር ኃላፊነት አለባቸው[1]።

ተጠሪ አካላት	በጋራ ምክር ቤቱ መተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 64 መሰረት በክልል እና/ወይም በከተማ አስተዳደር የተደራጁ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤቶች ለኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ተጠሪ ናቸው። ይህ ማለት የክልል እና/ወይም የከተማ አስተዳደር ምክር ቤቶች ወቅታዊ ሪፖርቶችን ዋናው ምክር ቤት የማቅረብ ግዴታ አለባቸው። በሌላ በኩል ደግሞ፣ ዋናው የጋራ ምክር ቤት በክልልና በከተማ አስተዳደር በሚገኙ ምክር ቤቶች ላይ የክትትል፣ የቁጥጥርና የድጋፍ የማድረግ ኃላፊነት ይኖረዋል።
የማስተባበር ኃላፊነት ያለው አካል	በጋራ ምክር ቤቱ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 33 መሠረት የአደረጃጀት ቋሚ ኮሚቴ ዋና ተግባርና ኃላፊነት በክልል እና/ወይም በከተማ አስተዳደር ያሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤቶችን ማደራጀት፣ ማጠናከር እና መደገፍ ነው። በዚህም መሰረት ይህ ኮሚቴ የሚከተሉትን ያከናውናል፦ • **ማደራጀትና ማጠናከር**፦ በክልል እና/ወይም በከተማ አስተዳደር የተቋቋሙ የጋራ ምክር ቤቶችን ያደራጃል፣ አቅማቸውን ያጎለብታል እንዲሁም ዘመናዊ የአሠራር ሥርዓት እንዲኖራቸው ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል። • **የግንኙነት መስመር መዘርጋት እና ልምድ ልውውጥ**፦ በክልል እ/ወይም በከተማ አስተዳደር ባሉ የጋራ ምክር ቤቶች መካከል የግንኙነት መስመሮችን በመዘርጋት የልምድ ልውውጥ እንዲኖር ምቹ ሁኔታዎችን ያመቻቻል። እነዚህ ተግባራት የበለጠ ለማሳለጥ እና ውጤታማ ለማድረግ የክልል እና/ወይም የከተማ አስተዳደር የጋራ ምክር ቤቶች ከአደረጃጀት ቋሚ ኮሚቴ ጋር በርቅርበት የሚሰራ አካል ቢመድቡ ግንኝነቶችን ለማስተባበር እና ለመከታተል የሚያችል ውጤትማ ሥራዎችን ማከሄድ ይችላሉ።
የኃላፊነት ክፍፍል	በዋናው ምክር ቤት እና በክልል እና/ወይም በከተማ አስተዳደር የጋራ ምክር ቤቶች የጋራ የሥራ ዕቅዶችን በማዘጋጀት እና ተግባራት በመምራት ሂደት ኃላፊንት ሊከፋፈሉ ይችላሉ። በዚህም እያንዳንዳቸው ያላቸውን አንፃራዊ አቅም በመጠቀም ከፍተኛ ውጤታማነት እንዲኖር ይደረጋል።

4. መደበኛ ሪፖርት ማቅረቢያና ግብረመልስ (Feedback) መንገድ መፍጠር

በመተዳደርያ ደንቡ አንቀጽ 64 ንኡስ አንቀጽ 4 መሰረት የክልል እና/ወይም የከተማ አስተዳደር የጋራ ምክር ቤቶች ዋናው የጋራ ምክር ቤት በየጊዜው መደበኛ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ አለባቸው። በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 5 ላይ እንደተጠቀሰው ዋናው የጋራ ምክር ቤት ለክልል እና/ወይም ለከተማ አስተዳደር የፖለቲካ ፓርቲዎች ምክር ቤቶች ክትትል፣ ቁጥጥር እና ድጋፍ ያደርጋል። ይህም ግብረመልስን የሚያጠቃልል ነው። ድንጋጌዎቹን ተግባራዊ ለማድረግ መደበኛ የሪፖርት ማቅረቢያ ማዕቀፎች ማዘጋጀት ለተቀናጀ አሠራር ወሳኝ ናቸው። ለዚህም ግብ ስከታመነት የሚከተሉትን ስልቶችን ተግባራዊ ማድረግ ጠቃሚ ይሆናል፦

የሪፖርት መርሐግብር	በበርካታ ተቋምት የምተገበረው እና የተለምደው የሪፖርት አቀራርብ መረሐ ግብር በሩብ ዓመት የተከፋፈለ እና ዓመታዊ አጠቃልይ ሪፖርት መድረጊያ የጊዜ ሰሌዳን የሚከተል ነው። በዚህም መሠረት የክልል እና/ወይም የከተማ አስተዳደር የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤቶች በየሩብ ዓመቱ አጭር የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት፣ እንዲሁም ዝርዝር ዓመታዊ የአፈጻጸም ሪፖርት ማቅረብ አለባቸው። አስቸኳይ ጉዳዮች ሲኖሩ ደግሞ ልዩ ዘገባዎችን ማቅረብ ይችላሉ።
ግብረመልስ መስጠት	መደበኛ ሪፖርት ማቅረብ ቀጣይነት ያለው ግብረመልስ መስጠት (feedback loops) ይፈጥራል። ይህም በጋራ ስምምነት ላይ የተመሠረተ ክትትልና ግምገማ ለማድረግ እና ማስተካከያ ለማድረግ ያስችላል። ይህ ደግሞ በዋናው የጋር ምክር ቤት እና በልልል እና/ወይም የከተማ አስተዳድር የግራ ምክር ቤቶች መካከል ያሉትን ትስስሮች በጥልቀት እንዲረዳና የአመራር ተግባሩን እንዲያጠናክር ያግዛል።
የግብረመልሶች ገንቢነት	በጋር ምክር ቤቱ አሠራር ውስጥ ገንቢ ግብረመልስ (constructive feedback) የመስጠት ባህል መዳበር አለበት። ትኩረቱ ጥፋትን ከመፈለግ ይልቅ በስልታዊ ማስተካከያዎች ላይ መሆን አለበት።

7.3. በጋራ ምክር ቤቶች መካከል ሀብት መጋራት እና አቅም ግንባታ

ዋናው የጋራ ምክር ቤት እና የክልል እና/ወይም የከተማ አስተዳደር የጋራ ምክር ቤቶች በትብብር እንዲሰሩ እና የጋራ ግቦችን እንዲያሳኩ፣ የሃብት መግራት እናእና የአቅም ግንባታ ወሳኝ ጉዳዮች ናቸው። የጋራ ምክር ቤቶች ሃብታቸውንና ዕውቀታቸውን ሲያዋህዱ ችግሮችን በቀላሉ መፍታት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችን አቅም ማሳደግን እና የሚያጋጠሙ ፈተናዎችን በጋራ በምፍታት የጋራ ምክር ቤቶቹን የእድገት ሂደትን ማፋጠን እና የምክር ቤቶቹን ሥራዎች ዘላቂና ውጤታማ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይችላሉ።

1. የሀብት መጋራትን ማመቻቸት

በዚህ አውድ ሀብት የሚለው እሳቤ የገንዝብ የብትን ብቻ የሚመለከት አይደለም። ይልቁንም ከገንዘብ ሀብት በተጨማሪ የጋራ ምክር ቤቱ ያሉትን እና ወደፊትም የሚያከማቸውን የእውቀት፣ የክህሎት፣ የግንኝነት/ኔትዎርክ፣ የሰነዶች፣ የቴክንክና መስል ጠቃሚ ግብዓቶችን የሚያካትት ነው። የሀብት መጋራትን ሂደትን ለማመቻቸት የሚከተሉትን ተግብራት ማከናውን ጠቃሚ ነው።

የሀብት ምዝገባ	በየዓመቱ የጋራ ምክር ቤቶቹ ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ ሲያዘጋጁ ያላቸውን የሰው ኃይል፣ የገንዘብ እና የቴክኒክ አቅሞችን በመገምገም ያላቸውን አቅም እና ክፍተት መለይት (Resource Mapping) ያስፈልጋል። ይህም ክፍተቶችን ለመድፈን የሀብት መጋራትን እና መከፋፈል አሰራርን ከፍ ለማድረግ ይረዳል።
የጋራ ሀብቶችን መጋራት	የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት እንደ ጎግል ድራይቭ ያሉ ክፍት የመረጃ ማከማቻና ማጋሪያ መድረኮችን በመፍጠር ሁሉም ምክር ቤቶች ያላቸውን እውቀትንና የጋራ ሰነዶችን ያለማቋረጥ እንዲያገኙ ማድረግ (Shared Resources) ይችላል። ለምሳሌ የአስተዳደር ቲፕሌቶችን፣ መመሪያዎችን፣ ስትራቲጂያዊ መርጃዎችን ማጋራት እና ሁሉም ምክር ቤቶች በፍህታዊነት እንዲጠወሙበት ማድረግ ይቻላል።

2. የጋራ የአቅም ግንባታ ተነሳሽነትን ማዳበር

የጋራ አቅም ግንባታ ሥራዎችን ማዘጋጀት የጋራ ምክር ቤቶች የጋራ ግቦችን ለማሳካት አቅማቸውንና ሀብታቸውን ለማጎልበት የሚያስችሉ የትብብር ፕሮግራሞችን ለመፍጠር የሚያስችል ነው። የእነዚህ ፕሮግራሞች ዓላማ በጋራ ምክር ቤቶች ውስጥና በመካከላቸው ያለውን ክህሎት፣ እውቀትና ሀብት በማሻሻል፣ በመጨረሻም በአንድ የተወሰነ የሥራ መስክ ላይ የበለጠ ውጤታማና ዘላቂ ውጤት ማስመዝገብ ነው። ከዚህ አንጻር የሚከተሉትን ማካሄድ ጠቃሚ ነው።

የዕውቀት እና የክህሎት ማጎልበቻ ስልጠናዎች	በመተዳደርያ ደንቡ መሰረት ዋናው የጋራ ምክር ቤት የክልል እና ወይም የከተማ አስተዳድር የጋራ ምክር ቤቶችን አቅም የመገንባት ኃላፊነት አለበት። ለዚህ ጥረት ስኬት የእያንዳንዱ ተሳታፊ የጋራ ምክር ቤት ልዩ የአቅም ፍላጎቶችን በትክክል ለመለየት ጥልቅ ምዘና ማካሄድ ወሳኝ ነው። የጋራ ምክር ቤቱ ከአጋር ተቋምት ጋር በምተባበር የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ለመስጠት ሀብት ማሰባሰብ ይጠበቅበታል። ይህም የጋራ ተነሳሽነቶች (initiatives) አፈፃፀማቸው ከፍተኛ ተጽዕኖ እንዲያሳድር የገንዘብ፣ የሰው ኃይል እና የቴክኒክ ሀብቶችን በአንድ ላይ ለማሰባሰብ ያስችላሉ።
ተለዋዋጭ አመራር ስልትን ማዳበር	የሥራ እቅድ ይዘቶችን እና አፈጻጸማቸውን በየጊዜው እየገመገሙ የአሠራር ሁኔታዎች ሲለዋወጡ ምላሽ ለመስጠት እንዲያስችሉ የማሻሻያ ዘዴዎችን መከተል ያስፈልጋል። በዚይም ተጨባጭ ልምድና ተመኩሮ ላይ የተመስረተ የጋራ ምክር ቤቶች መካከል የእውቀት፣ የክህሎት እና የተሻሉ ተሞክሮዎችን ማስተላለፍ እና ተቋሚዊ ትምህርትን ያጠናክራል።

3. እርስ በርስ መማማር (Peer Learning) እና ልምድ እንዲለዋወጡ ማበረታታት

እርስ በርስ መማማር (Peer Learning) አንዳንድ ጊዜ ከእኩያ ወደ እኩያ መማማር በመባል ይታወቃል። ይህ ዘዴ የክልል እና/ወይም የከተማ አስተዳደር የጋራ ምክር ቤቶች እና በጋራ ምክር ቤቶች ውስጥ የሚገኙ አባላት እርስ በርስ ያላቸውን እውቀትና ልምድ በመጠቀም እድገታቸውን የሚያፋጥኑበት ዘዴ ነው። የተለያዩ የክልል እና/ወይም የከተማ አስተዳደር የጋራ ምክር ቤቶች የገንዮሽ የግንኝነት መስመር ፈጠረው ከተለመደው የሥልጠና መንገዶች ባሻገር እርስ በርስ መማማር እና ልምድ መለዋወጥ ይችላሉ። ይህ ዘዴ ውጤታማ፣ ቀጣይነት ያለው እና ወጪ ቆጣቢ ነው። ከሁሉም በላይ ደግሞ፣ የጋራ ምክር ቤቶች አባላት ይህንኑ የመማማር ሂደት አሁን እየተጠቀሙበት ሊሆን ይችላል። ይህን ለማሳካት የክልል እና/ወይም የከተማ አስተዳደር የጋራ ምክር ቤቶች የሚከተሉትን ማካሂድ ይችላሉ፦

የልምድ ልውውጥ ጉብኝቶች	የክልል እና/ወይም የከተማ አስተዳደር የጋራ ምክር ቤቶች መካከል እየተዘዋወሩ፣ አንዱ ከሌላው የተሳካ ስልቶችንና ምርጥ ተሞክሮዎችን መመልከትና መማር ይችላሉ።
ከተሞክሮ መማርን ማጠናከር	ምክር ቤቶቹ በትብብር ልውውጥ የተገኙ ግንዛቤዎችን ስልታዊ በሆነ መንገድ መለየት፣ መተንተን እና መተግበር አለባቸው። ይህ ደግሞ ለወደፊት የትብብር እቅድ ጥንካሬ ለመስጠት ከስኬቶችም ሆነ ከውድቀቶች የተገኙ ተሞክሮዎችንና ትምህርቶችን መመዝገብን ይጨምራል።
ግንኙነቶችን መገንባት	የጋራ ልምድ መለዋወጫ መድረኮች እና መደበኛ ያልሆኑ ግንኙነቶች፣ ለምሳሌ ቡድን የማጠናከሪያ ስብሰባዎች፣ በግለሰቦች መካከል ያለውን ትስስር ለማጠናከር፣ መተማመንን ለመገንባት እና የትብብር ባህልን ለማሳደግ ወሳኝ ናቸው።

ለመጽሐፉ ዝግጅት በማጣቀሻነት ጥቅም ላይ የዋሉ ዋቢ ጽሑፎችና መጽሐፍት

1. NDI (2023): “Post-Election Public Opinion Survey.” National Democratic Institute, Addis Ababa, Ethiopia
2. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 38 ንዑስ አንቀጽ 2ን ይመልከቱ።
3. የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011ን ይመልከቱ።
4. Hailu, S. (2018). Challenges and prospects of the Democratization process in Ethiopia. International Journal of Political Science and Development, 6(1), 27-38.

የምዕራፍ አንድ ማስታወሻ

1. Konrad-Adenauer-Stiftung. (2011). Political Parties: Functions and Organisation in Democratic Societies.
2. Heywood, A. (2019. Politics. Palgrave Macmillan.
3. Dalton, R. J., & Wattenberg, M. P. (Eds.). (2002). Parties without partisans: Political change in advanced industrial democracies. Oxford University Press.
4. Bass, B. M., & Riggio, R. E. (2006). Transformational Leadership (2nd ed.). Lawrence Erlbaum Associates.

የምዕራፍ ሁለት ማስታወሻ

1. O.P. Jindal Global University፣ (2024): “What is Public Policy? Definition, Scope, Features, Types & More።”
2. Pepperdine University፡ (2023) “Exploring Different Types of Public Policy።” School of Public Policy።
3. Blavatnik School of Government, (2025): “A guide to evidence-based policymaking.”
4. Kilonzo, S. M., & Ojebode, A. (2023). Research methods for public policy. Public policy and research in Africa, 63-85.
5. National Planning Commission and the United Nations in Ethiopia (2015): “Assessment of Ethiopia’s Progress towards the MDGs.”
6. UNICEF Ethiopia (2023): “Learning and development.”
7. Simply Stakeholders (2025): “Policy Consultation & the Importance of Stakeholders.”

የምዕራፍ ሦስት ማስታወሻ

1. O.P. Jindal Global University፣ (2024): “What is Public Policy? Definition, Scope, Features, Types & More።”
2. Pepperdine University፡ (2023) “Exploring Different Types of Public Policy።” School of Public Policy።
3. Blavatnik School of Government, (2025): “A guide to evidence-based policymaking.”
4. Kilonzo, S. M., & Ojebode, A. (2023). Research methods for public policy. Public policy and research in Africa, 63-85.
5. National Planning Commission and the United Nations in Ethiopia (2015): “Assessment of Ethiopia’s Progress towards the MDGs.”
6. UNICEF Ethiopia (2023): “Learning and development.”
7. Simply Stakeholders (2025): “Policy Consultation & the Importance of Stakeholders.”

የምዕራፍ አራት ማስታወሻ

1. European Institute of Peace, (2021) “Fake news misinformation and hate speech in Ethiopia: A vulnerability assessment.”
2. Assembly, U. G. (2025). International covenant on civil and political rights.
3. የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ (2012)፡ “የጥላቻ ንግግርን እና የሐሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር 1185/2012።”
4. CIPESA, (2020): “Analysis of Ethiopia’s Hate Speech and Disinformation Prevention and Suppression Proclamation No.11 85 /2020.”
5. University of Amsterdam (2023): “How do new political parties garner media attention?”
6. Matias Rodsevich (2025): “How to get media coverage.”
7. Benjamin Ball (2024): “Media Interview Tips to Survive. Expert Media Interview Skills.”
8. Juicer, 2025): “Tips for Creating a Successful Social Media Political Campaign Strategy.”

የምዕራፍ አምስት ማስታወሻ

1. Salzburg Global (2025) “Building Truly Inclusive Democracies.”
2. UN Women (2024): “Why so few women are in political leadership, and five actions to boost women’s political participation.”
3. Odihr, O. (2014). Handbook on promoting women’s participation in political parties.
4. IPU (2021): “Youth participation in national parliaments.”
5. Mohammed Shuker, F., & Hashim Sadik, H. (2024). A critical review of rural youth unemployment in Ethiopia. International Journal of Adolescence and Youth, 29(1), 2322564.
6. Deželan, T. (2018). Youth & Political Parties: A Toolkit for Youth-friendly Politics in Europe. European Youth Forum.
7. NDI (2023): “Principles and Practices of Youth Engagement for Political Parties.”
8. ILO (2013): “Inclusion of People with Disabilities.” Addis Ababa.
9. የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ (1987) “የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግሥት፡ አዋጅ ቁጥር 1/1987።”
10. የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ (2000) “የአካል ጉዳተኞች የሥራ ስምሪት መብት አዋጅ ቁጥር 568/2000።”
11. የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ (2001) “የኢትዮጲያ የሕንጻ አዋጅ ቁጥር 624/2001።”
12. “የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ (2011): “የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/11.”
13. Sida, (2014): “Disability Rights in Ethiopia.”
14. Demo Finland, (2023): “Inclusion of persons with disabilities in political parties.” POLICY BRIEF.
15. የኢትዮጲያ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምክር ቤት (2017)፡ “የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት መተዳደሪያ ደንብ።” ህዳር 2017፣ አዲስ አበባ
16. Elect Her, (2024): “Building A Culture Of Inclusion And Accountability: Women In Politics In Scotland.”h

የምዕራፍ ስድስት ማስታወሻ

1. የኢትዮጲያ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምክር ቤት (2017)፡ “የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት መተዳደሪያ ደንብ።” ህዳር 2017፣ አዲስ አበባ
2. Boone, (2025): “Coalition leadership.” EBSCO Research.
3. Spang, F. (2023). Compromise in political theory. Political Studies Review, 21(3), 594-607.

የምዕራፍ ሰባት ማስታወሻ

1. የኢትዮጲያ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምክር ቤት (2017)፡ “የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት መተዳደሪያ ደንብ።” ህዳር 2017፣ አዲስ አበባ

